መስከረም

* የዋጋ ንድፈ ሐሳብ
* ድንበር ዘለል ሞኖፖሎች በታዳጊ አገሮች ላይ የሚፈጽሟቸው ደባዎች
* የኒካራጓ ሕዝብ ፀረኢምፔሪያሊስት ትግልና የዩናይትድ እስቴትስ ደባ

ማርክሳዊ ሌኒናዊ የርዕዮተዓለም መጽሔት

ቅጽ ፰ ቁጥር 33
መጋቢት 1980

መስከረም

ቅጽ ፰ ቁጥር
መጋቢት 1980 33

ማርክሳዊ ሌኒናዊ የርዕዮተዓለም መጽሔት

ማውጫ

ገጽ

* የዝግጅት ገጽ 3

* የዋጋ ንድፈ ሐሳብ 7
  — ከልዩ ልዩ ጽሑፎች የተቀነባበረ

* ድንበር ዘለል ሞኖፖሎች በታዳጊ አገሮች ላይ የሚፈጽሟቸው ደባዎች 32
  — ወልደ ዮሐንስ ወርቅነህ

* የኒካራጓ ሕዝብ ፀረኢምፔሪያሊስት ትግልና የዩናይትድ እስቴትስ ደባ 58
  — ዝናቡ ከበደ

በኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ

ርዕዮተዓለም መምሪያ እየተዘጋጀ በየሦስት ወር የሚወጣ

መስከረም 1973 ተመሠረተ

አድራሻ

የፖስታ ሣጥን ቁጥር — 80001
የስልክ ቁጥር — 113000

Proudly brought to you by
www.binyamhk.wordpress.com



WWW.BINYAMHK.WORDPRESS.COM

ያለ አብዮታዊ ንድፈ-ሐሳብ
አብዮታዊ እንቅስቃሴ ሊኖር አይችልም!

በታሪክ የታነፀ አንድነት ይበልጥ እንዲጠናከር

የሰው ልጅ ልዩ ልዩ የዘር ግንዶች በታሪክ ሂደት በተለያዩ ምክንያቶችና አጋጣሚዎች እየተወራረሱ ፣ በኢኮኖሚ ፣ በፖለቲካና በባህል መቀራረብ እያሳዩና ሁኔታ በፈቀደ መጠን እየተዋሐዱ መጥተዋል ። ይህ የታሪክ ሂደት በፈጠረው ግፊትም በልዩ ልዩ አካባቢዎች ሕዝቦች አያሌ የወል ጥያቄዎች በጋራ በማንሣት መልስ ለመስጠት ሲጥሩ ይታያሉ ።

በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚታይ አጠቃላይ የዓለም ሕዝቦች አንድነት ሂደት የነባራዊ የታሪክ ፈቃድ ሆኖ የብዙ ብሔረሰቦችና ማኅበረሰቦች መኖሪያ በሆነች ኢትዮጵያም በጉላ መልኩ ይታያል ። የዚች ሀገር ብሔረሰቦችና በልዩ ልዩ የዕድገት ደረጃ ላይ የሚገኙ ማኅበረሰቦች ባለፉት የጋራ የታሪክ ጉዞ ምክንያት የወል ማኅበራዊ ህልውናቸውን እያፀኑ መጥተዋል ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ህልውናውን እያፀና መምጣቱ በኅብረት ከንዱ በሁሉም መስክ የተሟላ ነፃነት ለመቀዳጀት የሚያስችለውን ምዕራፍ ለመያያዝ አብቅቶታል ። ይሁን እንጂ ይህ በኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ፍላጐትና ተጋድሎ የተደረሰበት የዕድገት ደረጃና አርአያነቱ በብዝበዛና በጭቆና ተጠቃሚ መሆኑን የህልውናቸው መሠረት ያደረጉ ጥቂት ወገኖችን አሳስቧቸዋል ። የልዩ ልዩ ብሔረሰቦች ሠርቶ አዳሪዎች ሁሉ ለጋራ ጥቅማቸው ማበራቸው ኃያልነታቸው በመሆኑና በዚህም ላይ በኢሕዲሪ ምሥራታው እኩልነታቸውንና የጋራ ብልፅግናቸውን እንደሚያሰፍኑ የተረጋገጠ በመሆኑ በጭቆናና በብዝበዛ ላይ ህልውናቸውን የመሠረቱትን ወገኖች አሳስቧቸዋል ። ስለዚህም ከቅርብና ከሩቅ ተረዳድተው የሕዝቡን ታሪካዊ አንድነት ጭምር መፈታተንን መርጠዋል ። የሕዝቡን የብርታት ምንጭ ፣ ማለትም ኅብረቱን ለማላላትና በተለይ የሀረቱን ሰሜናዊ ክፍል በመቁረስ ህልውናዋን አዳክመው በቁጥጥራቸው ሥር ለማዋል በየመስኩ ጥቃት በመሰንዘር ላይ ናቸው ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላቶቹ ለጥቅማቸው ሲሉ ሊከፋፍሉት ወይም ለራሱ ውድቀት ምክንያት እንዲሆን በወሬ ሊፈቱት ይሞክሩ እንጂ የልዩ ልዩ ብሔረሰቦች ፣ እምነቶች ፣ ቋንቋዎች ወዘተ ገፅታዎች የተጠናቀሩበት ሕዝብ መሆኑ የጋራ ህልውናውን ለማስከበር መሠረታዊ ችግር ሆኖበት አያውቅም ። የጋራ ነፃነቱን ለማስከበር ምንጊዜም በአንድነት

በዚህ ጽሁፍ ውስጥ በተለይ ካልተጠቀሰ በስተቀር የዘመን አ.አ.አ ነው ።

ተሰልፏል ። ዛሬ ደግሞ አብዮቱ በፈጠረለት ምቹ ሁኔታ ነፃነቱን ከውጭ ጥቃት መጠበቅ ብቻ ሳይሆን በመካከሉ የተሟላ እኩልነትን እያሰፈነ ከመምጣትም ሌላ የጋራ ብልፅግናን ለመቀዳጀት በጋራ በመታገል ላይ ይገኛል ።

በየዘመኑ በተለያዩ ነባራዊ የታሪክ አጋጣሚዎች በማለፍ የዛሬውን የጋራ ሀልውና የተቀዳጁት የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ አካሎች በሂደት በልዩ ልዩ ቅርፅ ሊታወቁ ቢችሉም በመሠረቱ ኩሽ (ካም፣ ሐም)፣ ሴም ፣ ኒሎቲክ ከሚባሉ መሠረታዊ ግንዶች የመነጩ ናቸው ። በዘመናት ውስጥ በፍልሰት ፣ በጦርነት ፣ በንግድ ወዘተ. ባደረጉት እንቅስቃሴና ግንኙነት ሊወራረሱና የጋራ ሕይወት ባለቤት ሊሆኑ በቅተዋል ።

በተለይ የሕዝብ መናኸሪያ በሆኑት ከተሞች የአያሌ ብሔረሰቦች አባላት ለጋራ ጥቅማቸው እጅግ ተቀራርበው ፣ በጋብቻ ጭምር ተሣሥረውና ተዋሕደው በአንድነት ይኖራሉ ።

የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች አባላት ከአንድ በላይ ሁለት ፣ ሦስት አንዳንዴም የበለጡ ቋንቋዎችን መናገራቸው የርስበርስ ግንኙነታቸውንና መወራረሳቸውን የሚያሳይ አንዱ ምልክት ነው ። የጋራ ቋንቋ ወይም ቋንቋዎች መዳበር አያሌ የአገራችንን ዜጎች በሰፈራ ፣ በሥራ መስክ ስምሪት ፣ በጋብቻና በመሳሰሉት ማኅበራዊ ምክንያቶች በተለያዩ የሀገሪቷ ክፍሎች እንዲሰራጩና እንዲተዳደሩ ረድቷቸዋል ። በዚህ ሂደትም በአኗኗር ፣ በልማድ ፣ በሥነልቦናና በመሳሰሉት የወል እንጂ በውል የዚህ ወይም የዚያኛው ብሔረሰብ ብቻ ናቸው ሊባሉ የማይችሉ ማኅበራዊ ገጽታዎች እየተስፋፉ መጥተዋል ።

ይህ በታሪክ የታነፀ አንድነት በአብዮቱ ሂደት ይበልጡኑ በእኩልነት ላይ በመመሥረት የጠለቀ መሠረት እየያዘ እንዲመጣ ተደርጓል ። የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች ሠርቶ አደሮች ሁሉ አንዱ ከሌላው ሳይለይ አብዮታቸው ያስገኘላቸው ዲሞክራሲያዊ ድሎች የጋራ ተጠቃሚ ከመሆናቸውም ሌላ በልዩ ልዩ የጋራ መድረኮች በመደራጀት መብታቸውን የሚያስከብሩበትንና የዕድላቸው ወሳኝ እነሱው እራሳቸው መሆናቸውን የሚያረጋግጡበትን ሁኔታ ፈጥረዋል ። ከዚህ አኳያ የኅብረተሰቡ መሪ ኃይል የሆነው የኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ ፣ የብዙኀኑ ሠርቶ አደሪ ሕዝብ ሥልጣን መግለጫ የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክና እንዲሁም ሕዝባዊ ድርጅቶች ዋንኞቹ መተማመኛ ናቸው ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዕድገቱ ካለው ከፍተኛ ፍላጐትና ለዚሁ ከሚያደርገው ጥረት ጐን በውጭ ተስፋፊዎችና በውስጥ ጠባብ ዓላማ በሚያራምዱ ከሃዲዎች ሤራ ምክንያት የሚጋረጥበትን እንቅፋት መቋቋምም አንዱ ግዴታው ሆኗል ። ሀገራችን በተፈጥሮ ሀብት የታደለች ፣ በተለይ ለጐረቤቶቿ የህልውናና የልማት መሠረት የሆኑ የአያሌ ወንዞች ባለቤት ፣ የምዕራብና የምሥራቅ አገሮች አንዱ ዋነኛ አገናኝ ለሆነው ለቀይ ባሕር በስፋት አዋሳኝ በመሆኗ የቅርብ ሆኑ የሩቅ ተስፋፊ ኃይሎች ሲመኟትና ይልቁንም በቁጥጥራቸው ሥር ለማዋል ጥቃት ሲሰነዝሩባት ኖረዋል ።

የውጭ ወራሪዎች ኢትዮጵያን ለመያዝ ከተጠቀሙባቸው ዘዴዎች አንዱ ሕዝቡን በሃይማኖትና በቀበሌ በመከፋፈል እርስበርስ ማጋጨትና ረዳት መስሎ ለመግባት በመሞከር ነበር ። ለምሳሌ በአፍሪካ አህጉር የመጀመሪያ ቅኝ ገዥዎችና በዚሁ አህጉር የባሪያን ንግድ ካስፋፉት መካከል ተጠቃሽ የሆኑት የፖርቱጋል የገዢ መደብ መሪዎች ኢትዮጵያን

በተጽዕኗቸው ክልል ውስጥ ለማስገባት ፣ ቀስ በቀስም ቅኝ ግዛታቸው ለማድረግ ይጥሩ የነበረው የክርስትናን ሃይማኖት በማስፋፋት ስምና በወቅቱ በሀገሪቷ ውስጥ በሃይማኖት ሽፋን ይካሄድ በነበረው የገዢ መደቦች የርስበርስ ግጭት ክርስቲያኖችን የሚረዱ በመምሰል ነበር ።

የኦቶማን ቱርክ ተስፋፊዎችም ቀደም ሲል በ1517* ግብፅን ከወረሩ በኋላና በወቅቱ የፖርቱጋል ቅኝ ገዢዎች በቁጥጥራቸው ሥር ለማቆየት የሚፈልጉትን ምሥራቅ አፍሪካን ለመያዝ ፣ እንዲሁም ወደ መሃል አፍሪካ ለመግባት ይጥሩ በነበረት ጊዜ ኢትዮጵያን ለመውረር የተጠቀሙበት አንዱና ጉልህ ዘዴ የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ የሆኑ በምሥራቅና በደቡብ ምሥራቅ ይገኙ የነበሩ የአንዳንድ የገዢ መደብ አባላትን በክርስቲያኑ ነገሥታት ላይ እንዲያምጹ በመገፋፋት ነበር ። ቱርኮች በዚህ ሤራቸው ተደጋጋሚ ግጭቶች እንዲቀሰቅሱ በማድረግ በተለይ ከ1527 እስከ 1542 በክርስትናና በእስልምና ሃይማኖት ስም ለማስገበርና ለንግድ ኬላዎች ቁጥጥር ለተካሄደው የኢትዮጵያውያን ገዢ መደብ አባላት የእርስበርስ ጦርነት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል ። በጦርነቱ ሂደት የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮቹን ለመርዳት በሚል ስም ከኦቶማን ግዛት በመጣ ኃይል ጭምር ከፍተኛ ዝርፊያ በመካሄዱ የሀገሪቷ ሀብት እንዲባክን የኢኮኖሚ ዕድገት እንዲተጓጎል ፣ ሕዝብ ከኑሮው እንዲፈናቀልና የማዕከላዊ መንግሥት ቁጥጥር እንዲዳከም ተደርጓል ።

በ19ኛው ምዕተ ዓመት ወደ አፍሪካ የመጡ የአውሮፓ ተስፋፊዎች ቀደም ሲል የኦቶማን ቱርክና በኋላም የግብፅ ተስፋፊዎች እንዲሁም የፖርቱጋል ቅኝ ገዢዎች የኢትዮጵያን ሕዝብ ለመከፋፈል የተጠቀሙበትን ሥልት በላቀ ሁኔታ ተግባራዊ አድርገውታል ። ከ1855 እስከ 1868 ፣ በአፄ ቴዎድሮስ መሪነት በመሳፍንት የሥልጣን ሽሚያ ታጥኳ የነበረችውን ኢትዮጵያን እንደገና አንድነቷን በፅኑ መሠረት ላይ ለማቆም ተይዞ የነበረው ከፍተኛ ጥረት የተደናቀፈው ፣ ከ1872 እስከ 1889 በአፄ ዮሐንስ አራተኛ አማካይነት የውጭ ጥቃትን በመከላከል ጠንካራ ኢትዮጵያን ለማቆየት የተካሄደው ትግል ፈተና የገጠመው ፣ በዳግማዊ አፄ ምኒልክ የተመራውን የአገር ግንባታ ፣ ማዕከላዊ መንግሥትን የማጠናከርና የዘመናዊ አኗኗርን መሠረት ለመጣል የተደረገውን እንቅስቃሴ በአጭሩ ለመቅጨት የተሞከረው በቅኝ ገዢዎች ሤራ መሆኑን ታሪክ በገሐድ ያወሳል ።

ቅኝ ገዢዎች በሀገራችን ላይ ጥቃት በሰነዘሩበት ጊዜ ሁሉ የውስጥ ከሃዲዎች በምንደኝነት ማሰለፍ የሥልታቸው ቋሚ አካል ነበር ። ጠባብ ፍላጐታቸውን ለማርካት ሲሉ በየጊዜው ለጠላት ያደሩ ከሃዲዎች ለአያሌ የዚች አገር ዜጎች ሕይወት ማለፍና ለሀገር ኢኮኖሚ መዳከም ታሪክ የማይረሳው አፍራሽ ድርሻ አበርክተዋል ። ይህ ሁኔታ በቀድሞ ዘመናት ብቻ ሳይሆን በቅርቡም በሕዝባዊ አብዮታችን ዓመታት በግልፅ ታይቷል ። በአሁኑ ጊዜም በሰሜኑ የአገራችን ክፍል የውክልና ጦርነት የሚያካሂዱብን ተገንጣይና ሽብር ፈጣሪዎች ከላይ ከተጠቀሱት የማይለዩና የከፋ ምሳሌነታቸው ወራሾች ናቸው ።

የትናንቶቹም ሆኑ የዛሬዎቹ ከሃዲዎች ሕዝብን ለመሠዋዕትነት መዳረጋቸው አሌ ባይባልም የሕዝቡን ወኔ እንደሚመኙት ሰልበው ፍላጐታቸውን ዳር ለማድረስ ከቶውንም አልቻሉም ። ሕዝቡ ጥቃት በተቃጣበት ጊዜ ሁሉ በጠላት እንደሚታሰበው በተስፋ መቁረጥ

ያጉበደደበት አጋጣሚ የለም ። የኢትዮጵያ ሕዝብ የቱንም ያህል ጥቃትና ችግር ቢፈትነው በቁጭት የኅብረት ክንዱን አጠንክሮ መነሣት እንጂ አሜን ብሎ ተዋራጅነትን የመቀበል ባሕርይ የለውም ። ይህ የተጋዳይነት መንፈስና ግብሩ በአድዋ ጦርነት (1896) በፋሽስት ኢጣሊያ ወረራ (እ.ኢ.ት.ዮ.አ.1928—1933) እና በሌሎችም የአገራችን የነፃነት ተጋድሎዎች ወቅት በጉልህ ታይቷል ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በአንድነት ላይ በተመሠረተ ኃይሉ በየጊዜው አንፀባራቂ ድሎችን የተጐናጸፈ ቢሆንም ዛሬም ጠላቶቹ የእሱ የሆነውን ከመመኘትና ይልቁንም አርአያነቱን ለማጥፋት ከመሞከር ወደኋላ አላሉም ። በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል በተገንጣዮችና በሽብር ፈጣሪዎች ሲካሄድ የቆየውና በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እንደገና የተባባሰው የጥፋት ድርጊት ለዘመናት የኃይላችን ምንጭ ሆኖ የኖረውን አንድነታችንን የማናጋት ተልዕኮ ያለውና በፀረ ኢትዮጵያ ኃይሎች ግፊትና ሰፊ ድጋፍ የሚካሄድ ነው ። ይሁን እንጂ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደካሁን በፊቱ ሁሉ ለአሁኑም የጠላት ጥቃት ሳይዘናጋ የውድ ሀገሩን ህልውናና በአብዮቱ የጨበጣቸውን ታሪካዊ ውጤቶች አሳልፎ ላለመስጠት ዳግመኛ የኅብረት ክንዱን አንሥቷል ። ዛሬም እንደትናንቱ ሰብአዊና ቁሳዊ ኃይሉን አስተባብሮ ጠላቶቹን ለመደምሰስ ተንቀሳቅሷል ። የወንበዴዎች ምርጫ በኃይል በመጠቀም ሕዝብ በመሥዋዕትነቱ ያስከበረውን አንድነት መናድ ፡ ሕዝብ በመሥዋዕትነቱ ያለማውን ማፍረስ ከሆነ ሕዝቡ ደግሞ ክንዱን አበርትቶ የተሰነዘረበትን ጥቃት ከመመከትና ከመደምሰስ ሌላ ምርጫ ሊኖረው ይችላል ? ስለዚህ የኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ 8ኛ መደበኛ ስብሰባ በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል በኩል ያንዣበበውን እጅግ አሳሳቢ ሁኔታ ለማስወገድ “ሁሉም ነገር ወደጦር ግንባር” በማለት ያቀረበውን ወቅታዊ ጥሪ ሁለገብ በሆነ መልክ በተግባር መተርጐም ሊታለፍ የማይችል ነው።

የምንታገለው በጦርነቱ ግንባር ከገጠሙን ወንበዴዎች ጋር ብቻ ሳይሆን በተዘዋዋሪ ከአዝማቾቻቸው ኢምፔሪያሊስትና አድኀሮት ኃይላት ጋር መሆኑንም መገንዘብ ይኖርብናል ። በጠላቶቻችን በኩል የሰልታቸው አንዱ ገፅታ በተቻላቸው መጠን ጦርነቱ በአጭሩ እንዳያበቃና ተራዝሞ በተለይ ኤኮኖሚያችንን እንዲያዳክም በመሆኑ ይህንኑ በቅድሚያ አውቆ በሁሉም ረገድ ዝግጁ መሆን እጅግ አስፈላጊ ነው ። ከዚህ አንፃር የተሟላ ጥረት እስከተደረገ ድረስ የጠላትን ሤራ ማክሸፍና ጥቃቱን መደምሰስ ይቻላል ። በኃይል የመጣን ጠላት በተመጣጣኝ ሁኔታ መመከት አማራጭ የሌለው ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ሰላምን በሰላማዊ መንገድ ለማስፈን የሚደረገው ጥረት በበለጠ ሊለፋበት እንደሚገባ አያጠያይቅም።

የኢትዮጵያ ሕዝብና አብዮት ፍላጐት ሀገርን በሰላም መገንባት ነበር ። ለዚህ ነው ችግሩን በሰላም ለመፍታት ፓርቲና መንግሥታችን ብዙ ጊዜ ጥሪ ያቀረበው ። ሰላምን በሰላማዊ መንገድ የማግኘት ጥረታችን ፍሬ ካጣ በጦርነት ማግኘት አማራጭ የሌለው ውሳኔያችን ይሆናል ። ጦርነት ፀረሰው ፣ ፀረሀብት ፣ ፀረባሕል በመሆኑ የሚጠላ እንጂ የሚወደድ አይደለም ። ከጦርነት በስተቀር አንድነታችንን ፣ ነፃነታችንና ተከብሮ የኖረ ዳር ድንበራችንን ማስከበር የምንችልበት ሌላ ምርጫ ከሌለን ግን ልናካሂደው እንገደዳለን ። ስለዚህ በዚህ ትግላችን በአሸናፊነት ለመወጣት ኃይላችንን አሰባስበን ተገንጣዮችን መደምሰስ ይኖርብናል ።

የዋጋ ንድፈ ሐሳብ*

መግቢያ

የአንድ አገር የኢኮኖሚ ፖሊሲ ፓርቲ ወይም መንግሥት በኅብረተሰቡ ኢኮኖሚያዊ ሕይወት ውስጥ በመደቦች ፣ በማኅበራዊ ክፍሎች ፣ በብሔሮች መካከል ያለውን ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት የሚቆጣጠርበትና ብሔራዊ ኢኮኖሚን የሚመራበት ፣ አስተሳሰብ ፣ የረዥምና የአጭር ጊዜ ትልሞችና ስልቶች የተቀናጁበት መሣሪያ ነው ።

የኢኮኖሚ ፖሊሲ ባሕርያትና ማኅበራዊ አቅጣጫ የሚወሰኑት ይህ ፖሊሲ በመነጨበትና ተግባራዊ በሚሆንበት ፖለቲካዊ ሥርዓትና ይህንን ሥርዓት በሚገዙት ነባራዊ የዕድገት ሕግጋት ነው ። ከዚህም በላይ የኅብረተሰቡን ተጨባጭ ታሪካዊ ሁኔታ ፣ በአገሪቱ ውስጥ ያለውን የኃይል አሰላለፍ ፣ ብሔራዊና ዓለምአቀፋዊ ሁኔታዎችን የሚያገናዝብ ይሆናል ። የኢኮኖሚ ፖሊሲ የሥርዓተ ማኅበሩ የዕድገት ደረጃዎች በሚፈጥሩት ሁኔታዎችና ተግባራት ላይ የሚመሠረት ፣ ብሎም በተለያዩ ቅርጾችና ስልቶች በመጠቀም ተግባራዊ የሚሆን ነው ። የካፒታሊስቱ ኅብረተሰብ የኢኮኖሚ ፖሊሲ በካፒታሊስታዊ የግል ይዞታ ላይ የተመሠረተ ፣ በባሕርዩም ሆነ በዓላማው ብዝበዛን ለማቆየት የሚጥርና ከሰፊው ሕዝብ ፍላጐት በተቃራኒ የቆመ በመሆኑ መደባዊ ትራኔውን የሚያባብስ እንጂ የተሟላ ማኅበራዊ ዕድገትን የሚያስገኝ አይሆንም ።

የሶሻሊስት የኢኮኖሚ ፖሊሲ በማምረቻ መሣሪያዎች የጋራ ባለቤትነት ላይ የተመሠረተ በመሆኑ በባሕርዩም ሆነ በዓላማው ከካፒታሊዝም የኢኮኖሚ ፖሊሲ የተለየ ነው ። ዓላማውም በየጊዜው እያደገ የሚሄደውን የሕዝብ ፍላጐት ማርካትና የኑሮ ደረጃቸውን ማሳደግ ነው ። የአንድን አገር የተፈጥሮ ሀብትና የሰው ኃይል በተቀነባበረና ኢኮኖሚያዊ በሆነ መንገድ ጥቅም ላይ በማዋል ለኅብረተሰቡ ፍጆታና ለወደፊት የምርት ማሳደጊያ የሚውል የጥሪት ክምችት መፍጠር ነው ። የተመጣጠነ የኑሮ ደረጃ ዕድገትም ሊገኝ የሚችለው ኢኮኖሚው በማዕከላዊ ፕላን መመራት ሲችል በመሆኑ የሶሻሊዝም የኢኮኖሚ ፖሊሲ በማዕከላዊ ፕላን የሚንቀሳቀስ ነው። በማዕከላዊ ፕላን የሚመራ ኢኮኖሚ ደግሞ ተጨባጩን ሁኔታ ለመገምገም ፣ የወደፊቱን የዕደገት አቅጣጫ ለመቀየስና ዕቅዱን ተግባራዊ ለማድረግ የዋጋ ፖሊሲ ሊኖረው ይገባል ።

ፓርቲና መንግሥት በአንድ በተወሰነ የኅብረተሰብ የዕድገት ደረጃ በሸቀጥና በገንዘብ መካከል ያለውን ግንኙነት ለመምራት የነደፉትና የሚያራምዱት መሥመር የዋጋ ፖሊሲ ይባላል ። የዋጋ ፖሊሲ የአጠቃላዩ የኢኮኖሚ ፖሊሲ አካል ሲሆን በዚህ አጠቃላይ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ውስጥ ቁልፍ ቦታ ያለው ነው ። ምክንያቱም የኢኮኖሚያዊ

* ከልዩ ልዩ ጽሑፎች የተቀነባበረ

ሕይወት የተለያዩ ዘርፎች ከዋጋ ፖሊሲ ጋር በቅርብ የተያያዙ በመሆናቸው ነው ። ሠርቶ አደሩ ሕዝብ በዋጋ ንረት ምክንያት የኑሮ ደረጃው እንዳይናጋ ፣ ምርትና ምርታማነት እንዲበረታታ ፣ የአምራቾችና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች የማምረቻ ወጪን ለመሸፈንና የፋይናንስ አቅማቸውን የሚያሻሽል የዋጋ አተማመን ሥርዓት እንዲዘረጋ ፣ ለልማት የሚያስፈልገውን የጥሪት ክምችት ለመፍጠርና ለማዳበር እንዲቻል የዋጋ ፖሊሲ የበኩሉ ድርሻ አለው ።

በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ውስጥ የተረጋጋ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ እንዲኖር ዋጋ እንደአግባቡ ሥራ ላይ ይውላል ። በአቅርቦትና ፍላጐት መካከል ያለው ግንኙነት ሚዛናዊ እንዲሆን ፣ በተለያዩ የኢኮኖሚ ዘርፎችና ክልሎች ሀብት እንዲከፋፈል ፣ የኢኮኖሚ ዕድገት እንዲፋጠን ፣ የተሻለ የምርትና የፍጆታ መዋቅር እንዲፈጠር ፣ የአንድን ምርት ዋና በዕቅድ በመለወጥ ከምርቱ ጋር ተጓዳኝ የሆኑ የኢኮኖሚ ዘርፎች እንዲጐለብቱ ለማድረግ በሚያስችል መልክ ሥራ ላይ ይውላል ። ለማምረቻ መሣሪያዎች ተገቢ የሆነ ዋጋ በመተመን ማሺን አቅራቢ ተቋሞች ዘመናዊ ማሺኖችን ለማቅረብ እንዲገፋፉ እንዲረዳ ይደረጋል ። በመሆኑም በአንድ ሀገር ውስጥ የዋጋ ፖሊሲ በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ሕይወት ውስጥ ከፍተኛ ሚና አለው ። ነገር ግን ይህን ጠቀሜታውን በትክክል ለመረዳትና ለሀገር ዕድገት በሚጠቅም መልክ በሥራ ላይ ለማዋል ሰፊና ጠለቅ ያለ ግንዛቤ ይጠይቃል ። የዚህ ጽሑፍ ዓላማም ለዚህ ግንዛቤ አስተዋጽኦ ማድረግ ነው ።

ጽሑፉ የዋጋ ንድፈ ሐሳብን ምንነትና በተለይ ከብዝበዛ ነፃ የሆነ ኅብረተሰብ ለመገንባት ከሚደረገው ጥረት አንፃር ያለው ልምድ ምን እንደሚመስል የሚቃኝ ነው ። በቅድሚያም የዋጋ ንድፈ ሐሳብን መሠረት በማድረግ እሴትን ፣ የእሴት ሕግን፣* የመሬት ኪራይን እንመለከታለን።

1. ማርክሳዊ የዋጋ ንድፈ ሐሳብ

የገንዘብ ሸቀጥ ግንኙነት እስካለ ድረስ ዋጋ ይኖራል ። ሸቀጥ ፣ ገንዘብና ዋጋ እርስ በርሳቸው በጥብቅ የተሳሰሩ ማኅበራዊ ክስተቶች ናቸው ። ዋጋ የእሴት ገንዘባዊ መግለጫ እንደመሆኑ በርሱ አማካይነት በአንድ ሸቀጥ ላይ የፈሰሰው ማኅበራዊ አስፈላጊ የሥራ ጉልበት ምን ያህል እንደሆነ ይታወቃል ። ከዚህ ባሕርይ አንፃር ሲታይ በሶሻሊስት ሥርዓት ያለው ዋጋ በሌሎች ቅድመ ሶሻሊስት በሆኑ ሥርዓተ ማኅበራት ውስጥ ካለው ዋጋ የሚለይ አይደለም ። ይሁንና ሚናው በሚተመንበት ሥርዓቱና ስልቱ አንፃር ከሌሎቹ ይለያል ። በሶሻሊዝም ዋጋ ለኅብረተሰብ ዕድገት የሚያገለግል የሶሻሊስት ኢኮኖሚ ፈርጅ ነው።

ከዚህ ሚናውና አገልግሎቱ አንፃር በሶሻሊዝም ዋጋ በዕቅድ ከሚመራ ኢኮኖሚ ጋር የተያያዘ ነው ። እንደሚታወቀው በመደብ በተከፋፈሉ በቅድመ ሶሺሊስት ሥርዓተ ማኅበራት ዋጋ ግብታዊ ከሆኑ ክንውኖች ጋር የተያያዘ ከመሆኑም ሌላ ገበያ ምርትን የሚቆጣጠርበትና የሚመራበት ዓይነተኛ መንገድና መሣሪያም ነው ። ይህም ከእሴት ሕግ አሠራር ጋር የተያያዘ ነው ። የዚህን ሕግ ውስጣዊ ባሕርያት

* የእሴት ሕግ በመሠረቱ በዘመነ ኢምፔሪያሊዝም ተፈፃሚነት ያለው ቢሆንም ከቅድመ ሞኖፖል ካፒታሊዝም ለየት ያለ መልክ ይይዛል ። በዚህ ጽሑፍ ሕጉን ለመመርመር የምንሞክረው በቅድመ ሞኖፖል ካፒታሊዝም በሚታየው መልኩ ይሆናል ።

ጠልቆ ለመመርመርና በሶሻሊስት ሥርዓተ ማኅበር ተግባራዊነቱን ለመረዳት በቅድሚያ ስለ እሴትና ከዚሁ ጋር ተዛማጅ የሆኑ ጽንሰ ሐሳቦችን መገንዘብ ያስፈልጋል ።

1.1. የእሴት ንድፈ ሐሳባዊ መሠረት[1]

“የካፒታሊስት ስልተ ምርት በሰፈነባቸው ኅብረተሰቦች ውስጥ ያለው ሀብት የሚከሰተው እንደ ከፍተኛ የሸቀጦች ክምችት ሲሆን መለኪያውም አንድ ነጠላ ሸቀጥ ነው ። ስለዚህም ምርምራችን (ስለ ካፒታሊስት ሥርዓት) ከሸቀጥ ትንተና መጀመር ይኖርበታል”[2] በማለት ማርክስ ካፒታል የተሰኘውን መጽሐፉን ይጀምራል።

በመጀመሪያ ደረጃ ሸቀጦች ጠቃሚ ወይም የጠቀሜታ እሴት ያላቸው ሲሆኑ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ የሰው የሥራ ኃይል የፈሰሰባቸው ፣ ማለትም የሰው የሥራ ኃይል የተጠናቀረባቸው በመሆኑ የልውውጥ እሴት ያላቸው ናቸው ። ሸቀጦች የሚመረቱት በገበያ አማካይነት ለሚካሄድ ልውውጥ ነው ።

በታሪክ ሂደት የሸቀጥ ምርት የተከሰተው በጥንታዊ የጋርዮሽ ኅበረተሰብ ማክተሚያ አካባቢ ከአምስት እስከ ሰባት ሺህ ዓመታት በፊት መሆኑን ታሪካዊ መረጃዎች ይጠቁማሉ ። ለሸቀጥ ምርት መከሰት ምክንያት የሆኑት የሁለት አስፈላጊ ሁኔታዎች መሟላት ማለትም የማኅበራዊ የሥራ ክፍፍል መስፋፋትና የምርት መገልገያዎች በግል መያዝ ናቸው ።

በጋርዮሽ ሥርዓት ማክተሚያ አካባቢ ከብት ማርባት ከእርሻ በመለየቱ የመጀመሪያው ማኅበራዊ የሥራ ክፍፍል ተከሰተ ። እያደርም ዕደ ጥበብ ከእርሻ ተነጠለ ፣ በእነኝህ የተለያዩ የሥራ መስኮች የተሰማሩ አምራቾች የምርት ፍላጐታቸውን ለማርካት ምርታቸውን መለዋወጥ ግዴታቸው ሆነ ። ለምሳሌ ገበሬው የምርት መገልገያ መሣሪያዎችን (ማረሻ ፣ ዶማ፣ ወዘተ) ለማግኘት ከዕደ ጥበቡ ሰው ፣ የዕደ ጥበቡ ሰው በበኩሉ ለምግቡ የሚሆኑትን መሠረታዊ የምግብ ሰብሎች ለማግኘት ከገበሬው ጋር ምርት መለዋወጥ ነበረበት ። ልውውጡ ሊካሄድና ሊዳብር የሚችለው የማኅበራዊ የሥራ ክፍፍል በመኖሩ ነው። ስለዚህም ነው ክፍፍሉ ለሸቀጥ ወይም ለገበያ ተብሎ ለሚመረት ምርት መከሰት አስፈላጊ ሁኔታ ነው የሚባለው ።

የምርት መገልገያዎች በግል መያዝም ምርት የግል እንዲሆንና በሽያጭ (በሸቀጥነት) እንዲቀርብ ነባራዊ አመች ሁኔታ ፈጥሯል ። በቅድመ ሸቀጥ ኢኮኖሚ የግል ሀብት ባለመኖሩ የምርት ልውውጡ በሽያጭ ወይም በግገር መልክ አይካሄድም ነበር ። ከምርት ኃይሎች ዕድገት ጋር እያደር የምርት መገልገያዎች በግል መያዝ የተወሰኑ የምርት ዓይነቶችን በግል በማምረት ሌሎች በግል ያመረቱትን ምርት በግገር መልክ በልውውጥ ለማግኘት ማለትም የሸቀጥ ልውውጥን ለማስፋፋት የራሱን አስተዋጽኦ አድርጓል። በግገር መልክ ልውውጥ ሊካሄድ የቻለው የግል ይዞታ የሆነ ምርት በመኖሩ ሲሆን የግል ምርት ሕልውና ሊያገኝ የቻለውም የምርት መሣሪያዎች በግል በመያዛቸው ነበር ። ስለሆነም የማምረቻ መሣሪያዎች የግል ባለቤትነት ለሸቀጥ ምርት መስፋፋት እንዱ ቅድመ ሁኔታ ነበር ።

የሸቀጥ ምርት ቀላልና ካፒታሊስት በመባል በሁለት ይከፈላል ። የቀላልም ሆነ የካፒታሊስት የሸቀጥ ምርት መሠረት ማኅበራዊ የሥራ ክፍፍልና የምርት መገልገያ

ዎች የግል ባለቤትነት ነው ። ሁለቱ በመሠረቱ ቢመሳሰሉም ልዩነት አላቸው ። በቀላል ሸቀጥ ምርት ሂደት አምራቹ በግሉ የምርት መሣሪያዎችና በራሱ (ምናልባትም በቤተሰቡ አባላት) ጉልበት በመጠቀም ለገበያ (ለማኅበራዊ ልውውጥ) ያመርታል። ካፒታሊስት የሸቀጥ ምርት የሠራተኛን ጉልበት በመበዝበዝ የሚካሄድ ነው ። ካፒታሊስቱ ሠራተኞችን በምንዳ በመቅጠርና ተረፈ ምርት በማስመረት የሸቀጥ ምርቱን በስፋት ያካሂዳል ። በቅድመ ካፒታሊስት ሥርዓተ ማኅበሮች ውስጥ ይካሄድ የነበረው የሸቀጥ ምርት በአመዛኙ ቀላል የሸቀጥ ምርት ነው ። ይሁን እንጂ ይህ ሁኔታ በቅድመ ካፒታሊስት ሥርዓተ ማኅበራት ብቻ የተወሰነ አይደለም ። በካፒታሊዝም ፣ ከዚያም አልፎ ወደ ሶሻሊዝ በሚደረገው የሽግግር ወቅትም ሕልውና ያለው ሲሆን የሚያከትመው በኮሚኒስት ሥርዓት ይሆናል ።

የካፒታሊስት የሸቀጥ ምርት ያደገው ቀላል የሸቀጥ ምርትን መሠረት በማድረግ ነው ። ቀላል የሸቀጥ ምርት ወደ ካፒታሊስት የሸቀጥ ምርት ያመራው በአንድ በኩል የምርት ኃይሎች በማደጋቸውና ማኅባራዊ የሥራ ክፍፍል በመስፋፋቱ ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የምርት መገልገያዎች በካፒታሊስት የግል ይዞታ ሥር በመዋላቸው ነበር ። በካፒታሊዝም ሥርዓተ ማኅበር የሰው ልጅ የሥራ ኃይል ሳይቀር ወደ ሸቀጥነት የተለወጠበት ፣ እንደ ማንኛውም ሸቀጥ በገበያ ላይ እንዲሸጥ የተደረገበትና በምርት ሂደት ውስጥ የሸቀጥ ምርት የበላይነት የያዘበት ወይም የገነነበት ሥርዓት ነው ።

በሸቀጥ ኢኮኖሚ አንድ ሸቀጥ ከሌላ ሸቀጥ ጋር በምን መጠን እንደሚለዋወጥ እንዴት ለመተመን ይቻላል? ለሚለው ጥያቄ ካርል ማርክስ ምላሽ ሲሰጥ ሸቀጦች ሁሉ በጠቀሜታ እሴትነታቸው የተለያዩ ሲሆኑ ሁሉም የሰው የሥራ ውጤት በመሆናቸው ደግሞ የወል ባሕርይ አላቸው ፤ በመሆኑም የሸቀጦችን የልውውጥ እሴት (እሴት) ለመተመን የሚቻለው "በሸቀጦች ሁሉ የወል ባሕርይ ላይ በመመሥረት" ነው ብሏል ።

ለሸቀጦች የጋራ ባሕርይ የሰጣቸው የሰው ልጅ ሥራም ተጨባጭ ሥራ እና ረቂቅ ሥራ በመባል የሚታወቁ የራሱ ጥንድ ባሕርያት አሉት ። ማናቸውም የተወሰነ ግብ ለማስገኘት ጥቅም ላይ የሚውል የሥራ ኃይል ተጨባጭ ሥራ በመባል ይታወቃል ። ለምሳሌ አናጢነት ፣ ግንበኝነት ፣ ወዘተ. ተጨባጭ ሥራዎች ናቸው ። እነኝህ የሥራ ዓይነቶች በዓይነታቸው እጅግ በጣም ብዙ ናቸው ። ረቂቅ ሥራ በማናቸውም ተጨባጭ የሥራ ሂደት ውስጥ በዓይነት ሳይለይ የሚፈሰው ወይም የሚውለው የሰው የሥራ ኃይል ነው ። ሸቀጦች በጠቀሜታቸው የሚለያዩ ቢሆንም በውስጣቸው በጋራ በያዙት በረቂቅ ሥራ ምክንያት ተመሳሳይነት አላቸው ። የሸቀጦች የልውውጥ እሴት መሠረትም ይኸው ረቂቅ ሥራ ነው ።

እንግዲህ ሸቀጦች በጠቀሜታ እሴትነታቸው የተለያዩ የሙያ ውጤቶች ማለትም የተጨባጭ ሥራ ውጤቶች ሲሆኑ ፣ በልውውጥ እሴትነታቸው ደግሞ የረቂቅ ሥራ ውጤቶች ናቸው ። የሸቀጦች የልውውጥ እሴት የሚወሰነው ሸቀጡን ለማምረት በፈሰሰው ማኅበራዊ ተቀባይነት ባለው የሥራ ጊዜ ነው ። ማኅበራዊ ተቀባይነት ያለው የሥራ ጊዜ የሚባለው በተለመደው የአሠራር ሁኔታ ፣ በወቅቱ ባለው አማካይ ዕውቀትና የአሠራር ቅልጥፍና ደረጃ መሠረት አንድን ዕቃ ለማምረት የሚያስፈልገው የሥራ ጊዜ ነው ። ምንም እንኳ ከላይ

እንደተገለጸው የሸቀጥ ምርት ገኖ የታየው በካፒታሊስት ስልተ ምርት ቢሆንም ይህ የምርት ዓይነት የታየባቸውን ሥርዓቶች በሙሉ የሚያቅፍ በእሴት ሕግ የሚገዛ አጠቃላይ የሆነ ግንኙነት አለ ። ይህ ግንኙነት ለሸቀጦች ዋጋ ዋነኛ መሠረት ነው ።

የሸቀጦች ግንኙነት ሸቀጦችን ለማምረት ባስፈለገው ማኅበራዊ ተቀባይነት ባለው የሥራ ጊዜ ሲከሰት የሥራ ማኅበራዊ ይዘት በሸቀጦች ግንኙነት ወይም ልውውጥ ይገለጣል ። በዚህ ሁኔታ የአንድ ሸቀጥ የእሴት መጠን ከጠቅላላው የኅብረተሰብ የሥራ ጊዜ ውስጥ ሸቀጡን ለማምረት የወሰደውን የጊዜ ድርሻ ይገልጻል ። ይህም የሸቀጡ ድርሻ እያንዳንዱን ሸቀጥ በተወሰነ ተዛምዶ (ratio) ከሌሎች ሸቀጦች ጋር በእኩያዊነት ለመታየት ያስችለዋል ። አሁን ኅብረተሰብ በደረሰበት የዕድገት ደረጃ ለሸቀጦች እሴት በመለኪያነት የሚያገለግለውና የእሴት ሁለንተናዊ መለኪያ የሆነው ገንዘብ (ወርቅ) ሲሆን የሸቀጡ የእሴት መጠን በገንዘብ መልኩ ዋጋ ነው ።

2. የሸቀጥ ምርትና ልውውጥ ውስጣዊ የቁጥጥር ሕግ

ስለሸቀጥ ኢኮኖሚ አንዳንድ መሠረታዊ ጽንሰ ሐሳቦችን ካየን ከዚህ በመነሣት የሸቀጥ ውስጣዊ ቁጥጥር ሕግ ስለሆነው ስለ እሴት ሕግ ምንነት ለማብራራት እንሞክር ።

በሸቀጥ ኢኮኖሚ እያንዳንዱ አምራች (ገበሬ ፣ የዕደ ጥበብ ባለሙያ ወይም ካፒታሊስት*) ምርቱን ለገበያ ያቀርባል ። ይሁን እንጂ ማናቸውም ቢሆኑ ኅብረተሰቡ የሚፈልጋቸውን ምርቶች በዓይነትና በብዛት በውል አስቀድመው ለማወቅ ወይም በትክክል ለመተንበይ ስለማይችሉ በተቻላቸው መጠን የሥራ ጊዜያቸውን እንዲሁም የምርት መገልገያዎችን የሚደለድሉት ባለፈው የገበያ ሁኔታ ላይ በመመሥረት ከፍተኛ ገቢ ወይም ትርፍ ለማስገኘት ያስችሉናል ብለው የሚገምቷቸውን ምርቶች በአነስተኛ የሥራ ጊዜ በማምረት ነው ። በዚህ የተነሣ እያንዳንዱ አምራች ገቢውን (ትርፉን) ለማሳደግ ካለው ዓላማ አንፃር በሚያደርገው ውድድር ከኅብረተሰቡ (ከገበያው) ፍላጎት በላይ የሆነ የሸቀጥ ምርት ለገበያ ይቀርባል ።[3] በልውውጡ ሂደት እያንዳንዱ አምራች ለገበያ ያቀረባቸው ሸቀጦች የእሴት መጠን የሚለካው እሱ ለማምረት በፈጀበት የሥራ ጊዜ ሳይሆን ሸቀጡን ለማምረት በሚያስችለው ማኅበራዊ ተቀባይነት ባለው የሥራ ጊዜ ነው ። እያንዳንዱ አምራች በተሰማራበት የምርት ዘርፍ የፈጀበት የሥራ ጊዜ ማኅበራዊ ተቀባይነት ካለው የሥራ ጊዜ የበለጠ ወይም ያነሰ ሊሆን ይችላል ። ማኅበራዊ ተቀባይነት ካለው ጊዜ በታች የፈጁት ሸቀጥ አምራቾች ከቀሩት የተሻለ ገቢ ወይም ትርፍ ያገኛሉ ። በዚህ ውድድር ሂደት ማኅበራዊ ተቀባይነት ካለው የሥራ ጊዜ በላይ በመውሰድ ሸቀጣቸውን ያመረቱ ስለሚከስሩ ከውድድሩ ለመውጣት ይገደዳሉ ። የቀሩት ግን በውድድሩ ውስጥ ለመቆየት ከመቼውም በተሻለ ሁኔታ በአነስተኛ አስፈላጊ የሥራ ጊዜ በማምረት ተወዳዳሪዎቻቸውን ከገበያ ለማስወጣት ይጥራሉ ። ይህ የእሴት ሕግ ውጤት ሲሆን ሕጉ የሸቀጥ ኢኮኖሚ በሰፈነባቸው ሁሉ የዋጋዎችን እንቅስቃሴ የሚቆጣጠር ኃይል ነው ። በአጭሩ የእሴት ሕግ ሸቀጦች ሲለዋወጡ ልውውጡ የሚካሄ

* ካፒታሊስቱ ቀጥታ አምራች ባይሆንም በገበያ እንደአምራች ሆኖ ነው ሸቀጡን የሚያቀርበው ።

ደው በሚለዋወጡት ሸቀጦች ውስጥ በተጠናቀረው ማኅበራዊ ተቀባይነት ባለው የሥራ ጊዜ መጠን መሆኑን የሚቆጣጠር ነው ።[4]

አንድ ሸቀጥ ለማምረት የሚያስፈልገው የሥራ ጊዜ ካልተለወጠ የሸቀጡ እሴትም የማይለወጥ ሲሆን ነገር ግን ሸቀጡን ለማምረት የሚወስደው የሥራ ጊዜ ከእያንዳንዱ የሥራ ምርታማነት መለዋወጥ ጋር አብሮ ይለዋወጣል ። ይህ ምርታማነት በልዩ ልዩ ሁኔታዎች የሚወሰን ሲሆን ከእነዚህም መካከል የሠራተኛው አማካይ የዕውቀት ደረጃ ፣ የሳይንስ ዕድገት ደረጃና በምርት ሥራ ላይ የዋለበት መጠን ፣ የምርት ማኅበራዊ አደረጃጀት ፣ የምርት መገልገያዎች ብዛትና የማምረት ዐቅም እንዲሁም የተፈጥሮ ሁኔታዎች ይገኛሉ ።[5]

“በምንም ዓይነት ዘዴ የተለያዩ ሸቀጦች ዋጋ ተዛምዶ ቢተመን ወይም ቁጥጥር ቢደረግበትም በዋጋዎቹ መካከል ሊከሰት የሚችለውን ውጣ ውረድ ምንጊዜም የሚቆጣጠረው (የሚገዛው) የእሴት ሕግ ነው ”[6]

የእሴት ሕግ በሸቀጥ ኢኮኖሚ ላይ ያለው የቁጥጥር ባሕርይ ፣ ሊያስከትላቸው የሚችለው ውጤቶችና የዕድገት አቅጣጫዎች የሚከተሉት ናቸው ።[7]

ሀ/ የእሴት ሕግ አሠራር በሸቀጥ ምርት ሂደት ውስጥ የምርት መገልገያዎችና የሥራ ኃይል በተለያዩ የምርት ዘርፎች ግብታዊ በሆነ መንገድ (spontaneously) እንዲደለደሉ ይመራል ፣ ይቆጣጠራል ። (Allocation and distribution functions)

የአንድ ኅብረተሰብ የምርት ፍላጐት በመጠን የሚገለጥና ሊገለጥ የሚችል ቢሆንም የካፒታሊስቱ ኅብረተሰብ የምርት ሂደት በጥናትና በዕቅድ ላይ የሚመሠረት አይደለም ። ካፒታሊስቶች አንድ ዓይነት ምርት ለማምረት ፈቃደኛ የሚሆኑትና የሚያመርቱት ምርቱ በገበያ የተሻለ ትርፍ የሚያስገኝ መሆኑን ሲያምኑበት ነው ። በዚህ ዓይነት ብዙ ካፒታሊስቶች የተሻለ ትርፍ የሚያስገኝ አንድ ሸቀጥ ማምረት ይጀምራሉ ።

ማምረቱም እየቀጠለ ሲሄድ የሸቀጡ ምርት መጠን ኅብረተሰቡ ከፈለገው በላይ ይሆንና ዋጋው ይቀንሳል ። ቀድም ሲል በትርፍ ይሸጥ የነበረው በኪሣራ መሸጥ ይጀምራል ። በዚህ ጊዜ ብዙ ካፒታሊስቶች ይህን ሸቀጥ ማምረት በማቆም ያላቸውን የሥራ ኃይልና ካፒታላቸውን ለሌላ ዓይነት ሸቀጥ ምርት ያውላሉ ወይም ይደለድላሉ ። ለዚህ ውሣኔ ወይም ድልድል መሠረታዊ መንሥኤ የሸቀጥ ሕግ ነው።[8]

ለ/ እያንዳንዱ አምራች ከጥቅሙ አንፃር የተቻለውን ሁሉ በማድረግ በአነስተኛ የሥራ ጊዜ ለማምረት በሚያደርገው ጥረት ማለትም ማኅበራዊ ተቀባይነት ባለው የሥራ ጊዜ ገደብ ውስጥና ቢቻልም ባነሰ የሥራ ጊዜ መጠን ለማምረት በሚያደርገው ውድድር የቴክኖሎጂን መሻሻል ያፋጥናል ፤ በአጠቃላይም የምርት ኃይሎች እንዲዳብሩ በመገፋፋት የምርት ኃይሎች ዕድገት አቅጣጫ ወደ ከፍተኛ ደረጃ እንዲደርስ ያደርጋል ።

በካፒታሊስቱ ምርት ሂደት የዚህ ዓይነቱ ውድድር ወይም ግፊት የማያቋርጥ በመሆኑ በየጊዜው በሚደረስበት የምርት ኃይሎች የዕድገት ደረጃ በተሻለ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ የሚጠቀሙ ካፒታሊስቶች የላቀ ትርፍ ያገኛሉ ።

ይህ ወድድር በእሴት ሕግ ግፊት የሚካሄድ በመሆኑ ነው ሕጉ ለምርት ኃይሎች ዕድገት አስተዋጽኦ ያደርጋል የሚባለው ።

ሐ/ አመቺ ሁኔታ በተፈጠረበት ሁሉ የእሴት ሕግ ቀላል የሸቀጥ ምርት ወደ ከፍተኛ ካፒታሊስት የሸቀጥ ምርት ማለት ሁለንተናዊ የሸቀጥ ምርት ወደ ገነነበት ስልተ ምርት እንዲሸጋገር ያደርጋል ።

“የዋጋ እንደሁኔታው ከእሴት በላይም ሆነ በታች መዋገርቅ የሚያስከትለው የምርት መገልገያና የሥራ ኃይል አሠረጫጨት ቅጥ ማጣት ፣ በሸቀጥ አምራቾች መሀል የገቢ ብሎም የሀብት መበላለጥንና ፉክክርን ያፋፍማል ” ።[9] የተጠናከሩትና በውድድሩም አሸናፊ የሆኑት ጥቂት ካፒታሊስቶች አነስተኛ የሸቀጥ ምርት የሚያመርቱ ግለሰቦችን እየዋጧቸው ከውድድሩ ያስወጧቸዋል ።

የእሴት ሕግ የሚሠራው በሸቀጥ ኢኮኖሚ ማምረት ልውውጥ ሂደት ውስጥ በግብታዊነት ቢሆንም ያለው የመቆጣጠር ባሕርይ በቀላሉ ሊታይ አይችልም ። ይህ ሕግ ሰዎች በሸቀጥ ማምረትና ልውውጥ ሂደት ውስጥ ከፍተኛ ገቢ (ትርፍ) ለማግኘት በሚያደርጉት ግላዊ እንቅስቃሴ የሚመራ ፣ የማኅበራዊ ሥራ ውጤት የሆነና መልሶ በእነሱ የወደፊት እንቅስቃሴ ላይ ቁጥጥር የሚያደርግ ነባራዊ ሕግ ነው ።

ጠቅለል ባለ መልክ ሲታይ የእሴት ሕግ በሸቀጥ ኢኮኖሚ የምርት ኃይሎች ድልድል ተቆጣጣሪ ፣ የዕድገቱን አቅጣጫ መሪ፤ በሸቀጥ ምርት ልውውጥ ሂደት የሰዎች ግንኙነት ውጤት የሆነ ፣ ግን መልሶ በኅብረተሰብ ግንኙነት ላይ ተጽዕኖ የሚያደርግ ግብታዊ የሆነ ነባራዊ የኢኮኖሚ ሕግ ነው። እንደማንኛውም ነባራዊ ሕግ ሰዎች አውቀውት ሆን ብለው ለኅብረተሰብ ዕድገትና ለማኅበራዊ ጥቅማቸው ሲሉ ግብታዊ ባሕርያቱን ያግሩት እንጂ ሊሽሩት ያልቻሉት ሕግ ነው ። የእሴት ሕግ በቅድመ ካፒታሊስት የነበረ ፣ በድኅረ ካፒታሊስት ያለና ወደፊትም የሸቀጥ ምርት እስካለ ድረስ የሚኖር ሕግ ነው ። የሸቀጥ ምርት ከፍተኛ ደረጃ በደረሰበት በካፒታሊስት ሥርዓት በተደጋጋሚ መድረስና የኢኮኖሚ ቀውስ እንዲደርስና ለብዙ ሠርቶአደሮች ሥራ አጥነት ፣ ለአያሌ ቤተሰብ መፍረስና ለማኅበራዊ ችግሮች መከሰት ምክንያቱ ምን እንደሆነ ፣ በአንፃሩም የተመረተው ምርት የሕዝቡ ገቢ አቅም በመዳከሙ ገገር አጥቶ የሚበሰብስበት ሁኔታ ለመረዳት የሚቻለው የእሴት ሕግን ምንነት ለመገንዘብ ሲቻል ነው ።

3. የአቅርቦትና የፍላጐት አመሠራረት

እንደሚታወቀው በአጠቃላይ ካፒታሊስቱ የሚያመርተው ሸቀጥ ውጤት የሚለካው ለእሱ ሊሰጠው ከሚችለው የጠቀሜታ እሴት አንፃር ሳይሆን ሸቀጡ ከሚያስገኝለት ትርፍ አንፃር ነው ። ከፍተኛ ትርፍ ለማግኘት እያንዳንዱ ካፒታሊስት ከሌሎች ካፒታሊስቶች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ሁኔታ ተወዳዳሪ ሲሆን ይህንንም ውድድር በሁለት ክፍሎ ማየት ይቻላል ።

በመጀመሪያ በአንድ የተወሰነ የምርት ዘርፍ (intra-industry) የተሰማሩ ካፒታሊስቶች ያመረቷቸውን ሸቀጦች ለመሸጥ እርስ በርሳቸው ይወዳደራሉ ። በዚህም ሂደት በተለያየ ሁኔታ የተመረቱ ፣ ነገር ግን የጥራት ደረጃቸው እኩል የሆኑ ተመሳሳይ ሸቀጦች እሴቶቻቸው የተለያዩ ቢሆንም የሚሸጡት በአንድ የገበያ እሴት ይሆናል ።

ከዚህም የሚነሣው ጥያቄ አንድ የገበያ እሴት እንዴት ይፈጠራል? የሚል ሲሆን በመጀመሪያ ደረጃ አምራቾች ሸቀጦቻቸውን በአንድ የጋራ ገበያ ማቅረባቸውን እንደመነሻ አድርጐ መውሰድ ያስፈልጋል። የእያንዳንዱ ሸቀጥ እሴት ከገበያ እሴት በላይ ወይም በታች ቢሆንም በኢንዱስትሪው ለተመረቱት ሸቀጦች ሁሉ እንደ አንድ የገበያ እሴት የሚያገለግል አማካይ መሸጫ ሊኖር ይችላል። ዳሩ ግን ይህ የማይሆንበት የአቅርቦትም ሆነ የፍላጐት ሁኔታዎች አሉ። ፍላጐት ከአቅርቦት ከበለጠ ሸቀጦች የሚሸጡት ከጠቅላላው ማኅበራዊ ፍላጐት አንፃር ከፍተኛ ወጪ ያለው ሸቀጥ በተመረተበት እሴት ሊሆን ይችላል። አቅርቦት ከፍላጐት ከበለጠ ደግሞ በሸቀጦቹ ዋጋ ከአማካይ እሴት በታች ሊሆን ይችላል። በዚህ ምክንያት የገበያው እሴት ከአማካይ እሴት ከፍም ዝቅም ሊል ይችላል። ስለዚህ የገበያውን እሴት ለመወሰን በአንድ በኩል የገበያውን ፍላጐት ማወቅ በሌላ በኩል ደግሞ አቅርቦትን ከፍላጐት ማጣጣም ያስፈልጋል። ከዚህ በኋላ የተለያዩ የምርትና የማኅበራዊ ፍላጐት ሁኔታዎችን የሚያሟሉ ከሸቀጦቹ አማካይ እሴት የገበያ እሴት ለኢንዱስትሪው ይመሠረታል። በዚህ ሁኔታ በአንድ የኢንዱስትሪ ዘርፍ የተመሠረቱና ተመሳሳይ ውስጣዊ የጥንቅር ደረጃ ያላቸው ሸቀጦች ዋጋቸው በገበያ እሴት ይወሰናል።

ሌላው የውድድር መስክ የካፒታሊስት ኢኮኖሚ ባለ ብዙ የምርት ዘርፎች በመሆኑ የተለያየ የካፒታል ውስጣዊና ቴክኒካዊ ጥንቅሮቹ እያደጉ ካፒታል በብሔራዊ ደረጃ ሲስፋፉ የሚከሰተው የውድድር ዓይነት ነው። በተለያዩ የምርት ዘርፎች የተሰማሩ ከበርቴዎች ካፒታላቸውን ከፍተኛ የትርፍ መጣኔ ወደሚያስገኝበት ዘርፍ በማዞር በሙአለንዋያቸው (በኢንቨስትመንታቸው) ከፍተኛ የትርፍ መጣኔ ለማግኘት በሚያደርጉት ውድድር (inter-industry competition) በሁሉም ዘርፍ የሚገኙት የትርፍ መጣኔዎች ወደ አንድ አማካይ የሆነ የትርፍ መጣኔ ያመራሉ።

የካፒታሊስት ውድድር በዚህ ሁኔታ እየዳበረ በሄደ መጠን ሸቀጦች የሚለዋወጡት በእሴታቸው መጠን መሆኑ ቀርቶ በማምረቻ ዋጋቸው* ወደ መሆን ያመራል። ያም ሆነ ይህ ምንም ጊዜ ቢሆን የሸቀጦች ዋጋ የሚወሰነው በእሴታቸው ሲሆን ሸቀጦችን ለማምረት የፈጀው ማኅበራዊ ተቀባይነት ያለው የሥራ ጊዜ ዝቅ ካለ የማምረቻ ዋጋቸውም ዝቅ ይላል፤ ከፍ ካለ ደግሞ እንዲሁ ከፍ ይላል።

የሸቀጦችን የማምረቻ ዋጋ ከእሴቶቻቸው ሊያዛቡ ከሚችሉት ሁኔታዎች መካከል ዋና ዋናዎቹ፦ ሀ/ የሸቀጦች ልውውጥ በአጋጣሚ ወይም አልፎ አልፎ እንዲሆን መደረግ፤ ለ/ በሻጭና በገዥ መካከል ቀጥተኛ ልውውጥ በሚደረግበት ጊዜ በሁለቱም በኩል በቂ ሸቀጦች አለመገኘትና ሐ/ በሸማቹ በኩል በተፈጥሮ ሁኔታዎች የተነሣ ወይም በሰው ሠራሽ ሁኔታዎች ሳቢያ ዋጋ ለማስወደድ ወይም ቀንሶ ለመሸጥ የሚያስገድዱ ሁኔታዎች መኖር ናቸው። እነዚህ ሁኔታዎች የፍላጐትና የአቅርቦት ሚዛንን ሊለውጡ ይችላሉ።

የአቅርቦትና የፍላጐት ሚዛን መዛባት በጠቀሜታ እሴትና በእሴት፤ በሸቀጥና በገንዘብ፤ በሻጭና በገዢ መካከል ያለውን

* አንድ ሸቀጥ ለማምረት ሲል ካፒታሊስቱ የማምረቻ መሣሪያዎችን ለመግዛትና የሰው የሥራ ኃይል ቀጥሮ ለማሠራት የሚያወጣው የተጠቃለለ ወጪ ነው። የማምረቻ ወጪ ተረፈ እሴትን ሳይጨምር የሚሰላ በመሆኑ ከሸቀጦች እሴት የተለየ ነው። የካፒታሊስት የማምረቻ ወጪ ካፒታሊስቱ በሸቀጡ ምርት ውስጥ የራሱን ጉልበት አለማፍሰሱን ነገር ግን ካፒታሉን ብቻ ወጪ ማድረጉን የሚያሳይ ነው።

ግንኙነት ያንፀባርቃል፤ የአቅርቦትና የፍላጐት ሚዛን በአንድ በኩል የገበያ ዋጋ ከገበያ እሴት ወይም ከማምረቻ ዋጋ እንዴት እንደሚለይ ለማስረዳት ሲያስችል፤ በሌላ በኩል ደግሞ ይህ በእሴት ወይም በማምረቻ ዋጋ እና በዋጋ መካከል ያለውን ልዩነት ለማጥበብ ያለውን አዝማሚያ ያስረዳል።[10]

የሸቀጦች የገበያ ዋጋ የሚወሰነው በውድድር ሲሆን ይህም ውድድር በሻጮች መካከል፤ በገዢዎች መካከል፤ እንዲሁም በሻጮችና በገዢዎች መካከል የሚደረግ ነው። የአንድ ሸቀጥ አቅርቦት ከኅብረተሰቡ ፍላጐት በጣም ያነሰ ሲሆን፤ በገዢዎች መካከል የሚኖረው ውድድር ከፍተኛ፣ በሻጮች መካከል ያለው ውድድር ደግሞ ዝቅተኛ በመሆኑ የመሸጫው ዋጋ ከፍተኛ ይሆናል። በካፒታሊስት ሥርዓት አብዛኛውን ጊዜ ከፍ ያለ ትርፍ ለማግኘት ምርትን በስፋት ለገበያ ለማቅረብ ስለሚሞከር ከፍላጐት በላይ በሻጮችና በገዢዎች መካከል በተለይም በሻጮች መካከል የመረረ ውድድር ያስከትልና የዋጋ ማሽቆልቆልና የቴክኖሎጂ ለውጥ ይከሰታል።

እዚህ ላይ ዋጋው ከፍተኛ ወይም ዝቅተኛ ነው ሲባል ከምን አንፃር ነው? የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። የአቅርቦትና የፍላጐት ሚዛን (ግንኙነት) የመሸጫ ዋጋ ውጣውረድን ከወሰነ፤ በአቅርቦትና በፍላጐት መካከል ያለውን ግንኙነት ምን ይወስነዋል?

አቅርቦት በሸቀጥ መልክ የተመረተውን ምርት የሚያመለክት ሲሆን ፍላጐት ደግሞ በገንዘብ መልክ የሚገለጽ ማኅበራዊ የመግዛት አቅምን የሚያሳይ ነው። ሁለቱም ተነጣጥለው የማይታዩና አንዱ በሌላው ሕልውና ላይ የበኩሉን ሚና በሚጫወትበት ሁኔታ የተያያዙ ናቸው። አቅርቦት ሸቀጦች በተወሰነ መጠን እንዲመረቱና የተወሰነ ዋጋ እንዲኖራቸው ዘማድረግ ፍላጐትን ይቀርፃል፤ መልክ ያስይዛል። ፍላጐትም በተራው የሸቀጥ ምርትን መጠንና አወቃቀር (structure) ይወስናል። በካፒታሊስት ኅብረተሰብ ውስጥ በፍላጐትና በአቅርቦት መሐከል ያለው ግንኙነት ካፒታሊስቱ በየትኛው የምርት ዘርፍና አቅጣጫ ሙአለንዋዩን ቢያሰማራ ከፍተኛ ትርፍ ማግኘት እንደሚችል ያመለክታል። አቅርቦት ከፍላጐት ያነሰ እንደሆነ የሸቀጥ ዋጋ ከማምረቻ ወጪው በላይ ከፍተኛ ዕድገት ይኖረዋል። በዚህ ወቅት ቀደም ሲል የተመረቱ ሸቀጦች ገዢ ስለማይኖራቸው ዋጋቸው ይቀንሳል። ካፒታሊስቶችም ከፍተኛ ትርፍ የሚገኝበትን ሸቀጥ ለማምረት በሚያስችሏቸው የምርት ዘርፎች ሙአለንዋያቸውን ያሰማራሉ። በዚህም ሳቢያ ከፍተኛ ምርት ለገበያ ስለሚቀርብ አቅርቦት ከፍላጐት በላይ ይሆናል። በሻጮችና ገዢዎች እንዲሁም በሻጮች መካከል ያለው ውድድር የሸቀጡ ዋጋ ከገበያው እሴት ወይም ከማምረቻ ዋጋው በታች እንዲወርድ ያደርገዋል። እንደገና ካፒታል ከዚህ ዘርፍ ለቆ ሌላ ከፍተኛ (የትርፍ መጣኔ) የገበያ ዋጋ ወዳለበት ዘርፍ ስለሚሰማራ በዚህ ሁኔታ የአቅርቦትና ፍላጐት ሚዛን እንደገና ሲጠበቅ የሸቀጡ መሸጫ ዋጋና የማምረቻ ዋጋው እኩል ይሆናል።

ካፒታል በአንድ በኩል የገበያው ዋጋ ከማምረቻ ዋጋ ከፍ ወደ አለበት ኢንዱስትሪ በመግባት፤ በሌላ በኩል ደግሞ የገበያው ዋጋ ከማምረቻ ዋጋው ዝቅ ካለበት በመውጣት በገበያ ዋጋና በማምረቻ ዋጋ መካከል ያለው ልዩነት እንዲጠበብ ሁል ጊዜ ግፊት ያደርጋል።

አጠቃላይ በካፒታሊስት ኢኮኖሚ እን

ቅስቃሴ ውስጥ በሻጮች (አምራቾች) መካከል ፣ በገዢዎች (ሸማቾች) መካከልና በገዢዎችና በሻጮች መካከል የሚደረገው ውድድር ለሸቀጡ ጥራት ፣ ብዛትና ፣ የዋጋ ዝቅተኛነት አስተዋጽኦ አለው ። በዚህም መሠረት የሸቀጥ ዋጋ በውድድር (አቅርቦትና ፍላጐት) ሲወሰን በአንጻሩ ደግሞ አቅርቦትና ፍላጐት በምን ይወሰናል? ለሚለው ጥያቄ ማርክሳዊ ሌኒናዊ ፖለቲካ ኢኮኖሚ የሚሰጠው መልስ በእሴት ሕግ የሚል ነው ።

4. ማርክሳዊ ሌኒናዊ የመሬት ኪራይ ንድፈ ሐሳብ

በካፒታሊስት ኢኮኖሚ ውስጥ የሸቀጥ ምርት ሁለንተናዊነት ያገኘ በመሆኑ ሸቀጥ የሚሆኑት በኢንዱስትሪ ተመርተው የሚወጡ ምርቶች ብቻ ሳይሆኑ የሰው ጉልበት፣ መሬትና የሰው ጉልበት ፈሶባቸው በተፈጥሮ ረዳትነት የሚገኙ ምርቶች ማለትም በሸቀጥ መልክ ልውውጥ የሚቀርቡት የእርሻ ምርቶች ጭምር ናቸው ።

እንደሚታወቀው ሁሉ የኢንዱስትሪ ሸቀጦች ዋጋ መሠረት ሸቀጦችን ለማምረት የፈጀው ማኅበራዊ ተቀባይነት ያለው የሥራ ጊዜ ወይንም እሴታቸው ነው ። ማኅበራዊ ተቀባይነት ያለው የሥራ ጊዜ ደግሞ የሚወሰነው በጊዜው ባለው አማካይ የቴክኖሎጂ ደረጃና የማምረት ሁኔታ መሆኑ ተመልክቷል ። በኢንዱስትሪው መስክ የምርቶች ዋጋ አወሳሰን በአማካይ ወጪ ላይ የተመሠረተ ከሆነ በእርሻው ክፍለ ኢኮኖሚ የዋጋ አመሠራረት በምን ላይ የተመረኰዘ ነው?

የእርሻ ውጤቶችን ለማምረት ከፍተኛ ድርሻ ያለው መሬት ነው ። መሬት ከሌሎች የምርት መገልገያዎች ለየት ያለ ጠባይ ያለው ሲሆን ይህም ጠባዩ የሚገለጽባቸው መልኮች ፡-

ሀ መሬት የሰው የሥራ ውጤት አለመሆኑ ፣
ለ መጠኑ የተወሰነ በመሆኑ እንደ ካፒታል ሊበዛና ሊራባ አለመቻሉና
ሐ በማንኛውም አገር ውስጥ ቢሆን የተለያየ የለምነት ደረጃ ያላቸው የመሬት ዓይነቶች መኖራቸው ናቸው ።

በካፒታሊስት አገሮች መሬት በግል ባለቤትነት ሥር ያለ ቢሆንም እንደ ፊውዳሉ ሥርዓተ ማኅበር በፊውዳል ባለመሬቶችና በገባሮች መሀከል ካለው የምርት ግንኙነት የተለየ ነው ። አብዛኛውን ጊዜ መሬቱን የሚያርሱት እራሳቸው የመሬት ከበርቴዎች ሳይሆኑ በእርሻ ተግባር ላይ ለማዋል ለፈለገ ካፒታሊስት መሬቱን ያከራያሉ ። መሬቱን የተከራየው ካፒታሊስት የእርሻ ሠራተኞችን ቀጥሮ በማሰራት ተረፈ እሴት እንዲፈጠር ያደርጋል። በዚህ ሁኔታ የተፈጠረውን ተረፈ እሴት ካፒታሊስቱ በሁለት ይከፍለዋል ። አንደኛውን ክፍል የግል ትርፍ በማድረግ ለራሱ ሲያስቀር ሌላውን ክፍል በመሬት ኪራይ ስም ለባለመሬቱ ያስተላልፋል ። በመሆኑም የመሬት ኪራይ ንድፈሐሳብ ከሚከተሉት ሁኔታዎች የሚነሣ ይሆናል።

ሀ/ የመሬት ከበርቴው መሬቱን ለካፒታሊስት ማከራየት ፣
ለ/ መሬቱን የተከራየው ካፒታሊስት በቅጥር ሠራተኞች አማካይነት የምርት ሥራውን ማከናወንና
ሐ/ የተፈጠረውን ተረፈ እሴት (surplus value) የመሬት ከበርቴውና ካፒታሊስቱ መካፈል ናቸው ።

በካፒታሊስም ሥርዓተ ማኅበር ሁለት ዓይነት የመሬት ኪራይ ያለ ሲሆን እነርሱም የልዩነት ኪራይና ፍጹማዊ ኪራይ በመባል ይታወቃሉ ። እነዚህ የኪራይ ዓይነቶች ምንድን ናቸው?

4፡1 የልዩነት ኪራይ Differential Rent)

ቀደም ብሎ እንደተገለጸው በኢንዱስትሪ ውስጥ የሸቀጦች እሴትም ሆነ የማምረቻ ዋጋቸው የሚወሰነው አማካይ የቴክኖሎጂና የአመራረት ሁኔታዎችን በታሳቢነት በመውሰድ ነው ። በእርሻ ውስጥ ግን ሁኔታው ከዚህ ለየት ያለ ነው ። መሬት ውሱን በመሆኑ እንደተፈለገው ለመጨመርና ለማስፋፋት አይቻልም ። የተለያዩ ማሣዎች የተለያየ የለምነት ደረጃ ስላላቸው በእነዚህ ሁኔታዎች የተነሣ የሚሰጡትም የምርት መጠን ይለያያል ። ከዚህም በተጨማሪ ለከተሞችና ለመንገዶች ቅርብ የሆነ እርሻ ያላቸው ገበሬዎች ምርታቸውን በቀላሉና በትንሽ ወጪ ለገበያ ለማቀረብ እንደሚችሉ ለመገመት አያዳግትም ። ነገር ግን በገበያ ላይ የሚፈለገው ምርት ለምና ቅርብ በሆኑ መሬቶች ላይ ብቻ በሚመረተው ስለማይረካ የገበያውን ፍላጐት ለማርካት ዝቅተኛ የለምነት ደረጃ ባላቸው መሬቶች ላይ የተመረተውም ምርት ለገበያ ይቀርባል። ስለዚህ የምርቱ እሴት (ዋጋ) የሚወሰነው አማካይ የለምነት ደረጃ ባላቸው መሬቶች ላይ በተመረተው ምርት ሳይሆን ዝቅተኛ የለምነት ደረጃ ባለው ነው ። ይህም የሚሆንበት ምክንያት መሬት የተወሰነ በመሆኑ ፣ ለም መሬቶችን እንደተፈለገው ለማስፋፋት ስለማይቻልና በመጨረሻ የለምነት ደረጃ ያሉ መሬቶችን የሚያርሱ ካፒታሊስቶችም ቢሆኑ ትርፍ ማግኘትና ኪራይ መክፈል ስለሚኖርባቸው ነው ። ትርፍ የማያገኙ ከሆነ ግን ካፒታላቸውን ከግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ በማውጣት ወደ ኢንዱስትሪ ምርት ለመዞር ይገደዳሉ።

ከላይ እንደተጠቀሰው ዝቅተኛ ለምነት ያለውን መሬት የሚያርሰው ካፒታሊስት ትርፍ የሚያገኝ ከሆነ ሌሎች በአማካይና በለምነት ደረጃ የሚገኙትን ማሣዎች የሚያርሱ ካፒታሊስቶች ከአማካይ ትርፍ በላይ ተጨማሪ ትርፍ ያገኛሉ ። ይህ በአፈር ለምነት ልዩነት የሚገኝ ትርፍ የልዩነት ኪራይ በመሆን በመሬት ከበርቴው ይወሰዳል ። ይህን በመሬት ለምነት ምክንያት የሚመጣውንና የመሬት ከበርቴው በኪራይ መልክ የሚወስደውን ትርፍ ካርል ማርክስ የልዩነት ኪራይ ቁጥር 1 በማለት ይጠራዋል ። የዚህን የልዩነት ኪራይ አፈጣጠር የሚያሳይ አኀዛዊ መግለጫ አባሪ 1 ላይ ቀርቧል ።

ከላይ ከተጠቀሰው የልዩነት ኪራይ ቁጥር 1 በተጨማሪ የልዩነት ኪራይ ቁጥር 2 በመባልም የሚታወቅ የኪራይ ዓይነትም አለ ። ይህም የሚከሰተው መሬት የተከራየው ካፒታሊስት ምርትን ለማሳደግ ተጨማሪ ሙአለንዋይ በመሬቱ ላይ በማዋል ፣ እንደ መስኖ ፣ መንገዶች ፣ መጋዘን ፣ ትራክተር ፣ ማዳበሪያ የመሳሰሉትን መጠቀም ሲጀምር ነው ። የኮንትራቱ ጊዜ እስካለቀ ድረስ በተሻሻለ ቴክኖሎጂ በመጠቀም የሚገኘው ተጨማሪ ትርፍ የተከራዩ ካፒታሊስት ሲሆን የኮንትራቱ ጊዜ አልቆ ኮንትራቱን ለማደስ ሲፈልግ ግን የመሬት ከበርቴው ይህን ተጨማሪ ትርፍ በልዩነት ኪራይ ቁጥር 2 መልክ ይወስድበታል ። አለበለዚያ ኮንትራቱን አያድስለትም ። ምንም እንኳ ካርል ማርክስ በካፒታል ቅጽ 3 ውስጥ የተለያዩ ታሳቢዎችን በመውሰድ የልዩነት ኪራይ ቁጥር 2ትን ቢተነትንም የመጨረሻው ማጠቃለያ የዚህ የኪራይ ምንጩ የምርታማነት ማደግ መሆኑን ይገልጻል ።

4:2 ፍጹማዊ ኪራይ (Absolute Rent)

ከላይ ከተጠቀሱት ሁለት ዓይነት የልዩነት ኪራዮች በተጨማሪ በካፒታሊዝም ውስጥ ፍጹማዊ የመሬት ኪራይ በመባልም የሚታወቅ የመሬት ኪራይ ዓይነት አለ ። ቀደም ብሎ እንደተመለከተው የልዩነት ኪራይ የሚፈጠረው ለም በሆኑ ማሣዎች ላይ ሲሆን ጠፍ ማሣዎች የልዩነት ኪራይ ለመፍጠር አይችሉም ። ሆኖም በእርሻ ምርቶች ላይ በሚታየው ከፍተኛ የፍላጐት መጠን ምክንያት እነዚህም መሬቶች ቢሆኑ በእርሻ ሥራ ላይ መዋል አለባቸው ። እዚህ ላይ የሚነሣው ጥያቄ ከእነዚህ መሬቶች የልዩነት ኪራይ የማይገኝ ከሆነ ካፒታሊስቱ ከየት አምጥቶ የመሬት ኪራይ ይከፍላል ? የሚለው ነው ። ይህንን ኪራይ ካፒታሊስቱ ለመክፈል የሚችለው የእርሻ ምርቱን ከማምረቻ ዋጋው በላይ ሲሸጥ ብቻ ነው ። ይህም ማለት በመጨረሻ ዝቅተኛ የለምነት ደረጃ ያለውን መሬት የሚያርሰውም ካፒታሊስት ቢሆን ከአማካይ ትርፍ (average profit) በላይ ተጨማሪ ትርፍ ማግኘት ሲኖርበት ይህ ተጨማሪ ትርፍ ነው ፍጹማዊ ኪራይ በመሆን ለመሬት ከበርቴው የሚከፈለው ።

በማርክስ አገላለጽ ለፍጹማዊ ኪራይ መከሰት ሁለት ሁኔታዎች አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ሲሆን እነርሱም ፡—

ሀ/ የመሬት በግል በሞኖፖል መያዝና
ለ/ በግብርናው ውስጥ የሚታየው የካፒታል ውስጣዊ ጥንቅር ከኢንዱስትሪው ያነሰ መሆን ናቸው ።

የመሬት በሞኖፖል መያዝ ካፒታል ከኢንዱስትሪ ወደ ግብርና በቀላሉ እንዳይዘዋወር ይገታዋል ። በዚህም የተነሣ ካፒታሊስቱ መሬት ለማረስ ሲፈልግ የመሬት ከበርቴውን ፈቃድ ማግኘት ያለበት ሲሆን ለዚህም ኪራይ መክፈል ይኖርበታል ። በካፒታሊዝም ውስጥ በግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ የሚታየው የቴክኖሎጂ ዕድገት በኢንዱስትሪ ከሚታየው ያነሰ ነው ። በሌላ አገላለጽ በግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ የሚታየው የካፒታል ውስጣዊ ጥንቅር ከኢንዱስትሪው ያነሰ ስለሆነ በኢንዱስትሪው ክፍለ ኢኮኖሚና በግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ተመሳሳይ የሆነ ሙአለንዋይ ወጪ ቢደረግ ከግብርናው የበለጠ ተረፈ እሴት ይገኛል ። ምክንያቱም የተረፈ እሴት መጣኔ የሚወሰነው በካፒታል ውስጣዊ ጥንቅር በመሆኑ ነው ። ነፃ የሆነ የካፒታል እንቅስቃሴ ቢኖር ኖሮ ካፒታል ከፍተኛ ተረፈ እሴት ወደሚገኝበት ወደ ግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ስለሚጎርፍ የትርፍ መጣኔ በሁለቱም ክፍለ ኢኮኖሚዎች ተመሳሳይ ይሆን ነበር ። ነገር ግን ይህ እንዳይሆን የመሬት በሞኖፖል መያዝ ያግደዋል ። በዚህም የተነሣ የግብርና ምርቶች ባለው የሞኖፖል ይዞታ ምክንያት ከማምረቻ ዋጋቸውና ከአማካይ ትርፍ ድምር በላይ ስለሚሸጡ ይህ ተጨማሪ ትርፍ በፍጹማዊ ኪራይ መልክ ወደ መሬት ከበርቴው ኪስ ይገባል ። የዚህ ፍጹማዊ የመሬት ኪራይ አሰላል አባሪ 2 (Annex 2) ላይ ተመልክቷል ።

ቀደም ሲል እንደተመለከተው ከላይ የተጠቀሱት የመሬት ኪራይ ዓይነቶች (የልዩነትና ፍጹማዊ) የተለያዩ ቢመስሉም በካፒታሊስት ኢኮኖሚ ውስጥ የተጣመሩና አብረው የሚሄዱ ናቸው ። ከዚህ በተጨማሪ በትክክለኛ መልኩ ሲታይ የመሬት ኪራይ ምንጩ የእርሻ ወዛደሮችን በመበዝበዝ የሚገኘው ተረፈ እሴት ነው።

በአጠቃላይ የካፒታሊስት የመሬት ኪራይ ንድፈ ሐሳብ በግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ውስጥ በሚሳተፉ ሦስት መደቦች ማለትም በመሬት ከበርቴዎች ፣ በካፒታሊስቶችና በእርሻ ወዛደሮች መካከል ያለውን ግንኙነት የሚገልጽ ነው ቢባልም ሁኔታው ተለውጦ የሚገኝበት አጋጣሚ መኖሩን ማስተዋል ያስፈልጋል ። አንዳንድ ጊዜ የመሬት ከበርቴዎች መሬታቸውን ከማከራየት ይልቅ እራሳቸው ሠራተኛ ቀጥረው ያሳርሱታል ። በዚህ ጊዜ ከመሬት ኪራይ በተጨማሪ ለካፒታሊስቱ ይሄድ የነበረው ትርፍም ለመሬት ከበርቴዎች ይሆናል ማለት ነው ። በአንዳንድ አጋጣሚዎች ደግሞ የመሬት ከበርቴው መሬቱን ለካፒታሊስቶች ብቻ ሳይሆን ለአነስተኛ ገበሬዎችም ያከራያል ። እነዚህ አነስተኛ ገበሬዎች መሬቱን የሚያሳርሱት ወዛደር ቀጥረው ሳይሆን በራሳቸውና በቤተሰባቸው ጉልበት ነው ። የመሬት ከበርቴውም ከነዚህ አነስተኛ ገበሬዎች የሚሰበስበው ኪራይ ይኖራል ። እዚህ ላይ የሚነሣው ጥያቄ ገበሬዎቹ እንደ ካፒታሊስቱ የጉልበት ሠራተኛ ቀጥረው የሚያሠሩ ከሆነ ለመሬት ከበርቴው የሚከፈለው ኪራይ ከየት ይመጣል ? የሚለው ነው ። ማርክስ ለዚህ መልስ ሲሰጥ እነዚህ አነስተኛ ገበሬዎች በኪራይ መልክ የሚሰጡት የሥራቸውን ውጤት አንድ ክፍል ነው ። ይህም ማለት የተለየ መልክ ይኑረው እንጂ አነስተኛ ገበሬዎች የሚበዘበዙት ልክ እንደ ፋብሪካ ወዛደር ነው ።

በካፒታሊዝም ውስጥ በእርሻው ክፍለ ኢኮኖሚ ከዚህ ለየት ያለ ሁኔታም አለ ። አብዛኛዎቹ ትናንሽ ገበሬዎች የእርሻ ሥራን የሚያካሂዱት መሬት በመግዛትና የራሳቸውን ማሣዎች በማረስ ነው ። ይህ ሁኔታ ደግሞ በካፒታሊዝም ውስጥ የመሬት ዋጋ እንዴት ይወሰናል ? ወደሚለው ጥያቄ ያመራል ። እንደሚታወቀው መሬት የሰው የሥራ ውጤት ባለመሆኑ እሴት የለውም ። እሴት ከሌለው ደግሞ ዋጋው እንዴት ይወሰናል ? የሚል ጥያቄ የሚያስከትል በመሆኑ መልሱን ለማግኘት እንደገና ወደ መሬት ኪራይ ንድፈ ሐሳብ መመለስ ግድ ይሆናል ።

ምንም እንኳን መሬት እሴት ባይኖረውም ዋጋው የሚወሰነው ከመሬቱ ላይ የመሬት ከበርቴው በሚያገኘው የኪራይ መጠንና በጊዜው ባለው የባንክ ወለድ መጠን ይሆናል ። ለምሳሌ አንድ የመሬት ከበርቴ ከመሬቱ በዓመት ብር 5,000 ኪራይ ቢሰበስብ ከበርቴው መሬቱን በሚሸጥበት ጊዜ ቢያንስ ይህንን ያህል ገንዘብ በየዓመቱ ለማግኘት የሚያስችለው የገንዘብ ምንጭ መኖር አለበት ። ይህም ማለት የመሬቱን ሽያጭ ገቢ ባንክ ውስጥ ቢያስቀምጠው በዓመት ቢያንስ ብር 5,000 ወለድ የሚያስገኝለት መሆን ይኖርበታል ። በጊዜው ባንክ የሚሰጠው ወለድ 4 በመቶ ቢሆን ምን ያህል ገንዘብ ባስቀምጥ ነው 4 በመቶ ወይንም ብር 5,000 በየዓመቱ ላገኝ የምችለው ብሎ ያስባል ። በዚህም መሠረት ቢያንስ መሬቱን ብር 125,000 መሸጥ ይኖርበታል ። ከዚህም በተጨማሪ በመሬቱ ላይ አንዳንድ መሠረተ ልማቶች ተዘርግተው ከሆነ የነሱን ዋጋ ይጨምርበታል ። ከዚህ ለመረዳት እንደሚቻለው ትናንሽ ገበሬዎችም ሆኑ ትላልቅ ገበሬዎች መሬት ቢገዙና የራሳቸውን ማሣዎች ቢያርሱም በተዘዋዋሪ መንገድ በቅድሚያ የመሬት ኪራይ ከፍለዋል ማለት ነው ። ለዚህ ነው ማርክስ የመሬት ዋጋ የተጠራቀመ ኪራይ (capitalised rent) ነው ያለው ።

ከካፒታሊዝም ዕድገት ጋር የመሬት ኪራይ እያሻቀበ ይሄዳል ። በግብርና ሥራ ላይ የሚውለው የእርሻ መሬት መጠን

እየሰፋ በሄደ ቁጥር ፍጹማዊ የመሬት ኪራይ እየጨመረ የሚሄድ ሲሆን የልዩነት ኪራይም እንዲሁ ይጨምራል ። አዳዲስ መሬቶች በግብርና ሥራ ላይ በዋሉ ቁጥር የለምነት ደረጃ ልዩነት እየሰፋ ስለሚሄድ እንዲሁም በቴክኖሎጂ ዕድገትና በግብርናው ውስጥ በሚዘረጉ አንዳንድ መሠረተ ልማቶች ምክንያት የልዩነት ኪራይ በዚያው መጠን ይጨምራል ። ከዚህም ጋር አብሮ የመሬት ዋጋ እየጨመረ ይሄዳል ። ይህ ሁሉ ትርፍ ግን የሚገባው ወደ መሬት ከበርቴው ኪስ ነው ።

በአጠቃላይ የልዩነት ኪራይ ኅብረተሰቡ ከአፈር ለምነትና ከቴክኖሎጂ ዕድገት የሚያገኘውን ከፍተኛ ጥቅም በመሬት ከበርቴዎች እንዲነጠቅ የሚያደርግ ሲሆን ፍጹማዊ ኪራይ ደግሞ የግብርና ምርቶች ማለትም የምግብ እህልና የኢንዱስትሪ ጥሬ ዕቃ ዋጋ ከፍተኛ እንዲሆን የሚያደርግ ነው። ይህም የሞኖፖል ዋጋ የእሴት ሕግ በግብርና ምርቶች ዋጋ ላይ እንዳይሠራ ይከላከላል ። ፍጹማዊ የመሬት ኪራይን በተዘዋዋሪ መንገድ የሚከፍለው የምርት ተጠቃሚው ነው ።

የልዩነት ኪራይ ቁጥር 2 መኖር ደግሞ በቴክኖሎጂ ዕድገት የሚገኘውን ተጨማሪ ትርፍ የመሬት ከበርቴው እንዲወስደው ስለሚያደርግ በግብርናው ውስጥ ቴክኖሎጂ በፍጥነት ማለትም በኢንዱስትሪው የሚታየውን ያህል እንዳያድግ ገቺ ኃይል ሊሆን ይችላል ።

5· ሶሻሊስታዊ የዋጋ ንድፈ ሐሳብ

5·1· የሶሻሊስታዊ የዋጋ ንድፈ ሐሳብ ታሪካዊ አመጣጥ

ቀደም ብሎ እንደተመለከተው በካፒታሊስት ስልተ ምርት ውስጥ ዋጋ የሚወሰነው በእሴት ሕግ መሠረት ነው ። ማለትም የሸቀጦች የልውውጥ ሚዛን የሚወሰነው እነሱን ለማምረት በሚወጣው ማኅበራዊ አስፈላጊ የሥራ ጊዜ ነው ። ከዚህ ቀጥሎ በሶሻሊስት ሥርዓት የእሴት ሕግ ሚና ይኖረዋል ወይም ካለውስ ይህ ሚና ምን ይመስላል ? የሚሉትን ጥያቄች ለመዳሰስ ይሞከራል ።

እንደሚታወቀው ማርክስ ኮሚኒስት ኅብረተሰብን በሁለት ደረጃ በመክፈል የመጀመሪያውና ሁለተኛው ደረጃ ብሎ የሰየመ ሲሆን እነዚህም በተለምዶ አነጋገር ሶሻሊስትና ኮሚኒስት ኅብረተሰብ ተብለው የሚታወቁት ናቸው ። በኮሚኒስት ኅብረተሰብ ውስጥ የሸቀጥ ምርት ስለሚከስም የእሴት ሕግም አብሮ ይከስማል ። ነገር ግን በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ውስጥ የእሴት ሕግ ተግባራዊ ይሆናል ወይ ? የሚለው ጥያቄ ብዙ ያወዛገበ ስለሆነ በዚህ ጉዳይ ላይ በማርክሲስቶች መካከል ሲካሄድ የነበረውን ውይይት በጣም ባጭሩም ቢሆን መዳሰሱ ጉዳዩን የበለጠ ለመረዳት ያስችላል ።

የማርክስ ንድፈሐሳባዊ ሥራ እጅግ አመዛኙ ያተኮረው የካፒታሊዝምን “ውስጣዊ የእንቅስቃሴ ሕጎች” በማጤን ላይ ስለነበር የወደፊቱ ሶሻሊስት ኅብረተሰብ አሠራር ምን ይመስላል ? በሚለው ጥያቄ ላይ እምብዛም አላተኮረም ።

ይህ ማለት ግን ማርክስ ስለመጪው ሶሻሊስት ኅብረተሰብ በምርምር ሥራዎቹ ውስጥ አጠቃላይ ሐሳቦችን አልሰነዘረም ማለት አይደለም ። በተበታተነ መልካቸው ቢገኙም ብዙ የተጠቀሱ ሐሳቦች አሉ ።

እነዚህ አባባሎች የተፈለገውን ያህል ስፋት አግኝተው አለመሠራታቸውና የተሠሩትም ቢሆኑ በተለያዩ መንገዶች በመተርጎም የማርክስ ተከታዮችም ሆኑ ተቃዋሚዎች ሲከራከሩባቸው ቆይተዋል ። የክርክሩን ዋና ዋና ነጥቦች እንመልከት ።

በአጠቃላይ ማርክስና ኤንግልስ በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ውስጥ ስለ እሴት መጥፋትና ስለ እሴት ሕግ በሚያወሱበት ቦታ ሁሉ ትኩረታቸው የሸቀጥ ምርት ስለተወገደበት ኅብረተሰብ ፣ ማለትም ስለኮሚኒስት ኅብረተሰብ ነው ማለት ይቻላል ። ነገር ግን ሶሻሊስት አብዮት በሚካሄድባቸው አንዳንድ አገሮች ውስጥ የወዛደሩ መደብ በአንድ አፍታ ሁሉንም የማምረቻ መሣሪያዎች በባለቤትነት ሊይዝ እንደማይችል ይገነዘቡ ነበር ። በእንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ ፣ በተለይ የገበሬው ኅብረተሰብ ቁጥር ከፍተኛ በሚሆንበትና የግል እርሻ ምርት በተስፋፋበት ኅብረተሰብ ውስጥ የሸቀጥ ምርት ሰፊ ሚና ስለሚኖረው የእሴት ሕግ ሚና ምን ይሆናል ? እንዴትስ ይገለጻል ? የሚሉት ጥያቄዎች ግልጽ መልሶች የሚሹ ናቸው ።

እነዚህ ጥያቄዎች በተለይ ጎልተው የተነሡት ከሩሲያው አብዮት በኋላ መሆኑ በንድፈሐሳብና በተግባር መሐከል ያለውን ተዛምዶ በጉልህ ያንፀባርቃል ። የሩሲያ አብዮት ባለፈባቸው ልዩ ልዩ ደረጃዎች ሁሉ (ማለትም የጦርነት ኮሚኒዝም*፣ አዲሱ የኢኮኖሚ ፖሊሲ**፣ የፕላን ወቅት ወዘተ.) ይህ ጉዳይ በተለያዩ መድረኮች የተነሣና ብዙ ያከራከረ ነበር ።

ለምሳሌ በጦርነት ኮሚኒዝም ወቅት የገበያ ሚና በጣም ዝቅተኛ ፣ የራሽን አሠራር ግን የጐላ ስለነበር የእሴት ሕግ ተግባራዊነት ውሱን ነበር። በዚህ ሁኔታ ውስጥ ነው ። ቡካሪን የሚባለው የሶቭየት ኅብረቱ የኢኮኖሚ ምሁር በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ውስጥ የእሴት ሕግ ምንም ሚና ስለማይኖረው በሌላ መልክ መተካት አለበት የሚለውን አስተያየት ያራመደው ። ይህ አስተሳሰብ በተወሰኑ የአገሪቷ ኢኮኖሚስቶች ዘንድ ተቀባይነት የነበረው ቢሆንም ሌኒን ግን የሠራተኛው መደብ ሥልጣን ከያዘ በኋላ ለተወሰነ ጊዜ የገንዘብ ሸቀጥ ግንኙነቶችን ማቆየት አስፈላጊ መሆኑን ተገንዝቦ ነበር ። በጦርነት ኮሚኒዝም ወቅት የገንዘብና ሸቀጥ ግንኙነቶችን ተግባራዊ ለማድረግ ባለመቻሉ በምርት መጠን ስሌት ላይ በተመሠረተ (በፊዚካል) ፕላኒንግ መተማመን ግዴታ ሆኖ ነበር ። ይህን ወቅት መለስ ብሎ ሲመለከት ሌኒን እንደሚከተለው ጽፎ ነበር ፦— “እኛ ያሰብነው—እንዲያውም የመሰለን ማለቱ ይበልጥ ትክክል ይሆናል—አንድም በቂ ምክንያት ሳይኖረን በትናንሽ የገበሬ ይዞታዎች አገር ውስጥ የመንግሥት ምርትና የመንግሥት ሥርጭትን በኮሚኒስት መርሆዎች ላይ እንመሠርታለን ብለን ነበር ። ግን ጊዜ ስህተታችንን አሳይቶናል ።”[11] በሌላ አነጋ

---

*የጦርነት ኮሚኒዝም ፣ የርስበርስ ጦርነትና የውጭ ወራሪዎች ሩሲያን ባናወጡበት የጦርነት ዓመታት (1918—1920) የሶቭየት መንግሥት ያራምደው የነበር የኢኮኖሚ ፖሊሲ ነው ። የዚህም ፖሊሲ ባሕርይ ኢኮኖሚው ከገበያ ጋር ያለውን ግንኙነት በማቋረጡ ፣ ጥሬ ሀብትን የማከፋፈሉን ተግባር ማዕከላዊ በማድረግና በመላሰሉት የሚገለጽ ነው ።

**አዲሱ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ፣ሶቭየት ኅብረት ከካፒታሊዝም ወደሶሻሊዝም ሽግግር ማድረግ በጀመረችበት በ1921 የሩሲያ ኮሚኒስት ፓርቲ ዐሥረኛ ጉባዔ ላይ ፀድቆ የወጣና በወዝ አደሩ የበላይ ገገርነት መንግሥት በተግባር የተተረጐመ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ነ ው ። የዚህ ፖሊሲ መሠረታዊ ዓላማዎች በገንዘብ ሸቀጥ ግንኙነቶች መገልገል ፣ የሶሻሊስት ኢኮኖሚን መገንባት ፣ የሠራተኛውን መደብ ከሰፊው ገበሬ ጋር ያለውን ፣ኅብረት ማጠናከርና የአምራቾች የኅብረት ሥራ ማኅበራትን በማደራጀት ወደ ሶሻሊዝም ማሸጋገር ነበር ።

ገር ከእሴት ሕግ መላቀቅ አልተቻለም ነበር ማለት ነው ።

የርስ በርስ ጦርነቱ ባበቃበት ወቅት ከኢኮኖሚው ላይ የደረሰው መንኮታኮት ከፍተኛ ስለነበር የጊዜው ዋናው ተግባርም ኢኮኖሚውን እንደገና መገንባትና በወዝአደሩ የበላይ ገዥነት ስር ከካፒታሊዝም ወደ ሶሻሊዝም ሽግግር ማድረግ ሲሆን የአዲስ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ዋና ዓላማም ይኸው ነበር። በዚህ ወቅት ኢኮኖሚው በአንድ በኩል ከሞላ ጐደል በፕላን መርህ በሚገዛ የመንግሥት ኢንዱስትሪ ክፍለ ኢኮኖሚ ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ለገበያ ሕጎች ተገዢ በሆነ አነስተኛ የሸቀጥ ክፍለ ኢኮኖሚ ተከፍሎ ነበር ። በመሆኑም በጣም አከራካሪ የነበረው ጉዳይ በመንግሥት ይዞታ የነበረው ክፍለ ኢኮኖሚ እስከምን ድረስ ነው ለገበያ ሕጎች ተገዢ የሚሆነው የሚለው ነበር ። በሌላ አነጋገር ፣ በአጠቃላይ የሶቭየት ኢኮኖሚ ውስጥ የእሴት ሕግ ተጽዕኖ ምን ያህል ነበር ? ጥያቄው ኢኮኖሚያዊ ጥያቄ ብቻ ሳይሆን ፖለቲካዊም በመሆኑ በየጊዜው የተሰጡ መልሶች ከተለያዩ የፖለቲካ ዝንባሌዎች ጋር የተቆራኙና ይካሄዱ የነበሩት ውይይቶች በጣም የከረሩ ነበሩ። በአዲሱ የኢኮኖሚ ፖሊሲ የመጀመሪያ ወቅት ላይ አብዛኛዎቹ ጸሐፊዎች በፕላንና በገበያ መሐከል በነበረው ውድድር የበላይነቱን የያዘው ገበያ ነው ይበሉ እንጂ የኋላ ኋላ በፕላን የመመራት አስፈላጊነትን የተቀበለው ክፍል የበላይነቱን እየያዘ መጥቷል ። በሌላ አባባል በዚያ ወቅት በሶቭየት ኅብረት ውስጥ የእሴት ሕግ ተግባራዊ እንደነበር ፣ ነገር ግን ተግባራዊነቱ ካፒታሊስት ኅብረተሰብ ውስጥ ከነበረው ተግባራዊነት የተለየ እንደሆነ አጠቃላይ ግንዛቤ ላይ የተደረሰ ለመሆኑ በጊዜው ይሠራባቸው ከነበሩ የፖለቲካ ኢኮኖሚ ማስተማሪያ መጻሕፍት መገንዘብ ይቻላል።

በ1930ዎቹ አጋማሽ አዲሱ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ወቅት አክትሞ የመጀመሪያው የአምስት ዓመት ፕላን በሥራ ላይ መዋል ሲጀምር የእሴት ሕግ ተግባራዊነት ጥያቄ እንደገና በአዲስ መልክ የውይይት ርዕስ ሆኖ ቀርቦ ነበር ። ጊዜው የፕላን ወቅት በመሆኑ በአብዛኛው ተቀባይነት የነበራቸው አስተያየቶች የፕላኑን ሚና የሚያጎሉና ፣ በአንጻሩ ደግሞ የእሴት ሕግን ሚና የሚያኮስሱ ነበሩ ። ይሁንና በወቅቱ ነጥሮ የወጣና ሰፊ ተቀባይነት የነበረው አስተያየት በካፒታሊዝም የኢኮኖሚ ሕጎችና በሶሻሊዝም የኢኮኖሚ ሕጎች መሐከል መሠረታዊ ልዩነት አለ የሚለው ነበር። ከዚህ አኳያ በሶቭየት ኅብረት የሶሻሊዝም ኢኮኖሚ ችግሮች በሚል ርዕስ በ1952 የታተመው የስታሊን ጽሑፍ ከፍተኛ ተሰሚነት ነበረው ለማለት ይቻላል ። ጽሑፉ ውስጥ የተገለጹት አስተያየቶች ለሶሻሊስት የዋጋ ንድፈሐሳብ መሠረትነት ለረጅም ጊዜ አገልግለዋል ። አስተያየቶቹ በርካታ ቢሆኑም የእሴት ሕግን በሚመለከት ዋናዎቹ ፡—

ሀ/ በሶሻሊስት ሥርዓት ውስጥ የእሴት ሕግ ተግባራዊነት አለው ፣ ሸቀጦችና የሸቀጥ ምርት ባሉበት ሁሉ የእሴት ሕግ በግድ ተግባራዊ ይሆናል ፣ በሶቭየት ኅብረት ውስጥ የእሴት ሕግ ተግባራዊነት በሸቀጥ ልውውጥ ብቻ ሳይሆን በሸቀጥ ምርትም ይገለጻል ።

ለ/ ይህ ማለት ግን የእሴት ሕግ ተግባራዊነት በካፒታሊዝም ውስጥ ያለውን ያህል ስፋት አለው ፣ ወይም ደግሞ ምርትን ይቆጣጠራል ማለት አይደለም። በሶሻሊስት ሥርዓት ውስጥ ተግባራዊነቱ ውሱን ነው ፣ ምክንያቱም የሸቀጥ ምርት ውሱን ነውና ።

ሐ/ በኮሚኒስት ኅብረተሰብ ውስጥ የሸቀጥ ምርት ስለሚጠፋ ፣ የእሴት ሕግ ተግባራዊነት አይኖረውም ።

የሚሉ ናቸው [12]

ከ1952 በኋላ የታተሙት የፖለቲካ ኢኮኖሚ ማስተማሪያ መጻሕፍት በመሠረቱ የስታሊንን አቋም የሚያንፀባርቁ ቢሆኑም ከንድፈ ሐሳብም ሆነ ከዋጋ ሥርዓት ተግባራዊነት አንፃር በሶቭየት ኅብረትና በሌሎች ሶሻሊስት አገሮች በርካታ ውይይቶች ሲካሄዱ ቆይተዋል ፣ አሁንም በመካሄድ ላይ ናቸው ። ከንድፈሐሳብ አንፃር የእሴት ሕግን አስመልክቶ የተለያዩ አስተሳሰቦች ስንዘረዋል ። ይሁን እንጂ ከአፈፃጸም አንፃርም በተለያዩ አገሮች የተሻለ ነው የሚሉትን በተግባር አውለው ቢገለገሉበትም እስከአሁን ከነዚህ ተግባራዊ ልምዶች አዲስ ንድፈሐሳብ ፈልቆ በአጠቃላይ ተቀባይነት አግኝቷል ማለት ያስቸግራል ።

ማርክሲስቶች የእሴት ሕግን ተግባራዊ በማድረግ አንፃር ወይም በሶሻሊስት የዋጋ ንድፈሐሳብ ላይ ሙሉ በሙሉ ተመሳሳይ አቋም ይዘዋል ለማለት ባይቻልም የእሴት ሕግ ከሰዎች ፍላጎትና አስተሳሰብ ነፃ የሆነ ነባራዊ ሕግ መሆኑን ሁሉም ይቀበላሉ ። በዚህም ግንዛቤ ላይ በመመሥረት ሕጉ በሶሻሊስት ብሔራዊ ኢኮኖሚ ፕላን ውስጥ ጠቀሜታ በሚሰጥበት ሁኔታ ተግባራዊ እንዲሆን ይጥራሉ ። በጥረታቸውም ሁሉም የየራሳቸውን አስተዋጽኦ እያደረጉ ነው ። ከዚህ ቀጥሎ ይህን ጥረት ፣ አስተዋጽ እና አሠራር ዘርዘር አድርገን እንመለከታለን ።

5.2. የሶሻሊስት የዋጋ ንድፈ ሐሳብ መሠረታዊ ሐሳቦች

ንድፈሐሳብ በመሠረቱ የሚመነጨው ከተግባር እንደሆነና በበኩሉ ደግሞ በተግባር ላይ ተጽዕኖ እንደሚያደርግ የታወቀ ነው ። ዋጋን በሚመለከት የተለያዩ ሶሻሊስት አገሮች በአንድ በኩል የጋራ ገጠመኞች ሲኖራቸው በሌላ በኩል ደግሞ በአሠራር ባጋጠሟቸው ችግሮችና ለመፍትሔ በተጠቀሙባቸው ዘዴዎች አንፃር የተጓዙባቸው ጐዳናዎች የተለያዩ ናቸው ። ይህ በመሆኑ ከሁሉም ልምድ ነጥሮ የወጣና በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት ያለው አንድ ወጥ የዋጋ ንድፈሐሳብ አለ ለማለት ያስቸግራል።

የሸቀጥ –ገንዘብ ግንኙነቶች ባሉበት ኅብረተሰብ ውስጥ የእሴት ሕግ የግድ ተግባራዊ ይሆናል ። እርግጥ በሶሻሊስት ሥርዓት ውስጥ አምራች መደብ የምርት መገልገያዎች ባለቤት በመሆኑ የምርት ማኅበራዊ ባሕርይ የተሟላ ይሆናል ። እንደካፒታሊስቱ የሸቀጥ ምርት ለትርፍ ብቻ ሳይሆን በቅድሚያ የተጠቃሚውን ሕዝብ ፍላጎት ለማርካት የታቀደ ነው ። ለተጠቃሚው ኅብረተሰብ የሚደርሰውም በገበያ ውስጥ በሸቀጥ–ገንዘብ ልውውጥ አማካይነት ነው። በሶሻሊዝም የሸቀጥ–ገንዘብ ግንኙነቶችን መጠቀም አስፈላጊ ነው ። ምክንያቱም ሁለት የሶሻሊስት ይዞታ ዓይነቶች (የመንግሥትና የኅብረት ሥራ ማኅበራት) በመኖራቸውና በነዚህ በሁለቱ ይዞታዎች መካከል ማንኛውም ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት በሸቀጥ ገንዘብ ግንኙነት በገንዘብና በልውውጥ አማካይነት እንዲከናወን ሁኔታዎች ስለሚያስገድዱ ነው ። በዚህ የዕድገት ደረጃ ምርትን ለሠራተኛውም ሆነ ለኅብረት አራሹ መደብ ለማዳረስ የሚቻለው "ከእያንዳንዱ እንደችሎታው ለእያንዳንዱ እንደሥራው" በሚለው የሶሻሊስት የምርት ውጤት ክፍፍል መርህ በመሆኑና ይህንንም መርህ ተግባራዊ ለማድረግ የሚቻለው በሸቀጥ–ገንዘብ ግንኙነት አማካይነት ብቻ በመሆኑ ነው ። እነዚህ ግንኙነቶች

ጨርሰው የሚከስሙት በኮሚኒስት ሥርዓተ ማኅበር ብቻ ነው ።

እንደማናቸውም በመደብ በተከፋፈለ ቅድመ ሶሻሊስት ኅብረተሰብ ሁሉ በሶሻሊስት ሥርዓትም ውስጥ ዋጋ የእሴት ገንዘባዊ መግለጫ ነው ። ስለሆነም ዋጋ አንድን ሸቀጥ ለማምረት የወጣውን አማካይ የኅብረተሰብ የሥራ ውጤት ያመለክታል ። እንዲሁም በሻጭና በገዥ መሀከል ያለውንም ግንኙነት ይወስናል ። በሶሻሊስት ሥርዓት ውስጥ ዋጋ የሚወሰነው በዕቅድና ከሶሻሊዝም የኢኮኖሚ ሕጎች ጋር በተጣጣመ መንገድ ነው ። ይሁን እንጂ ዋጋ በካፒታሊስቱ ኅብረተሰብ ያሉትን ባሕርያትና ሚና በመገንዘብ በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ውስጥ የሚኖሩት ባሕርያት በዋጋና በተግባራቱ መካከል ያለውን ግንኙነት ፤ በተለይም ከእሴት ጋር ስላለው ተዛምዶ የተሳሳተ ግንዛቤ የሚይዙ ጥቂቶች አይደሉም ። ለምሳሌ በካፒታሊስት ኢኮኖሚ ዋጋ ግብታዊ በሆነ መንገድ የመቆጣጠር ተግባር ያለው በመሆኑ ከተወሰነ እሴት በልጦ ወይንም አንሶ መገኘቱ ተገቢ ነው ፤ በሶሻሊዝም ግን ዋጋ በምንም ዓይነት ከእሴት በልጦ ወይንም አንሶ መገኘት የለበትም የሚሉ አሉ ። በእነርሱ እምነት ይህን ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ቢገኝም እንኳ በተለያዩ ስልቶች ከእሴት ጋር ያለው ልዩነት በጣም ጠባብና ጊዜያዊ መሆን ይገባዋል ፤ እንዲያውም ከመርሀ አንፃር ዋጋ እሴትን በትክክልና በእኩል ማንፀባረቅ አለበት ይላሉ ። ይሁንና ይህ አባባል በጣም የተዘወተረና የተደጋገመ ቢሆንም ሁልጊዜ ተግባራዊ ሊሆን ይችላል ለማለት አይቻልም ። በሶሻሊስት ሥርዓተ ማኅበር ዋጋ ማኅበራዊ አገልግሎቱን በሚያከናውንባቸው ጊዜያት ሁሉ ከእሴት በልጦ ወይም አንሶ ሊገኝ ይችላል ። ደግሞም ሊሆን ይገባዋል ። ዋጋ ከእሴት ሊበልጥ ወይንም ሊያንስ የሚያስችሉ በርካታ ሁኔታዎች አሉና ። ከነዚህም መሀከል ጥቂቶቹ ፤

ሀ በምርትና በፍጆታ መካከል ልዩነት ሲኖር በአንድ በኩል አቅርቦት ከፍላጐት አንሶ እጥረት እንዳይከሰት ፤ በሌላ በኩል ደግሞ አቅርቦት ከፍላጐት ልቆ የምርት መባከን እንዳይኖር በሁለቱ መካከል ተገቢውን ሚዛን ለመጠበቅ ሲባል ዋጋ ከእሴት እንዲለይ ይደረጋል። ይሁን እንጂ ይህ ዘዴ ጊዜያዊ ችግሮችን መፍቻ እንጂ ዘላቂ መፍትሔ እንዳልሆነ መታወቅ አለበት።

ለ ዝቅተኛ ገቢ የሚያገኘው የኅብረተሰብ ክፍል አንዳንድ መሠረታዊ የሆኑ ሸቀጦችን በዝቅተኛ ዋጋ ለመግዛት እንዲችል ሲባል የነዚህ ሸቀጦች ዋጋ ከእሴታቸው እንዲያንስ ያደርጋል ። በአጠቃላይ ፍጆታቸው እንዲበረታታ የሚፈለጉ የምርት ዓይነቶች በሙሉ ከእሴታቸው ባነሰ ዋጋ ይሸጣሉ ። በአንጻሩም ፍጆታቸው እንዳይስፋፉ የሚፈለጉ ሸቀጦችና የቅንጦት ምርቶች ከእሴታቸው በበለጠ ዋጋ እንዲሸጡ ይደረጋል ።ይህ በመሠረቱ ብሔራዊ ገቢን በአግባቡ ለማከፋፈል ከሚቀየስ ማኅበራዊ ፖሊሲ ጋር የተቆራኘ አሠራር ነው ።

ሐ/ የቴክኒክ ዕድገትን ለማፋጠን እንዲቻል አዳዲስ መሣሪያዎችና ቴክኖሎጂዎች በሥራ ላይ እንዲውሉ ለማድረግ ዋጋቸው ከእሴታቸው ዝቅ እንዲል ይደረጋል።

መ/ አንዳንድ የኢኮኖሚ ዘርፎች በፍጥነት አድገው የክምችት ዐቅምን በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዲያዳብሩ ሲፈለግ ለምርት ተግባር የሚጠቀሙባቸው ሸቀጦች ዋጋ ከእሴታቸው ዝቅ እንዲል ይደረጋል ። በአንፃሩም ለሌሎች ዘርፎች

የዚህ ተቃራኒ የሆነ ሁኔታ ሊፈጥር ይችላል ።

በአጠቃላይ በነዚህና በሌሎችም ምክንያቶች በዋጋና በእሴት መሀከል አለመጣጣም ሊኖር ይችላል ።

ይሁን እንጂ ለዘለቄታው መታቀድ ያለበት ግን በእሴትና በዋጋ መካከል መጣጣም መፍጠር ነው ። በአንዳንድ አስገዳጅ ምክንያቶች ዋጋ ከእሴት ባይጣጣምም ፤ ዞሮ ዞሮ ዋጋን ለመወሰን ተጨባጭና ነባራዊው ሁኔታ ማኅበራዊ አስፈላጊ ሥራ ነው። ስለሆነም የምርት መቀነስ እንዳይከሰት በተለይ ከረዥም ጊዜ ዕቅድ አንፃር ይህ አለመጣጣም ከመጠን በላይ እንዳይሆን መጠንቀቅ ያስፈልጋል ። ይህን በሚመለከት ሚዛናዊ ፖሊሲ ማመንጨቱና ተግባራዊ ማድረጉ ቁልፍ የሆነ የሶሻሊስት የዋጋ ፖሊሲ ጉዳይ ነው ።

5.3. በሶሻሊስት ሥርዓት የዋጋ ሚና

በካፒታሊስት ሥርዓት ኢኮኖሚው የሚመራው በገበያ ኃይሎች ስለሆነ ዋጋ የምርትን መጠንና ዓይነት ፤ የገቢ ክፍፍልንና የኢኮኖሚውን የዕድገት አቅጣጫ በሚመለከት ከፍ ያለ ተጽዕኖ ሲኖረው ሶሻሊስት ኢኮኖሚ ግን በዕቅድ የሚመራ በመሆኑ የዋጋ ሚና በካፒታሊስቱ ሥርዓት ውስጥ እንደሚታየው የጐላ አይደለም ። ይሁን እንጂ በሶሻሊስት ሥርዓትም ውስጥ አንዳንድ ተግባሮችን ስለሚያከናውን ሚናውን ማኮሰስ ፤ ወይም ጨርሶ እንደሌለ መቁጠር ስህተት ነው ። ዋጋ የሸቀጥ ልውውጥ ፖሊሲ መሣሪያ እንደመሆኑ መጠን ምንነቱን ተረድቶ በአግባቡ ለሚጠቀምበት ኅብረተሰብ ጠቃሚ ውጤት የሚያስገኝ ፤ በሚገባ ለማይጠቀምበት ግን ውስብስብ ችግሮችን የሚያስከትል መሆኑ በቅድሚያ መታወቅ ይኖርበታል ። ከዚህ በመነሣት በሶሻሊስት ሥርዓት የዋጋን ሚና እንደሚከተለው በአራት ከፍሎ መመልከት ይቻላል ።

ሀ/ ዋጋ ለመለኪያነት ፤ የዋጋ ዓይነተኛ ተግባር ሸቀጥን ለማምረት የፈሰሰውን ማኅበራዊ አስፈላጊ ሥራ ወይም የሸቀጥ እሴትን ማመልከትና መለካት ነው ። የማናቸውም ምርት ወጪ በዋጋ አማካይነት ይለካል ። በዋጋ አማካይነት የሸቀጦች ልውውጥ ይፈጸማል ። ከአምራች እስከ ተጠቃሚው ድረስ ያለው እንቅስቃሴ በዋጋ አማካይነት ይመዘናል ። በመሆኑም ዋጋ በሸማቹና በሻጩ ላይ ኢኮኖሚያዊ ተጽዕኖ ለማሳደር የምርት ዝውውርን በፕላን ለመምራት ያስችላል ።

ሶሻሊስት ኢኮኖሚ በዕቅድ የሚመራ እንደመሆኑ ዋጋ በዕቅድ አሠራር ውስጥ አገልግሎት ያበረክታል ። የዕቅድ ግቦች በቁሳዊና በገንዘብ መልክ የሚገለጹ ሲሆን ግቦች በገንዘብ የሚገለጹት ዋጋን መሠረት በማድረግ ነው ። ይህም የተለያዩ የምርት ግቦችን በጋራ መለኪያ ለመግለጽ ከመርዳቱ ባሻገር የተለያዩ ዘርፎችን ምርት ለማነፃፀር በክምችትና በፍጆታ መካከል ያለውን ተዛምዶ ለመግለጽ በአጠቃላይ የዕቅዱን ውስጣዊ ተዛምዶ ለማየት ያገለግላል ።

ለ/ ዋጋ በመቆጣጠሪያነት ፤ ዋጋ እሴትን ከመለካት ተግባሩ ጐን መላውን የምርት ሂደትና የሸቀጥ እንቅስቃሴ የመቆጣጠር ተግባር ያከናውናል ። በዕቅድም ረገድ ያለው ሚና እጅግ ከፍተኛ ነው ። የዕቅድ አፈጻጸም አመልካቾች የሚገለጹበት በገንዘብ መልክ ስለሆነ የዋጋ ዕቅድ አፈጻጸምን ግምገማ ፤ ክትትልንና ቁጥጥርን አስመልክቶ ከፍተኛ ግልጋሎት ይሰጣል ። በአጠቃላይ ዋጋ በመለኪያነትና በመቆጣጠሪያነት

የሚያከናውናቸው ተግባራት በአንድ አገር ኢኮኖሚ ውስጥ የሒሳብ አያያዝ ዋንኛ ፈርጅ በመሆን ያገለግላል ፤ በዋጋ ሳይገለገሉ የሶሻሊስት ኢንዱስትሪን ተግባራት ማከናወንና ማስተዳደር አይቻልም ።

ሐ/ ዋጋ ለገቢ ክፍፍል ፤ ዋጋ ከተወሰነ እሴት በልጦ ወይም አንሶ ሲተመንና ተግባራዊ ሲሆን በምርት ሂደት የተፈጠረው ትረፈ እሴት ከአንድ ዘርፍ ወደ ሌላው ዘርፍ ዳግም እንዲከፋፈል ያደርጋል ። ይህ የክፍፍል ተግባር ኢኮኖሚን ለማዳበር ወይም የተወሰኑ ማኅበራዊ ቅራኔዎችን ለመፍታት ለምሳሌ በገጠርና በከተማ ፤ በተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች መሀከል ያለውን የኑሮ ደረጃ ልዩነት ለማስቀረት ዓላማ ኖሮት ሊከናወን ይችላል ። ይህ ተግባር በተለያዩ መልኮች ቢከናወንም ዞሮ ዞሮ በብሔራዊ ኢኮኖሚ ውስጥ የተፈጠረን ብሔራዊ ገቢ የማከፋፈል ሂደት ከመሆን ውጭ የሚታይ አይሆንም ።

መ/ ዋጋ በማበረታቻነት ፤ በዋጋ አማካይነት በአምራቾችና በሸማቾች ላይ ዓላማ ያለው ኢኮኖሚያዊ ግፊትና መነሣሣት መፍጠር ይቻላል ። የዋጋ መጨመር ወይም መቀነስ ምርትን የማምረት ወይም የመሸጥ ሂደት ፤ የቴክኒክ ዕድገት ፤ የታቀዱ የፕላን ክንውኖችና ሌሎችም ኢኮኖሚያዊ ተግባራት እንዲከናወኑ ግፊትና መነሣሣት ይፈጥራል ። የሶሻሊስት መንግሥት በሚያወጣው የዋጋ ፖሊሲ አማካይነት የሶሻሊስት እንዱስትሪዎች ለኅብረተሰቡ ጠቃሚ የሆኑ ምርቶችን እንዲያመርቱ በብሔራዊ ፕላን ውስጥ የታቀዱ ተግባራት አትኩሮት አግኝተው እንዲሟሉ ግፊት ያሳድራል ። በዘመናችን በኢኮኖሚያዊ ስልቶች በመገልገል ኢኮኖሚውን በሁሉም መልኩ እንዲያድግ ግፊት ማድረግ እጅግ ጠቃሚ ውጤት አለው ። በዚህ ሥልት አማካይነት የፋብሪካ ፍላጐት ከኅብረተሰቡ ፍላጐት ጋር እንዲቀናጅ በዕቅድ የተያዙ ተግባራትና በፍላጐት መሀከል ተገቢው መጣጣም እንዲኖር ማድረግ ይቻላል ።

5.4. የዋጋ አወሳሰን ዘዴዎች

ማርክስ እንዳስገነዘበው የአንድ ሸቀጥ እሴት ሦስት ክፍሎች ሲኖሩት እነርሱም ቋሚ ካፒታል ፤ ተለዋዋጭ ካፒታልና ትርፍ ናቸው ። ለቋሚ ካፒታልና ለተለዋዋጭ ካፒታል የሚውለው ወጪ ተጠቃሎ የማምረቻ ወጪ ይባላል ። ከዚህ መሠረታዊ ሐሳብ ስንነሣ እሴትን በሁለት ዐበይት ክፍሎች ማለትም በማምረቻ ወጪና በትርፍ ክፍሎ ለማየት ይቻላል። የዋጋ አወሳሰንም የሚመሠረተው በነዚህ ሁለት የማይነጣጠሉ የእሴት ክፍሎች (በማምረቻ ወጪና በትርፍ) ላይ ይሆናል ። ይሁንና እነዚህ ሁለት ክፍሎች ለዋጋ አወሳሰን ዓላማ ማገልገል እንዲችሉ የተወሰነ ደረጃ ሊኖራቸው ይገባል ። ለምሳሌ የማምረቻ ወጪ ይብዛ ይነስም ፋብሪካው በሚሠራበት ሁኔታ ፤ በምርታማነትና በመሳሰሉት ላይ በመመሥረት ደረጃው ሊወሰን ይገባል። ዋጋን ለመወሰን በየትኛው ደረጃ የሚገኘው ፋብሪካ በመነሻነት ያገለግል ? የሚለው ጥያቄ መልስ ማግኘት ይኖርበታል ። በጥሩ የሥራ ሁኔታ የሚገኝ ፋብሪካን የማምረቻ ወጪውን መሠረት በማድረግ ብንነሳ ሸቀጦች ዝቅተኛ ዋጋ ይኖራቸዋል ። በሌላ መልኩ ማለትም በዝቅተኛ የሥራ ሁኔታ የሚሠራን ፋብሪካ በመውሰድ ብንነሣ ደግሞ ከፍተኛ ዋጋ ይኖራቸዋል ። እንዲህ ዓይነቱን አስቸጋሪ ሁኔታ ለማስወገድ የዋጋ አወሳሰን መሠረት አድርጐ የሚነሣባቸው የማምረቻ ወጪና ትርፍ አንድ የተወሰነ ደረጃ (normative)

ሊበጅላቸው ይገባል ። የማምረቻ ወጪ ለዋጋ አተማመን መሠረት ተደርጎ ከተወሰደ በአጠቃላይ በማምረት ሂደት ውስጥ ለዋሉት ነገሮች ማለትም ለጥሬ ዕቃ ፤ ቁሳቁሶች ፤ የሥራ ኃይል ወዘተ. የወጡትን ወጪዎች በትክክል ማስላትና ደረጃ መስጠት ያስፈልጋል ። በዚሁ ሁኔታ ለዋጋ አወሳሰን ትርፍ በመሠረትነት ከተወሰደ እንዲሁ የአትራፊነት ደረጃ ሊወጣለት ይገባል ማለት ነው ።

የዋጋ አወሳሰንን ከባድ የሚያደርጉት እነዚህ ከላይ ያነሣናቸው የዋጋ አወሳሰን መሠረቶች ደረጃዎቻቸውን ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ለመግለፅ ማስቸገሩና ሌሎችም ጉዳዩን ውስብስብ የሚያደርጉ ነገሮች መኖራቸው ነው ። የማምረቻ ወጪዎች በየጊዜው የሚለዋወጡ እስከሆነ ድረስ ቋሚ የማምረቻ ወጪ ይህ ነው ብሎ ለማመልከት አስቸጋሪ ይሆናል ። ከዚህም በላይ የማምረቻ ወጪዎች ባሕርያቸውን በየጊዜው እንዲለዋወጡ የሚያደርጉ በርካታ ተጨባጭ ሁኔታዎች በመኖራቸው ዘወትር ትክክለኛነት አይኖራቸውም ። የትርፍን ደረጃ መወሰን ሌላው ይበልጥ አስቸጋሪ ጉዳይ ነው ። በዚህ ረገድ ትርፍን ከመቶ እጅ ለማስላት በየትኛው የእሴት ክፍል ላይ መመሥረት ይኖርብናል? ይህስ ስሌት ስንት መሆን ይኖርበታል? የሚሉ ሁለት መልስ ሊያገኙ የሚገባቸው ጥያቄዎች ሊነሱ ይችላሉ ። የሚሰጠው መልስ እንደየሀገሩ ሊለያይ ይችላል ። በአብዛኞዎቹ የሶሻሊስት አገሮች የዋጋ አወሳሰን ትርፍ ከማምረቻ ወጪ ዋጋ ጋር ባለው ተዛምዶ አንፃር በመቶ በማስላት ላይ የተመሠረተ ነው ።

ነገር ግን በአጠቃላይ በሁሉም ሶሻሊስት አገሮች የዋጋ አወሳሰንን በሚመለከት አንድ ወጥ የሆነ ዘዴ የለም ። የተለያዩ አገሮች በየራሳቸው ገጠመኞች በመጠቀም በተለያዩ የዋጋ አወሳሰን ዘዴዎች ይገለገላሉ ። በመሆኑም የተለያዩ የዋጋ አወሳሰን ዘዴዎች አሉ ። ሁሉም ዘዴዎች ከማምረቻ ወጪ በመነሣት በርሱ ላይ ሊታከል የሚገባውን ትርፍ ለማስላት መሞከራቸው አንድ የጋራ ባሕርይ እንዲኖራቸው ሲያደርግ ይህ የሚታከለው ትርፍ በምን ላይ የታሰበ ይሁን ? በደመወዝ ወጪ ፤ (በተለዋዋጭ ካፒታል) ፤ በማምረቻ ወጪ (ቋሚና ተለዋጭ ካፒታል ተደምረው) ፤ በካፒታል ወጪ ወይስ በደሞዝና በካፒታል ወጪ ቅንብር ላይ የሚታሰብ ይሁን? ለሚለው ጥያቄ የሚሰጡት መልስ እንዲለያዩ ያደርጋቸዋል። እነዚህን የዋጋ አተማመን ዘዴዎች በዝርዝር እንመልከት ፤

ሀ/ ትርፍ በደመወዝ ወጪ ላይ ሲታሰብ፣ በዚህ ዘዴ መሠረት ዋጋ የሚወሰነው የታቀደውን የትርፍ መጣኔ ከተለዋዋጭ ካፒታል ወጪ ጋር በማባዛት ውጤቱን ከማምረቻ ወጪ ጋር በማዳመር ነው ።

ይህ ዘዴ የሚያተኩረው ለሰው ጉልበት በዋለው ወጪ ላይ ስለሆነ ዋጋ ከእሴት ጋር እንዲቀራረብ ያደርጋል ። ይሁን እንጂ ከፍተኛ የደመወዝ መጠን ለሚከፈልባቸው የምርት ሁኔታዎች ትኩረት ስለሚሰጥ ምርታማነትን ለማሳደግ የሚያበረታታ አይደለም ።

ለ/ ትርፍ ከጠቅላላ የማምረቻ ወጪ ላይ ሲታሰብ ፤ በዚህ ዘዴ መሠረት የትርፍ መጣኔ የሚሰላው ከጠቅላላ የማምረቻ ወጪ ጋር በማብዛት ይሆናል ። በዚህ ዘዴ ዋጋን ማስላት ቀላል ቢሆንም ዘርፎች የማምረቻ ወጪያቸውን ከፍ ባደረጉ ቁጥር ዋጋ እንዲጨምር ስለሚያደርግ የወጪ ቅነሳን አያበረታታም ።

ሐ/ ትርፍ በካፒታል ወጪ ላይ ሲታሰብ፣ በዚህ ዘዴ ትርፍ የሚሰላው በምርት

መገልገያዎችና በደሞዝ ወጪ ላይ ተመሥርቶ ነው ።

ይህ ዘዴ የምርት መገልገያዎች በቁጠባ እንዲሠራባቸውና ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች በሥራ ላይ እንዲውሉ የሚያበረታታ ሲሆን ትኩረቱ ለሰው ጉልበት በዋለው ወጪ ላይ ስላልሆነ ዋጋ ከእሴት እንዲርቅ ያደርጋል ።

መ/ ትርፍ በደመወዝና በካፒታል ወጪ ላይ ሲታሰብ ፣ ይህ ዘዴ ከላይ በፊደል "ሀ" እና "ሐ" የቀረቡትን የአሰላል ዘዴዎች ለማስታረቅ የሚሞክር ሲሆን ትርፉ በከፊል በደመወዝ ወጪ ላይ ፣ በከፊል ደግሞ በካፒታል ወጪ ላይ እንዲሰላ ያደርጋል ።

ይህ ዘዴ ለሰው ጉልበትና ለምርት መገልገያዎች የዋለውን ወጪ ለማካተት ቢሞክርም ውስብስብ በመሆኑ በቀላሉ ተግባራዊ ለማድረግ ያዳግታል ።

እነዚህ ዋና ዋናዎቹ የዋጋ አወሳሰን ዘዴዎች ሲሆኑ ሌሎችም አሉ ። የሁሉም የጋራ ባሕርይ በማምረቻ ወጪ ላይ መመርኮዛቸውና የሸማቹን ፍላጐት ለማገናዘብ አለመሞከራቸው ነው ። ነገር ግን ፍላጐትን ለረዥም ጊዜ ችላ ማለት ደግሞ የበኩሉን ችግር ስለሚያስከትል ዋጋዎች በሚወሰኑበት ጊዜ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል ።

6. በሶሻሊስት ሥርዓት የመሬት ኪራይ ንድፈሐሳብ ፣ የሶሻሊዝምን የዕድገት ጐዳና በመረጡ ሀገሮች ውስጥ መሬት በቀጥታ የሕዝብ ሀብት መሆን ፍጹማዊ የመሬት ኪራይን ያስወግዳል ። ምክንያቱም ፍጹማዊ ኪራይ ከመሬት የግል ይዞታ ጋር የተያያዘ በመሆኑ ነው ። በተጨማሪም ሙአለንዋይ በመጠቀም የሚገኝ ትርፍ በመሬት ከበርቴዎች ስለማይወሰድ በግብርና ክፍለ ኢኮኖሚ የቴክኖሎጂ ለውጥና ዕድገትን ለማምጣት አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል ።

በብዙዎቹ ሶሻሊስት አገሮች መሬት የመንግሥት (የሕዝብ) ሀብት በመሆኑ ፍጹማዊ የመሬት ኪራይ አይከፈልበትም ። ሆኖም በለምነት ደረጃ ልዩነት ምክንያት የሚከሰተውን ትርፍ የመንግሥት እርሻዎችም ሆኑ የማኅበር እርሻዎች ያለጥረታቸው ያገኙት ስለሆነ በምርት ታክስ (production tax) መልክ ሲወሰድባቸው በመሬቱ ለምነት ተጠቃሚ አልሆንም በማለት ለለምነት እንክብካቤ ከማድረግ እንዳይገታቸው በታክስ አተማመን ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል ።

በሶሻሊስት አገሮች ውስጥ የግብርና ምርቶችን ዋጋ ለሕዝብ ጥቅምና ለኢኮኖሚ ዕድገት መፋጠን በሚረዳ ሁኔታ ለመወሰን አንዱ አስቸጋሪ ጉዳይ የልዩነት ኪራይ ቁጥር 1ም ሚና ይኑረው የሚለው ጥያቄ ነው ። ይህንን በማስመልከት ቼኮሽ ናጂ የተባለው ሀንጋሪያዊ ኢኮኖሚስት የሶሻሊስት ዋጋ ንድፈሐሳብና የዋጋ ፖሊሲ በሚለው መጽሐፉ ውስጥ እንደሚከተለው አስቀምጦታል ። "የልዩነት ኪራይ ቁጥር 1ን በመሬት ታክስ አማካይነት መውሰድ ይቻል ነበር ። ነገር ግን ይህንን ችግር በትክክል ለማቃለል የሚችል የታክስ ሥርዓት በየትኛውም የሶሻሊስት አገር የለም"።[13]

የልዩነት ኪራይ ቁጥር 1 በግብርና ምርቶች ዋጋ አወሳሰን ውስጥ የሚጫወተውን ሚና በሚመለከት በተለያዩ ሶሻሊስት አገሮች ከፍተኛ ክርክሮች ይካሄዱ ነበር ። በሶቪዬት ኅብረት በተደረጉት ውይይቶች ላይ ተሳታፊ የነበሩት ኢኮኖሚስቶች የግብርና ምርቶች ዋጋ በመጨረሻው የሥባት ደረጃ (የለምነት) ላይ በሚገኘው መሬት ወጪ ላይ ይመሥረት የሚለውን ሐሳብ ተቃውመዋል ። በእነርሱ አመለካከት ይህ አሠራር ተግባራዊ የሚሆነው በካፒታሊስት ኢኮኖሚ ብቻ ሲሆን በካፒታሊስት ኢኮኖሚም ቢሆን ይህ ተግባራዊ የሚሆነው የግብርና ምርቶች ዋጋ አወሳሰን ግብታዊ ሲሆን ብቻ ነው ። የቼኮዝሎቫኪያ ኢኮኖሚስቶችም ቢሆኑ ተመሳሳይ አመለካከቶችን አንፀባርቀዋል ። የግብርና ምርቶች ዋጋ በዝቅተኛ የሥባት ደረጃ በሚገኙ የማኅበር ወይንም የመንግሥት እርሻዎች ወጪ የተመሠረተ እንደሆነ መካከለኛና ከፍተኛ የለምነት ደረጃ ባለው መሬት የሚጠቀሙት በልዩነት ኪራይ መልክ የሚያገኙት ተጨማሪ ገቢ የሚወሰድባቸው ስለሌለ ሁኔታው ምርትን ለመጨመርም ሆነ ፣ የማምረቻ ወጪያቸውን ለመቀነስ የሚገፋፋቸው አይሆንም ። ነገር ግን የግብርና ምርቶች ዋጋ በአማካይ የለምነት ደረጃ በሚገኙ ማሣዎች ወጪ የተመሠረተ እንደሆነ ከፍተኛ የለምነት ደረጃ ባላቸው መሬቶች የሚጠቀሙ አምራቾች የሚያገኙት የልዩነት ኪራይ ይቀንሳል ። በዚህ ምክንያት ይህ ዓይነት የግብርና ዋጋ ፖሊሲ በመጠኑም ቢሆን የልዩነት ኪራይን ውሱን ያደርገዋል ። በዚህ "የአማካይ ወጪ" አመለካከት ከአማካይ በታች የሥባት ደረጃ ያላቸው አምራቾች ኪሣራ ይደርስባቸዋል። ይህንን ችግር ለማቃለል በነዚህ ድርጅቶች ውስጥ የሚሠሩ ገበሬዎች ገቢ ዝቅተኛ ሲሆን ፣ ከዚህም በተጨማሪ ኅብረተሰቡ ምርታቸውን እስከፈለገው ድረስ ከመንግሥት ድጎማም እንዲሰጣቸው ሊደረግ ይችላል ። ይህም ገበሬዎቹን ለማገዝ ሲባል በአብዛኛው በሶሻሊስት አገሮች የሚሠራበት ዘዴ ነው ።

የልዩነት ኪራይን በመጠኑም ቢሆን ለመገደብ አንዳንድ ሶሻሊስት አገሮች የሚጠቀሙበት ዘዴ ደግሞ የግብርና ምርቶችና ዋጋ እንደአካባቢው የተለያየ ማድረግ (Regional differentiation of prices) ነው። በዚህ የአሠራር ዘዴ ዋጋዎች የሚታዩት (የሚተመኑት) በየማምረቻ አሀዶች (በእርሻ) ሳይሆን በአካባቢ ነው ። የሶቭዬት ኅብረት የግብርና ምርቶች ዋጋም በዚህ መርህ ላይ የተመሠረተ ነው ። የዚህም መሠረታዊ ምክንያት የተስተካከለ ሚዛናዊ የዕድገት ሁኔታ ለመፍጠር ነው ።

"የአማካይ" ወይም "የጠፍ" መሬቶች ወጪ በግብርና ምርቶች ዋጋ ላይ ያለውን ተጽዕኖ በሚመለከት በሀንጋሪ ከፍተኛ ውይይቶች የተካሄዱ ሲሆን በመጨረሻም ከሚከተሉት ማጠቃለያዎች ላይ ለመድረስ ችለዋል ።

ሀ/ የተወሰኑ የመሬት ዓይነቶች ለተወሰኑ የምርት ዓይነቶች ብቻ ተስማሚ መሆናቸውን መቀበልና በዚህም መሠረት የምርት እስፔሻላይዜሽን ማድረግ እንጂ አንድ ዓይነት ምርት በሁሉም መሬቶች ላይ ሊመረት ይችላል የሚለው ታሳቢ በዋጋ አወሳሰን ጊዜ መወሰድ የለበትም ። የተለያዩ የምርት ዓይነቶች ለነርሱ በሚስማማ የመሬት ዓይነት ላይ ብቻ መመረት አለባቸው የሚለው አስተሳሰብ ተቀባይነት ካገኘ የሚቀረፀው የዋጋ ፖሊሲ የአመራረት ብቃትንም (economic efficiency) ከግምት ውስጥ ሊያስገባ ይችላል ።

ለ/ የመንግሥት የመግዣ ዋጋ በሚወሰንበት ጊዜ መንግሥት ከጠቅላላው ምርት ውስጥ ምን ያህሉን ነው ለመግዛት የሚፈልገው? (በሙሉ ፣ ግማሹን ፣ ወይንም አነስተኛ መጠን) የሚለው ጥያቄም መመለስ አለበት ። በዚህ አስተሳሰብ በዋጋ አወሳሰን ጊዜ ከአማካይ የለምነት ደረጃ በታች ያሉ እርሻዎችን ወጪ ከግምት ውስጥ የማስገባት ጥያቄ የሚነሣው መንግሥት አንድን የምርት ዓይነት ሙሉ በሙሉ (በሞኖፖል) ሲገዛ ብቻ ይሆናል ። ሆኖም "የመሬት ኪራይ" እንደዋጋ መወሰኛ ታሳቢ ሆኖ ሊወሰድ የሚችለው መንግሥት የአንድ

የእህል ዓይነት የምርት መጠን እንዲጨ ምር ወይንም እንዲቀንስ ሲፈለግ ነው። ጠፍ መሬቶች እንዲታረሱ በማድረግ የም ርት መጠን እንዲጨምር ሲፈለግ የማም ረቻ ዋጋ መጨመርን ያስከትላል ። በእን ጻሩ ግን መንግሥት የሞኖፖል ግዥ የሚያ ካሂድባቸው የምርት ዓይነቶች የዋጋ አወሳ ሰን በሌላ መልክ መታየት እንዳለበት የሀን ጋሪ ኢኮኖሚስቶች ይስማማሉ ። ከዚህም በተጨማሪ ሶሻሊስት የዋጋ አወሳሰን የልዩ ነት ኪራይ ሚናን ውስን ያድርገው እንጂ ጨርሶ እንዳላጠፋው እነዚሁ ኢኮኖሚስ ቶች ይናገራሉ ።

በአብዛኛው ሶሻሊስት አገሮች እርሻ ዎች ከገበያ ቦታ ባላቸው ርቀት ምክንያት የሚፈጠረውን የልዩነት ኪራይ ቁጥር 1ን ከስሌት ለማውጣት የሚጠቀሙበት ዘዴ በመግዣ ዋጋ አወሳሰን ውስጥ የማጓጓዣ ወጪን በሙተው ነው ። ይህም የሚሆነው በደንብ የተስፋፉ የግዢ ጣቢያዎችና አስተ ማማኝ የሆኑ የማጓጓዣ ዘዴዎች ስላሏቸው ነው ።

በአጠቃላይ ከላይ ለማሳየት እንደተሞከ ረው "የመሬት ኪራይን" ሚና በዋጋ አወሳ ሰን ጊዜ በታሳቢነት መውሰድን በሚመለ ከት በሶሻሊስት አገሮች ውስጥ የተለያዩ አመለካከቶችና አሠራሮች አሉ ። የመሬት ኪራይ (የሥጣት ደረጃ ልዩነት) ያለውን ሚና በተለያየ መንገድ ለማጥበብ ቢሞከ ርም ጨርሶ ማጥፋቱ ቀላል እንዳልሆነ ከልምዳቸው ለመረዳት ይቻላል ።

ከዚህ በላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በሶሻሊስት አገሮች በተካሄዱት የኢኮኖሚ ማሻሻያ ለውጦች ሁሉ የሸቀጥና የገንዘብ ግንኙነቶች (የዋጋ) ሚና በኢኮኖሚው አስ ተዳደር ውስጥ ምን ያህል ድርሻ ይሰጠው ? በሶሻሊስት የኢኮኖሚ አስተዳደር ዲሞክራ ሲያዊ ማዕከላዊነት ተጠብቆ የእሴት ሕግ ጠቃሚ ጐኖችን እንዴት አድርጐ ለኢኮኖ ሚና ለማኅበራዊ የተፋጠነና የተሟላ ዕድ ገት ለመጠቀም ይችላል ? የሚሉትና ተዛማ ጅነት ያላቸው ጥያቄዎች ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቷቸው ቆይቷል ፣ እየተሰጣቸውም ነው። በሂደቱም አያሌ ችግሮች ገጥመዋል ፣ በመሠረቱ በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ፣ በካፒ ታሊስት ኅብረተሰብ እንደሚደረገው ዋጋ ለግብታዊ የእሴት ሕግ አሠራር የማይተው እንዲያውም የሕጉን ነባራዊ አሠራር በትክ ክል ተረድቶ እንደተጨባጩ ሁኔታ ለሕ ዝብ የተሟላ ዕድገት በሚበጅ መልክ ለመ ጠቀም ጥረት ስለሚደረግ በሚደረገው ሰፊ ጥረት ውስጥ የሚያጋጥሙ ችግሮች ናቸው።

በሁሉም ሶሻሊስት አገሮች በዋጋ ፖሊሲ አማካይነት የምርት ኃይሎችን ዕድ ገት ለማፋጠን ፣ የተለያዩ የኢኮኖሚ ዘርፎ ችን ዕድገት የተስተካከለ ለማድረግ ወይም እንደተጨባጩ ሁኔታንና እንደ አስፈላጊ ነቱ የአንዱን ዘርፍ ዕድገት የበለጠ ለማፋ ጠን ፣ የኅብረተሰቡን በተለይም የሰፊውን ሕዝብ የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻልና መሠረታዊ ሸቀጦች እንዲቀርቡለት ለማድረግ ወዘተ ጥረት ተደርጓል ።

የግርጌ ማስታወሻ

1. L.A. Alexandrov and others. The *Teaching of political Economy: A Critique of Non-Marxist Theories* (Moscow: Progress Publishers, 1981). የኢቡትን ጽንሰሐሳብ በተመለከተ በቡርዧው ፖለቲካ ኢኮኖሚና በማርክሳዊ ሌኒናዊ ፖለቲካ ኢኮኖሚ መካከል ያለውን ልዩነት በማነጻጸር ያቀርባል ።
2. ካርል ማርክስ ፣ ካፒታል ቅጽ 1. (አዲስ አበባ ፣ ኩራዝ አሳታሚ ፣ 1976) ገጽ 3 ፣
3. Anna-Justta Pietsch, interview with prof. J.Kornai. "Shortage as a fundamental problem of centrally planned economices and the Hungrian reform", *Economic Planning*, Vol. 18, No,3. 1982 as summarised in J.Kornai, Economics of Shortage Amsterdam. (North-Holland, 1980). *Passim.*
4. የኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ፣ ርዕዮተዓለም መምሪያ፣ማርክሳዊ ሌኒናዊ ፖለቲካ ኢኮኖሚ ፣ የካፒታሊስት ስልተምርት ክፍል 2 ፣ የካቲት 1974. ገጽ 63.
5. ካርል ማርክስ ፣ ገጽ 35.
6. K. Marx *Capital* Vol, III (Mosscow: Progress Publishers, 1962), P. 174.
7. P.I.Nikitin, *the Fundamental of Political Economy* (Moscow: Progress Publishers, 1983), PP.63—67.
8. *Ibid*, PP. 65—66 and M.N. Ryndina and G.P. Chernikov. eds. *Political Economy of Capitalism* (Moscow; Progress Publishers, 1985), PP.65—66.
9. የኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ርዕዮተዓለም መምሪያ ፣ ማርክሳዊ ሌኒናዊ ፖለቲካ ኢኮኖሚ የካፒታሊስት ስልተምርት ክፍል 2 ፣ 12—67
10. K.Marx *Selected Works* Vol.I. (Moscow: Progress Publishers, 1976), PP.142—174 and L.A Alexandrov and others. See also Bela Csikos – Nagy *Socialist Price Theory and Price Policy* (Budapest: Akademia, 1975), PP. 9 – 123.
10. See Bela Csikos – Nagy, p.76.
11. J.Stalin, Economic Problem of Socialism in the USSR, Supplement to *New Times*, No, 44, 1952.
13. Bela Csikos – Nagy, p. 204.

Differential Rent I

Annex I

Land	Capital outlay (Dollars)	Average Profit (Dollars)	Output (Centners)	Individual Price of production (Dollars)		Social Price of Prodúctin		Differential Rent I (Dollars)
				Total Produce	One centner	One centner	Total Produce	
Best	100	20	20	120	6	12	240	120
Average	100	20	15	120	8	12	180	09
Worst	100	20	10	120	12	12	120	—

Source:— M.N. RYNDINA, G.P CHERNIKOV, G.N. KHUDOKORMOV – Fundamentals of political Economy, Progress Publishers, Moscow, 1980, Page 79.

Absolut Rent

Annex II

Branches	Organic Composition of capital	Surplus Value	Value of Product	Individual rate of profit	Average rate of profit	Average Profit	Price of Production	Absolut rent
Industry	80c + 20V	20	120	20%	20%	20	120	
Agriculture	60c 40V	40	140	40%	20%	20	120	20

Source,— ibid – Page 81.

መስከረም

* የዋጋ ንድፈ ሐሳብ
* ድንበር ዘለል ሞኖፖሎች በታዳጊ አገሮች ላይ የሚፈጽሟቸው ደባዎች
* የኒካራጓ ሕዝብ ፀረ-ኢምፔሪያሊስት ትግልና የዩናይትድ እስቴትስ ደባ

ማርክሳዊ ሌኒናዊ የርዕዮተዓለም መጽሔት

ቅጽ ፰ ቁጥር **33**
መጋቢት 1980

መስከረም

ቅጽ ፰ ቁጥር 33
መጋቢት 1980

ማርክሳዊ ሌኒናዊ የርዕዮተዓለም መጽሔት

ማውጫ

ገጽ

* የዝግጅት ገጽ 3

* የዋጋ ንድፈ ሐሳብ 7
— ከልዩ ልዩ ጽሑፎች የተቀነባበረ

* ድንበር ዘለል ሞኖፖሎች በታዳጊ አገሮች ላይ የሚፈጽሟቸው ደባዎች 32
— ወልደ ዮሐንስ ወርቅነህ

* የኒካራጓ ሕዝብ ፀረኢምፔሪያሊስት ትግልና የዩናይትድ እስቴትስ ደባ 58
— ዝናቡ ከበደ

በኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ
ርዕዮተዓለም መምሪያ እየተዘጋጀ በየሦስት ወር የሚወጣ
መስከረም 1973 ተመሠረተ

አድራሻ
የፖስታ ሣጥን ቁጥር — 80001
የስልክ ቁጥር — 113000

ድንበር ዘለል ሞኖፖሎች በታዳጊ አገሮች ላይ የሚፈጽሟቸው ደባዎች

ወልደ ዮሐንስ ወርቅነህ

መግቢያ

የቀጥታ ቅኝ አገዛዝ በመወገዱ ፖለቲካዊ ነፃነታቸውን ያገኙ አገሮች ብዛት በ2-4 እጅ ጨምሯል ። ከነዚህም አገሮች መሀከል ሁለት ሦስተኞቹ ታዳጊ አገሮች በሚለው ስያሜ የሚጠሩ ናቸው ።

እነዚህ አገሮች በኢኮኖሚ ፣ በባሕል ፣ በማኅበራዊ ሕይወት ፣ በአስተዳደር ሥርዓት ፣ በሚያራምዱት የዕድገት ፈለግና በመሳሰሉ ጉዳዮች የተለያዩ ናቸው ። ይሁንና ከነዚህ ልዩነቶቻቸው ጎን በዓለምአቀፍ የኢኮኖሚ አወቃቀር ሥርዓት ውስጥ በጋራ ስያሜ እንዲጠሩ ያስቻላቸው የወል ባሕርያትም አሏቸው ። ከነዚህ የወል ባሕርያት መካከል ዋነኞቹ ፤

አንደኛ ፡ ሕዝባቸውና የተፈጥሮ ሀብታቸው በበለፀጉ የካፒታሊስት አገሮች በመበዝበዝ ላይ መሆናቸው ከኢምፔሪያሊስት መንግሥታትና ከድንበር ዘለል ሞኖፖሎች ምዝበራ ለመላቀቅና ነፃ ኢኮኖሚያዊ ሕይወት ለመገንባት የሚያደርጉት ፖለቲካዊ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥረቶች ፤

ሁለተኛ ፡ እነዚህ አገሮች ለሚታገሉለት ኢኮኖሚያዊ ነፃነት መሠረት በመሆን የሚያገለግላቸው የራሳቸው የሆነ ውስጣዊ የኢኮኖሚ አደረጃጀት ለመዘርጋት የሚያደርጉት ትግል ፤

ሦስተኛ ፡ የበለፀጉ ካፒታሊስት አገሮች በውጭ የኢኮኖሚ ግንኙነቶች አማካይነት ታዳጊ አገሮችን ለመበዝበዝ ያላቸውን ኃይል ለመገደብ ብሎም ለማስወገድ የሚያስችል አዲስ ዓለምአቀፍ የኢኮኖሚ ሥርዓት ለማስፈን የሚያደርጉት የጋራ ትግል ናቸው ።

ታዳጊ አገሮች ከዓለም የቆዳ ስፋት ከግማሽ በላይ ፣ ከሕዝብ ብዛት 70% ያህሉን ፣ ከኢንዱስትሪ ምርት ደግሞ 15% የሚይዙ ናቸው ። በጥሬ ሀብት አቅርቦት ለምሳሌ ከብረትና ከመዳብ ምርት 50% ፣ ከቦክሳይት ምርት 30% ለዓለም ገበያ ያቀርባሉ ። ከክምችት አንፃርም ቢሆን ለምሳሌ ክሮም 100% አልማዝ 90% ፣ ቆርቆሮ 85% ፣ ኒኬል 85% ፣ የተፈጥሮ ጋዝ 74% ፣ ቦክሳይት 69% ፣ ማንጋኒዝ 64% መዳብ 56%፤ ያልተጣራ ክሮም 30% የያዙ በመሆናቸው ከፍተኛ የጥሬ ሀብት ባለፀጎች ናቸው ። ይሁንና ከዚህ ከፍተኛ ክምችት ውስጥ የታዳጊ አገሮች ድርሻ ከጠቅላላው የዓለም ድርሻ ከአሥር አንድ ብቻ ሆኖ ይገኛል ።[1] የተቀረው ዘጠኝ እጅ እየተዘረፈ ወደ ኢምፔሪያሊስት አገሮች በማያቋርጥ ሁኔታ በመጋዝ ላይ ይገኛል ። ኢምፔሪያሊስት አገሮች በድንበር ዘለል ሞኖፖሎች አማካይነት በታዳጊ አገሮች ኢኮኖሚያዊ ፣ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ሕይወት ላይ የሚያደርሱት በደል መጠኑ እጅግ የከፋ ነው ።

ድንበር ዘለል ሞኖፖሎች

በበለፀጉ ካፒታሊስት አገሮች በቅድሚያ በብሔራዊ ክልል ከዚያም በዓለምአቀፍ ደረጃ የምርትና የካፒታል መከማቸትና መማከል ፣ በተለይም ደግሞ ካፒታልን ከብሔራዊ ክልል አሻግሮ በሌሎች አገሮች ኢኮኖሚያዊ ሕይወት ውስጥ እንዲንቀሳቀስ ማድረግ መጀመሩ ዓለምአቀፍ ግንኙነቶች እንዲሰፉና ዓለምአቀፍ ሞኖፖሎች እንዲመሠረቱ ምቹ ሁኔታን ፈጥሯል ።

በ19ኛው ምዕተ ዓመት ማክተሚያ ላይ በበለፀጉ ካፒታሊስት አገሮች የተወሰኑ የኢኮኖሚ መስኮችን በመያዝ የተከሰቱት ዓለምአቀፍ ሞኖፖሎች በ20ኛው ምዕተ ዓመት መባቻ ላይ የእነዚህን አገሮች ታላላቅ የኢንዱስትሪ ዘርፎች በመቆጣጠር የኢምፔሪያሊዝም አይነተኛ ባሕርይ በመሆን አድገዋል ። ዛሬ ዋና ዋናዎቹ 500 ዓለምአቀፍ ሞኖፖሎች ከካፒታሊስት ሀገሮች ጠቅላላ ብሔራዊ ምርት ከሦስት እጅ አንዱን ፣ ከኢንዱስትሪ ምርት ግማሽ ያህሉን ያመርታሉ ። ከካፒታሊስቱ ዓለም ጠቅላላ ንግድ 60% በቀጥታ በቁጥጥራቸው ሥር ሲያውሉ የዳበሩ ካፒታሊስት አገሮች ወደ ውጭ ከሚልኩት ካፒታል አጠቃላይ መጠን ደግሞ 90% ያህሉን ይይዛሉ ።[2]

ዓለምአቀፍ ሞኖፖሎች ከብሔራዊ ክልላቸው ውጭ ካፒታላቸውን በማንቀሳቀሳቸው ሁሉም የጋራ ባሕርይ ይኑራቸው እንጂ ከአክሲዮን ካፒታላቸው ምንጭና ከባለቤትነት ባሕርያቸው አኳያ ሲታዩ የባለብዙ ብሔር ሞኖፖሎች* (Multinational Monopolies) እና ድንበር ዘለል (Transnational Monopolies) ሞኖፖሎች ተብለው በሁለት ይከፈላሉ ።

ድንበር ዘለል ሞኖፖሎች ካፒታልን ከአገራቸው ውጭ በመላክ በሚያደርጉት ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ አኳያ ዓለምአቀፍ ባሕርይ ያላቸው የኢምፔሪያሊስት አገሮች ኢኮኖሚያዊ ድርጅቶች ናቸው ።[3]

በካፒታሊስት ዓለም የሚገኙ ማንኛዎቹም ትላልቅ ኢኮኖሚያዊ ድርጅቶች ሞኖፖሎች እንደማይባሉ ሁሉ በካፒታል ምንጫቸው ብሔራዊ የሆኑ ዓለምአቀፍ የኢኮኖሚ ድርጅቶችን ሁሉ ድንበር ዘለል ሞኖፖሎች ናቸው ማለት ያስቸግራል ። ዓለምአቀፍ ድርጅቶች ድንበር ዘለል ሞኖፖል የሚባሉት አንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ የዓለም ካፒታሊስት የኢኮኖሚ ዘርፎች ላይ ጠንካራ ቁጥጥር ማድረግ ሲችሉና በእነዚህ የኢኮኖሚ ዘርፎች የበላይነት ኖሯቸው የሞኖፖል አቋም ሲመሠርቱ ነው ። በመሆኑም የተሰማሩባቸውን አገሮች ሉአላዊነት ጥሰው ለመግባትና በአኳያውም ከነዚህ አገሮች ሊሰነዘርባቸው የሚችለውን የአፀፋ ጥቃት ለመመከት የሚያስችል ኢኮኖሚያዊ አቅም የሌላቸው አነስተኛ የንግድ ድርጅቶችን ድንበር ዘለል ሞኖፖሎች ናቸው ማለት ትክክለኛ አጠቃቀም አይሆንም ።

*ባለብዙ ብሔር ሞኖፖሎች (Multinational Monopolies) የሚባሉት ከሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ አገሮች ባሟሉት የአክሲዮን ካፒታል የተመሠረቱና በብዙ አገሮች የጋራ ቁጥጥር የሚመሩ የኢምፔሪያሊስት አገሮች የኢኮኖሚ ድርጅቶች ናቸው ።

በሌላ በኩል ደግሞ ድንበር ዘለል ሞኖፖሎች ከኢምፔሪያሊዝም መሠረታዊ ባሕርያት ጋር የተገናዘቡ መሆናቸው እየታወቀ በካፒታል ምንጫቸው ብሔራዊ የሆኑ የሶሻሊስት አገሮች የውጭ ንግድ ድርጅቶችን ድንበር ዘለል ሞኖፖሎች በሚለው ጽንሰ ሐሳብ ውስጥ አዳምሮ ማቅረቡ የኢምፔሪያሊስቶችን ድንበር ዘለል ሞኖፖሎች መሠረታዊ ይዞታቸውን ለማድበስበስ ካልሆነ በቀር ትክክል አይደለም ።

በመሆኑም በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ድንበር ዘለል ሞኖፖሎች የምንላቸው በዓለም አቀፍ የካፒታሊስት ኢኮኖሚ ውስጥ የሞኖፖል አቋም የመሠረቱትን ግዙፍ የኢምፔሪያሊስት አገሮች የኢኮኖሚ ተቋሞችን ነው። እንዲህ ዓይነቶቹ ድንበር ዘለል ሞኖፖሎች በ1970ዎቹ ማከተሚያ ላይ በቁጥራቸው ከ400 በላይ እንደነበሩ መረጃዎች ይጠቁማሉ ።[4]

ድንበር ዘለል ሞኖፖሎች ከባለብዙ ብሔር ሞኖፖሎች ይልቅ እያደጉና እየተስፋፉ በመሄድ ላይ ናቸው ። ዛሬ እነዚህ ሞኖፖሎች ከካፒታሊስቱ ዓለም የኢንዱስትሪ ምርት ውጤት 40% ፣ ከውጭ ንግድ 60% ፣ ከቴክኖሎጂ ውጤቶች 80% በቁጥጥራቸው ሥር አውለዋል ። ከብሔራዊ ድንበራቸው ውጭ ባዋቀሯቸው ቅርንጫፎቻቸው ከ33 ሚሊዮን ሰዎች በላይ ቀጥረው በማሠራት ላይ ይገኛሉ ።[5] በሚቀጥሉት አሥር ዓመታት ከላይ ከተጠቀሰው መጠን እየጨመሩ እንደሚሄዱ ኢኮኖሚስቶች ይናገራሉ ።

የአንዳንድ ድንበር ዘለል ሞኖፖሎች የዓመት ሽያጭ ከበርካታ አገሮች ብሔራዊ ገቢ በልጦ ይታያል። ለምሳሌ በዩናይትድ ስቴትስ ከሚገኙ ድንበር ዘለል ሞኖፖሎች ውስጥ የሦስቱ ዋና ዋና ድንበር ዘለል ሞኖፖሎች (“ኤክሶን” “ሞቢልና” “ጄኔራል ሞተርስ”) ዓመታዊ ሽያጭ የአውስትሪያን ፣ የዴንማርክን ፣ የግሪክንና የኒውዚርላንድን የተጠቃለለ ምርት ይበልጣል ።[6] ጄኔራል ሞተርስ በ1975 ብቻ 35,000 ሚሊዮን ዶላር ገቢ አግኝቷል ። ይህ ገንዘብ በማዕከላዊ አሜሪካ ካሉ አገሮች (ከቺሊ ፣ ከቦሊቪያ ፣ ከኢኳዶር ፣ ከፓራጓይ ፣ ከኡራጓይ ፣ ከፔሩ ፣ ከሃይቲና ከዶሚኒካን ሪፐብሊክ) አጠቃላይ ብሔራዊ ምርት (GNP) ይበልጣል ። የአፍሪካ አካባቢንም ብንቃኝ 24 ኋላቀር የአፍሪካ አገሮች ተጠቃለው የአይ·ቲ·ቲን ያህል የኢኮኖሚ አቅም የላቸውም ።[7]

ድንበር ዘለል ሞኖፖሎች መዋቅራቸውን በስፋት በመዘርጋት የተለያዩ አገሮችን ተረፈ እሴት ስለሚመዘብሩ ፣ የሳይንስና የቴክኖኖሎጂ አምራቾችና ተጠቃሚዎች በመሆናቸው ፣ ዘመናዊና የተቀላጠፈ የሥራ አደረጃጀት ስላላቸውና የተፈጥሮ አካባቢ መበከልን ፣ የጥሬ ሀብት አጠቃቀምን ፣ የቀረጥና የምንዛሬ አከፋፈልን አስመልክቶ ለምዝበራቸው ቁሳዊና ሕጋዊ አመችነት ያላቸውን አካባቢዎች በመምረጥ ካፒታላቸውን የሚያሻግሩ በመሆኑ ከፍተኛ የትርፍ መጠን እያገኙ በካፒታሊስቱ የኢኮኖሚ ሥርዓት ውስጥ ከፍተኛ ዓለምአቀፍ ኃይል ለመሆን በቅተዋል ።

ከሁሉም በላይ ለድንበር ዘለል ሞኖፖሎች ትርፍ ዋነኛ ምንጭ የሆኑት ታዳጊ አገሮች ናቸው ። ከተባበሩት መንግሥታት የንግድና የልማት ጉባኤ (ከአንክታድ) የተገኘ መረጃ እንደሚያመለክተው በ1970ዎቹ ብቻ ድንበር ዘለል ሞኖፖሎች ከታዳጊ አገሮች የዘረፉትን ትርፍ 72·2 ሚሊያርድ ዶላር ነበር ። አንድ የተባበሩት መንግሥታት ጥናት በተጨማሪ እንደሚጠቁመው ዩናይትድ ስቴትስ ከብሔራዊ ድንበሯ ውጭ ካሳማራችው ሙአለንዋይ ውስጥ “ከሦስተኛው ዓለም” የተገኘው የትርፍ መጠን 18% ሲሆን በዚሁ ወቅት በምዕራብ አውሮፓ ካዋለችው ሙአለንዋይ ያገኘችው አማካይ ትርፍ 9·8% ብቻ ነበር ። በ1970ዎቹ ዩናይትድ ስቴትስ ወደ ታዳጊ አገሮች ያሳማራችው ከብሔራዊ ድንበሯ ውጭ ከተሰማራው ካፒታል 35% ሲሆን ከዚህ ካፒታል የተገኘው ትርፍ ግን ከብሔራዊ ክልል ውጭ የተሰማራው ካፒታል ተጠቃሎ ካስገኘው ትርፍ 60% የያዘ ነበር።[8] ድንበር ዘለል ሞኖፖሎች በአፍሪካና እስያ በሥራ ላይ ከሚያውሉት እያንዳንዱ መቶ ዶላር ከ26—31 ዶላር ፣ በላቲን አሜሪካ ደግሞ ከ10 እስከ 16 ዶላር ትርፍ ያገኛሉ።[9] ከነዚህ መረጃዎች የምንገነዘበው ድንበር ዘለል ሞኖፖሎች አነስተኛ ሙአለንዋይን በማሰማራት በአጭር ጊዜ ውስጥ የዳለበ ትርፍ ማግኘት የሚችሉት ከታዳጊ አገሮች መሆኑን ነው ።

2. የድንበር ዘለል ሞኖፖሎች ዓላማና የብዝበዛ ስልት

ድንበር ዘለል ሞኖፖሎች ኢምፔሪያሊዝም በታዳጊ አገሮች ላይ ጥቃት የሚሰነዝርባቸው የዘመኑ ዓይነተኛ መሣሪያዎች ናቸው ። በመሆኑም የድንበር ዘለል ሞኖፖሎች ዓላማ ጥንድ ነው ። በአንድ በኩል የኢምፔሪያሊዝም የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ፖሊሲ እንዲቀጥል አስፈላጊውን ሁሉ መፈጸም ፤ በሌላ በኩል ደግሞ የታዳጊ አገሮችን ጥሬ ሀብትና ርካሽ ጉልበት በመበዝበዝ ትርፋቸውን ማዳለብ ነው ። ድንበር ዘለል ሞኖፖሎች ይህንን ዓላማቸውን ተግባራዊ ለማድረግ ፖለቲካዊና ወታደራዊ ፣ ርዕዮተ ዓለማዊና ኢኮኖሚያዊ ስልቶችን ይጠቀማሉ ።

2·1· ወታደራዊና ፖለቲካዊ ስልቶች

የቀጥታ የቅኝ አገዛዝ ሥርዓት በሰፈነባቸው ዘመናት (ከ18ኛው እስከ 20ኛው ምዕት ዓመት የመጀመሪያዎቹ አጋማሽ ድረስ) ይህ ስልት የኢምፔሪያሊስት መንግሥታት ዋነኛ የመበዝበዣ ስልት ሆኖ ቆይቷል ። ቀጥታ ቅኝ አገዛዝ ተወግዶ በእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ በመተካቱ “በጠመንጃ አፈሙዝ አስገድዶ” የመበዝበዙ ስልት ከቀድሞው ግርድፍና የፈጠጠ መልኩ ተለውጦ ለአዲሱ የዓለም አቀፍ ሁኔታ አመቺ በሆነ መንገድ በማገልገል ላይ ይገኛል ። በቅርቡ በ1980ዎቹ ዩናይትድ ስቴትስ በግሬናዳ ፣ በሊቢያና ዛሬም በኒካራጓ ሕዝብ ላይ የፈጸመችውና የምትፈጽመው ወታደራዊ ጣልቃ ገብነት ይህ ስልት ዛሬም ለማገልገሉ በቂ ምሳሌ ነው ። በተለይም ዛሬ ኢምፔሪያሊዝም በድንበር ዘለል ሞኖፖሎች አማካይነት የታዳጊ አገሮችን ብሔራዊ ክልል ጥሶ መግባት በመቻሉ በዘመናችን በማራመድ ላይ ያለው ወታደራዊና ፖለቲካዊ ስልቶቹ ከውጭና ከውስጥ የተቀናጁ በመሆናቸው አደገኛነታቸው አይሎ ይታያል ። ድንበር ዘለል ሞኖፖሎች ተራማጅ ሥርዓትን ለመመሥረት የሚታገሉ የአርነት ንቅናቄዎችን በመከፋፈል ማዳከም ፣ የካፒታሊስት የኢኮኖሚ የዕድገት ፈለግ የማይከተሉትን አስተዳደሮችን ማስገልበጥ ወይም ፀረ አብዮተኞችን በማደራጀትና ፣ በማስታጠቅ የርስ በርስ ጦርነት እንዲካሄድና ኢኮኖሚያቸው እንዲዳከም ማድረግ ነው ።

ድንበር ዘለል ሞኖፖሎች በተለያዩ የዓለም ክፍሎች በሚኖሩ ታዳጊ አገሮች ሕዝቦች ደህንነትና መንግሥታት ላይ ከፈጸሟቸው ወታደራዊ ፖለቲካዊ ደባዎች መካ

ክል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው ።

1· በ1971 የፓናማ ፣ የሆንዱራስና የኮስታሪካ መንግሥታት በዩናይትድስቴትስ ሙዝ ኩባንያዎች ላይ የውጭ ንግድ ቀረጥ በመጨመራቸው ኩባንያዎቹ ግንባር ፈጥረው በተጠቀሱት አገሮች ውስጥ ብዝበዛ ለማካሄድ 5 ሚሊዮን ዶላር ለጉቦ አዋጡ ። ከመዋጮው ሌላ እነዚህ ኩባንያዎች የታሸገ ሙዝ ከየወደቡ ላለማንማት ባደረጉት አድማ 145,000 ሣጥን (የታሸገ ሙዝ) ከጥቅም ውጭ አደረጉ ። ዩናይትድ ብራንድ በመባል የሚታወቀው ሞኖፖል ደግሞ ሌላ ታክቲክ በመቀየስ ለሆንዱራስ የኢኮኖሚና የንግድ ሚኒስትር ለነበረ ባለሥልጣን 1.25 ሚሊዮን ዶላር ጉቦ በመስጠት በአንድ ሣጥን ሙዝ 0.50 ሳንቲም ለሆንዱራስ መንግሥት ቀረጥ እንዲከፍል የተወሰነውን ወደ 0.25 ሳንቲም አስቀንሷል ። በዚህም አማካይነት ከ6 7 ሚሊዮን ዶላር የሚሆን የሆንዱራስን ሕዝብ እንጡራ ሀብት ዘርፏል ።[10]

2· መንግሥታት የአገሬቸውን የሠራተኛ ጉልበትና የተፈጥሮ ሀብት በመዝበዝ ላይ የተሰማሩትን ድንበር ዘለል ሞኖፖሎች ለመውረስ እቅድ ሲያወጡ ወይም መንግሥታዊ መመሪያ ሲያስተላልፉ ሞኖፖሎች የጋራ ግንባር በመፍጠር ያድማሉ ። ለምሳሌ "የቬንዙዌላ መንግሥት የነዳጅ ዘይት ኢንዱስትሪዎችን ለመውረስ በተዘጋጀ ጊዜ እርምጃው ተግባራዊ እንዳይሆን አሰናክለዋል ።"[11]

3· ለሞኖፖሎቻቸው እንቅስቃሴ ምቹ ሆነው የማይገኙ የታዳጊ አገር መሪዎችን ለማስገደል ቡድኖችን ያደራጃሉ ። ለምሳሌ በ1970ዎቹ የፈረንሳዩ ማሪዩስ ዶ ማድጋስካር የተባለው ድንበር ዘለል ሞኖፖል የማዳጋስካሩን ፕሬዚዳንት አር· ራትሲማንድራቫ እንዲገደሉ ድርጊቱን ለሚፈጽሙ ቡድኖች ገንዘብ መክፈሉ ተጋልጧል ።[12]

4· በ1974 በናይጀር የተደረገውን ወታደራዊ መፈንቅለ መንግሥት ያቀነባበሩና ተግባራዊም ያደረጉት በሀገሪቷ የነበሩ ፍራንች – ፒኪኒ – ዩጊኒ – ኩልማን ፣ ሮትሺልድ ሃውስና ፍራንክ ዌስት ጀርመን ሰመር – ግሩፕ የተባሉ የፈረንሳይና የጀርመን ፌዴራል ሪፐብሊክ ሞኖፖሎች መሆናቸው ታውቋል ። መፈንቅለ መንግሥት ከተካሄደ በኋላ የአገሪቷን ሮስፌት ፣ ዩራንዩምና የዘይት ክምችት በቀላሉ ዋጋ ተስማምተው ለመያዝ በቅተዋል ።[13]

5· በ1960 ዩኒየን ሚኒየር (Union Miniere) በመባል የሚታወቀው የቤልጅግ ሞኖፖል የኢምፔሪያሊስት አፈቀላጤ የነበረውን ሞይስ ሾምቤን ለመርዳት በካታንጋ ክፍለ ሀገር (ቀደም ሲል ኮንጐ በዛሬይቱ ዛየር) የተቀጣጠለውን ሕዝባዊ አመፅ እንዲያከሽፉ ለወታደሮች ገንዘብ ከፍሏል ።[14]

6· ከ1960 1970 በምዕራብ አፍሪካ በምትገኘው ናይጄሪያ ውስጥ በኢቦና በሃውሳ ጎሳዎች መካከል የተደረገው የርስ በርስ ጦርነት እንዲነሳሳ ያደረገውና እጁኩን የረዳው ኢ·ኤል·ኤፍ·ኢራፕ (ELF – ERAP) የሚባለው ንብረትነቱ የፈረንሳይ መንግሥት የሆነው የዘይት ኩባንያ እንደነበረ ታውቋል ።[15]

7· የአንጐላ ሕዝብ ለ650 ዓመታት ሲመዘብረው የኖረውን የፖርቱጋልን ቅኝ አገዛዝ ለመገርሰስ ሕዝቡን ያነሳሳውና መርቶም ለነፃነት ያበቃው የኤም·ፒ·ኤል·ኤ ፓርቲ ነው። ይሁን እንጂ የአንጐላ ሕዝብ የፖለቲካ ነጻነቱን ብቻ ሳይሆን ኢኮኖሚያዊ ነፃነቱንም እውን ለማድረግ የሶሻሊስት ፈለግን በመከተሉ በሀገሪቱ የተሰማሩ ድንበር ዘለል ሞኖፖሎች በጠላትነት መሰለፋቸው አልቀረም ። ገልፍ አይል የተባለው የነዳጅ ዘይት ሞኖፖል የአንጐላን ፀጥታ የሚያናጉ ሽብር ፈጣሪዎችን በማደራጀት ፣ በገንዘብና በሞራል በመርዳት የተቻለውን ሁሉ ጥረት ማድረጉ ታውቋል።[16]

8· ሕጋዊውን የሱሪናም መንግሥት ለመገልበጥ ፀረ አብዮተኞችን በማሰባሰብ ስምንት ጊዜ ሙከራ ተደርጎ ሳይሳካ የቀረውን ሴራ ያደራጀው ሱራልኮ (Surinam Aluminium Co.) የተባለው የደች ኩባንያ ነበር።[17]

9· የኢንዶኔዥያ ሠራተኛ ሕዝብና ተራማጅ ኃይሎች የጃፓን ፣ የደችና የዩናይትድስቴትስ መንግሥታት የዘረጉባቸውን የብዝበዛ መዋቅር በጣጥሰው ነፃነታቸውን ከተጐናፀፉ ከ25 ዓመታት በኋላ መላውን ሕዝብ ወደ ብልፅግና ጐዳና ይመራ የነበረውን ሕጋዊ መንግሥት የገለበጡት በአገሪቷ ለረጅም ጊዜያት በብዝበዛ ላይ ተሰማርተው የነበሩና መንግሥቱ እርምጃ የወሰደባቸው ድንበር ዘለል ሞኖፖሎች (ዩኒሮያል ፣ ዩኒየን ካርባይድ ፣ ሲንጀር ስዊንግ ማሺን ፣ ናሽናል ካሽ ሬጅስትር ፣ ጋሩዳ አየር ላይንስ ፣ ሞቢል አይል ፣ ፓልሞሊቭና ላክስ) ናቸው ። እነዚህ ድንበር ዘለል ሞኖፖሎች ከሲ·አይ·ኤ· ጋር በመሆን ፀረ – አብዮተኞችን አደራጅተው በ1965 የኢንዶኔዥያ አብዮት እንዲቀለበስ አድርገዋል ። በሩቅ ምሥራቅ የረጅም ዘመን ትግል ታሪክ ባለውና 3 ሚሊዮን አባላት ባሉት የኢንዶኔዥያ ኮሚዩኒስት ፓርቲ አባላት ፣ ፓርቲው ባደራጃቸው 20 ሚሊዮን የሠራተኛ ፣ የገበሬ ፣ የሙያና የተለያዩ ሕዝባዊ ድርጅቶች አባላት ላይ ግፍ እንዲፈፀም የማቴሪያልና የሞራል ድጋፍ ሰጥተዋል ፣ ሴራውንም አቀናጅተዋል ። በዚህም 600,000 የሚሆኑ መስዋዕት እንዲሆኑ ማድረጋቸውን መረጃዎች ያመለክታሉ ።[18]

10· ከ1950 – 1954 በጓቲማላ ሥልጣን ይዞ የነበረውን የአርቤንስን ዲሞክራሲያዊ መንግሥት ለማስገልበጥ ዩናይትድ ፍሩት በመባል የሚታወቀው የዩናይትድ ስቴትስ ኩባንያ የገንዘብ ዕርዳታ አድርጓል ።[19]

11· ከ1960 – 1970ዎቹ ዓመታት ድረስ ቦይንግ ፣ ሬይኖልድስ ፣ ኢንገርሶል – ራንድ አንደርሰን ፣ ኬላይቶንና ኩባንያው ፣ ኤክሶን ፣ ሞቢል እና ገልፍ አይል የተባሉት ታዋቂ የዩናይትድ ስቴትስ ድንበር ዘለል ሞኖፖሎች በታዳጊ አገሮች ለሚገኙ ባለሥልጣኖች በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠር ጉቦ መስጠታቸውን ለዩናይትድ ስቴትስ ምክር ቤት አረጋግጠዋል ። በተለይም ገልፍ አይል በደቡብ ኮሪያ ተራማጅ ሥርዓት እንዳይመሠረት ለፓክ ቹንግ ሁዌ አድኃሪ መንግሥት 3 ሚሊዮን ዶላር መስጠቱን አምኗል ።[20]

12· በ1970ዎቹ መግቢያ ላይ በተለያዩ አገሮች ውስጥ ሎክሂድ 22 ሚሊዮን ፣ ኖርትሮፕ 30 ሚሊዮን ፣ እንዲሁም ኤክሶን 50 ሚሊዮን ዶላር በተለያዩ ጊዜያት ለፀረ—ሕዝብ ድርጊት ማከናወኛ ጉቦ ሰጥተዋል ።[21] የዩናይትድ ስቴትስ ላይብራሪ ኦፍ ኮንግሬስ ባንድ ወቅት እንደገለፀው ከአገሪቷ ታዋቂ ድንበር ዘለል ሞኖፖሎች መካከል 20ዎቹ ልዩ ልዩ ፀረ ሕዝብ ተግባራትን ለሚያከናውኑላቸው ወኪሎቻቸው ለጉቦና ለፖለቲካ ሥራዎች 306 ሚሊዮን ዶላር መዋጮ መክፈ

ላቸውን አጋልጧል ።[22]

ድንበር ዘለል ሞኖፖሎች በታዳጊ አገሮች ተሰማርተው የተለያዩ ተግባራትን በሚያከናውኑበት ወቅት ሁኔታዎችን አጥንቶ የሚያዘጋጇቸው ድርጅት ያስፈልጋቸዋል ። ለዚሁ ተግባር ሲ.አይ.ኤ. ለዩናይትድ ስቴትስ የንግድ ድርጅቶችና መስሎቻቸው የተለያዩ አገልግሎቶችን ይሰጣል ።[23] ሲ.አይ.ኤ. በድንበር ዘለል ሞኖፖሎች ቅርንጫፍ ሽፋንና እርዳታ የአንድን አገር የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ሁኔታ በማጥናት አለመረጋጋት እንዲፈጠርና የተተኮረበት ሀገርም ባጠቃላይ ቀውስ ውስጥ እንዲወድቅ ጥረት ከማድረግ አያቆጠብም ። ይህም ድርጊት በድንበር ዘለል ኩባንያዎች ዘንድ እንደ ኢኮኖሚ ልውውጥ ፣ ሳይንሳዊ ፣ ቴክኒካዊና ፖለቲካዊ መረጃዎች በጥብቅ የሚጠበቅ ምሥጢር ነው ።

የምዕራብ አውሮፓ ካፒታሊስት መንግሥታትና ዩናይትድ ስቴትስ አንድ ላይ በመሆን ድንበር ዘለል ሞኖፖሎቻቸው በታዳጊ አገሮች ይበልጥ የሚስፋፉበትንና በዚያ በተሰማሩበት አገር ውስጥ አንድ ችግር ቢፈጠርባቸው እንዴት እርዳታ ማግኘት እንደሚችሉም መንገድ ቀይሰዋል ። የዚህን ተልዕኮ ስትራቴጂና ታክቲክ የሚቀይሱ የሳይንስ ማዕከሎችና ተቋሞች እያስፋፉ ናቸው ። ከተቋቋሙት ማዕከሎች መካከል አቨርሲስ ፕራይቬት ኢንቨስትመንት ኮርፖሬሽን (Overseas Private Investment Corporation (OPIC)) ይገኛል ። ይህ ድርጅት በአንድ አገር ውስጥ እንደ ሕዝባዊ ንቅናቄ ፣ አብዮት ፣ ወዘተ. ያሉ ሁኔታዎች ከተፈጠሩና በድንበር ዘለል ኩባንያዎች ንብረት ላይ ጉዳት ካደረሱ ካሣ የሚከፍል ነው ። ኦፒክ (OPIC) በድርጊቱ በዩናይትድ ስቴትስ መንግሥት ዘንድ እጅግ የተደገፈ ፣ ትኩረትም የተሰጠው ነው ። ሌሎችም እንደዚሁ በሞኖፖሎቹ የተቋቋሙና ራሳቸውን የሚጠብቁባቸው ድርጅቶችም አሏቸው ። ከነዚህ መካከል ዓለም አቀፍ የዘገባና የመረጃ ሥርዓት (International Information and Reporting System) ፣ ቢዝነስ ኢንቫይሮመንት ሪስክ ኢንዴክስ (Business Environment Risk Index (BERI)) ፣ ወርልድ ፖለቲካል ሪስክ ፋውንዴሽን (World Political Risk Foundation (WPRF) እና የመሳሰሉት ይገኛሉ ።[24] የነዚህ ድርጅቶች ዓይነተኛ ተልዕኮም ድንበር ዘለል ሞኖፖሎች ሙአለንዋይን በሥራ ላይ እንዴት ማዋል እንደሚገባቸው ወይንም በስምሪታቸው ወቅት ሊያጋጥሟቸው የሚችሉ ሁኔታዎችን በቅድሚያ ማጥናትና ኩባንያዎቹ እንዲጠነቀቁ ማድረግ ነው ።

ርዕዮተዓለማዊ ስልቶች

የዚህ ስልት መሠረታዊ ዓላማ የኢምፔሪያሊስት መንግሥታትና የድንበር ዘለል ሞኖፖሎች የግል ካፒታል ወደ ታዳጊ አገሮች እንዲገባ ብሎም ካፒታሊስታዊ የምርት ግንኙነቶች እየተጠናከሩ እንዲሄዱ ርዕዮተዓለማዊና ሥነ ልቦናዊ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ነው ።

ለዚህ ዓላማቸው ተግባራዊነት ካፒታሊስቱን ዓለም ከታዳጊ አገሮች ጋር የሚያገናኙትን የተለያዩ አውታሮች በመገልገል የባሕልና የኅሊና ወረራ ያካሂዳሉ ። በታዳጊ ሀገሮች ሕዝቦች ላይ የርዕዮተዓለምና የሥነ ልቦና ጦርነትን ያካሂዳሉ ። የካፒታሊስቱን ሥርዓት "ትክክለኛነት" የሚያብራሩ የሕትመት (የፕሬስ) የእይታና ፣ የድምጽ ትንብሮችን በማዘጋጀትና በማሰራጨት የታዳጊ አገሮች ሕዝቦችን መንፈሳዊ ሕይወት በሚያመች መንገድ ለመቅረጽ ይጥራሉ ። የዩኔ

ስኮ ኤክስፐርቶች ያደረጉት አንድ ጥናት እንደሚያመለክተው የእንግሊዝና የፈረንሳይ ቴሌቪዥኖች በአንድ ዓመት ውስጥ እያንዳንዳቸው 20,000 ሰዓቶች ፣ የጀርመን ፌዴራል ሪፑብሊክ ቴሌቪዥን 6,000 ፣ የዩናይትድ ስቴትስ መንግሥት 300,000 ሰዓቶች የያዙ የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች ወደ ታዳጊ አገሮች ያሰራጫሉ ።[25]

በአያሌ የአፍሪካ ፣ የእስያና የላቲን አሜሪካ አገሮች ውስጥ ለሕዝብ ከሚቀርቡት የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች መካከል 90% የቡርዧውን ማኅበራዊ ሥርዓት ባሕል የሚያንፀባርቁና ከምዕራቡ ዓለም የመጡ ናቸው ። ለምሳሌ ያህል ጓቲማላ ከምታቀርባቸው የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች 84% ፣ ናይጀሪያ 63% ፣ ኡራጓይ 62% ፣ የመን አረብ ሪፐብሊክ 57% ፣ ኩዌትና ቺሌ 55% ኢራቅ 52% ፣ ዶሚኒካ ሪፐብሊክ ደግሞ 52% ከምዕራቡ ዓለም የመጡ ናቸው ።[26] ይህ ሁኔታ በመጠኑ ይለያይ እንጂ በሌሎችም መገናኛ ብዙኃን ላይ የሚታይ ነው ።

ጥቂት ድንበር ዘለል ሞኖፖሎች ከካፒታሊስቱ ዓለም የመረጃ (የኢንፎርሜሽን) ሥርዓት ውስጥ 75% በቁጥጥራቸው ሥር ያደረጉና[27] በተለይ ደግሞ የታዳጊ አገሮችን ብሔራዊ ክልል ጥሰው በመግባት ቅርንጫፎቻቸውን የዘረጉ በመሆናቸው በታዳጊ አገሮች መንፈሳዊ ሕይወት አቀራረፅ ላይ የሚያደርጉት የተቀነባበረ ሴራ እጅግ የከፋ ነው ። በታዳጊ አገሮች ከፍተኛ የትምህርት ተቋሞች የባሕል ማዕከሎች ወዘተ. ውስጥ የራሳቸውን ምሁራን በማዘጋጀት የተለያዩ ፀረ ሶሻሊዝም አስተሳሰቦችን ያሰራጫሉ ። ዛሬ ሰፍኖ በሚታየው የተዛባ ዓለም አቀፍ የመረጃ ሥርዓት በመጠቀም የታዳጊ አገሮችን ሕዝቦች መንፈሳዊ ሕይወት በመበረዝ ለራሳቸው ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ዓላማዎች ተግባራዊነት አመቺ ሁኔታ ለመፍጠር ያሴራሉ ።

4. ኢኮኖሚያዊ ስልቶች

ይህ ስልት የኢምፔሪያሊስት መንግሥታትና ድንበር ዘለል ሞኖፖሎች ታዳጊ አገሮችን ለመበዝበዝ ከሚጠቀሙባቸው የተለያዩ ስልቶች መካከል ዋነኛው ሲሆን ሦስት ዓላማዎች አሉት ። እነርሱም ፣—

ሀ/ የበለፀጉ አገሮችና የድንበር ዘለል ሞኖፖሎች ካፒታል ያለአንዳች ችግር በታዳጊ አገሮች ኢኮኖሚያዊ ሕይወት ውስጥ እንዲገባ አስፈላጊ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ፣

ለ/ ታዳጊ አገሮችን በበለፀጉ ካፒታሊስት አገሮች ቁጥጥር ሥር ሊያውሉ የሚችሉ ኢኮኖሚያዊ መዋቅሮችን ለይቶ ማጠናከር ፣

ሐ/ ዛሬ በካፒታሊስቱ ዓለምና በታዳጊ አገሮች መካከል ሰፍኖ የሚታየውን ያልተስተካከለ ዓለምአቀፍ የኢኮኖሚ ግንኙነት እንዳለ ማቆየት ናቸው ።

እነዚህ ዓላማዎች በካፒታሊስት መንግሥታት በተለይም ድንበር ዘለል ሞኖፖሎች በሚያደርጓቸው የተለያዩ ኢኮኖሚያዊ ስልቶች ተግባራዊ እንዲሆኑ ይደረጋል። ከእነዚህ ኢኮኖሚያዊ ስልቶች ጥቂቶቹን እንመልከት ።

4.1. ካፒታልን በተለያዩ መንገዶች ወደ ታዳጊ አገሮች ማስማራት

ካፒታልን ወደ ታዳጊ አገሮች በማስማራት የበለፀጉ አገሮችና ድንበር ዘለል ሞኖፖሎች የሚያጋብሱት ትርፍ እጅግ ከፍተኛ ነው ። ለምሳሌ በ1970ዎቹ ዓመታት የበለፀጉ ካፒታሊስት አገሮች ካፒታላ

ቸውን እንደሚከተለው ወደ ታዳጊ አገሮች አስማርተዋል ። በላቲን አሜሪካ 55.7% ፣ በአፍሪካ 13.1% ፣ በቅርብና በመካከለኛው ምሥራቅ አገሮች 4.1% ፣ በደቡብ ምሥራቅ እስያና በሩቅ ምሥራቅ አገሮች 27.1% ። ባለፉት አሥር ዓመታት የካፒታሊስት አገሮች ሙአለንዋይ "አዲሶቹ ኢንዱስትሪያዊ አገሮች" በመባል በሚታወቁት ታዳጊ አገሮች (ብራዚል ፣ ኮሎምቢያ ፣ ሜክሲኮ ፣ ኢንዶኔዥያ ፣ ወዘተ.) ላይ ያተኮረ እንደነበር መረጃዎች ይጠቁማሉ ።[28]

ድንበር ዘለል ሞኖፖሎች በታዳጊ አገሮች "የተጽዕና ክልላቸውን" ለማጠናከር በመሀከላቸው የሚያካሄዱት ትግል ቀላል አይደለም ። ለምሳሌ የዩናይትድ ስቴትስ ሞኖፖሎች ወደውጭ ከሚልኩት ካፒታላቸው ሁለት ሦስተኛውን የሚያሰማሩት በላቲን አሜሪካ አገሮች ነው ። የጃፓን ሞኖፖሎች ደግሞ በእስያ (የቅርብ ምሥራቅ አገሮችን ጨምሮ) አገሮች ሲሆን የምዕራብ አውሮፓ ሞኖፖሎች በአመዛኙ ካፒታላቸውን የሚያሰማሩት በአፍሪካና በእስያ አገሮች ነው ። በአፍሪካ የተሰማራው የምዕራብ አውሮፓ ካፒታል ዩናይትድ ስቴትስና ጃፓን በዚህ አካባቢ ካሰማሩት ድምር ካፒታል በሁለት እጅ አካባቢ የበለጠ ነው። ከዚህ የካፒታል ስርጭት አዝማሚያ በዘመኑ የካፒታሊዝም ሦስት ማዕከሎች (ዩናይትድ ስቴትስ ፣ ምዕራብ አውሮፓና ጃፓን) መካከል የተጽዕና ክልል በማበጀት ያለውን መሯሯጥ መገንዘብ ይቻላል ።

የበለፀጉ ካፒታሊስት አገሮች በድንበር ዘለል ሞኖፖሎች አማካይነት ካፒታላቸውን በቀጥታ በታዳጊ አገሮች የምርት ሂደት (በኢንዱስትሪ ፣ በእርሻ ፣ በንግድ ፣ ወዘተ.) ውስጥ በማሳተፍ ወይንም በወለድ በማበደር ፣ ካልሆነም ለፖለቲካ ዓላማቸው "በዕርዳታ" መልክ በመስጠት የታዳጊ አገር ሕዝቦችን ይመዘብራሉ ፣ ብለውም የካፒታሊስቱ ጥገኞች እንዲሆኑ ያደርጋሉ።

ሀ/ ካፒታላቸውን በቀጥታ በምርት ሂደት ውስጥ በማዋል

ድንበር ዘለል ሞኖሎፖሎች ከብሔራዊ ክልላቸው ውጭ በመሠረቷቸው ቅርንጫፎቻቸው ውስጥ ቀጥረው ከሚያሠሯቸው ሠራተኞች መሀከል አያሌ የታዳጊ አገሮች ዜጎች ይገኛሉ ። ለምሳሌ በኤሌክትሮኒክስ ምርትና በኤሌክትሮቴክኒክ ሥራ ላይ የተሠማራው የደች ድንበር ዘለል ሞኖፖል በ70 አገሮች ውስጥ ባሉት ቅርንጫፎች 390,000 ሠራተኞችን በመቅጠር ያሰራል። ከነዚህ ሠራተኞች መሀከል 38,000 የሚሆኑት የታዳጊ አገር ሠራተኞች ናቸው ። ድንበር ዘለል ሞኖፖሎች በዚህ መልክ የታዳጊ አገሮችን ሠራተኛ ጉልበትና የተፈጥሮ ሀብት ይመዘብራሉ ። የአብዛኛዎቹ ድንበር ዘለል ሞኖፖሎች የተረፈ እሴት መጣኔ (Rate of Surplus Value) ከ2–3 እጅ የሚበልጥ ነው ።[29]

ከ1969–1982 ድንበር ዘለል ሞኖፖሎች በታዳጊ አገሮች በተሰማሩባቸው ሀርፎች በ470% ዕድገት አሳይተዋል ። በዚህ ተግባር ላይ የተሰማሩ አንዳንዶቹ ያገኙትን የነፍስ ወከፍ ድርሻ ከሚከተለው ሠንጠረዥ መመልከት ይቻላል ።[30]

በ1970ዎቹ መጀመሪያ ላይ የዩናይትድ ስቴትስ የንግድ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ያወጣው መግለጫ እንደሚጠቁመው የአገሪቱ (የዩናይትድ ስቴትስ) ድንበር ዘለል ሞኖፖሎች ከ1970–1979 በነበሩት ዓመ

የሞኖፖል ስም	ሽያጩ የተካሄደበት ዘመንና ያገኘው ትርፍ	
	1969	1982
ኤክሶን	14.9 ቢሊዮን ዶላር	88.5 ቢሊዮን ዶላር
ሮያል ሼል	9.7 ቢሊዮን ዶላር	80.5 ቢሊዮን ዶላር
ሞቢል	6.6 ቢሊዮን ዶላር	54.6 ቢሊዮን ዶላር
ብሪትሽ ፔትሮሊየም	3.4 ቢሊዮን ዶላር	49.1 ቢሊዮን ዶላር

ታት መካከል በእስያ ፣ በላቲን አሜሪካና በአፍሪካ 12.6 ቢሊዮን ዶላር በሥራ ላይ አውለው ባካሄዱት የብዝበዛ ስልት 48.8 ቢሊዮን ዶላር የተጣራ ትርፍ አግኝተዋል ።[31] ይህም በሥራ ላይ ካዋሉት ገንዘብ ጋር ሲመጣጠን በ4 እጥፍ የሚበልጥ ነው ።

ድንበር ዘለሎች እንዱስትሪዎቻቸውን በታዳጊ አገሮች አስማርተው ፣ በዚያው አምርተውና ሸጠው ብቻ ከፍተኛ ትርፍ የሚያጋብሱ አይደሉም ። የታዳጊ አገሮችን የተፈጥሮ ሀብት በመሚጠጥ ወደ ሀገራቸው ይወስዳሉ ። ብርቅና በአጭር ጊዜ ውስጥ የማይተኩ ማዕድናትን በመሚጠጥ ረገድ ያደረሱት ዘረፋ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ነው ። ለምሳሌ የዩናይትድ ስቴትስና የእንግሊዝ ድንበር ዘለል ሞኖፖሎች ለ33 ዓመታት በዛምቢያ ውስጥ የመዳብ ማዕድን በማውጣት ሥራ ላይ ተሰማርተው በነበሩበት ወቅት 89 ሚሊዮን ቶን ያልተነጠረ መዳብ ከአገሪቷ አግዘዋል ።[32]

ለ/ ብድር በመስጠት

ብድር በመስጠት የሚያደርጉት ብዝበዛና ተጽዕኖም እጅግ የከፋ ነው ። ከ1970–1980ዎቹ መጀመሪያ በነበሩት ዓመታት መካከል በእስያ ፣ በአፍሪካና በላቲን አሜሪካ ሕዝቦች ላይ የኢኮኖሚ ቀውስ ደርሷል። ይህ የኢኮኖሚ ቀውስ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ በካፒታሊስት አገሮች ላይ በተደጋጋሚ የደረሰው ቀውስ ተቀጥላ ነበር ። በጦርነቱ የተጐዱ የኢምፔሪያሊስት መንግሥታት ለማገገም እንዲችሉ ታዳጊ አገሮችን ለመበዝበዝ የሚያስችል አዲስ ስልት ዘረጉ ። ይህም ሁኔታ የታዳጊ አገሮች አጠቃላይ ብሔራዊ ምርት (GNP) እንዲቀንስ አደረገ ። በዚህ ቀውስ የተነሳ ታዳጊ አገሮች ያፈበረኳቸው ምርቶች ዋጋ እያሽቆለቆለ ፣ በአኳያውም ያለባቸው ዕዳና ወለድ እያሻቀበ በመምጣቱ የነዚህ አገሮች ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ አሳሳቢ ደረጃ ላይ ሊደርስ ችሏል ። ጓድ መንግሥቱ ኃይለማርያም ይኸንኑ የዕዳ ጫና አስመልክተው በ8ኛው የገለልተኛ ሀገሮች ስብሰባ ላይ እንደገለፁት "ሞኖፖሎች በትርፍ መልክ ወደ አገራቸው የሚያጋብሱት ከፍተኛ ካፒታል በረሃብና በድህነት የሚሰቃዩትን ሕዝቦች ሳይቀር ለአስከፊ ምዝበራ ዳርጓቸዋል ።

"የኤኮኖሚው ችግር ተባብሶ በነበረበት ከ1975–1985 ባለው ጊዜ ውስጥ ብቻ ምዕራባውያን አበዳሪዎች 900 ቢሊዮን ዶላር በብድርና ወለድ ክፍያ መልክ ከታዳጊው ዓለም ሰብስበዋል ።

"በሌላ በኩል ባለፉት አምስት ዓመታት ውስጥ የታዳጊው ዓለም የብድር ወለድ ክፍያ ወደ 235 ቢሊዮን ዶላር አድጓል ።"[33]

በ1986 በታዳጊ አገሮች ላይ የነበረው ብድር ከነወለዱ ወደ አንድ ትሪሊዮን[34] ይደርሷል ። ለምሳሌ ዘጠኝ ታዳጊ አገሮች ያለባቸውን የውጭ ዕዳ ከነዚህ ቀጥሎ ባለው ሠንጠረዥ አማካይነት እንመልከት ።[35]

በ1981 እና በ1983 የታዳጊ አገሮች ያገር ውስጥ ምርት በ0.5 ዕድገት ሲያሳይ የውጭ ዕዳ ከ706 ቢሊዮን ወደ 843 ቢሊዮን ዶላር ከፍ በማለት በ20% ዕድገት አሳይቷል ፤ በእነዚሁ ዓመታት ውስጥ የላቲን አሜሪካ አገሮች አጠቃላይ ያገር ውስጥ ምርት በዕዳ ጫና የተነሣ በ2·8% አሽቆልቁሏል ።[36] ባሁኑ ጊዜ የላቲን አሜሪካ አገሮች በየመቱ የሚከፍሉት ወለድ 40,000 ሚሊዮን ዶላር ሲደርስ ፤ ድንበር ዘለሎች በአህጉሩ ሥራ ላይ ካዋሉት ሙአለንዋይ በየመቱ የሚያገኙት የተጣራ ትርፍ 55,000 ሚሊዮን ዶላር ደርሷል። የእነዚህአገሮች ዕዳ ... በሚቀጥሉት 10 ዓመታት ውስጥ ወለዱ ወደ 400,000 ሚሊዮን ዶላር ይደርሳል[37] የሚል ግምት አለ። ታዳጊ አገሮች በአሁኑ ወቅት ዕዳውን ቀርቶ ወለዱን እንኳን መክፈል አልቻሉም። ለምሳሌ በ1975 ታዳጊ አገሮች ዋናውን ሳይጨምር የተጣራ የባንክ ወለድ የከፈሉት 9.5 ቢሊዮን ዶላር ሲሆን ፤ በ1981 ወደ 46.5 ቢሊዮን ከፍ ብሏል ። የዓለም ባንክ በመባል የሚታወቀው (International Bank for Reconstruction and Development) ኤክስፐርቶች እንዳመለከቱት ታዳጊ አገሮች ከሚሰጣቸው የውጭ "ዕርዳታ" ውስጥ 85 በመቶውንና ከውጭ ንግድ ከሚያገኙት ገቢ 25 በመቶውን ለዕዳ እንደሚከፍሉ ገልጸዋል ።[38]

በዚህ ዕዳቸው መናር ምክንያት ታዳጊ አገሮች የወጠኑአቸውን የልማት ትልሞች ለማከናወን ተስኗቸዋል ። የልማት ትልሞችን ለማከናወን አለመቻል በአበዳሪዎቹ መንግሥታት የተጽዕኖ ክልል ሥር እንዲወድቁ ቅድመ ሁኔታን አመቻችቷል ።

ሐ/ "ዕርዳታ" በመስጠት

በዓለም ኅብረተሰብ ዘንድ መተሳሰብ ፣ መቀራረብ ፣ በችግር ጊዜ መረዳዳት ፣ በአንዱ አገር ላይ ሰው ሠራሽ ወይንም የተፈጥሮ አደጋ ሲከሰት ፈጥኖ በመድረስ ሕዝቡን ከችግር ማዳንና ሕይወቱን ማትረፍ እጅግ አስፈላጊ ነው ። በዚህ ዓይነት መረዳዳት ላይ የተመሠረተ ዕርዳታ ለማንም የዓለም ኅብረተሰብ አስፈላጊ ነው ። ታዳጊ አገሮች በሰብአዊነት ፣ በእኩልነትና የአንድን አገር ሉአላዊነት በማይጻረር መንገድ ዕርዳታን ይሻሉ ። ነገር ግን "ዕርዳታ" የፖለቲካ ዓላማ ማስፈጸሚያ ከሆነ አደገኛነቱ ቀላል አይደለም ፤ የዚህ ዓይነት ዕርዳታ ተቀባዩን አገር የሚጎዳ ነው ።

ተበዳሪ	ጠቅላላ ዕዳ (በቢሊዮን ዶላር)	የውጭ ዕዳ በነፍስ ወከፍ (ዶላር)	በአጠቃላይ የአገር ውስጥ ምርት የሚሸፍነው የዕዳ መጠን (በ%)
ብራዚል	100	769	37.2
ሜክሲኮ	94	1,205	60
አርጀንቲና	44	1,486	83
ደቡብ ኮሪያ*	36	923	47
ቬንዙዌላ	34	2,073	53
ቺሊ	21	1,810	95
ግብፅ*	19.2	492	136.6
ፔሩ	12.7	675	81
ኡራጓይ	4.6	1,586	90

በ1982 የነበረባቸውን ዕዳ ያመለክታል ።

ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ለታዳጊ አገሮች የሚደረገው "ዕርዳታ" ከእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ፖሊሲ ጋር የተያያዘ ፤ ማለትም ቀደም ብለው ቅኝ ገዢ የነበሩ መንግሥታት የቀድሞ ቅኝ ግዛቶቻቸውን እንደጥንቱ ለመዝረፍ አለመቻላቸውን ከተገነዘቡ በኋላ የቀየሱት ፖለቲካዊ መሣሪያ ነው ። ዓላማቸውም ከታዳጊ አገሮች የገገር መደብ አባላት ጋራ የቅርብ ግንኙነት በመፍጠር ጥሬ ሀብታቸውን መዝረፍ ፤ የሸቀጥ ማራገፊያ ሥፍራ ማድረግና ለድንበር ዘለል ሞኖፖሎቻቸው ስምሪት አስተማማኝ ቀጣናን መፍጠር ነው ።

ታዳጊ አገሮች በራሳቸው እንዳይተማመኑና የፋይናንስ ጥገኛ እንዲሆኑ ከሚያደርጓቸው ተጽዕኖዎች መካከል አንዱ "ዕርዳታ" ነው ። ካፒታሊስት አገሮች በውጭ "ዕርዳታ" እየታገዙ ታዳጊ አገሮችን በራሳቸው የብዝበዛ መረብ ሥር ማስገቢያና ተጽዕኖ ማሳደሪያ መሣሪያም አድርገው ይጠቀሙበታል ። ይህ ፖለቲካዊ ተጽዕኖ ያለበት የውጭ "ዕርዳታ" ለጪዎች አገሮች ምን ጥቅም እንዳለው በእነዚህ አገሮች መሪዎች ጭምር በብዙ አጋጣሚዎች ተገልጿል ።

1. *ዕርዳታ*

ሀ. ለዩናይትድ ስቴትስ ዕቃዎችና አገልግሎት ለጪዎች (Goods and Services) መሸጫ ዓይነተኛ የገበያ ሥፍራን የሚያስገኝ ፤

ለ. ለዩናይትድ ስቴትስ ሞኖፖሎች አውራር የሚያመች አዲስ የባሕር ማዶ ገበያዎች እንዲፈጠሩ ግፊት የሚያደርግ፤

ሐ. ለዩናይትድ ስቴትስ ድርጅቶች የሚበጁ የ"ዕርዳታ" ተቀባዩን አገር ብሔራዊ ኢኮኖሚ ወደ ካፒታሊስት ሥርዓት እንዲያመራ የሚያደርግ ፤ ወይንም መንገድ የሚከፍት ነው ።[39] *(ዮጂን ብላክ—አሜሪካዊው የቀድሞ ዓለም ባንክ ፕሬዚዳንት)*

2. ዕርዳታ ዩናይትድ ስቴትስ በዓለም ላይ የተጽዕኖ ክልልን የምታስፋፋበት ፤ ወደ ኮሚዩኒዝም ሥርዓት የሚጓዙ አገሮችን የምትቆጣጠርበት ወይንም የምትገድብበት መሣሪያ ነው ።[40] *(ጆን ኤፍ ኬኔዲ)*

3. ማስታወስ ያለብን የውጭ "ዕርዳታ" ዓላማ ሌሎች አገሮችን የምንረዳበት ሳይሆን በትክክል ራሳችንን የምንረዳበት ነው ።[41] *(ሪቻርድ ኒክሰን)*

4. በምንሰጠው ዕርዳታ ተቀባዩ አገር የራሳችንን ሸቀጦችንና አገልግሎት ለጪዎችን ስለሚገዛበት ኢኮኖሚያችንን ያዳብራል ። ለምሳሌ ለዓለም ባንክና ለላቲን አሜሪካ ፤ ለእስያና ለአፍሪካ አህጉራት ልማት ለተቋቋሙ ባንኮች ከምንከፍለው ከያንዳንዱ ዶላር ተመልሶ በዩናይትድ ስቴትስ ኢኮኖሚ ውስጥ የሚውለው ሁለት ዶላር ነው ።[42] *(ሳይረስ ቬንስ—የዩናይትድ ስቴትስ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ነበሩ ።)*

5. የውጭ "ዕርዳታ" ፕሮግራምን በሚመለከት ያለን ትልቁ ስህተት ገንዘብን ወደ ውጭ እንደምንልክ ተደርጐ መወሰዱ ነው ። ነገር ግን አንልክም ። የውጭ "ዕርዳታ" የዩናይትድ ስቴትስ ዕቃዎችን፣ ኤክስፐርቶችን ፣ አገልግሎት መስ

ጫዎችንና የምግብ ዕርዳታን ያጠቃልላል ። ሁሉም እኛ እንደገና ለምናጠናቸውና ለምናጸድቃቸው ለተወሰኑ ፕሮጀክቶች የሚውሉ ናቸው ። ... ከምንሰጠው ዕርዳታ 93% የሚውለው በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ለሚደረጉ ክፍያዎች ነው ።[43] (የዩናይትድ ስቴትስ ባለሥልጣን ዊሊያም ጉድ)

6. ሁለት ሦስተኛ የሚሆነው "ዕርዳታችን" ከእንግሊዝ ለሚገዙ ዕቃዎችና መገልገያዎች ተመልሶ ይውላል ። ... ንግድ ዕርዳታን ይከተላል ። በመጀመሪያ ባሕር ማዶ ለሚገኙ አገሮች ፋብሪካዎችን እናቋቁማለን ፤ ይህንን ... (በ"ዕርዳታ" ላይ) እንጨምራለን ...። ምክንያቱም ትክክልና በረጂሙ ዕቅዳችን ውስጥ ስላለ ነው ።[44] (ኤርል ግሬንስቲድ—እንግሊዛዊው የባሕር ማዶ ሚኒስትር የነበሩ)

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ፖለቲካዊ ዓላማ ያለው "ዕርዳታ" ምን ዓይነት ሥራ እንደሚሠራበት በግልጽ የተነገረ ነው ። ስለዚህ ዓይነት ተግባር የሚውለው "ዕርዳታ" በሚገባ የሚጠናና የሚቀነባበር ነው ። ካፒታሊስት መንግሥታት "ዕርዳታን" ለፖለቲካዊ ዓላማ ለማዋል ሲፈልጉ በመጀመሪያ ዕርዳታውን የሚቀበል አገር ውስጣዊ የፖለቲካ አቋም ፤ የውጭ ፖሊሲ አቅጣጫ ፤ ለውጭ የግል ድርጅቶች (ሞኖፖሎች) ሙአለንዋይ የሚያደርገው እንክብካቤ ፤ እንዲሁም ሌሎችን የ"ዕርዳታ" ሰጪውን አገር ፖለቲካዊ ሥርዓት የማይነኩ ሆነው ከተገኙ በኋላ ይሰጣሉ ። እነዚህ ተመቻችተው በ"ዕርዳታ" መልክ ከገቡ በኋላ ታዳጊ አገሮች በራሳቸው ብሔራዊ ዕቅድ አወጣጥ ፤ አወሳሰንና አመራር ላይ የበላይነት እንዳይኖራቸው በማድረግ የራሳቸውን ጥቅም ያዳብራሉ ። በተልዕኳቸው መሠረት የራሳቸው ሸቀጥ ማራገፊያ ፤ ተራማጅ ሥርዓት እንደይመሠረት መገደቢያና በየጊዜው የሚፈጠርባቸውን ቀውስ መጠገኛ አድርገው ይጠቀሙበታል ።

4.2. በሳይንስና ቴክኖሎጂ ግኝቶች በመጠቀም

የሳይንስና ቴክኖሎጂ ግኝቶች ታዳጊ አገሮች ከኋላቀርነት እንዲላቀቁና ፈጣን ዕድገት እንዲያደርጉ ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ ። ይሁንና ኢምፔሪያሊስት መንግሥታት የሳይንስና ቴክኖሎጂ ግኝቶችን ለታዳጊ አገሮች ዕድገት ሳይሆን ታዳጊ አገሮችን ጥገኛቸው ማድረጊያና ዕድገታቸውን መግቻ መሣሪያ አድርገው ይጠቀሙባቸዋል ። ከፖለቲካ ጋርም አቆራኝተው ለልዩ ልዩ ተልዕኳቸው ማስፈጸሚያ ያውሏቸዋል ።

በኢንዱስትሪ የዳበሩ አገሮች በምርምርና ልማት (Research and Development) ሥራ ላይ የተሰማሩ ዜጎቻቸው ከዘመናዊ ቴክኖሎጂ አመራር ጋር የተዋወቁ ናቸው ። በካፒታሊስቱ ዓለም ለምርምርና ልማት ሥራ ከሚወጣው ወጪ 96% የሚሸፍኑት ታዳጊ አገሮች ሲሆኑ የታዳጊ አገሮች ደግሞ እስከ 4% ዝቅ ይላል ። በአሁኑ ጊዜ በኢንዱስትሪ በዳበሩ አገሮችና በታዳጊ አገሮች ያሉ የምርምርና ልማት ሠራተኞች ቁጥር ባሉበት አህጉር ለሚኖር ሕዝብ ምን ያህል እንደሚደርሱ ቀጥሎ ያለውን አኃዝ እንመልከት ።

— በእስያ ያሉት ሳይንቲስቶችና መሐንዲሶች ለ10,000 ሰዎች 22 ፤
— በአፍሪካ ያሉ ሳይንቲስቶችና መሐንዲሶች ለ10,000 ሰዎች 6 ፤
— በላቲን አሜሪካ ያሉ ሳይንቲስቶችና መሐንዲሶች ለ10,000 ሰዎች 69 ፤
— በኢንዱስትሪ የዳበሩ አገሮች (ምዕራብ) ያሉ ሳይንቲስቶችና መሐንዲሶች ለ10,000 ሰዎች 112 አሏቸው ።[45]

ከተጠቀሰው መረጃ መረዳት እንደሚቻለው ታዳጊ አገሮች በራሳቸው ሳይንቲስቶችና መሐንዲሶች የሥራ ውጤቶች ከመጠቀም ይልቅ በምዕራቡ ቴክኖሎጂ በሰፊው ለመገልገል ይገደዳሉ ።

በፓቴንት ፤ በላይሰንስ ፤ በንግድ ምልክት ፤ በመሣሪያና በሥራ አመራር አገልግሎት ድንበር ዘለል ሞኖፖሎች ታዳጊ አገሮችን ይበዘብዛሉ ። ለምሳሌ ፋየርስ ቶን የተባለው የዩናይትድ ስቴትስ ኩባንያ ለአንድ የህንድ ኩባንያ ላደረገው የቴክኒክ አገልግሎት ለመጀመሪያ ጊዜ 300,000 ዶላር ከተቀበለ በኋላ ለአሥር ዓመታት በያመቱ 285,000 ዶላር ተቀብሏል ።[46]

ድንበር ዘለል ሞኖፖሎች ታዳጊ አገሮችን ለፓቴንት ፤ ለንግድ ፈቃድ ፤ ለንግድ ምልክት ፤ ለዶክዩመንትና ለአገልግሎት በያመቱ ከ3-5 ቢሊዮን ዶላር ያስከፍሏቸዋል ። ባሁኑ ወቅት በዓለም ውስጥ 3.5 ሚሊዮን ፓቴንቶች ሲገኙ ፤ ከነዚህ መካከል 6% ወይንም 210,000 ፓቴንቶች ያህሉ በታዳጊ አገሮች ውስጥ ናቸው ። በነዚህ አገሮች ውስጥ ከተሰማሩት መካከል 1/6ኛው ማለትም 35,000 ፓቴንቶች የታዳጊ አገሮች ሲሆኑ ቀሪዎቹ ከ175,000 በላይ የሚሆኑት በውጭ ድርጅቶች ቁጥጥር ሥር ናቸው ። ከጥቂት ዓመታት በፊት በአምስት አገሮች (በህንድ ፤ በቱርክ ፤ በግብፅ ፤ በፓኪስታንና በትሪንዳድ) ላይ የተካሄደው ጥናት እንደሚጠቁመዉ በነዚህ አገሮች ውስጥ ያሉ ፓቴንቶች 89% የውጭ ይዞታ ናቸው ።[47] በአጠቃላይ በ1975 ታዳጊ አገሮች ለፓቴንቶች ፤ ለላይሰንስ ፤ ለንግድ ምልክቶችና ለሥራ አመራር አገልግሎቶች በየዓመቱ 1,100 ሚሊዮን ዶላር ለሞኖፖሎች ይከፍሉ ነበር ። በ1985 ይህ ክፍያ በዓመት 6,000 ሚሊዮን ዶላር ጨምሯል ።[48]

ባሁኑ ወቅት የቴክኖሎጂ ገበያን በቁጥጥራቸው ሥር ያደረጉ የዩናይትድ ስቴትስ ፤ የጀርመን ፌዴራል ሪፐብሊክ ፤ የስዊስ ፤ የእንግሊዝ ፤ የፈረንሳይና የጃፓን ኩባንያዎች ናቸው ። በ1970ዎቹ አጋማሽ ላይ በታዳጊ አገሮች አገልግሎት ላይ ከነበሩት ፓቴንቶች መካከል 4/5ኛዎቹ የተጠቀሱት አገሮች ይዞታዎች ነበሩ ።[49]

ድንበር ዘለል ሞኖፖሎች ታዳጊ አገሮች በእርሻና በጥሬ ዕቃ አምራችነት እንዲቆዩ ፤ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ውጤቶችን እንዳይጠቀሙ በማድረግ ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ ። ለምሳሌ በ1960ዎቹ ማብቂያና በ1970ዎቹ መጀመሪያ ላይ ላይቤሪያ በአፍሪካ ከሚገኙ አገሮች መካከል በጐማ ሀብት የታወቀች አገር ስትሆን ፤ እስከቅርብ ጊዜ ድረስ የራሷ ጐማ ፋብሪካ እንዳይኖራት ተጽዕኖ አድርገውባታል ። በዚሁ ወቅት በታንዛኒያ አልማዝ የሚያመርቱ የውጭ ኩባንያዎች በአገሪቱ ውስጥ ዝቅተኛውን የአልማዝ ማምረቻ መሣሪያ እንኳን ለማቋቋም አልፈለጉም ። ቤኒን ለሲሚንቶ ምርት የሚሆን በቂ የተፈጥሮ ሀብት እያላት የሲሚንቶ ፋብሪካዎች ኮንስትረክሽን ሥራ የማቋቋሙን ተግባር ለ15 ዓመታት እንዲጓተት አድርገዋል ።[50]

በኢንዱስትሪ የዳበሩ መንግሥታት ቴክኖሎጂን ወደ ታዳጊ አገሮች ልከው ከሚያካሂዱት ብዝበዛ በተጨማሪ በማሠልጠንና በሥራ አመራር ስም ለሞኖፖሎቻቸው ደህንነትና መስፋፋት ቅድመ ሁኔታን የሚያመቻቹ ድርጅቶችንም እስከ መመሥረት ደርሰዋል ። በ1964 የተመሠረተው ኢንተ

ርናሽናል ኤግዚኩትቭ ሰርቪስ ኮርፕስ (International Executive Service Corps – IESC) ይህንን ጉዳይ በሚመለከት ከሚጠቀሱት መካከል አንዱ ነው ። ይህ ድርጅት ለታዳጊ አገሮች የሥራ አመራርን ባሕርይ "ለማስተዋወቅ" የተመሠረተ ሲሆን ባሁኑ ወቅት በ29 ታዳጊ አገሮች ውስጥ ቋሚ ቢሮዎች አሉት ። ቁጥራቸው 8,500 የሚሆኑ የዩናይትድ ስቴትስ ዜጎች በዚህ ድርጅት ተቀጥረው በታዳጊ አገሮች ለሚገኙ የግል ድርጅቶች "አገልግሎቶች" ይሰጣሉ ። ከዚህም በላይ ከዩናይትድ ስቴትስ ሞኖፖሎችና ታዋቂ ነጋዴዎች ጋራ የቅርብ ግንኙነት እንዲፈጥሩ ያበረታቷቸዋል ። በዚህ መሠረት ድርጅቱ ከ1965-1979 ባለው ጊዜ ውስጥ በ60 አገሮች ውስጥ 5,500 ፕሮጀክቶችን ሠርቷል ።[51] ከዚህ የአሠራር ስልት መረዳት እንደሚቻለው በጉልህ ከሚታየው ቁሳዊ ልክት ሌላ የምዕራባውያንን የሞኖፖል አሠራርና ግንኙነቶችን የሚደግፉግለሰቦችን ወይንም ማኅበራዊ ቡድንን በመፍጠር "የአገልግሎት" ልክት (Invsible Export) ማከናወን የድንበር ዘለል ሞኖፖሎችና የኢምፔሪያሊስት መንግሥታት ተቀዳሚ ተግባር ነው ።

4.3. ምሁራንን በማስኮብለል

የሠለጠነ የሰው ኃይል ለአንድ አገር ሁለገብ ግንባታ ግብ መምታት ከፍተኛውን ሥፍራ ይይዛል ። ታዳጊ አገሮችም የፖለቲካ ነፃነታቸውን ከተጐናጸፉ በኋላ ዐቅም በፈቀደ መጠን ዜጎቻቸውን ለኢንዱስትሪ አመራርና አሠራር ማሠልጠናቸው አልቀረም ። ነገር ግን ከነዚህ መካከል ቁጥራቸው እጅግ ብዙ የሆኑ ምሁራን በየጊዜው ወደ ዳበሩ ካፒታሊስት አገሮች የሚኮበልሉ በመሆናቸው የሠለጠነ የሰው ኃይል እጥረት ገጥሟቸዋል ። የታዳጊ አገሮችን ምሁራን በማስኮብለል ረገድ ድንበር ዘለል ኩባንያዎች የሚፈጥሩት ግፊት ከፍተኛ ሲሆን በዚህ ጥረታቸው የየመንግሥታቸው ድጋፍ አይለያቸውም ። ስለዚህ የጋራ ጥረት ሲ.ፒ. አግራሲንጋም የሚባሉ ጸሐፊ ሲያስረዱ ፣

ምሁራንን የማስኮብለል ተግባር የሚካሄደው በሁለት ዓይነት መንገድ ነው ፤ አንደኛው ካፒታሊስት መንግሥታት የታዳጊ አገሮች ምሁራንን እንደልብ ለማስገባት የሚያስችል ላላ ያለ የኢምግሬሽን ፖሊሲ ማውጣት ሲሆን ፣ ሁለተኛው የምዕራባውያን ሞኖፖሎች በረቀቀ ዘዴ እና በሚማርክ ክፍያ እየተጠቀሙ እንዲኮበልሉ ግፊት ማድረግ ነው[52] ብለዋል ።

የታዳጊ አገሮች ምሁራንን በማስኮብለል ረገድ ውስብስብ ተግባሮችን ከሚያከናውኑት ድንበር ዘለል ሞኖፖሎች መካከል ዌስትንግ ሃውስን ፣ ቦይንግን ፣ አላይድ ኬሚካልንና ሌሎችንም በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል ።[53] እነዚህ ድንበር ዘለሎች ለራሳቸውና ለሌሎችም መሰል ተቋሞች የፊዚክስ ፣ የምህንድስናና ፣ የተፈጥሮ ሳይንስ ፣ የህክምናና የምርምር ሳይንቲስቶችን እያስኮበለሉ ይገለገሉባቸዋል ። ምሁራንን የማስኮብለሉ ተግባር እንዲሰምርላቸው ከዩናይትድ ስቴትስ ዲፕሎማቲክና ፕሮፓጋንዳ ተቋሞች ፣ ከቴክኒክና ዕርዳታ ተቋሞች ፣ ነፃ ትምህርት ከሚሰጡ ድርጅቶች ጋር በመተባበር በቀጥታና በተዘዋዋሪ በሚያደርጉላቸው ድጋፍ ይሠራሉ ። ከነዚህ ድንበር ዘለል ሞኖፖሎች ጐንም በመሰለፍ መንግሥታዊ ተቋሞችና የግል ድርጅቶች ምሁራንን በማስኮብለሉ ተግባር የማያቋርጥ ድጋፍ ይሰጣሉ ። ኢምፔሪያሊስት መንግሥታት ለሚፈልጉት የሥራ ዘርፍ ሠራተኞችን ለማሠልጠን የሚፈጀውን ገንዘብና የሥልጠና ጊዜ ፣ ከዚያም ከሙያው ጋራ ለመተዋወቅና ልምድ ለማካበት የሚወስደውን ጊዜ ለማሳጠር ሲሉ ሠልጥነው በሥራ ላይ የቆዩ በሳል ምሁራንን የሚማርክ ደመወዝ በመክፈል ያስኮበልላሉ ። በዚህ መንገድ ሳይንቲስቶችን ፣ መሃንዲሶችንና ቴክኒሺያኖችን ከታዳጊ አገሮች ወደ ካፒታሊስት አገሮች በማስኮብለል የታዳጊ አገሮችን የሳይንስና የቴክኖሎጂ ዐቅም ያዳክማሉ ። የዩናይትድ ስቴትስ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበሩት ዲን ረስክ መንግሥታቸው ለታዳጊ አገሮች ኮብላይ ምሁራንና የቴክኒክ ሠራተኞች የሚያደርገውን ማስኮብለል ጥቅም አስመልክተው ሲናገሩ "አገራችን ከፍተኛ ችሎታና የበሰለ ሙያ ያላቸውን የውጭ ኮብላዮችን ተቀብላ ለማስተናገድ በመቻልዋ የታደለች ናት ። የውጭ ኮብላዮች ምሁራንን በሚገባ ተንከባክበን መያዝ መቻል ለተፈጥሮ ሀብታችን ተገቢውን እንክብካቤ እንደማድረግ ይቆጣራል"[54] ሲሉ የታዳጊ አገሮች ምሁራን ወደ ካፒታሊስት አገሮች መኰብለል ምን ያህል ጠቀሜታ እንዳለው ገልጸዋል ።

ከ1962 - 1973 በነበረው ጊዜ ውስጥ ከታዳጊ አገሮች ወደ ዩናይትድ ስቴትስ ፣ ካናዳና እንግሊዝ የኮበለሉትን ባለሙያዎችና የቴክኒክ ሠራተኞችን ብዛት ከሚከተለው ሠንጠረዥ ስንመለከት[55] ዲን ረስክ ያሉትን አባባል የሚያረጋግጥ ሆኖ እናገኘዋለን ።

እንክታድ በዘገበው መሠረት እነዚህ ምሁራን ከ1961 – 1972 በተጠቀሱት አገሮች ውስጥ በሥራ ላይ በተሰማሩበት ወቅት መንግሥታቱ 46 ቢሊዮን ዶላር ማለትም በያመቱ 3.8 ቢሊዮን ዶላር አድነዋል ። ዩናይትድ ስቴትስ ለሰው ኃይል ሥልጠና ታወጣው ከነበረው ገንዘብ መካከል ከላይ በተጠቀሱት ዓመታት ውስጥ ኮብልለው ወዳገሪቷ ከገቡት መካከል በያመቱ ከፊዚክስ ባለሙያዎች 642,000 ዶላር ፣ ከሌሎች ሳይንቲስቶች 237,000

ኩብለላው የተካሄደበት ዘመን	ዩናይትድ ስቴትስ	ካናዳ	እንግሊዝ	ወደ ሦስቱ አገሮች የኮበለሉት ብዛት
1962	9,024	1,381	—	10,405
1963	11,029	1,525	4,600	17,154
1964	11,418	1,873	—	13,291
1965	11,001	3,707	3,230	17,938
1966	13,986	5,548	—	19,534
1967	23,361	7,897	2,900	34,158
1968	28,511	6,930	2,420	37,861
1969	27,536	7,585	1,720	36,841
1970	33,596	6,118	1,000	40,914
1971	38,647	5,184	1,270	45,101
1972	39,106	5,360	377	44,843
1973	31,939	—	—	31,939
ጠቅላላ	279,354	53,108	17,517	349,979

ዶላር ፣ እንዲሁም ከመሐንዲሶች 272,000 ዶላር አድናለች ።[56] በሌላ በኩል ደግሞ ወደ ዩናይትድስቴትስ ከገቡ የታዳጊ አገር ምሁራን መካከል 57% የሚሆኑት የዶክተርና የማስተርስ ዲግሪ ያላቸው ሲሆኑ በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ በያመቱ የኖቤል ሽልማት ከሚሸለሙት መካከል 33% የሚሆኑት የውጭ ምሁራን ናቸው ።[57]

ከ1961 እስከ 1980ዎቹ ዓመታት ቁጥራቸው 500,000[58] የሚሆኑ ምሁራን ከእስያ፣ ከአፍሪካና ከላቲን አሜሪካ ወደ ዩናይትድ ስቴትስ ፣ እንግሊዝና ካናዳ ኮብልለዋል።[59] በአንክታድ ጥናት መሠረት ባሁኑ ጊዜ ቁጥራቸው ከ100,000 በላይ መሐንዲሶችና የሳይንሳዊ ምርምር ባለሙያዎች ፣ 123,000 ቴክኒሺያኖችና ሌሎችም ኤክስፐርቶች ከታዳጊ አገሮች ወደ ኢምፔሪያሊስት አገሮች ኮብልለዋል ።[60]

ከፍተኛ የምሁራን ኩብለላ የሚታየው በእስያ አህጉር ነው ። በተለይም ህንድ ቁጥራቸው ከፍተኛ የሆነ ምሁራን ይኮበልሉባታል ። ከዚህች አገር ብቻ ከ4,000 — 5,000 የሚሆኑ ከፍተኛ ሙያ ያላቸው ምሁራን በያመቱ ወደ ዩናይትድ ስቴትስ ይኮበልላሉ ። እነዚህም የምርምር ሠራተኞች ፣ መሃንዲሶችና የህክምና ዶክተሮች ናቸው ። በቅርቡ የህንድ መንግሥት መረጃ አገልግሎት እንደጠቆመው ዩናይትድ ስቴትስና አንዳንድ ካፒታሊስት መንግሥታት በሚያሳድሩት ግፊት የተነሣ ከዐሥር አንድ የህክምና ባለሙያዎች በያመቱ እንደሚኮበልሉባት ገልጿል ።[61] ምሁራንን በማስኮብለል በሀገራቸው ላይ የሚፈፀመውን ደባ የተገነዘቡ የሕንድ ምሁር በታዳጊ አገሮች ምሁራን ላይ የሚፈጸመው “የአእምሮ ብዝበዛ ወይንም ምሁራንን የማስኮብለል ድርጊት ረሀብና የሕዝብ ቁጥር መብዛት በአንድ ሀገር ላይ ከሚያደርሱት ችግር ጋር የሚመጣጠን ነው”[62] በማለት ተናግረዋል ።

ፊሊፒንስ ከህንድ ቀጥላ ምሁራን በብዛት የሚኮበልሉባት አገር ናት ። ከነዚህ ኮብላዮች መካከል አብዛኞዎቹ የህክምና ሠራተኞች ናቸው ። ከታይላንድም እንደዚሁ በርካታ የህክምና ዶክተሮች ወደ ዩናይትድ ስቴትስ ይኮበልላሉ ። በ1970ዎቹ መጀመሪያ ላይ ከታይላንድ ኮብልለው በዩናይትድ ስቴትስ የህክምና አገልግሎት በመስጠት ላይ የነበሩ የህክምና ባለሙያዎች ቁጥር በታይላንድ ገጠር ተሰማርተው ይሠሩ የነበሩትን የህክምና ዶክተሮች ይበልጥ ነበር ።[63] ከነዚህ አገሮች በተጨማሪ ፓኪስታን ፣ ደቡብ ኮሪያ ፣ ቱርክ ፣ ብራዚል፣ ቺሊ ፣ ግብፅና ናይጀሪያ ልዩ ሙያ ያላቸው ምሁራን ከሚኮበልሉባቸው አገሮች መካከል ዋንኞቹ ናቸው ።

ምሁራንን በመደለል ከታዳጊ አገሮች በማስኮብለል የታወቁት ዩናይትድ ስቴትስ ፣ እንግሊዝና ካናዳ ሲሆኑ ከ1961 እስከ 1967 ድረስ 81,000 የፊዚክስ ባለሙያዎችን ጨምሮ 300,000 ስፔሻሊስቶችንና 100,000 የምርምር ሠራተኞችን አስኩብልለዋል ። በዚህም ተግባራቸው ዩናይትድ ስቴትስ 30 ቢሊዮን ፣ ካናዳ 10 ቢሊዮን ፣ እንግሊዝ 3.5 ቢሊዮን ዶላር ለሰው ኃይል ሥልጠና ይወጣ የነበረውን ወጪ አድነዋል ። ይህም ሲጠቃለል ወደ 50 ቢሊዮን ዶላር ይጠጋል ።[64] በምሁራኑ መኮብለል ምክንያት በታዳጊ አገሮች ላይ ግን በያመቱ የ5 ቢሊዮን ዶላር ኪሣራ እየደረሰባቸው ነው ።[65] ታዳጊ አገሮች በሚኮበልሉባቸው ባለሙያዎች ምትክ ሌሎችን ለማሠልጠን በያመቱ ከ100 እስከ 150 ሚሊዮን ዶላር ያወጣሉ ።[66] እነኚህ አገሮች ብቁ የሆኑ

የሥራ ዘርፎችን የሚሸፍኑ ዜጎቻቸው በሚታጡበት ወቅት በከፍተኛ ደመወዝ የውጭ ዜጎችን ለመቅጠር ይገደዳሉ ። ባለፉት 15 ዓመታት ውስጥ ታዳጊ አገሮች ባማካይ ቁጥራቸው 425,000 ለሚደርሱ በሀገራቸው ተሰማርተው በመሥራት ላይ ለነበሩ የውጭ ኤክስፐርቶች በያመቱ ከ4 — 5 ቢሊዮን ዶላር ለመክፈል ተገደዋል።[67] አንድ ታዳጊ አገር አንድን መሃንዲስ ለማሠልጠን ከ25,000 እስከ 40,000 ፣ አንድን ቴክኒሺያን ለማሠልጠን ደግሞ ከ12,000 እስከ 15,000 ዶላር ወጪ ያደርጋል ።[68] በዚህ ስሌት መሠረት ዩናይትድ ስቴትስ ከላይ በተጠቀሱት ዓመታት መካከል ከታዳጊ አገሮች ካስኮበለለቻቸው ምሁራን 33.9 ቢሊዮን ዶላር አድናለች።[69]

4.4 ቁሳዊና ሕጋዊ አመቺነትን መርጠው በማሰማራት

በታዳጊ አገሮች የሥራ ኃይል ርካሽ ስለሆነ ፣ የሠራተኛ ማኅበራት ስለሌሉ ወይም ቢኖሩም የሠራተኛውን ጥቅም ለማስከበር ያላቸው አቅምና ልምድ እጅግ ውሱን በመሆኑ ለከፍተኛ ምዝበራ የተመቻቹ ናቸው ። ለምሳሌ በደቡብ ኮሪያ ፣ በታይዋን ወይም በደቡብ አፍሪካ ላሉ ሠራተኞች የሚከፈለው ምንዳ ዩናይትድ ስቴትስ ወይም ጀርመን ፌዴራል ሪፐብሊክ ውስጥ የሚሠሩ ሠራተኞች ከሚያገኙት ምንዳ በጣም ያነሰ ነው ። በተጨማሪም በብዙ ታዳጊ አገሮች ውስጥ የሥራ ማቆም አድማ ማካሄድ በሕግ የተከለከለና የሥራ ሰዓቶችም ረዥም መሆን ለድንበር ዘለል ሞኖፖሎች ዘረፋ ምቹ ሁኔታን ፈጥሮላቸዋል ። እንዲሁም በነዚህ አገሮች የጥሬ ሀብት አጠቃቀምን ፣ የቀረጥ አከፋፈልንና የተፈጥሮ አካባቢ መበከልን አስመልክቶ ባብዛኛው ጠንካራ ሕጎች ገና ባለመደንገጋቸው ድንበር ዘለል ሞኖፖሎች የታዳጊ አገሮችን ኢኮኖሚያዊ ሀብት በመሚጠጥ ላይ ይገኛሉ ። ድንበር ዘለል ሞኖፖሎች አካባቢን በመበከል ረገድ የሚያደርሷቸውን ማኅበራዊ ችግሮች በውል ማጤን እንዲቻል አንዳንድ መረጃዎችን እንመልከት ።

1. ዩኒየን ካርባይድ* ፀረተባይ ኬሚካሎችን የሚያመርቱ ሁለት ፋብሪካዎች ሲኖሩት አንደኛው በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ በምዕራብ ቨርጂኒያ የሚገኝ ሲሆን ሌላው በህንድ አገር በማዲያፕራዴሽ ክፍለ ሀገር ብሆፓል ቀበሌ የተቋቋመ ነው ። በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ያለው ፋብሪካ በኮምፒዩተር የሚጠበቅ ፣ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ያለው ፣ አምልጦ ወደ ውጭ መፍሰስ ሲሞክር ወዲያውኑ የሚያቆም ዘመናዊ መቆጣጠሪያ የተሠራለት ነው ። በብሆፓል ያለው ግን ጋዙ ወይንም ኬሚካሉ ቢያፈተልክ አመልካች መሣሪያ የሌለው ፣ ተገቢ ጥንቃቄ ያልተደረገለትና ለአደጋ የተጋለጠ ነው ። በርካታ ሕዝብ በሚኖርበት ቀበሌ የተቋቋመው ይህ የኬሚካል ፋብሪካ ከጥንቃቄ ጉድለት የተነሣ በ1985 አምልጦ በወጣው የዩኒየን ካርባይድ መርዝ 2,500 ሰዎች ሲሞቱ ከ200,000 በላይ በሚሆኑ የአካባቢው ነዋሪዎች ላይ ከፍተኛ ጉዳት ደርሷል ።[70] በ1986 ታትሞ የወጣው ኢንተርናሽናል አፌርስ መጽሔት እንደዘገበው

* ዩኒየን ካርባይድ ዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ከሚገኙና ኬሚካልን ከሚያመርቱ አምስት ድንበር ዘለል ሞኖፖሎች መካከል አንደኛው ነው ። ይኸው ድንበር ዘለል ሞኖፖል አደገኛ ኬሚካሎችን አምርቶ ለወታደራዊ አገልግሎት የሚያቀርብ ሲሆን ለፔንታጎንም ዋንኛ የሥራ ተቋራጩ ነው ።

ዶላር ፣ እንዲሁም ከመሐንዲሶች 272,000 ዶላር አድናለች ።[56] በሌላ በኩል ደግሞ ወደ ዩናይትድስቴትስ ከገቡ የታዳጊ አገር ምሁራን መካከል 57% የሚሆኑት የዶክተርና የማስተርስ ዲግሪ ያላቸው ሲሆኑ በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ በያመቱ የኖቤል ሽልማት ከሚሸለሙት መካከል 33% የሚሆኑት የውጭ ምሁራን ናቸው ።[57]

ከ1961 እስከ 1980ዎቹ ዓመታት ቁጥራቸው 500,000[58] የሚሆኑ ምሁራን ከእስያ፣ ከአፍሪካና ከላቲን አሜሪካ ወደ ዩናይትድ ስቴትስ ፣ እንግሊዝና ካናዳ ኮብልለዋል።[59] በአንክታድ ጥናት መሠረት ባሁኑ ጊዜ ቁጥራቸው ከ100,000 በላይ መሐንዲሶችና የሳይንሳዊ ምርምር ባለሙያዎች ፣ 123,000 ቴክኒሺያኖችና ሌሎችም ኤክስፐርቶች ከታዳጊ አገሮች ወደ ኢምፔሪያሊስት አገሮች ኮብልለዋል ።[60]

ከፍተኛ የምሁራን ኩብለላ የሚታየው በእስያ አህጉር ነው ። በተለይም ህንድ ቁጥራቸው ከፍተኛ የሆነ ምሁራን ይኮበልሉባታል ። ከዚህች አገር ብቻ ከ4,000–5,000 የሚሆኑ ከፍተኛ ሙያ ያላቸው ምሁራን በያመቱ ወደ ዩናይትድ ስቴትስ ይኮበልላሉ ። እነዚህም የምርምር ሠራተኞች ፣ መሃንዲሶችና የህክምና ዶክተሮች ናቸው ። በቅርቡ የህንድ መንግሥት መረጃ አገልግሎት እንደጠቆመው ዩናይትድ ስቴትስና አንዳንድ ካፒታሊስት መንግሥታት በሚያሳድሩት ግፊት የተነሣ ከዐሥር አንድ የህክምና ባለሙያዎች በያመቱ እንደሚኮበልሉባት ገልጿል ።[61] ምሁራንን በማስኮብለል በሀገራቸው ላይ የሚፈፀመውን ደባ የተገነዘቡ የሕንድ ምሁር በታዳጊ አገሮች ምሁራን ላይ የሚፈጸመው "የአእምሮ ብዝበዛ ወይንም ምሁራንን የማስኮብለል ድርጊት ረሀብና የሕዝብ ቁጥር መብዛት በአንድ ሀገር ላይ ከሚያደርሱት ችግር ጋር የሚመጣጠን ነው"[62] በማለት ተናግረዋል ።

ፊሊፒንስ ከህንድ ቀጥላ ምሁራን በብዛት የሚኮበልሉባት አገር ናት ። ከነዚህ ኮብላዮች መካከል አብዛኞዎቹ የህክምና ሠራተኞች ናቸው ። ከታይላንድም እንደዚሁ በርካታ የህክምና ዶክተሮች ወደ ዩናይትድ ስቴትስ ይኮበልላሉ ። በ1970ዎቹ መጀመሪያ ላይ ከታይላንድ ኮብልለው በዩናይትድ ስቴትስ የህክምና አገልግሎት በመስጠት ላይ የነበሩ የህክምና ባለሙያዎች ቁጥር በታይላንድ ገጠር ተሰማርተው ይሠሩ የነበሩትን የህክምና ዶክተሮች ይበልጥ ነበር ።[63] ከነዚህ አገሮች በተጨማሪ ፓኪስታን ፣ ደቡብ ኮሪያ ፣ ቱርክ ፣ ብራዚል፣ ቺሊ ፣ ግብፅና ናይጀሪያ ልዩ ሙያ ያላቸው ምሁራን ከሚኮበልሉባቸው አገሮች መካከል ዋንኞቹ ናቸው ።

ምሁራንን በመደለል ከታዳጊ አገሮች በማስኮብለል የታወቁት ዩናይትድ ስቴትስ ፣ እንግሊዝና ካናዳ ሲሆኑ ከ1961 እስከ 1967 ድረስ 81,000 የፊዚክስ ባለሙያዎችን ጨምሮ 300,000 ስፔሻሊስቶችንና 100,000 የምርምር ሠራተኞችን አስኩብልለዋል ። በዚህም ተግባራቸው ዩናይትድ ስቴትስ 30 ቢሊዮን ፣ ካናዳ 10 ቢሊዮን ፣ እንግሊዝ 3.5 ቢሊዮን ዶላር ለሰው ኃይል ሥልጠና ይወጣ የነበረውን ወጪ አድነዋል ። ይህም ሲጠቃለል ወደ 50 ቢሊዮን ዶላር ይጠጋል ።[64] በምሁራኑ መኮብለል ምክንያት በታዳጊ አገሮች ላይ ግን በያመቱ የ5 ቢሊዮን ዶላር ኪሣራ እየደረሰባቸው ነው ።[65] ታዳጊ አገሮች በሚኮበልሉባቸው ባለሙያዎች ምትክ ሌሎችን ለማሠልጠን በያመቱ ከ100 እስከ 150 ሚሊዮን ዶላር ያወጣሉ ።[66] እነኝህ አገሮች ብቁ የሆኑ

የሥራ ዘርፎችን የሚሸፍኑ ዜጎቻቸው በሚታጡበት ወቅት በከፍተኛ ደመወዝ የውጭ ዜጎችን ለመቅጠር ይገደዳሉ ። ባለፉት 15 ዓመታት ውስጥ ታዳጊ አገሮች ባማካይ ቁጥራቸው 425,000 ለሚደርሱ በሀገራቸው ተሰማርተው በመሥራት ላይ ለነበሩ የውጭ ኤክስፐርቶች በያመቱ ከ4 — 5 ቢሊዮን ዶላር ለመክፈል ተገደዋል።[67] አንድ ታዳጊ አገር አንድን መሃንዲስ ለማሠልጠን ከ25,000 እስከ 40,000 ፣ አንድን ቴክኒሺያን ለማሠልጠን ደግሞ ከ12,000 እስከ 15,000 ዶላር ወጪ ያደርጋል ።[68] በዚህ ስሌት መሠረት ዩናይትድ ስቴትስ ከላይ በተጠቀሱት ዓመታት መካከል ከታዳጊ አገሮች ካስኮበለለቻቸው ምሁራን 33.9 ቢሊዮን ዶላር አድናለች።[69]

4.4 ቁሳዊና ሕጋዊ አመቺነትን መርጠው በማሰማራት

በታዳጊ አገሮች የሥራ ኃይል ርካሽ ስለሆነ ፣ የሠራተኛ ማኅበራት ስለሌሉ ወይም ቢኖሩም የሠራተኛውን ጥቅም ለማስከበር ያላቸው አቅምና ልምድ እጅግ ውሱን በመሆኑ ለከፍተኛ ምዝበራ የተመቻቹ ናቸው ። ለምሳሌ በደቡብ ኮሪያ ፣ በታይዋን ወይም በደቡብ አፍሪካ ላሉ ሠራተኞች የሚከፈለው ምንዳ ዩናይትድ ስቴትስ ወይም ጀርመን ፌዴራል ሪፑብሊክ ውስጥ የሚሠሩ ሠራተኞች ከሚያገኙት ምንዳ በጣም ያነሰ ነው ። በተጨማሪም በብዙ ታዳጊ አገሮች ውስጥ የሥራ ማቆም አድማ ማካሄድ በሕግ የተከለከለና የሥራ ሰዓቶችም ረዘም መሆን ለድንበር ዘለል ሞኖፖሎች ዘረፋ ምቹ ሁኔታን ፈጥሮላቸዋል ። እንዲሁም በነዚህ አገሮች የጥሬ ሀብት አጠቃቀምን ፣ የቀረጥ አከፋፈልንና የተፈጥሮ አካባቢ መበከልን አስመልክቶ ባብዛኛው ጠንካራ ሕጎች ገና ባለመደንገጋቸው ድንበር ዘለል ሞኖፖሎች የታዳጊ አገሮችን ኢኮኖሚያዊ ሀብት በመሟጠጥ ላይ ይገኛሉ ። ድንበር ዘለል ሞኖፖሎች አካባቢን በመበከል ረገድ የሚያደርሷቸውን ማኅበራዊ ችግሮች በውል ማጤን እንዲቻል አንዳንድ መረጃዎችን እንመልከት ።

1. ዩኒየን ካርባይድ* ፀረተባይ ኬሚካሎችን የሚያመርቱ ሁለት ፋብሪካዎች ሲኖሩት አንደኛው በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ በምዕራብ ቨርጂንያ የሚገኝ ሲሆን ሌላው በህንድ አገር በማዳያፕራዴሽ ክፍለ ሀገር ብሆፓል ቀበሌ የተቋቋመ ነው ። በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ያለው ፋብሪካ በኮምፒዩተር የሚጠበቅ ፣ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ያለው ፣ አምልጦ ወደ ውጭ መፍሰስ ሲሞክር ወዲያውኑ የሚያቆም ዘመናዊ መቆጣጠሪያ የተሠራለት ነው ። በብሆፓል ያለው ግን ጋዙ ወይንም ኬሚካሉ ቢያፈተልክ አመልካች መሣሪያ የሌለው ፣ ተገቢ ጥንቃቄ ያልተደረገለትና ለአደጋ የተጋለጠ ነው ። በርካታ ሕዝብ በሚኖርበት ቀበሌ የተቋቋመው ይህ የኬሚካል ፋብሪካ ከጥንቃቄ ጉድለት የተነሣ በ1985 አምልጦ በወጣው የዩኒየን ካርባይድ መርዝ 2,500 ሰዎች ሲሞቱ ከ200,000 በላይ በሚሆኑ የአካባቢው ነዋሪዎች ላይ ከፍተኛ ጉዳት ደርሷል ።[70] በ1986 ታትሞ የወጣው ኢንተርናሽናል አፊርስ መጽሔት እንደዘገበው

* ዩኒየን ካርባይድ ዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ከሚገኙና ኬሚካልን ከሚያመርቱ አምስት ድንበር ዘለል ሞኖፖሎች መካከል አንደኛው ነው ። ይኸው ድንበር ዘለል ሞኖፖል አደገኛ ኬሚካሎችን አምርቶ ለወታደራዊ አገልግሎት የሚያቀርብ ሲሆን ለፔንታጎንም ዋንኛ የሥራ ተቋራጩ ነው ።

ይኸው ድንበር ዘለል ሞኖፖል በብራዚል የኤሌክትሪክ ኃይል መሥመር በሚዘረጋበት ወቅት በአማዞን ወንዝ ተፋሰስ ውስጥ ቶርዶን — 101 (Tordon -101) በመባል የሚታወቀውን ዕፅዋትን የሚያጠፉ መርዝ በመርጨት በአገሪቷ የደን ሀብት ላይ ጥፋት አድርሷል። በተጨማሪም 7,000 የሚሆኑ የአካባቢው ነዋሪዎች በመርዙ ተጐድተዋል ፤ ከእነዚህም መካከል የሞቱ ይገኛሉ ።[71]

2. ሃክስትና ባየር የሚባሉ የጀርመን ፌዴራል ሪፐብሊክ ድንበር ዘለል ሞኖፖሎች እንዳይሸጡ የተከለከሉ መድኃኒቶችን ለሜክሲኮ መንግሥት በመሸጥ የበርካታ ዜጐችን ጤና በማቃወስ ለብዙ ሰዎች ሕይወት መጥፋት ምክንያት ሊሆኑ ችለዋል ።[72]

3. ኢንተርናሽናል አፈርስ በ1986 እትሙ እንደዘገበው የቴክሳኮ ባሕር ማዶ ቅርንጫፍ የሆነው የናይጂሪያ አይል ፊልድ በናይጀር ወንዝ ውስጥ "ለሙከራ" የረጨው 400,000 በርሜል የዘይት ኬሚካል በ320 መንደሮች ውስጥ በሚኖሩ 230,000 ሰዎች ላይ የዐይን ፡ የቆዳና የአንጀት በሽታን አስከትሏል ። በዚችው አገር ምሥራቃዊ ክፍልም ለኢኮኖሚያዊና ተፈጥሮአዊ መዛባት ምክንያት ሆኗል ።[73]

4. በፖርታሪካ ደሴት ላይ ያለው የፔትሮኬሚካል ኢንዱስትሪ ፍሳሽ አገሪቷ በምትተማመንባቸው የሸንኮራ አገዳ ተክልና የዓሣ ኢንዱስትሪ ላይ ጥፋት አድርሷል።[74]

5. በነሐሴ 1979 የወጣው ቢዝነስ ታይምስ እንደገለጸው በፊሊፕንስ ያሉ ባህርዛፎች በኢንዱስትሪ ፍሳሽ በመመረዛቸው ምክንያት የዓመት ዕድገታቸው መጠን በ9 እጅ ቀንሷል ።[75]

6. ከላይ በተጠቀሰው መጽሔት አገላለጽ መሠረት በኢንዶኔዢያና ማሌዥያ ያሉ ድንበር ዘለል ሞኖፖሎች በየጊዜው የሚያፈሱት መርዛማ ጋዝ ባስከተለው የአካባቢ ብክለት የተነሣ በተፈጥሮ ደኖች ላይ ከፍተኛ ጉዳት ደርሷል [76]

7. በ1986 የወጣው ኢንተርናሽናል አፈርስ እንደዘገበው ቹቪሮን በመባል የሚታወቀው የደች ኩባንያ የቡና ተክል ተባይን የሚያጠፋ ነው ። በአንድ ሚሊዮን ዶላር 125 ቶን ፀረ ተባይ መድሃኒት ለኬንያ መንግሥት ሸጧል ። ይህም የቡናን ተባይ ከማጥፋት ይልቅ የቡና ምርት ከ7—8% ዝቅ እንዲል አድርጓል ።[77]

8. ድንበር ዘለል ሞኖፖሎች በእስያና በእሺኒያ በያመቱ 1.8 ሚሊዮን ሄክታር ደን፣ በአፍሪካ ኮትዲቯ (በቀድሞዋ አይቮሪ ኮስት) ብቻ 400,000 ሄክታር ስፋት ያለው ደን አውድመዋል ። የመሬትን የተፈጥሮ ሚዛን በሚያጠኑ ምሁራን ግምት መሠረት በያዝነው ምዕት ዓመት ማብቂያ ላይ በቡርኪናፋሶ ለዝናም መጣል አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ደኖች በሙሉ የሚወድሙ ሲሆን ፣ የፊሊፕንስና የማሌዢያ ደኖች የያዝነው ክፍለ ዘመን ከማለቁ በፊት ተመሳሳይ ዕድል የሚገጥማቸው ናቸው ።[78]

9. የጀርመን ፌዴራል ሪፐብሊክ ድንበር ዘለል የዶርኒየርና ማስርሺሚት ቅርንጫፍ የሆነው ኦትራግ ከአገሩ ውጪ መካከለኛ ርቀት ያላቸውን ሚሳይሎች በዛየር ምድር ውስጥ ለመሥራት ፣ ለመሞከርና የኒኩሊየር ዝቃጭ መቅበሪያ ለማድረግ ዝግጅት ላይ እንዳለ ተጋልጧል ።[79]

10. ዶው ኬሚካል በመባል የሚታወቀው መርዝ ቀማሚ ድንበር ዘለል ሞኖፖል ዩናይትድ ስቴትስ በቬትናም ሕዝብ ላይ ወረራ ባካሄደችበት ወቅት የተወራረዋን አገር ዕፅዋት የሚያረግፍና በሰው ልጅ ጤንነት ላይ ቀውስ የሚፈጥር ኬሚካል አምርቶ ለዩናይትድ ስቴትስ መንግሥት ያቀርብ ነበር ።[80]

5. የታዳጊ አገሮች ፀረ-ድንበር ዘለል ሞኖፖል ትግል

በታዳጊና በበለፀጉ አገሮች መካከል የሚታዩ ያልተመጣጠኑ ፣ ኢኮኖሚያዊ ግንኙነቶችን ማስወገድ ፣ የታዳጊ አገሮችን የተፈጥሮ ሀብት ከድንበር ዘለል ሞኖፖሎችና የነዚሁ የበላይ ጠባቂ ከሆኑ ኢምፔሪያሊስት መንግሥታት ዘረፋ አድኖ ለታዳጊ አገሮች ሕዝቦች እንዲውል ማድረግ አስፈላጊነቱ አጠያያቂ አይደለም ። በመሆኑም ታዳጊ አገሮች ራስን የመቻል መርህን በመቀየስ የጋራ ትብብር መፍጠርና የተመጣጠነ ኤኮኖሚያዊ ግንኙነትን ማስፈን በሚቻልበት መሠረተ ሐሳብ ላይ መስማማት ከጀመሩ ውለው አድረዋል ። እንዲያውም የድንበር ዘለል ሞኖፖሎችን ጥቃት ለመከላከል የሚያስችሉ ተጨባጭ እርምጃዎችን ወስደዋል ። ታዳጊ አገሮች በተፈጥሮ ሀብታቸው ላይ ያላቸውን ሉአላዊነት ማረጋገጥ ቀዳሚ ተግባራቸው በመሆኑ በግዛታቸው ተሰማርተው የሀገራቸውን ሀብት በማሟጠጥ ላይ በሚገኙ ድንበር ዘለል ሞኖፖሎች ላይ የመውረስና በመንግሥት ቁጥጥር ሥር የማሠራት እርምጃ ወስደዋል። አንድ የእንክታድ ጥናት እንደሚያመለክተው ከ1970 እስከ 1980 ባሉት ዐሥር ዓመታት ውስጥ ብቻ በታዳጊ አገሮች ውስጥ 2,314 የመውረስ እርምጃዎች ተወስደዋል ።[81] ባለፉት ዐሥር ዓመታት የተወሰዱት የውርስ እርምጃዎች በታዳጊ አገሮች የሚገኙ ድንበር ዘለል ሞኖፖሎች ለተወረሰባቸው የኢኮኖሚ ተቋም የተሟላ ካሣ እንዲከፈላቸው ለመጠየቅ ተገደዋል ። ይህንንም ጥያቄአቸውን ተግባራዊ ለማድረግ ግንባር በመፍጠር የተለያዩ ተጽዕኖዎች በማድረግ ለማስገደድ በመሞከር ላይ ናቸው ።

በሌላ በኩል ደግሞ ታዳጊ አገሮች በጥሬ ሀብትና በቴክኖሎጂ የንግድ መስኮች ከካፒታሊስቱ ዓለም ጋር ያላቸውን የተዛባ የንግድ ሥርዓት ለመለወጥ አጥብቀው በመታገል ላይ ናቸው ። ይህ ትግል ደግሞ በባሕርዩ የታዳጊ አገሮችን የተቀናጀ ጥረትና ዓለምአቀፍ መድረክ መጠቀምን የሚጠይቅ ነው ። በዚህ ረገድ ታዳጊ አገሮች የሚያደርጉት ትግል እየተጠናከረ ነው ። በዓለምአቀፍ ደረጃ ጥሬ ሀብት ለመቆጣጠር የሚያስችልና ገበያ ውስጥ የዋጋ መዋዠቅ ሲፈጠር የተለየ ድጐማ በማድረግ የዋጋ መረጋጋትን ለመፍጠር የሚያስችሉ ተቋሞች እንዲመሠረቱ ያደረጉት ጥረት ለዚህ ተግባራቸው መልካም ምሳሌ ነው ። በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት "የቡድን 77" መመሥረት ከዚሁ ጥረት ጋር ተያይዞ የሚታይ ነው ። ይህ ቡድን በዓለም አቀፍ ንግድ ውስጥ ሰፍኖ የቆየውን ያልተመጣጠነ ሁኔታ ለማስወገድ የተለያዩ ሐሳቦችን አቅርቧል ።

ከዚህም በላይ ታዳጊ አገሮች በዓለምአቀፍ ድርጅቶች በተለይም በተባበሩት መንግሥታት የተለያዩ ድርጅቶች ውስጥ በእኩልነት ለመሳተፍና መድረከነቱን ለዚህ ዓላማቸው ለመገልገል የሚያደርጉት ትግል እየተጠናከረ መጥቷል ። በዚህ ረገድ የታዳጊ አገሮች ጥረት ፍሬ እያፈራ ነው ። በዓለም አቀፍ ድርጅቶችና ተቋሞች ውስጥ ውሳኔዎች በትክክለኛው መርህ ላይ የተመሠረቱ እንዲሆኑ ታግለዋል ። ቀደም ሲል ሰፍኖ የቆየውን የውሳኔ አወሳሰን መርህ (የድምጽ አሰጣጥ የሚወሰነው አገሮች ለድርጅቱ በሚከፍሉት የክፍያ መጠን ነው)

Proudly Brought to You

በመቃወም ድምጽ አሰጣጡ በድርጅቱ ውስጥ ባሉት አባላት መጠን መሆን እንዳለበት በማስገንዘብ ታግለዋል ።

በአጠቃላይ ታዳጊ አገሮች የሀገሮች ሉዓላዊነት እንዲከበር ፣ በሀገሮች የውስጥ ጉዳይ ኤኮኖሚያዊ ፣ ፖለቲካዊና ወታደራዊ ጣልቃ ገብነት እንዲሁም የተዛባ የኢኮኖሚና የኢንፎርሜሽን ሥርዓት እንዲወገድ ፣ በሰላም አብሮ መኖር መርህ ላይ የተመሠረተ ዓለም አቀፍ ግንኙነትና አዲስ ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ሥርዓት እንዲመሠረት ያላሰለሰ ትግል በማድረግ ላይ ናቸው ። አገሮች በዓለም አቀፍ ግንኙነቶች ውስጥ ተገቢውን ቦታቸውን ለማግኘት በሚያደርጉት ትግል ውስጥ አዲስ ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ሥርዓት ለማስፈን የሚያደርጉት የኅብረት ትግል ከፍተኛ ስፍራ ይዟል።

አዲሱ ዓለምአቀፍ የኢኮኖሚ ሥርዓት ፖለቲካዊ ነፃነታቸውን በቅርቡ የተጐናፀፉ መንግሥታት የተፈጥሮ ሀብቶቻቸውንና የሕዝቦቻቸውን የሥራ ኃይል ከድንበር ዘለል ሞኖፖሎች ምዝበራ ለማዳን የተነደፈ በእኩልነት ላይ የተመሠረተ መርህ ነው ። ይህም መርህ በሰፊው ተቀባይነት ያገኘው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የዓለምን ኢኮኖሚያዊ ግንኙነቶች ከመረመረ በኋላ በግንቦት ወር 1974 ባካሄደው 6ኛ ልዩ ስብሰባ ውሳኔ ቁጥር (3201 SVI) አዲስ ዓለምአቀፍ የኢኮኖሚ ሥርዓት እንዲመሠረት ባወጣው መግለጫ መሠረት ነው ።[82] አዲሱ ዓለምአቀፍ የኢኮኖሚ ሥርዓት በአገሮች ሉዓላዊነት መከበር ፣ በአገሮች መደጋገፍ ፣ ታዳጊ አገሮች በእኩልነት ላይ የተመሠረተ ትብብር እንዲፈጥሩ የሚያበረታታ ጽንሰ ሐሳብ ነው ። የዚህም ጽንሰ ሐሳብ መሠረታዊ መርሆዎች:-

- በተፈጥሮ ሀብታቸው ላይ ጥብቅ ቁጥጥር ማድረግ ፣
- የድንበር ዘለል ሞኖፖሎችን ድርጊት የሚገድብ ሕግ ማውጣት ፣
- ለመሠረታዊ ሸቀጦችና ታዳጊ አገሮች ወደ ውጭ ለሚልኳቸው ዕቃዎች ተመጣጣኝ ዋጋ መክፈል ፣
- የገንዘብን የመግዛት ኃይል ማሻሻል ፣
- የታዳጊ አገሮች ምርቶች ገበያ እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ፣
- የታዳጊ አገሮችን የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዕድገት ማጠናከር የሚሉ ናቸው።[83]

ልዩ ስብሰባው ያወጣው መግለጫ ታዳጊ አገሮች በመካከላቸው የቅርብ ግንኙነትን እንዲፈጥሩ ፣ የአምራቾች ማኅበራትን እንዲያቋቁሙ ፣ በመዘረፍ ላይ ያለውን የተፈጥሮ ሀብታቸውን እንዲንከባከቡ ያሳስባል ። ከዚህም በተጨማሪ የውጭ ግንኙነት ለማካሄድ አንድ የጋራ መመሪያ ወጥቷል ። ይህም :-[84]

- ታዳጊ አገሮች በተፈጥሮ ሀብቶቻቸው ላይ ብሔራዊ ሉዐላዊነት እንዲኖራቸው ዓለምአቀፍ ዋስትና መስጠት ፣
- በጥሬ ዕቃዎችና በተፈበረኩ ሸቀጦች መካከል የተመጣጠነ ዋጋ እንዲኖር ማድረግ ፣
- ያላንዳች ተጽዕኖ ከበለፀጉ አገሮች ጋር ንግድን ለማስፋፋት ትክክለኛ ምርጫ ማድረግ ፣
- የዓለምን ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ለማበረታታትና በቅርቡ ነፃ የወጡ መንግሥታትንም ዕድገት ለማፋጠን ለአምራቾች ማኅበራት እንቅስቃሴዎች ሁኔታዎችን ማመቻቸት ፣
- ዓለምአቀፍ የገንዘብ ሥርዓትን የተመጣጠነ ማድረግ ፣
- ታዳጊ አገሮች የኢንዱስትሪ ሸቀጦችን

ወደ ውጭ እንዲልኩ ማበረታታት ፣
- ወታደራዊ ወይንም ፖለቲካዊ ተጽዕኖ የሌለበት ዕርዳታ ማድረግ ፣
- በታዳጊ አገሮችና በበለፀጉት መካከል ያለውን ቴክኖሎጂያዊ መራራቅን ማጥበብ ፣
- የቴክኖሎጂ ዝውውርን ማመቻቸትና ታዳጊ አገሮች ለኢኮኖሚያቸው ተስማሚ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን እንዲፈጥሩ ማበረታታት ፣
- የዕዳ ጫናንና ከበለፀጉ አገሮች ወደታዳጊ አገሮች ከመጠን በላይ የሚጐርፉ ሸቀጦችን መጠን መቀነስ ፣
- “አእምሮ ዘረፋ” (ምሁራንን ማስኮብለል) እንዲቀርና ታዳጊ ሀገሮች ለኮበለሉባቸው ምሁራን ካሳ እንዲያገኙ ማድረግ
- የድንበር ዘለል ኮርፖሬሽኖች ስምሪትን በሚመለከት ሕግ ማውጣትና እንቅስቃሴያቸውንም መቆጣጠር ።

በዚህ መመሪያ መሠረት የታዳጊ አገሮች መንግሥታት የጋራ ኤኮኖሚያዊ ትብብርን መፍጠር የሚያዋጣና የዕድገት መፍትሔም መሆኑን ተረድተው ለተግባራዊነቱም የማይናቅ አስተዋጽኦ በማድረግ ላይ ናቸው ። በዚህም መሠረት በተለያዩ አህጉራት የሚገኙ አገሮች የሚገኙበትን መልክአ ምድራዊ ክልል ፣ የተፈጥሮ ሀብት ፣ ኤኮኖሚያዊ መተሳሰር ሌሎችንም መስፈርቶች ከግምት ውስጥ በማስገባት ከድንበር ዘለል ሞኖፖሎች ተጽዕኖ ራሳቸውን ለመከላከል የሚያስችሉ ዕቅዶችን አውጥተዋል። ለምሳሌ በ1971 በላቲን አሜሪካ አህጉር ያሉና የአንዲያን ቡድን* (Andean Group) በመባል የሚታወቁ አገሮች ድንበር ዘለል ሞኖፖሎች በየሀገሮቻቸው በሚያውሉት ሙአለንዋይ ፣ በፓቴንቶች ፣ በንግድ ፈቃድ ስምምነት ፣ በንግድ ምልክትና በመሳሰሉት ያደረሱባቸውን ዘረፋ ለመቋቋም ከሚያስችል ስምምነት ላይ ደርሰዋል ። ስምምነቱም አስፈላጊ የሆኑ የአገሮቻቸውን ኤኮኖሚያዊ ፖሊሲዎች በሚመለከቱ መርሆዎች ላይ የተመሠረተ ሲሆን ይህም “ውሳኔ 24” በመባል የሚታወቅ ስምምነት ነው ። የስምምነቱ ዓላማዎችም ፤[85]

- የአንዲያን አባል አገሮች ለኢኮኖሚያዊ ዕድገታቸው ኃላፊነትን መውሰድ፣
- አባል አገሮች ሙሉ በሙሉ በተፈጥሮ ሀብታቸው የመጠቀም መብታቸውን ማስከበር ፣
- ለብሔራዊ ድርጅቶችና ለአባል አገሮች ኤኮኖሚያዊ ዕድገት ትኩረት መስጠት ፣
- ለአባል አገሮች ዕድገት በጐ አስተዋጽኦ ማድረግ የሚችል የውጭ ካፒታል ሥራ ላይ ማዋል ፣ እንዳስፈላጊነቱ የውጭ ቴክኖሎጂንም ማስገባት የሚሉ ናቸው ።

መንግሥታት ቴክኖሎጂን ለመቀበልም ሆነ የውጭ ሙአለንዋይን በማስገባትና ለዚህ ተግባራዊነት ኃላፊነትን የሚወስድ አንድ ልዩ መንግሥታዊ ድርጅት ለማቋቋም ጥረት አድርገዋል ። የነዚህን ፈለግ የተከተሉ ሌሎች ታዳጊ አገሮችም የቴክኒክና የኢንዱስትሪ ግንባታ ልምድ ያላቸውን በሳል ምሁራን ለማግኘት እንዲችሉ የሚረዷቸው ልዩ ድርጅቶች መመሥረት አስፈ

* አንዲያን ቡድን በ1969 አምስት የላቲን አሜሪካ አገሮች (ኮሎምቢያ ፣ ቦሊቪያ ፣ ቺሊ ፣ ኤኳዶርና ፔሩ) በጋራ የውጭ ሙአለ ንዋይን ፣ የንግድ ፖሊሲዎችን ለማካሄድና በኤኮኖሚያዊ ልማት ለመረዳዳት የመሠረቱት የጋራ ገበያቸው ስም ነው ። ዓላማውም በአባል አገሮች መካከል ያለውን ሁሉንም የንግድ ታሪፎችን ለማስቀረትና በመካከላቸው ጤናማ የንግድ ልውውጥን እንዲያደርጉ ለማስቻል ነው ።

ላጊ መሆኑን ተገንዝበዋል ። እነዚህ ልዩ ዓይነት ድርጅቶች በአርጀንቲና ፣ በብራዚል ፣ በፊሊፒንስ ፣ በህንድ ፣ በኮሎምቢያ ፣ በማሌዢያ ፣ በሜክስኮ ፣ በደቡብ ኮሪያና በአንዳንድ አካባቢዎች ተቋቁመዋል ። ከተጠቀሱት መንግሥታት መካከል ህንድ ቴክኖሎጂን ወዳገሯ ይልኩ የነበሩ መንግሥታት ይጠቀሙበት የነበረውን የ"ግዢ ግዴታ" (Conditional Purchase) እንቀጽ እንዲቀር አድርጋለች ።

በኮሎምቢያም እንደዚሁ ከውጭ ድርጅቶች ጋር ተደራድሮ ቴክኖሎጂን የሚያስገባ በብሔራዊ ደረጃ ልዩ ምክር ቤት ተቋቁሞአል ። ይህ በብሔራዊ ደረጃ ተቋቁሞ የሚሠራው ድርጅት በንግድ ፈቃድ አጠቃቀም ብቻ ይባክን የነበረውን የአገሪቷን ወጪ 40 ከመቶ የቀነሰ ሲሆን በያመቱ ለዚህ ብቻ የተመደበውን ስምንት ሚሊዮን ዶላር ከማዳኑም በላይ የአገሪቷን ጥቅም የሚጻረሩ አንዳንድ ጉጂ አንቀጾችንም እስከማስወገድ ደርሷል ።[86]

ከ1974 ወዲህ ሰባት መሠረታዊ ሸቀጦችን ማለትም ቦክሳይትን ፣ ያልተነጠረ ብረትን ፣ ታንግስተንን ፣ ሜርኩሪን ፣ እንጨትን (ቲምበር) ፣ ስኳርና ሙዝን የሚያመርቱና የሚሸጡ መንግሥታት ማኅበር አቋቁመዋል እነዚህ መንግሥታት የሚያመርቷቸውን ዕቃዎች በተመጣጠነ የዓለም ገበያ ላይ በመሸጥ ኢምፔሪያሊስት መንግሥታት የሚያደርሱባቸውን ተጽዕኖ ለመከላከል ጥረት አድርገዋል ።[87]

በ1980 ሸቀጥ ወደ ውጭ የሚልኩ 75 ታዳጊ አገሮች በአባልነት የሚገኙበት 20 የአምራቾች ማኅበራት ተቋቁመዋል ። አንዳንድ የላቲን አሜሪካ ቡና አምራች አገሮች ቡና በመሸጥ ረገድ ብዝበዛን ለመከላከል ተደራጅተዋል ። ከ300 — 500 ሚሊዮን ዶላር ካፒታል ያለው የቡና አምራችና ሻጭ አገሮች ያሉበት "ቦጐታ ቡድን" በመባል የሚታወቅ ድርጅት መሥርተዋል ። ይኸው ድርጅት በ500 ሚሊዮን ዶላር ካፒታል የሚንቀሳቀሰውን "ፓንካፊ" የሚባለውን ተጨማሪ ቅርንጫፍ ለመመሥረት በቅቷል ።[88]

በአፍሪካ አህጉርም የኢምፔሪያሊስት ድንበር ዘለል ሞኖፖሎች የሚያደርሱትን ተጽዕኖ ለመከላከል መንግሥታት የተለያዩ አመቺ የንግድ ቀጣናዎችን በመመሥረት ላይ ናቸው ።* በአሁኑ ጊዜ በአህጉር በመመሥረት ላይ ያሉት የኢኮኖሚ ድርጅቶች ድንበር ዘለል ሞኖፖሎች በጥሬ ሀብት ግገርና በሸቀጥ ሽያጭ ረገድ ለበርካታ ዘመናት ይፈጽሙ የነበረውን ስውር ደባ ጭምር ይከላከላል ተብሎ ይገመታል ።

ታዳጊ አገሮች የድንበር ዘለል ሞኖፖሎችን ጥቃት ለመከላከል በክልልና በአህጉር ደረጃ ከመጠናከር በተጨማሪ ሶሻሊስት የእድገት ፈለግ መከተልንም እንደመፍትሔ አድርገው ወስደዋል ። ግንባር ከመፍጠሩ በተጨማሪ በብሔራዊ ደረጃ ማኅበራዊ አብዮትንም ማካሄድ ፣ ከሶሻሊስት አገሮች ጋር የቅርብ ግንኙነትንም መፍጠር አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል ።

ማጠቃለያ

ከላይ ከተዘረዘሩት መረጃዎች መረዳት እንደሚቻለው ድንበር ዘለል ሞኖፖሎች ፋይናንስን ወደ ታዳጊ አገሮች አዝምተው የአገሮቹን የተፈጥሮ ሀብትና ሠራተኛውን ከመበዝበዝ ፣ መንግሥታትን በቴክኖሎጂ

* ስለ አፍሪካ የኢኮኖሚ ሁኔታ በበለጠ ለማወቅ መስከረም ቅጽ 6፡ቁ.26 ፡ ሰኔ 1978 ፣ ቅጽ 7 ፣ ቁጥር 27፣ መስከረም 1979 መመልከት ይጠቅማል ።

ያዊ እጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ሥር ከማስገባት በተጨማሪ አሳሳቢና ከሰው ልጅ ሕይወት ጋር የተያያዘውን የተፈጥሮ አካባቢን በማዛባት በኩል የሚፈጽሙት ወንጀል ከዕለት ዕለት እየጨመረ ነው ። ይህ የሚያስረዳው ኢምፔሪያሊስት መንግሥታት ለሰው ልጅ ሰብአዊ ክብርና ህልውና የማይቆሙ ፣ የሰው ልጅ መኖሪያ ለሆነችውና ተተኪ ለሌላት ዓለም እንኳን እንክብካቤ የማያደርጉና የድንበር ዘለል ሞኖፖሎችም የነዚህን መንግሥታት ባለብዙ ፈርጅ ተልዕኮ ይዘው ወደ ታዳጊ አገሮች የተሰማሩ መሆኑን ነው ።

ድንበር ዘለል ሞኖፖሎች ለታዳጊ አገሮች ኢኮኖሚያዊ ዕድገት አጋዥ ኃይሎች ነን ብለው ቢሟገቱም ለታዳጊ አገሮች ኢኮኖሚ መቀጨጭና ለልማታቸውም መገታት ዓይነተኛ ምክንያት ናቸው ። ይህም በመሆኑ የታዳጊ አገሮች ሕዝቦች በድንበር ዘለል ሞኖፖሎች ላይ ቆራጥና አፋጣኝ የሆኑ እርምጃዎችን መውሰድ ከጀመሩ ቆይተዋል ። ከነዚህም መካከል በአገራቸው መሠረታዊ ለውጥ ማካሄድ ፣ የድንበር ዘለል ሞኖፖሎችን ይዞታ በመውረስ ኢኮኖሚያዊ መሠረታቸውን ማዳከም ፣ ቁልፍ የሆኑ የኢኮኖሚ ዘርፎችን በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ማድረግ ፣ የውጭ ካፒታል እንቅስቃሴን መቆጣጠር ፣ የየሀገሮቻቸው ሕዝቦች ገንዘባቸውን ለአገር ልማት እንዲያውሉ ማበረታታትና ዋስትና መስጠት ፣ ብሎም የምርት ኃይሎችን ዕድገት በአፋጣኝ ለማሳደግ የሚያግዙ ሁኔታዎችን መቀየስ ዋና ዋናዎቹ ናቸው ።

ታዳጊ አገሮች በዓለም አቀፍ የሥራ ክፍፍል ውስጥ ንቁና ብቁ ተሳታፊ በመሆን የሀብታቸው ተጠቃሚ እንዲሆኑ በሰላም አብሮ የመኖርንና የእኩልነትን መርህ ከሚያራምዱ ማናቸውም አገሮች ጋር ጠንካራ ግንኙነት መፍጠር ይኖርባቸዋል ። በተለይም ከሶሻሊስት አገሮች ጋር የቅርብ ግንኙነት መፍጠር ከድንበር ዘለል ሞኖፖሎች ስውር ደባ ለመላቀቅ ለሚደረገው ትግል ዓይነተኛ መፍትሔ ነው ።

ከዚህ በተጨማሪም በታዳጊ አገሮች መካከል ያለውን ግንኙነት አጠናክሮ የወልችግሮችን ለመወጣት ያላቸውን ሰብአዊና ቁሳዊ ሀብት በማቀናጀት ከኋላ ቀርነትና ከድንበር ዘለል ኩባንያዎች ብዝበዛ ለመላቀቅ ጥረት ማድረግ ቸል ሊባል የማይገባው ተግባር ነው ። በዚህ መስክ በሚደረገውም ትግል የሶሻሊስት ሀገሮች ያላሰለሰና ሁሉን አቀፍ ዕርዳታም የሚያበረታታ ነው ። ታዳጊ አገሮችም በዚህ መስክ በማድረግ ላይ የሚገኙት ጥረት የሚናቅ አይደለም ። የኢኮኖሚውንም መስክ በተመለከተ ልዩ ልዩ አመቺ የንግድ ቀጠናዎችን በማቋቋምና የተግባር መርሀዎችን በመንደፍ አመርቂ የሆኑ ጅምሮች በመታየት ላይ ናቸው ።

በፖለቲካውም መስክ እንደዚሁ በልዩ ልዩ አካባቢዎች የተከሰቱ ውጥረቶችን ለማርገብ የሚያስችሉ እርምጃዎችን ሰላማዊ በሆነ መንገድ በመውሰድ ለችግሮቻቸው የፖለቲካ መፍትሔ ለመስጠት የሚያደርጉት ጥረት በመጐልበት ላይ ነው ። ይሁን እንጂ ታዳጊ አገሮች ከድንበር ዘለል ሞኖፖሎች ተጽዕኖ ለመላቀቅ የሚያደርጉት ትግል ከዓለም አብዮታዊያን ኃይሎች ትግል ተነጥሎ የማይታይ በመሆኑ ውስብስብነቱና ፈታኝነቱም ከፍተኛ ስለሆነ ይበልጥ መተባበርንና የትግል አንድነትን መፍጠር ይሻል ።

የግርጌ ማስታወሻ

1. Andrei Vernikov, Sergi Shibayev, "The World Economic System and the Developing Countries," *International Affairs*,6 (June 1987) p.44.

2. ግሌ መዝገበ ቃላት (አዲስ አበባ ፥ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት ፥ 1978) ገጽ 351.
3. M.I. Volkov.ed. *A Dictionary of Political Economy* (Moscow: Progress Publishers, 1985) p.373.
4. የፖለቲካ ኢኮኖሚ መዝገበ ቃላት (ቡልጋሪያኛ) (ሶፊያ ፥ 1984) ገጽ 719.
5. *Business Week*, 14 March 1982, p.32.
6. ቶችና ትራንዳፊሎቭና ሂሳን ቢሃር ፥ የዘመኑ ካፒታሊዝም ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ (ቡልጋሪያኛ) (ሶፊያ ፥ 1985) ገጽ 97.
7. Yu, Stepanov, "The TNC in the Strategy for Imperialist Expansion," *International Affairs*, 12 (December 1985) p.69.
8. UN, *Multinational Corporation in World Development* (New York: UN, 1978), p.28.
9. Yuri Popov, *Essays in Political Economy: Imperialism and the Developing Countries* (Moscow: Progress Publishers, 1984), p. 159.
10. Paul Harrison, *Inside the Third World* (London : Penguin Books, Ltd., 1982), p.349.
11. *Ibid.*
12. *Ibid.*
13. *Ibid.*
14. Ivan Dimitriyev, "The Systems of Neocolonialist Exploitation: Old Policies in New Guise," *Reprints From the Soviet Press* XLII, No.11 – 12 (June 15 – 30, 1986) p.39.
15. Ibid.
16. *Ibid.*
17. Ibid.
18. Deridre Griswold, *Indonesia: The Bloodbath that was (Revised Edition of Indonesia : The Second Greatest Crime of the Century)* (New York : World View Publishers, 1975), p.20.
19. E.Nukhovich, *International Monopolies and the Developing Countries* (Moscow : Progress Publishers, 1980), p.202.
20. *Ibid.*, p.204
21. *Ibid.*, pp.203 – 204
22. ANC, *The Subversive and Exploitative of Transational Corporations : Working Document for 2nd AAPSO, International Conference on the Role of Transnational Corporations and Economic Development Strategies* (Addis Ababa : April 28 – May 1982 (Mimeo) p.25.
23. Stepanov, *op.cit.*, p.75.
24. *Ibid.*
25. A Grachev, N.Yermoshkin, *A New Information Order Or Psychological Warfare?* (Moscow : Progress Publishers, 1984), p.51
26. *Ibid.*, p.25.
27. *Ibid.*, *p.24*
28. *IPW Berichte, No.5, 1980 32* እንዲሁም ትችና ትራንዳፊሎቭ ገጽ 90
29. Yuir Popov, *op.cit.*, p. 158
30. *Political Economy of Capitalism* (Moscow : Progress Publishers,1985), p.192.
31. S.P Amarasingam, *Industrialized Nations of the West and the Third World* (Colombo : Swastica, 1982), p.50
32. *Ibid.*
33. አዲስ ዘመን ጋዜጣ ፥ ነሐሴ 24 ቀን 1978 ፥ ገጽ 9 ።
34. Sergi Shibayev, *op.cit.*, p.45.
35. *New Times*, No, 41, 1985, p. 22.
36. *Ibid.*
37. Fidel Casstro, *On Latin America's Unpayable Debt, Its Unforeseeable Consequences and Other Topics of Political and Historical Interest: Interview Granted to EFE News Agency* (La Habana, 1985), p.43.
38. *International Bank for Reconstruction and Development : Annual Survey*, 1982, p. 143. *Development Review* (Paris: OCED, 1981), p. 218.
39. Harrt Magdoff, *The Age of Imperialism: The Economics of US Foreign Policy* (New York: Monthly Review Press, 1969), p. 176.
40. Teresa Hayter, *The Creation of World Poverty* (London : Pluto Press, 1983), p.83
41. *Ibid.*, pp.83 – 84
42. *Department of State Bulletin, June* 1978, p.4 quoted by Amarasingam op. cit., p. 57.
43. William S.Guad, '*Foreign Aid: what It is : How it Works; Why we Provide,* ' The Department of State Bulletin, Vol. LIX, No. 1537 (9 December 1968) p.603.
44. Report in Overseas Development (November 1968) p. 9, quoted by Gunnar Myrdal, *The Callenge of World Poverty : A World Anti – Poverty Programme in Outline* (London: Pelikan Books, Ltd., 1971) p.347.
45. Amarasingam, *op.cit.*, p.92
46. *Ibid,*. p.98.
47. *Ibid.*, p.96.
48. A.Z.Stapovich, *The Strategy of Transnational Corporations* (Moscow : Progress Publishers, 1978), p.259.
49. Amarasingam, *loc.cit.*
50. Paul Harrison *op.cit.,p.103*
51. *The Department of Stat Bulletin*, July 1977, p.129.
52. Amarasingam, *op.cit.*, p.103.
53. A Fyodorova, "The Brain Drain", -An Imperilalist Policy," *International Affairs* 11 (November 1981) p.64.
54. Amarasingam, *loc.cit.*
55. Edwin P. Reubens, *Professional Migration from the less Developed Countries:* Feb. 1975 (Mimeo) p.42. Quoted by Michael P.Todorov, *Economics for a Developing World: An Introduction to Principles, Problems and Policies for Development* (Essex: Longman Group Ltd, 1981), p.284.
56. Amarasingam, *op.cit*, p.105.
57. A Fyodoraova, *op.cit.*, p.62.
58. Sergi shibayev, *op.cit*, p.46.
59. Yu.Stepanov, *loc.cit.*
60. *Ibid.*
61. N.Volkov, R, Zimenkov, *Technological Neocolonialism* (Moscow: Progress Publishers, 1986), p.63.
62. A Fyodorova, *op.cit.*, p.65.
63. N.Volkov, *loc.cit.*
64. Nukovich, *op.cit.*, p.201.
65. Sergi Shibayev, loc. cit.
66. Amarasingam, *op.cit.*, p. 102
67. Stepanov, *op.cit.*, p.73.
68. *Ibid.*
69. Amarasingam, *op.cit.*, p.105.
70. *"Rundown on Union Carbide,"* *New Times*, No.1, 1985, pp. 22-23.
71. *International Affairs*, No.1, 1986 p. 132.
72. *Ibid.*, p.133.
73. *Ibid.*
74. Ibid.
75. *Business Times*, August 10, 1979 quoted by Amarasingam, *op.cit.* p.48
76. *Ibid.*
77. *International Affairs*, No.1, 1986, *loc.cit.*
78. *Ibid.*
79. UNIDO, *Industrialization for 2000 New Dimesions* (Vienna: UNIDO, 1975), p.55. See also *International Affairs*, No.11, 1986, p.82.
80. *New Times*, No.1, 1986, p.26.
81. ቶችና ትሬንዳ ፊሎቭ ፥ የዘመኑ ካፒታሊዝም ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ (ቡልጋሪያኛ) ፥ ገጽ 122
82. *Towards the New International economic Order: Report of the Director General for the Development of International Economic Cooperation* (New York : UN, 1982), p.3.
83. *Ibid.*, p.10.
84. M.I. Volkov, *loc.cit.*
85. N.Volkov, *op.cit.*, p.25.
86. UNCTAD Doc., TD/Ac. 11/10/Rev. 1, April 22, 1974, p.24 in *Technological Neocolonialism*, op.cit., pp.72-73.
87. Towards the New International Economic Order, *loc.cit.*
Ibid.

መስከረም

* የዋጋ ንድፈ ሐሳብ
* ድንበር ዘለል ሞኖፖሎች በታዳጊ አገሮች ላይ የሚፈጽሟቸው ደባዎች
* የኒካራጓ ሕዝብ ፀረኢምፔሪያሊስት ትግልና የዩናይትድ እስቴትስ ደባ

ማርክሳዊ ሌኒናዊ የርዕዮተዓለም መጽሔት

ቅጽ ፰ ቁጥር 33
መጋቢት 1980

መስከረም

ቅጽ ፰ ቁጥር
መጋቢት 1980 33

ማርክሳዊ ሌኒናዊ የርዕዮተዓለም መጽሔት

ማውጫ

ገጽ

* የዝግጅት ገጽ 3

* የዋጋ ንድፈ ሐሳብ 7
  — ከልዩ ልዩ ጽሑፎች የተቀነባበረ

* ድንበር ዘለል ሞኖፖሎች በታዳጊ አገሮች ላይ የሚፈጽሟቸው ደባዎች 32
  — ወልደ ዮሐንስ ወርቅነህ

* የኒካራጓ ሕዝብ ፀረኢምፔሪያሊስት ትግልና የዩናይትድ እስቴትስ ደባ 58
  — ዝናቡ ከበደ

በኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ

ርዕዮተዓለም መምሪያ እየተዘጋጀ በየሦስት ወር የሚወጣ

መስከረም 1973 ተመሠረተ

አድራሻ

የፖስታ ሣጥን ቁጥር — 80001
የስልክ ቁጥር — 113000

የኒካራጓ ሕዝብ ፀረ ኢምፔሪያሊስት ትግልና የዩናይትድ እስቴትስ ደባ

ዝናቡ ከበደ

ባለፉት ጥቂት ዐሥርት ዓመታት በተለያዩ የዓለም ክፍሎች በርካታ አካባቢያዊ ግጭቶችና ጦርነቶች ተከስተው ለእያሌ ሰዎች ሕይወትና ንብረት መጥፋት ምክንያት ሊሆኑ ችለዋል ። "ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ በተከሰቱ ግጭቶችና ጦርነቶች ሳቢያ ከ20.691.000 በላይ ሰዎች ሕይወታቸውን አጥተዋል ።"[1] ይህን ያህል ሕይወት ላጠፉት ጦርነቶችና ለዓለም ሰላምና ፀጥታ መናጋት ዋንኛው ምክንያት ምንድን ነው? የሚለው ጥያቄ በብዙም ሰላም ወዳድ ኃይሎች ዘንድ የሚነግ ነው ።

ይህንን አሳሳቢ ጉዳይ ስናጤን በተለይም በአሁኑ ወቅት ጦርነት የሚካሄድባቸውና ወደፊትም ለዓለም ሰላምና ፀጥታ መናጋት የቅርብ ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ የውጥረት ቋቶች የሚገኙባቸውን ሥፍራዎች ስንመለከት የምንገነዘበው አንድ ቁም ነገር አለ ። ይኸውም የሰላም መታወክ የሚታይባቸው አካባቢዎች እጅግ ተፈላጊ የሆኑ ፖለቲካዊና ስትራተጂያዊ ክልሎች ፣ ሰፊ የተፈጥሮ ሀብት የሚገኝባቸው ፣ ለወታደራዊ መረማመጃና ለልዩ ልዩ ተፈላጊ ሸቀጦች መተላለፊያና በአካባቢው የሚገኙ ሀገሮችም የራሳቸውን የዕድገት ፈለግ በራሳቸው በመወሰን ብሔራዊ ጥቅማቸውን ለማስከበር ጥረት በማድረግ ላይ የሚገኙ መሆናቸው ነው ።

በዚህም መሠረት እነዚህን ሥፍራዎችም ሆነ መላውን ዓለም በወታደራዊ ኃይል አስገድደው በቁጥጥራቸው ሥር ለማዋል የዘወትር ምኞታቸው የሆነው ዓለም አቀፍ ኢምፔሪያሊስትና አድኀሮት ኃይላት በተለያዩ አካባቢዎች ግጭቶችና ጦርነቶች እንዲነሡ በመቀስቀስና የቀሰቀሷቸውንም ግጭቶች እንዲጋጋሙ በማድረግ ላይ ናቸው ።

ኢምፔሪያሊስትና አድኀሮት ኃይላት በተለያዩ የዓለም ክፍሎች በሚገኙ ተራማጅ መንግሥታት ላይ ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ ፣ ዲፕሎማሲያዊና ወታደራዊ ተጽዕኖዎችን በማሳደር ከራሳቸው የተደማጭነት ክልል ውስጥ እንዳይወጡ ያላሰለሰ ጥረት ያደርጋሉ ። ለዚህ ዓላማቸውም መሳካት እያሌ የጦር ሠፈሮችን መሥርተው ፈጣን ጣልቃ ገብ ሠራዊታቸውን በማሰለፍ ተራማጅ መንግሥታትን የማስገልበጥ ፣ አብዮታውያን መሪዎችን የማስገደል ፣ ቀጥተኛ ወታደራዊ ወረራዎችን የማካሄድና ሌሎችንም ፀረ አብዮትና ፀረ ሶሺሊዝም ዘመቻዎችን በሰፊው ተያይዘውት ይገኛሉ። በተጨማሪም የብሔራዊ አርነት ትግሎችን ከሌሎች አብዮታዊ ኃይሎች ለመነጠል በእነዚሁ ተራማጅ ኃይላት ላይ ከፍተኛ የሆነ የማጥላላትና መሠረተ ቢስ የሆኑ ውንጀላዎችን ያስተጋባሉ ። ይህም የብዝበዛ ምንጮቻቸው በሆኑት ታዳጊ ሀገሮች ውስጥ ፈጣን በሆነ ሁኔታ በመካሄድ ላይ የሚገኘውን አብዮታዊ እንቅስቃሴ በመገደብና ብሎም በማጥፋት የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ምዝበራቸው እንዳይቋረጥ ዋስትና ለመስጠት ነው ።

ለዚህ ዓይነቱ ጥቃት ዒላማ ሆነው ከሚገኙ ሀገሮች መካከል አንዷ ኒካራጓ ነች። የኒካራጓ አብዮት ከመቀጣጠሉ በፊት ሀገሪቱ ለብዙ ዓመታት የዩናይትድ እስቴትስ ኢምፔሪያሊዝም ጥገኛ ነበረች ። ከሳንዲኒስታ አብዮት መቀጣጠል በኋላ ግን የተወሰዱት ሥር ነቀል እርምጃዎች ይህን ጥገኝነት ያስቀሩ በመሆናቸው ጥቅማቸው የተነካባቸው በውስጥም ሆነ በውጪ የሚገኙ የአድኀሮት ወገኖች እጅና ጓንት በመሆን የኒካራጓን አብዮትና ድሎቹን ለመንጠቅ ከፍተኛ ጥቃት ሲፈፅሙ ቆይተዋል ።

ይህች ታዳጊ ሀገር ቅድመ አብዮት ከዩ[illegible]ተድ እስቴትስ ኢምፔሪያሊዝም [illegible] ምን ዓይነት ግንኙነት ነበራት? ከሳንዳ[illegible] አብዮት በኋላ ሀገሪቱ በተከተለችው [illegible]ነት አትጣሜ ለውጥ የተነሣ ከዩናይ[illegible]ትስ ጋር የነበራት ግንኙነት ምን መል[illegible]ያዘ? ምን ችግር አጋጠማት? ችግሩንስ ለመቋቋም ምን እርምጃዎች ወሰደች? በአንፃሩስ ምን ድጋፍ ታገኛለች? ባጠቃላይ ዛሬ በምን ሁኔታ ላይ ትገኛለች?

ቅድመ አብዮት ኒካራጓና ዩናይትድ እስቴትስ

ኒካራጓ 130,000 ካሬ ኪ./ሜትር ስፋትና 3,160,000 ሕዝብ ያላት በማዕከላዊ አሜሪካ ውስጥ የምትገኝ ሀገር ናት።[2] ኒካራጓ የሚለው የሀገሪቱም ስም የተገኘው የስፓኝ ቅኝ ገዢዎች በአካባቢው ከመስፈራቸው በፊት በዛሬይቱ ኒካራጓ ይኖሩ ከነበሩ ጎሳዎች መካከል የአንዱ መሪ ከነበረው ኒካራዎ ከሚባለው ሰው ስም ነው ። ይህች ሀገር በሰሜን ምሥራቅ ከሆንዱራስ ፣ በደቡብ ምዕራብ ከሰላማዊ ውቅያኖስ ፣ በደቡብ ከኮስታሪካና በምሥራቅ ደግሞ ከካሪቢያን ባሕር ጋር ትዋሰናለች ።

ዩናይትድስቴትስ ኒካራጓን በቁጥጥሯ ሥር አድርጋ የሀገሪቱን ሀብትና የሕዝቡን ጉልበት መመዝበር ከመጀመሯ በፊት አካባቢውን ይቆጣጠሩ የነበሩት የእስፓኝ ቅኝ ገዢዎች ነበሩ ። በ15ኛው ምዕት ዓመት መባቻ ላይ ኒካራጓን የቅኝ ግዛታቸው ያደረጉት የስፓኝ ቅኝ ገዢዎች ግራናዳና ሊዎን በመባል የሚታወቁትን ከተሞች በመቆርቆር የአስተዳደር ማዕከላቸው አድርገው ሲጠቀሙባቸው ቆይተዋል ። ከ1570ዎቹ* በኋላም ጓቲማላን ያስተዳድር የነበረ የእስፓኝ ጀኔራል ኒካራጓንም አጠቃሎ የመግዛት መብት ከእስፓኝ ማዕከላዊ መንግሥት የተሰጠው በመሆኑ የሁለቱን ሀገሮች ሕዝቦች በወታደራዊ ኃይል በማስገደድ የግፍ አገዛዙን ማካሄድ ጀመረ ። እያሌ ኒካራጓውያን ኢሰብአዊ በሆነ መንገድ ሲጨፈጨፉ ከዚሁ ጭፍጨፋ ያመለጡትም በአስከፊ ሁኔታ በገባርነት እንዲኖሩ ተገደዱ። ቅኝ ገዢዎች ቀስ በቀስ ይዞታቸውን በማስፋፋት ለእርሻ ምቹነት ያለውን የኒካራጓን ለም መሬት በመቀራመት የሀገሪቱ ሀብት ዋንኛ ተጠቃሚ ሊሆኑ ቻሉ ።[3] ቡና ፣ ካካዎ፣ በቆሎ ፣ ሙዝና ሌሎችንም አዝርዕት አብቃይ ከሆኑ ለም መሬቶች የሚገኙ ምርቶች በአውሮፓ ገና በማቆጥቆጥ ላይ ለነበረው ኢንዱስትሪ ጥሬ እቃ አቅርቦት ይውሉ ።

*በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የዘመን አቆጣጠር እ.አ ነው ።

ጀመር ። ግብርናም በኒካራጓ ኢኮኖሚ ውስጥ ዐቢይ ሥፍራ የሚሰጠው የሥራ መስክ ነበር ።

በ19ኛው ምዕት ዓመት መባቻ ላይ በኒካራጓ ውስጥ ልዩ ልዩ የኢኮኖሚ ዘርፎች እያደጉ በመምጣታቸው በፊውዳሉ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት ውስጥ የካፒታሊስት ስልተምርት ለማቆጥቆጥ ቻለ ። የቡርዧው መደብም እንደዚሁ በማደግ ላይ ነበር ። ካፒታሊስቶችም በምንዳ የማሠራት ፍላጐታቸው እየጨመረ በመምጣቱ የወዛደሩም መደብ ቁጥር አደገ ። ከወዛደሩና ከካፒታሊስት መደቦች ማደግ ጋር የፖለቲካ ፓርቲዎችም ማቆጥቆጥ በመጀመራቸው የቡርዧውን መደብ የሚወክል የሊበራልና በኒካራጓ የነበሩ የፊውዳል ጎሩዩ ነገሥታትን የሚወክል የወግ አጥባቂ ፓርቲዎች ተቋቋሙ ።[4] በእነዚህ ፓርቲዎችም መካከል የሥልጣን ሽኩቻ በሰፊው መካሄድ ቀጠለ ። በአሜሪካ የሚገኙ የእስፓኝ ቅኝ ግዛቶች ነፃ የመውጣት ሂደት ከ1810–1826 እየተፋፋመ በመምጣቱ ጓቲማላ ነፃነቷን ስትቀዳጅ ኒካራጓ ደግሞ ከሜክሲኮ ጋር እንድትቀላቀል ተደረገ ። ከ1823–1838 በነበረው ጊዜ ውስጥ ደግሞ ኒካራጓ በማዕከላዊ አሜሪካ አገሮች ፌዴሬሽን ውስጥ አባል ሆና ቆየች ። ኒካራጓ በፌዴሬሽኑ ውስጥ በቆየችበት ጊዜ በአገሪቷ ውስጥ በነበሩ ሊበራልና ወግ አጥባቂ ፓርቲዎች መካከል በተፈጠረው የሥልጣን ሽኩቻ የተነሣ ተከታታይ የእርስ በርስ ጦርነቶችና ግጭቶች ተካሂደዋል ። በ1838 የማዕከላዊ አሜሪካ አገሮች ፌዴሬሽን ሲፈርስ ኒካራጓም የፖለቲካ ነፃነት ልትቀዳጅ ቻለች ።[5] በዚህ ወቅት ብሪታኒያና ዩናይትድ ስቴትስ በኒካራጓ ውስጥ ተደማጭነት ለማግኘት ከፍተኛ የሆነ ፉክክር በማድረግ ላይ ይገኙ ነበር ። ሁለቱም ሀገሮች ኒካራጓን አቋርጦ የአትላንቲክንና የሰላማዊ (ፓስፊክ) ውቅያኖሶችን የሚያገናኝ ቦይ በመሥራት ስትራቴጂያዊና ኢኮኖሚያዊ ተፈላጊነት ያለውን የመካከለኛውን አሜሪካ ክልል ለመቆጣጠር ያላሰለሰ ጥረት ያካሄዱ ነበር በዚህም መሠረት በ1841 ብሪታኒያ በኒካራጓ የካሬቢያን ጠረፍ በኩል ፎሲካ ተብላ በምትጠራው የባሕር ወሽመጥ ላይ የምትገኝ ደሴት በቅኝ ግዛትነት ለመያዝ ቻለች ። ዩናይትድ እስቴትስም በበኩሏ ኒካራጓን በቁጥጥሯ ሥር ለማድረግ ባደረገችው ያላሰለሰ ጥረት በ1850 የክሌይተን–ቡልዌር ስምምነት[6] በመባል ይታወቅ የነበረውንና ዩናይትድ እስቴትስም ሆነች ብሪታኒያ በኒካራጓ ውስጥ በእኩልነት መስፋፋት የሚችሉ ለመሆኑ "ሕጋዊ" ዋስትና የሚሰጥ ውል ለመፈራረም ቻለች ። ከዚህም በመነሣት እያሌ የዩናይትድስቴትስ ድንበር ዘለል ኩባንያዎች ሙአለንዋይ ወደ ኒካራጓ በገፍ በማጉረፍ ቡና ፣ ሙዝና ሌሎችንም አዝርዕት አብቃይ መሬቶች በቁጥጥራቸው ሥር አደረጉ ። በ1855 በዊሊያም ዎከር የሚመራ የዩናይትድ እስቴትስ የጦር ቡድን ኒካራጓን በወታደራዊ ኃይል በመውረር አምባገነናዊ አገዛዙን አሰፈነ ። ዊሊያም ዎከር በዩናይትድ እስቴትስ መስተዳድር እየታገዘ ራሱን የኒካራጓ ገገር በማድረግ በ1856 ሾመ ። ይኸው ጀብደኛ አምባገነን ኒካራጓን ከያዘ በኋላ መላውን ማዕከላዊ አሜሪካ በቁጥጥሩ ሥር በማዋል ለዩናይትድ እስቴትስ ድንበር ዘለል ኩባንያዎች ሙአለንዋይ ዋስትና ለመስጠት ከፍተኛ ጥረት አካሄደ ። ዳሩ ግን የጓቲማላ ፣ የሆንዱራስና የኤልሳልቫዶር አርበኞች ባደረጉት የወል ትግል ዎከርን ከኒካራጓ አስወጥተው ሆንዱራስ ውስጥ በመያዝ የሞት ቅጣት እርምጃ ወሰዱበት ። ይህንኑ የዩናይትድ ስቴትስ አምባገነን ለማስወጣት በተደረገው ዘመቻ በግንባር ቀደምትነት በመዋጋት የውጊያ ብቃቱን ያሳየው ቲ· ማርቲንዝ ከ1857–1867 የኒካራጓ ፕሬዚዳንት በመሆን በ1858 ማናጓን ቆርቆሮ የሀገሪቱ ዋና ከተማ እንድትሆን አደረገ ።[7]

ከ1857–1893 በነበረው ጊዜ ውስጥ በኒካራጓ የታላላቅ መሬት ከበርቴዎችን፣ የካፒታሊስቶችንና የዩናይትድ እስቴትስ ኩባንያዎችን ጥቅም የማስከበር ዓላማ የነበረው ወግ አጥባቂ ፓርቲ ሥልጣን ይዞ ቆይቶ ነበር ። ከ1893 በኋላ ግን በወግ አጥባቂው ፓርቲ ውስጥ የተከሰተው መከፋፈል አመቺ ሁኔታን የፈጠረለት የሊበራል ፓርቲ መሪ የነበረው ጄ·ኤስ ዜላያ ሥልጣን ያዘ ። የሊበራል ፓርቲውም አንዳንድ ጥገናዊ ለውጦችን አካሂዶ ነበር ። ከተከናወኑት ዐበይት ተግባራት መካከል የብሔራዊ ቡርዧውን ጥቅም ከውጭ ካፒታሊስቶች ለመከላከል የሚያስችሉ እርምጃዎችን መውሰድ[8] ይገኝበታል ።

ይህም እርምጃ የዩናይትድ እስቴትስ ሞኖፖሊስቶችን እጅግ ያስቆጣ ጉዳይ ሆነ። ከዚህም የተነሣ በዩናይትድ እስቴትስና በኒካራጓ መካከል የነበረው ግንኙነትና ወዳጅነት እየቀዘቀዘና እየሻከረ መጣ ። በሥልጣን ላይ የነበረው የሊበራል ፓርቲም በዚሁ አጋጣሚ በመጠቀም ከሌሎች መንግሥታት ጋር ግንኙነት ለመመሥረት በመወሰን ከጃፓንና ከብሪታኒያ ጋር ኒካራጓን አቋርጦ በማለፍ አትላንቲክንና ሰላማዊ ውቅያኖስን የሚያገናኝ ቦይ የመሥራት ውል ተፈራረመ ።

ኒካራጓ ከሌሎች መንግሥታት ጋር ያደረገችው ስምምነት ያስቆጣትና በዚህችው ሀገር ያዋለችው ሙአለንዋይ የማትረፍ ምንጭ ሊደርቅ የተቃረበ መሆኑ ሥጋት ያደረባት ዩናይትድ እስቴትስ በወታደራዊ ኃይል መጠቀም የተሻለ አማራጭ መሆኑን ወሰነች ። በዚህም መሠረት ከውስጥ ተቀናቃኝ ኃይሎች ጋር ተመሳጥራ የታጠቁ ወታደሮቿን በመላክ የኒካራጓን ሉዓላዊነት በመድፈር የራሷ አሻንጉሊት የሆነ ወታደራዊ መንግሥት መሠረተች ። ዩናይትድ እስቴትስ በተለያዩ ጊዜያት በኒካራጓ ውስጥ ወታደራዊ ጣልቃገብነት በማድረግና ጥገኞቿን ሥልጣን ላይ በማፈናጠጥ የኒካራጓን ሕዝብ ጉልበትና ሀብት ስትመዘብር ቆይታለች ። ይኸውም ድርጊቷ አልበቃ ብሏት ከ1912 በኋላ ደግሞ "በኒካራጓ የሚገኙትን የዩናይትድ እስቴትስ ዜጎች ሕልውና ለመጠበቅ" በሚል ሰበብ ወታደራዊ ወረራ በማከናወን ኒካራጓን ቅኝ ግዛቷ ለማድረግ ቻለች ።[9] የዩናይትድ እስቴትስ ሞኖፖሊስቶችም የኒካራጓን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ በቁጥጥራቸው ሥር በማዋል በሀገሪቱ ሀብት አዛዥና ናዛዥ ሆነው ቆዩ ።

በ1914 በዋሽንግተን በተፈረመውና የብራያን–ቻሞሮ ውል በመባል በሚታወቀው ስምምምነት መሠረት ዩናይትድ እስቴትስ ኒካራጓን አቋርጦ በማለፍ የሰላማዊና የአትላንቲክ ውቅያኖሶችን የሚያገናኝ ቦይ የመሥራት "ሕጋዊ" መብት ልትቀዳጅ ቻለች ። የዩናይትድ ስቴትስን ጥቅም ለማስከበር ቃል ገብቶ ኒካራጓን የበለጠ ጥገኛ የሚያደርጉ ስምምነቶችን የተፈራረመው ቻሞሮ በ1917 የሀገሪቱ ፕሬዚዳንት ሆነ። ሁለቱ ሀገሮችም በፖለቲካና በኤኮኖሚ መስክ የነበራቸው መተሳሰር የበለጠ ጨመረ ።

ዳሩ ግን በ1925 በተደረገው ምርጫ የወግ አጥባቂውና የሊበራል ፓርቲዎቹ ጥምር አመራር ሥልጣን በመጨበጡ የዩናይትድ እስቴትስ ወታደሮች ኒካራጓን ለቀው ወጡ ። በዚሁ ዓመት በጥቅምት ወር የዩናይትድ ስቴትስ አሻንጉሊት የነበረው ቻሞሮ ባደረገው መፈንቅለ መንግሥትም እንደገና ሥልጣን ለመያዝ በመብቃቱ በሀገሪቱ ውስጥ የሚገኙ ቁልፍ የሥልጣን ቦታዎች በሙሉ በራሱ የቤተሰብ አባላት እንዲያዙ አደረገ ።[10]

በ1926 ደግሞ ዩናይትድ ስቴትስ እንደገና ባደረገችው ወታደራዊ ወረራ ቻሞሮን ከሥልጣን በማስወገድ የድንበር ዘለል ኩባንያዎቿን ጥቅም የሚያስከብርና ከዋሽንግተን የሚሰጠውን ማናቸውንም መመሪያ ተቀብሎ ተግባራዊ ሊያደርግ በሚችል ኃይል እንዲተካ አድርጋለች ። ዩናይትድ ስቴትስ በተለያዩ ጊዜያት በኒካራጓ ውስጥ በተደረጉ የፖለቲካ ሽኩቻዎች ስውር በሆነ መንገድ በመጠቀምና በጠብመንጃ አፈሙዝ በማስገደድ የኒካራጓን ሕዝብ ስትጨቁንና ስትመዘብር ቆይታለች ። ዳሩ ግን በ1917 የሩሲያ ታላቁ የጥቅምት አብዮት በድል አድራጊነት መከሰት በቅኝ ግዛትና በእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ሥርዓት ሥር በመማቀቅ ላይ የሚገኙ ሕዝቦችን የትግል ስሜት በመቀስቀስ የኒካራጓ አርበኞችንም የትግል ወኔ ያነሣሣና ለመሥዋዕትነት እንዲዘጋጁ ያደረገ ክስተት ሆነ ።

በዚህም መሠረት የመጀመሪያዎቹ የኮምኒስት ቡድኖች ለማቋቋም በመቻላቸው በ1925 የማርክሳዊና የሌበር ፓርቲዎች ተመሠረቱ ። በ1926 መገባደጃ አካባቢ ደግሞ በኤስ ሳንዲኖ የሚመራ የሽምቅ ተዋጊዎች እንቅስቃሴ ተጀመረ ።[11]

“የኒካራጓ ወግ አጥባቂና ሊበራል የፖለቲካ መሪዎች ጀግናና አርበኛ የሆነውን ሕዝባችንን ለመምራት ያልቻሉ ወሮበሎች ፣ ፈሪዎችና መንጋ ከሀዲያን ናቸው። ከወራሪዎች ጋር የተባበሩ የፖለቲካ መሪዎቻችን ከደዉናል ። ሆኖም እኛ ሠራተኞችና ገበሬዎች ከመካከላችን ሀቀኛ መሪዎችን እናፈልቃለን።”[12]

በማለት መሪር ጥላቻውን ይገልፅ በነበረው ሳንዲኖ ይመራ የነበረው የፖለቲካ ቡድን ባከናወናቸው የማንቃትና የማደራጀት ጥረት በአጭር ጊዜ ውስጥ ሕዝባዊ መሠረት ያለው ኃይል ሊሆን ቻለ ። የብዙኃን ኒካራጓውያንንም ድጋፍና አመኔታ ለመቀዳጀት በመቻሉ በዩናይትድ ስቴትስ ይታገዝ ከነበረው የኒካራጓ መንግሥት ሠራዊት ጋር ባደረጋቸው ፍልሚያዎች የበላይነትን እየተቀዳጀ መጣ ። ይህም የእርነት እንቅስቃሴ ግንባር የዩናይትድ ስቴትስ ወታደሮች በአስቸኳይ ኒካራጓን ለቀው እንዲወጡ ማስጠንቀቂያ አዘል ጥሪውን አስተላለፈ ። ይህም ጥሪ በመላው የላቲን አሜሪካ ሕዝቦች ዘንድ ተቀባይነትና ሁሉን አቀፍ ድጋፍ ተቀዳጀ ። ሳንዲኖና ተከታዮቹም ትግላቸውን በማጠናከር ከፍተኛ መሥዋዕትነት የጠየቁ ፍልሚያዎችን በዩናይትድ ስቴትስ ከሚታገዙ የኒካራጓ መንግሥት ወታደሮች ጋር ማድረጋቸውን ቀጠሉ ። ከኒካራጓ አርበኞች የማይበገር ወታደራዊ ተጋድሎና በዓለም ሕዝብ ዘንድ ያላሰለሰ ተቃውሞ የደረሰባት ዩናይትድ ስቴትስ ወታደሮቿን በጥር 1933 ኒካራጓን ለቀው እንዲወጡ አደረገች ። በዚሁ ዓመት የካቲት ወር በሳንዲኖና በኒካራጓ መንግሥት መካከል የስምምነት ውል ተፈረመ ።[13]

ሳንዲኖ ከስምምነቱ በስተጀርባ ተንኮል ያዘለ ሴራ መኖሩን በውል ለመገንዘብ አልቻለም ነበር ። ከዚህም የተነሣ በሳንዲኖና ተከታዮቹ ላይ ከፍተኛ የሆነ አደጋ አንዣበበ ። ይኸው ሴራ ተግባራዊ ከመሆኑ ጥቂት ቀናት በፊት ለዚህ ዐቢይ ተልዕኮ መሪነት በዩናይትድ ስቴትስ ተመልምሎ የነበረውና የኒካራጓ ብሔራዊ ዘብ ዋና አዛዥ አናስታሲዮ ሳሞዛ ታማኝ መኮንኖቹን በድብቅ አሰባስቦ ባደረገው ንግግር ፣

በኒካራጓ የዩናይትድ ስቴትስ አምባሳደር አርተር ብሌስ ሌን ሳንዲኖ ሰላምን አደፍራሽ በመሆኑ እንዲወገድ መንግሥታቸው የሚሻና ለዚህም ተግባር ማከናወኛ የሚውል ማናቸውንም ዓይነት ዕርዳታ ዩናይትድ ስቴትስ ለመስጠት ሙሉ ፈቃደኛና ዝግጁ መሆኗን ገልፀውልኛል ።[14]

ሲል አስታውቋቸው ነበር ። ሳሞዛና ግብረ አበሮቹ ከአርተር ብሌስ ሌን በተገባላቸው ቃል ኪዳንና በተሰጣቸው መመሪያ መሠረት ለእናት ሀገሩ ቀናዒና ለኒካራጓ ሕዝብ ከጭቆናና ምዝበራ ነፃ መውጣት ይታገል የነበረውን ሳንዲኖ ቤተ መንግሥት ለግብዣ ከተጠራ በኋላ በመያዝ ሊገድሉት ቻሉ ። በሳንዲኖ ግርማ ዙሪያ ተሰባስበው ይታገሉ የነበሩ አያሌ ኒካራጓውያንም እየታደኑ ኢሰብአዊ በሆነ ሁኔታ ተጨፈጨፉ ። በዩናይትድ ስቴትስ የሚታገዘው የሳሞዛ መስተዳድርም ያለተቀናቃኝ ሥልጣን ከጨበጠ በኋላ የኒካራጓን በር ለዩናይትድ ስቴትስ ድንበር ዘለል ኩባንያዎች በመክፈት የሀገሪቱን ንብረትና የሕዝቡን ጉልበት መመዝበሩንና ማስመዝበሩን ተያያዘው።

ከሳሞዛ ሥልጣን መያዝ በኋላም በኒካራጓ ድንበሮች ላይ መሽገው በተጠንቀቅ ላይ የነበሩት የዩናይትድ ስቴትስ የባሕር ኃይል ወታደሮች ወደ ሀገራቸው ተመለሱ። ይህም ሊሆን የቻለው የዩናይትድ ስቴትስን ድንበር ዘለል ኩባንያዎች ጥቅም ሊያስከብር የሚችል መንግሥት በኒካራጓ ለመቋቋም በመቻሉ ነበር ።

የሳሞዛ ቤተሰብም ከ1933 ጀምሮ የትውልድ ሀረጉን እየቆጠረ ከሥልጣን ላይ በመፈናጠጥ በኒካራጓ ሕዝብ ላይ የፈላጭ ቆራጭ አገዛዙን ለግማሽ ምዕት ዓመት ያህል አስፍኖ ቆይቷል ። የሳሞዛ ቤተሰብ በኒካራጓ ሥልጣን እንዲይዝ ከፍተኛ እገዛ ያደረገችው ዩናይትድ ስቴትስ በኒካራጓ የኢኮኖሚና የፖለቲካ የበላይነት ተቀዳጅታ ቆይታለች ። በተለይም ከ1909–1979 ዓመታት በነበረው ጊዜ ውስጥ ኒካራጓ የነበራት ነፃነት የይስሙላ ነበር ። ከዚህም የተነሣ የሀገሪቱን አመራር ሙሉ በሙሉ ይቆጣጠሩ የነበሩት የዩናይትድ ስቴትስ ድንበር ዘለል ኩባንያዎች ነበሩ ማለት ይቻላል ። የሳሞዛ አምባገነናዊ አገዛዝም በኒካራጓ ሕዝብ ጫንቃ ላይ ለብዙ ዓመታት ሊንሠራፋ የቻለው በዩናይትድ ስቴትስ በተደረገለት ድጋፍ ነበር ።

የዩናይትድ ስቴትስ ድንበር ዘለል ኩባንያዎች ወደ ኒካራጓ መግባት የጀመሩት በያዝነው ምዕት ዓመት መግቢያ ላይ ሲሆን በዚህም መሠረት በ1909 የዩናይትድ ስቴትስ የውሃ ላይ ጉዞ ኩባንያ በሙዝ ሀገሮች* ውስጥ የሚፈሱ ወንዞችን በቁጥጥራቸው ሥር በማድረግ የትራንስፖርት አገልግሎቶችንም ያዙ ። ብሉፊልድ ከምትባለው ከተማ በስተሰሜን በኩል ደግሞ ሌላው የዩናይትድ ስቴትስ ኩባንያ እጅግ ሰፊ በሆነ መሬት ላይ የሙዝ ተክል እርሻ ያከናውን ነበር ። ከዚሁ ሥፍራ ወደ ሰሜን ራቅ ብሎ ደግሞ የአሜሪካን የእንጨት መሰንጠቂያ ኩባንያ በ8,000 ካሬ ማይልስ ቦታ ላይ የነበሩ ዛፎችን የመጨፍጨፍ ሙሉ መብት ተሰጥቶት ነበር ። ሌሎችም የዩናይትድ ስቴትስ ኩባንያዎች በኒካራጓ ልዩ ልዩ ቦታዎች የሚገኙ ማዕድናትን በመቆፈር ይጠቀሙ ነበር። በፓስፊክ ዉቅያኖስ ላይ የምትገኘውን የኮሮንቶን ወደብ እንቅስቃሴም የሚቆጣጠረው ሌላው የዩናይትድ ስቴትስ ኩባንያ ነበር ። ግለሰብ አሜሪካውያንም ከእንግሊዞች ፣ ከጀርመኖችና ከሌሎችም አውሮፓውያን ሞኖፖሊስቶች ጋር በመሆን ስፋት ያለው የቡና ተክል መሬት የግላቸው አድርገው ተጠቅመዋል። በዚህም መሠረት ከ1909 ጀምሮ የሳንዳኒስታ አብዮት በአሸናፊነት እስከወጣበት ጊዜ ድረስ ቡና ፣ ወርቅ ፣ እንጨትና ሙዝ

* በላቲን አሜሪካ ውስጥ ሙዝ በብዛት አብቃይ ለሆኑ ሀገሮች የተሰጠ ስም ሲሆን ይህም ኮስታሪካን ፣ ሆንዱራስን ፣ ጓቴማላንና ፓናማን ያጠቃልላል ።

በ1926 ደግሞ ዩናይትድ ስቴትስ እንደገና ባደረገችው ወታደራዊ ወረራ ቻሞሮን ከሥልጣን በማስወገድ የድንበር ዘለል ኩባንያዎቿን ጥቅም የሚያስከብርና ከዋሽንግተን የሚሰጠውን ማናቸውንም መመሪያ ተቀብሎ ተግባራዊ ሊያደርግ በሚችል ኃይል እንዲተካ አድርጋለች ። ዩናይትድ ስቴትስ በተለያዩ ጊዜያት በኒካራጓ ውስጥ በተደረጉ የፖለቲካ ሽኩቻዎች ስውር በሆነ መንገድ በመጠቀምና በጠብመንጃ አፈሙዝ በማስገደድ የኒካራጓን ሕዝብ ስትጨቁንና ስትመዘብር ቆይታለች ። ዳሩ ግን በ1917 የሩሲያ ታላቁ የጥቅምት አብዮት በድል አድራጊነት መከሰት በቅኝ ግዛትና በእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ሥርዓት ሥር በመማቀቅ ላይ የሚገኙ ሕዝቦችን የትግል ስሜት በመቀስቀስ የኒካራጓ አርበኞችንም የትግል ወኔ ያነሣሣና ለመሥዋዕትነት እንዲዘጋጁ ያደረገ ክስተት ሆነ ።

በዚህም መሠረት የመጀመሪያዎቹ የኮምኒስት ቡድኖች ለማቆጥቆጥ በመቻላቸው በ1925 የማርክሳዊና የሌበር ፓርቲዎች ተመሠረቱ ። በ1926 መገባደጃ አካባቢ ደግሞ በኤስ ሳንዲኖ የሚመራ የሽምቅ ተዋጊዎች እንቅስቃሴ ተጀመረ ።[11]

"የኒካራጓ ወግ አጥባቂና ሊበራል የፖለቲካ መሪዎች ጀግናና አርበኛ የሆነውን ሕዝባችንን ለመምራት ያልቻሉ ወርበሎች ፣ ፈሪዎችና መንጋ ከሀዲያን ናቸው ። ከወራሪዎች ጋር የተባበሩ የፖለቲካ መሪዎቻችን ከደውናል ። ሆኖም እኛ ሠራተኞችና ገበሬዎች ከመካከላችን ሀቀኛ መሪዎችን እናፈልቃለን ።"[12]

በማለት መሪር ጥላቻውን ይገልፅ በነበረው ሳንዲኖ ይመራ የነበረው የፖለቲካ ቡድን ባከናወናቸው የማንቃትና የማደራጀት ጥረት በአጭር ጊዜ ውስጥ ሕዝባዊ መሠረት ያለው ኃይል ሊሆን ቻለ ። የብዙኃን ኒካራጓውያንንም ድጋፍና እመኔታ ለመቀዳጀት በመቻሉ በዩናይትድ ስቴትስ ደጋፊ ከነበረው የኒካራጓ መንግሥት ሠራዊት ጋር ባደረጋቸው ፍልሚያዎች የበላይነትን እየተቀዳጀ መጣ ። ይህም የአርነት እንቅስቃሴ ግንባር የዩናይትድ ስቴትስ ወታደሮች በአስቸኳይ ኒካራጓን ለቀው እንዲወጡ ማስጠንቀቂያ አዘል ጥሪውን አስተላለፈ ። ይህም ጥሪ በመላው የላቲን አሜሪካ ሕዝቦች ዘንድ ተቀባይነትና ሁሉን አቀፍ ድጋፍ ተቀዳጀ ። ሳንዲኖና ተከታዮቹም ትግላቸውን በማጠናከር ከፍተኛ መሥዋዕትነት የጠየቁ ፍልሚያዎችን በዩናይትድ ስቴትስ ከሚታገዙ የኒካራጓ መንግሥት ወታደሮች ጋር ማድረጋቸውን ቀጠሉ ። ከኒካራጓ አርበኞች የማይበገር ወታደራዊ ተጋድሎና በዓለም ሕዝብ ዘንድ ያላሰለሰ ተቃውሞ የደረሰባት ዩናይትድ ስቴትስ ወታደሮቿን በጥር 1933 ኒካራጓን ለቀው እንዲወጡ አደረገች ። በዚሁ ዓመት የካቲት ወር በሳንዲኖና በኒካራጓ መንግሥት መካከል የስምምነት ውል ተፈረመ ።[13]

ሳንዲኖ ከስምምነቱ በስተጀርባ ተንኮል ያዘለ ሴራ መኖሩን በውል ለመገንዘብ አልቻለም ነበር ። ከዚህም የተነሣ በሳንዲኖና ተከታዮቹ ላይ ከፍተኛ የሆነ አደጋ አንዣበበ ። ይኸው ሴራ ተግባራዊ ከመሆኑ ጥቂት ቀናት በፊት ለዚህ ዐቢይ ተልዕኮ መሪነት በዩናይትድ ስቴትስ ተመልምሎ የነበረውና የኒካራጓ ብሔራዊ ዘብ ዋና አዛዥ አናስታሲዮ ሳሞዛ ታማኝ መኮንኖቹን በድብቅ አሰባስቦ ባደረገው ንግግር ፣

በኒካራጓ የዩናይትድ ስቴትስ አምባሳደር አርተር ብሌስ ሊን ሳንዲኖ ሰላምን አደፍራሽ በመሆኑ እንዲወገድ መንግሥታቸው የሚሻና ለዚህም ተግባር ማከናወኛ የሚውል ማናቸውንም ዓይነት ዕርዳታ ዩናይትድ ስቴትስ ለመስጠት ሙሉ ፈቃደኛና ዝግጁ መሆኗን ገልፀውልኛል ።[14]

ሲል አስታውቋቸው ነበር ። ሳሞዛና ግብረ አበሮቹ ከአርተር ብሌስ ሌን በተገባላቸው ቃል ኪዳንና በተሰጣቸው መመሪያ መሠረት ለእናት ሀገሩ ቀናዒና ለኒካራጓ ሕዝብ ከጭቆናና ምዝበራ ነፃ መውጣት ይታገል የነበረውን ሳንዲኖ ቤተ መንግሥት ለግብዣ ከተጠራ በኋላ በመያዝ ሊገድሉት ቻሉ ። በሳንዲኖ ዓርማ ዙሪያ ተሰባስበው ይታገሉ የነበሩ እያሌ ኒካራጓውያንም እየታደኑ ኢሰብአዊ በሆነ ሁኔታ ተጨፈጨፉ ። በዩናይትድ ስቴትስ የሚታገዘው የሳሞዛ መስተዳድርም ያለተቀናቃኝ ሥልጣን ከጨበጠ በኋላ የኒካራጓን በር ለዩናይትድ ስቴትስ ድንበር ዘለል ኩባንያዎች በመክፈት የሀገሪቱን ንብረትና የሕዝቡን ጉልበት መመዝበሩንና ማስመዝበሩን ተያያዘው ።

ከሳሞዛ ሥልጣን መያዝ በኋላም በኒካራጓ ድንበሮች ላይ መሽገው በተጠንቀቅ ላይ የነበሩት የዩናይትድ ስቴትስ የባሕር ኃይል ወታደሮች ወደ ሀገራቸው ተመለሱ ። ይህም ሊሆን የቻለው የዩናይትድ ስቴትስን ድንበር ዘለል ኩባንያዎች ጥቅም ሊያስከብር የሚችል መንግሥት በኒካራጓ ለመቋቋም በመቻሉ ነበር ።

የሳሞዛ ቤተሰብም ከ1933 ጀምሮ የትውልድ ሀረጉን እየቆጠረ ከሥልጣን ላይ በመፈናጠጥ በኒካራጓ ሕዝብ ላይ የፈላጭ ቆራጭ አገዛዙን ለግማሽ ምዕት ዓመት ያህል አስፍኖ ቆይቷል ። የሳሞዛ ቤተሰብ በኒካራጓ ሥልጣን እንዲይዝ ከፍተኛ እገዛ ያደረገችው ዩናይትድ ስቴትስ በኒካራጓ የኢኮኖሚና የፖለቲካ የበላይነት ተቀዳጅታ ቆይታለች ። በተለይም ከ1909–1979 ዓመታት በነበረው ጊዜ ውስጥ ኒካራጓ የነበራት ነፃነት የይስሙላ ነበር ። ከዚህም የተነሣ የሀገሪቱን አመራር ሙሉ በሙሉ ይቆጣጠሩ የነበሩት የዩናይትድ ስቴትስ ድንበር ዘለል ኩባንያዎች ነበሩ ማለት ይቻላል ። የሳሞዛ አምባገነናዊ አገዛዝም በኒካራጓ ሕዝብ ጫንቃ ላይ ለብዙ ዓመታት ሊንሠራፋ የቻለው በዩናይትድ ስቴትስ በተደረገለት ድጋፍ ነበር ።

የዩናይትድ ስቴትስ ድንበር ዘለል ኩባንያዎች ወደ ኒካራጓ መግባት የጀመሩት በያዝነው ምዕት ዓመት መግቢያ ላይ ሲሆን በዚህም መሠረት በ1909 የዩናይትድ ስቴትስ የውሃ ላይ ጉዞ ኩባንያ በሙዝ ሀገሮች* ውስጥ የሚፈሱ ወንዞችን በቁጥጥራቸው ሥር በማድረግ የትራንስፖርት አገልግሎቶችንም ያዙ ። ብሉፊልድ ከምትባለው ከተማ በስተሰሜን በኩል ደግሞ ሌላው የዩናይትድ ስቴትስ ኩባንያ እጅግ ሰፊ በሆነ መሬት ላይ የሙዝ ተክል እርሻ ያከናውን ነበር ። ከዚሁ ሥፍራ ወደ ሰሜን ራቅ ብሎ ደግሞ የአሜሪካን የእንጨት መሰንጠቂያ ኩባንያ በ8,000 ካሬ ማይልስ ቦታ ላይ የነበሩ ዛፎችን የመጨፍጨፍ ሙሉ መብት ተሰጥቶት ነበር ። ሌሎችም የዩናይትድ ስቴትስ ኩባንያዎች በኒካራጓ ልዩ ልዩ ቦታዎች የሚገኙ ማዕድናትን በመቆፈር ይጠቀሙ ነበር ። በፓስፊክ ዉቅያኖስ ላይ የምትገኘውን የኮሮንቶን ወደብ እንቅስቃሴም የሚቆጣጠረው ሌላው የዩናይትድ ስቴትስ ኩባንያ ነበር ። ግለሰብ አሜሪካውያንም ከእንግሊዞች ፣ ከጀርመኖችና ከሌሎችም አውሮፓውያን ሞኖፖሊስቶች ጋር በመሆን ስፋት ያለው የቡና ተክል መሬት የግላቸው አድርገው ተጠቅመዋል ። በዚህም መሠረት ከ1909 ጀምሮ የሳንዳኒስታ አብዮት በአሸናፊነት እስከወጣበት ጊዜ ድረስ ቡና ፣ ወርቅ ፣ እንጨትና ሙዝ

* በላቲን አሜሪካ ውስጥ ሙዝ በብዛት አብቃይ ለሆኑ ሀገሮች የተሰጠ ስም ሲሆን ይህም ኮስታሪካን ፣ ሆንዱራስን ፣ ጓቲማላንና ፓናማን ያጠቃልላል ።

የሚመረትባቸውና የኒካራጓ የውጭ ገቢ ምንጮች የሆኑ የኢኮኖሚ አውታሮች በአብዛኛው በዩናይትድ እስቴትስ ኩባንያዎች ተይዘው ነበር ።[15] የዩናይትድ እስቴትስ መንግሥትም በኒካራጓ ውስጥ ሙአለንዋይ የነበራቸው ካፒታሊስቶች ጥቅም እንዳይደፈረጥ ከስውር ሴራ ጀምሮ እስከ ግልጽ ወረራ ድረስ በማድረግ የሀገሪቱን ሕልውና ሲፈታተን ቆይቷል ።

የቀድሞው የዩናይትድ እስቴትስ ፕሬዚዳንት ዊልያም ሐዋርድ ታፍት ይህንኑ አስመልክተው ባሰሙት ንግግር ፣ «የእኛ የውጪ ፖሊሲ የተቀረፀው በሌሎች ሀገሮች በሥራ ላይ የምናውለው ሙአለንዋይ ለማትረፍ እንዲችልና ኩባንያዎቻችንም አስተማማኝ ዋስትና እንዲኖራቸው ፈጣን የሆነ እርምጃ ለማድረግ በሚያስችል ሁኔታ ነው»[16] ብለዋል ። በዚህም መሠረት በኒካራጓ ውስጥ ከፍተኛ ካፒታል በማንቀሳቀስ እጅግ የከፋና የረቀቀ ምዝበራና ጭቆና ትፈፅም የነበረችው ዩናይትድ እስቴትስ ከ1909 ጀምሮ የባሕር ኃይሏን ከኒካራጓ ድንበሮች ላይ በማስፈር በሀገሪቱ ፖለቲካ ውስጥ የጎላ ሚና ለመጫወት ችላለች ። ዩናይትድ እስቴትስ በኒካራጓ የነበራት ጥቅም ምን ያህል ከፍተኛ እንደሆን ከሚጠቁሙ ማስረጃዎች መካከል "በ1971 በላቲን አሜሪካ ከነበረው 717 ቢሊዮን ዶላር የዩናይትድ እስቴትስ ሙአለንዋይ ውስጥ ከ215 ቢሊዮን ዶላር በላይ የሚሆነው በኒካራጓ ውስጥ እንደነበር መጥቀሱ በቂ ነው ።"[17]

የሳሞዛ የቤተሰብ አገዛዝ በዩናይትድ እስቴትስ እየታገዘ የብዝበዛና የጭቆና አገዛዙን እጅግ በከፋ ሁኔታ ቢያካሂድም ሰፊው የኒካራጓ ሕዝብ አሜን ብሎ አልተገዛም ። ሥርዓቱን በመታገል በአያሌ የትግል መስኮች ከፍተኛ መሥዋዕትነት ከፍሏል ።

የሳሞዛን መንግሥት ተቃዋሚ ከነበሩ የፖለቲካ ድርጅቶች መካከል በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀሰው በአብዛኛው ወጣት ወዛደሮችና ከ1934 የሳሞዛ ኢሰብአዊ ጭፍጨፋ ያመለጡ የሳንዲኖ ተከታዮች የሚገኙበትና በ1961 የተመሠረተው የሳንዲኒስታ ብሔራዊ የአርነት ግንባር[18] ነበር ። ይህም የፖለቲካ ቡድን በሳሞዛ ቤተሰብ አምባገነናዊ አገዛዝ በደረሰበት ፖለቲካዊ ተጽዕኖ የተነሣ ትግሉን በይፋ ለማከናወን ባለመቻሉ ሥራውን በኅቡዕ ማካሄዱን መረጠ ። ቀስ በቀስም ሕዝባዊ ድጋፍና መሠረት እያገኘ መጣ ። ባካሄዳቸውም የደፈጣ ውጊያዎች የትጥቅ ትግል ልምድና የውጊያ ብቃት ለመቀዳጀት በቃ ።

በኒካራጓ የሚገኙ ተራማጅ ግለሰቦችም ሆኑ ቡድኖች የዚህን ግንባር ዓላማ ተቀብለው ተግባራዊ አስተዋጽኦ በማድረግ የትግል አጋርነታቸውን አረጋገጡ ። ከሳንዲኒስታ የአርነት ግንባር ጋር ከተቀላቀሉት የፖለቲካ ቡድኖች አንዱ የኒካራጓ ሶሻሊስት ፓርቲ ይገኛል ። በዚህም መሠረት ከ1974 ጀምሮ ይኸው የአርነት ግንባር ከሳሞዛ አምባገነናዊ መንግሥት ጋር ግልጽ የሆነ የትጥቅ ትግል ማካሄዱን ቀጠለ ። ይህም ተራማጅ እንቅስቃሴ ዩናይትድ እስቴትስ የኒካራጓን ገበሬዎችና የመላውን ሕዝብ ትግል ለማፈን የምታከናውነውን ድብቅ ሴራ እንድታቆም በተለያዩ አጋጣሚዎች በይፋ አስታወቀ ። በወቅቱም 423 አሜሪካውያን በአማካሪነት ስም በኒካራጓ ውስጥ የስለላና ፀረ—የሽምቅ ውጊያ ተግባራትን ሲያከናውኑ ፣ ዩናይትድ እስቴትስም ለሳሞዛ መንግሥት የምትሰጠውን ዕርዳታ ከፍ አደረገች ። በዩናይትድ እስቴትስ የበላይ ተቆጣጣሪነት የሚመሩት ዓለምአቀፍ ድርጅቶች ማለትም ዓለምአቀፍ የልማት ባንክ ፣ ዓለምአቀፍ የልማት ድርጅትና ሌሎችም የገንዘብ ድርጅቶች ፣ በዩናይትድ እስቴትስ ፣ ጃፓን ፣ ካናዳ ምዕራብ ጀርመን ፣ እስፓኝና እሥራኤል ውስጥ የሚገኙ የግል የንግድ ባንኮች ሁሉ ለሳሞዛ መንግሥት የሚሰጡትን የገንዘብ "ዕርዳታ" እጅግ አሳድገው ነበር ። በ1971 ኒካራጓ ከዩናይትድ እስቴትስ ከምታገኘው የጦር መሣሪያ ዕርዳታ በተጨማሪ ከእስፓኝ ልዩ ልዩ የጦር አውሮፕላኖች አግኝታ ነበር ። በኒካራጓ የነበረውን የውጭ ካፒታል 80% የሚቆጣጠሩት በኒካራጓ ውስጥ ሙአለንዋይ የነበራቸው 59 የዩናይትድ እስቴትስ ድንበር ዘለል ኩባንያዎች ነበሩ ። ከሁሉም በላይ ደግሞ ሳሞዛ የኒካራጓን ብሔራዊ ሀብትና የዓለም አቀፍና ብሔራዊ የትራንስፖርት አውታሮችን 95% በቁጥጥሩ ሥር አውሎ ነበር ። ለም የሆኑ የእርሻ መሬቶችና መሠረታዊ ሸቀጦች ይመረትባቸው የነበሩ ኢንዱስትሪዎችም በሳሞዛና በቤተሰቡ ቁጥጥር ሥር ውለው ነበር ።[19]

የነፃነት እንቅስቃሴ ኃይላትም በኒካራጓ ውስጥ በመካሄድ ላይ የነበረውን በሥልጣን መባለግ ፣ ያለአግባብ መበልፀግና በሳሞዛና በክብር ዘቦቹ መኮንኖች አማካኝነት ይፈጸም የነበረውን ምዝበራ በይፋ በማጋለጥ ትግላቸውንም ይበልጥ ማጠናከር ያዙ ። ታኅሣሥ 29 ቀን 1972 ደግሞ በኒካራጓ እጅግ አደገኛ የሆነ የመሬት መንቀጥቀጥ ተከሰቶ የማናጓን ከተማ 60% በማፈራረሱ ለ14,000 ሰዎች መሞትና 200,000 ሰዎች ያለመጠጊያ መቅረት ምክንያት ሊሆን ቻለ ።[20] ይህንን አስቃቂ አደጋ መቋቋም የሚያስችል ዕርዳታም ከተለያዩ የዓለም አካባቢዎች ለኒካራጓ መንግሥት የተሰጠ ቢሆንም ሰብአዊነት የጐደላቸው ሳሞዛና ግብረአበሮቹ ዕርዳታውን ለግል ጥቅማቸው በማዋል በአደጋው ምክንያት ጉዳት የደረሰባቸውን አካባቢዎች ለማሻሻልም ሆነ ለችግሩ የተጋለጡ ኒካራጓውያንን የመርዳት ሙከራ አላደረጉም ። ሳሞዛ ብቻውን ለዚህ ዕርዳታ ከተሰበሰበው ገንዘብ 250 ሚሊዮን ዶላር በመውሰድ ለግል ጥቅሙ አውሏል ።[21] በዩናይትድ እስቴትስ የበላይ ጠባቂነት የሚመራው የሳሞዛ አምባገነን መንግሥት ያደረሰው ጭቆናና ምዝበራ ያንገፈገፈው የኒካራጓ ሠርቶ አደር ሕዝብ ባደረገው ሕዝባዊ ዐመፅ በጥር ወር 1979 መላዋን ኒካራጓ የለውጥ ማዕበል አጥለቀለቃት ። በዩናይትድ እስቴትስ ይታገዝ የነበረው የሳሞዛ አገዛዝም ሕዝባዊውን ዐመፅ በወታደራዊ ኃይል ለመግታት ከፍተኛ መፍጨርጨር ቢያደርግም ሙከራው አልተሳካም ። ሐምሌ 17 ቀን 1979 ሳሞዛ ኒካራጓን ለቆ ለመውጣት ተገደደ ። የሳንዳኒስታ ኃይላትም ሐምሌ 19 ቀን 1979 ማናጓን በመያዝ ጊዜያዊ ብሔራዊ የተሐድሶ መንግሥት መሠረቱ ።[22]

ሳሞዛና ተከታዮቹ በኒካራጓ ውስጥ እጅግ የከፉ ድርጊቶችን የፈጸሙ ከመሆኑም በላይ የሀገሪቱንም ሀብት በመዝረፍ ሊቀራመቱት ችለዋል ። ሳሞዛ ብቻ ግማሽ ቢሊዮን ዶላር በመዝረፍ የፈረጠጠ ሲሆን የሀገሪቱንም የውጭ ንግድ ገቢ ሙሉ በሙሉ ጠራርጎ በመውሰድ የ1.6 ቢሊዮን ዶላር ባለዕዳ እንድትሆን አድርጓታል ።[23] ሳንዳኒስቶች ድል በተጎናፀፉበት ወቅት የኋላቀርነትና ሰው ሠራሽ ችግሮች ሀገሪቱን አጥለቅልቀዋት ነበር ። በጦርነቱም ወቅት ሳሞዛ ባደረገው ተስፋ የመቁረጥ እርምጃ ቁልፍ የሆኑ የኢኮኖሚ አውታሮች በቦምብ እንዲደበደቡ በማድረግ 80% የሚሆኑት የኢኮኖሚ አውታሮች ከጥቅም ውጭ ሆነዋል ።[24]

የሳሞዛ የቤተሰብ አገዛዝ በተንኮታኮተበት ወቅት በሀገሪቱ ብሔራዊ ባንክ ካዝና 3.5 ሚሊዮን ዶላር ብቻ ቀርቶ ነበር ። በጦርነቱም ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሰው

ከሞቀቱም ሌላ ከሀገሪቱ ሕዝብ አንድ
ሦስተኛ የሚሆነው ከቤት ንብረቱ የተፈና
ቀለ በመሆኑ ኑሮው የተናጋ ነበር ። ሳንዳኒስ
ቶች ድል በተቀዳጁበት ወቅት ከነበሩት 3
ሚሊዮን የሀገሪቱ ዜጎች መካከል 200 ሺህ
ያህሉ ለሥራ አጥነት ፤ 70 % ደግሞ
ለማይምነት የተዳረጉ ነበሩ ።[25]

ሳንዳኒስቶች ሥልጣን ከጨበጡ በኋላ
የሀገሪቱን ደህንነት ከማስከበር በተጓዳኝ
ከፊታቸው የተደቀነው ግዙፍ ተግባር መላ
ውን የኒካራጓ ሕዝብ በማንቃትና በማደራ
ጀት ለሀገር ግንባታ በብቃት እንዲሰለፍ
ማድረግ ነበር ። የብሔራዊ ተሐድሶ መንግ
ሥት ስያሜም የተገኘው ከዚህ እኳያ ነው ።

የሳንዳኒስታ አብዮትና የአድኅሮት ኃይላት ከበባ

በማንኛውም ማኅበራዊ አብዮት ውስጥ
ታሪክን የሚሠራው ሠፊው ሕዝብ ቢሆ
ንም ፣ በእያንዳንዱ ታሪካዊ ወቅት ሕዝቡን
ለዚህ ኃላፊነት እንዲበቃ በግንባር ቀደምት
ነት የማስተባበርና የማደራጀት ብቃት ያላ
ቸው መሪዎች አስፈላጊነትም የማይታለፍ
ነባራዊ ግዴታ ነው ። የኒካራጓ ሕዝብ
ባሳለፋቸው መራራ የፀረ–ኢምፔሪያሊ
ስት የትግል ዘመናት በሀቀኝነት ተሰልፈው
መሥዋዕት የሆኑ መሪዎች የነበሩትን ያህል
የሕዝቡን ጥቅምና ፍላጎት ለግላዊ ጥቅም
የሸጡ ከሀዲ መሪዎችም ነበሩት ። የማያ
ልፍ ሥራ ሠርተው ካለፉ የኒካራጓ ጀግኖች
መካከል አንዱ ሳንዲኖ ነው ። ይህ ጀግና
በዩናይትድ እስቴትስ ኢምፔሪያሊዝምና
በሀገሪቱ የገዢ መደቦች ሲጨቆንና ሲመዘ
በር ለኖረው የኒካራጓ ሕዝብ ተቆርቋሪና
የጋለ ፍቅር የነበረው ስመጥር አርበኛ
ነበር። ሳንዲኖ ለቆመለት ሕዝባዊ ዓላማ
ግንባሩን ሳያጥፍ ሕይወቱን ለሀገሩ ሰፊ
ሕዝብ መሥዋዕት አድርጓል ። የሳንዲኖን
ዓላማ ከግቡ ለማድረስ ቆርጠው የተነሡ
የኒካራጓ ታጋዮች ለግማሽ ምዕት ዓመት
ያህል የሳሞዛን አምባገነናዊ መንግሥት
ሲፋለሙ ቆይተው ሥልጣን ለመያዝ በቅተ
ዋል ። በዚህም ትግል ውስጥ 50,000 ያህል
አርበኞች ሕይወታቸውን አጥተዋል።[26]
ከሳሞዛ አምባገነን አገዛዝ ጋር ሲፋለም
ውድ ሕይወቱን መሥዋዕት ያደረገና የሳን
ዳኒስታ ብሔራዊ የአርነት ግንባር ተባባሪ
መሥራች ካርሎስ ፎንሲካ ስለ ሳንዲኖ
ሲጽፍ "ሳንዲኖ የላቲን አሜሪካ ሕዝቦች
ከዩናይትድ እስቴትስ ኢምፔሪያዝም ጋር
ለሚያካሂዱት የረዥም ዘመናት ትግል ዓይ
ነተኛ ዓርማ ሆኗል"[27] ባለው መሠረት
የኒካራጓ ሕዝባዊ ትግልም በሳንዲኖ መሪነ
ትና ትልም ላይ የተመሠረተ በመሆኑ
የ1979 አብዮትም ሳንዲኒስታ ተብሎ ተሰይ
ሟል ። ሳንዳኒስቶችም ሥልጣን እንደያዙ
የሚከተሉት የዕድገት ፈለግ ሶሻሊዝም
መሆኑን ከማስታወቃቸውም በላይ በርካታ
ሥር ነቀል እርምጃዎችን ወስደዋል ።

ከተወሰዱት ዋና ዋና እርምጃዎችም
ጥቂቶቹ ፤

— የሳሞዛን ብሔራዊ ዘብ ማፍረስ ፤
— የሳሞዛን ሕገ–መንግሥት መሻር ፤
— የሳሞዛንና የአፈቀላጤዎቹን ንብረት
የሕዝብ ማድረግ ፤
— በግል ተይዘው የነበሩ ባንኮችንና ሌሎች
ንም የገንዘብ ድርጅቶች መውረስ ፤
— ማይምነትን የማጥፋት ዘመቻ ዕቅድ
ማወጣትና ተግባራዊ እንቅስቃሴ ማካ
ሄድ ፤
— የውጭ ሀገር ተወላጆች ንብረት የሆኑ
ባንኮችን አሠራር በጥብቅ መቆጣጠር ፤
— ሌሎችንም የኢኮኖሚ ዘርፎች መሬ
ትን፣ የውጭ ንግድ ፣ ወዘተ. በመንግ

ሥት ቁጥጥር ሥር ማዋል ናቸው ።[28]

ከላይ የተጠቀሱት ሥር ነቀል ለውጦች
በመወሰዳቸው በኒካራጓ ለዘመናት ተንሰራ
ፍቶ ያለገደብ የሀገሪቱን ሀብትና የሕዝቡን
ጉልበት ሲመዘብሩ የነበሩትን የውስጥና
የውጭ አድኅሮት የሚያስቆጣ በመሆኑ
እነዚሁ አድኅሮት ኃይላት ከፍተኛ መሥዋ
ዕትነት የተከፈለበትን የኒካራጓን አብዮት
ለመቀልበስ የተቀነባበረ ጥቃት አፋፋሙ ።

የሳሞዛ አምባገነናዊ መንግሥት በሕዝ
ባዊ ዐመፅ እንደተወገደ ሕዝቡ የጨለማው
ዘመን አብሮ ያከተመ መሆኑን በማመን
ዲሞክራሲያዊ የሆነ ማኅበራዊና ኢኮኖሚ
ያዊ ሥርዓት ሰላማዊ በሆነ መንገድ ለመገን
ባት የነበረው ጉጉት እጅግ ከፍተኛ ነበር ።
ዳሩ ግን ከሳንዳኒስታ አብዮት ድል ማብሠር
በኋላ የዩናይትድ እስቴትስ መንግሥት የጥ
ቃት ዘመቻውን በማካሄዱ ትግሉ ይበልጥ
ውስብስብና የላቀ መሥዋዕትነትም የሚጠ
ይቅ ሊሆን ችሏል ።

ዩናይትድ እስቴትስ ከውስጥና በአካባ
ቢው ከሚገኙ አድኃርያን ጋር በመመሳጠር
የኒካራጓን አብዮት በለጋው ለመቅጨት
ከፍተኛ ሙከራ ብታደርግም ፤ በካርተር
አስተዳደር ኒካራጓን በተመለከተ ትከተ
ለው የነበረው ፖሊሲ ሙሉ በሙሉ ጣልቃ
በመግባት በወታደራዊ ኃይል ለማንበርከክ
ሙከራ ማድረግ አልነበረም ። ይህም አቋም
የተወሰደው በቬትናም ተሞክሮ ውጤቱ
ሽንፈት በመሆኑ ነበር ። በቀጥታ ጣልቃ
ከመግባት ይልቅ እንደአማራጭ የታየው
በኒካራጓ ላይ ኢኮኖሚያዊ ፤ ፖለቲካዊና
ዲፕሎማሲያዊ ተጽዕኖ በማድረግ በሥል
ጣን ላይ ያለውን ሕዝባዊ መንግሥት
ቀውስ ውስጥ አስገብቶ በመጨረሻም ለማ
ስወገድ ሙከራ ማድረግ ነበር ። ፕሬዚዳ
ንት ሬጋን ሥልጣን ከጨበጡ በኋላ ግን
የዩናይትድ እስቴትስ የውጪ ፖሊሲ ማን
ኛውንም ኃይል በወታደራዊ ኃይል እስገ
ድዶ የተፈለገውን ውጤት ለመቀዳጀት
ይቻላል ከሚል ዕምነት ላይ መሠረቱን
የጣለ ነበር ። እኚሁ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት
በአንድ ወቅት "ነፃነትን" ለማስከበር
ሲባል ዩናይትድ እስቴትስ ቆራጥና አፋ
ጣኝ የሆኑ እርምጃዎችን በአስቸኳይ ካልወ
ሰደች በስተቀር በአሁኑ ወቅት በላቲን
አሜሪካ ውስጥ በተፈጠሩ ግጭቶች ፍርስራ
ሾች ላይ አዳዲስ ኩባዎች ይመሠረታሉ ።"[29]
በማለት የዕብሪት አቋማቸውን በይፋ
ገልጸዋል ። በዚህም መሠረት በመካከለ
ኛው አሜሪካ ውስጥ ሶሻሊስት የዕድገት
ፈለግን በመከተል ላይ የምትገኘውን ኒካራ
ጓን አቅጣጫ ማስቀየር በዩናይትድ እስቴ
ትስ ፖሊሲ ቀማሪዎች ዘንድ ዋንኛ የመነጋ
ገሪያ ርዕስ ሆነ ። የውስጥ ፀረ–አብዮት
ኃይሎችን አደራጅቶ በማስታጠቅ የሳንዲኒ
ስቶችን አብዮት መውጋት የወቅቱ የትግል
ስልት ሆኖ ተመረጠ ። ለዚህእኩይ ተግባር
በበላይ አስተባባሪነት የተመረጠው ሲ.አይ
ኤ. የተባለው የስለላ ድርጅት ነበር ።
ይኸው የስለላ ድርጅት አስፈላጊውን ዕቅድ
አውጥቶ በአስቸኳይ እንዲያቀርብ ከፕሬዚ
ዳንት ሬጋን መመሪያ ተላለፈለት ፤ ይህም
መመሪያ የፕሬዚዳንቱ መመሪያ ቁጥር 17
ተብሎ የሚታወቅ ነው ።[30] የሲ.አይ.ኤ.
ተግባርም የሳንዲኒስታን መንግሥት በመ
ፈንቀል የሳሞዛን አገዛዝ በቦታው መተካት
ነው ። ለዚህ ተልዕኮ መሳካት በመሣሪያነት
ያገለግሉ ዘንድ በሕዝባዊ ዐመፅ ተሸናፊ
የሆኑትን የሳሞዛን ብሔራዊ ዘብ አባላት
መልምሎ በማሠልጠንና በማስታጠቅ የኒካ
ራጓ ዲሞክራሲያዊ ኃይል (FDN) በሚል
ስም አደራጀ ።[31]

በብዙ አብዮቶች እንደታየው የቀድሞ
የገገር መደብ አባላት ከመንግሥታቸው
ሽንፈት በኋላ አገር እየለቀቁ የመደብ አጋሮ

ከመሞቱም ሌላ ከሀገሪቱ ሕዝብ አንድ
ሦስተኛ የሚሆነው ከቤት ንብረቱ የተፈና
ቀለ በመሆኑ ኑሮው የተናጋ ነበር ። ሳንዳኒስ
ቶች ድል በተቀዳጁበት ወቅት ከነበሩት 3
ሚሊዮን የሀገሪቱ ዜጎች መካከል 200 ሺህ
ያህሉ ለሥራ አጥነት ፤ 70 % ደግሞ
ለማይምነት የተዳረጉ ነበሩ ።[25]

ሳንዳኒስቶች ሥልጣን ከጨበጡ በኋላ
የሀገሪቱን ደህንነት ከማስከበር በተጓዳኝ
ከፊታቸው የተደቀነው ግዙፍ ተግባር መላ
ውን የኒካራጓ ሕዝብ በማንቃትና በማደራ
ጀት ለሀገር ግንባታ በብቃት እንዲሰለፍ
ማድረግ ነበር ። የብሔራዊ ተሐድሶ መንግ
ሥት ስያሜም የተገኘው ከዚህ እሳቤ ነው ።

የሳንዳኒስታ አብዮትና
የአድኅሮት ኃይላት ከበባ

በማንኛውም ማኅበራዊ አብዮት ውስጥ
ታሪክን የሚሠራው ሠፊው ሕዝብ ቢሆ
ንም ፤ በእያንዳንዱ ታሪካዊ ወቅት ሕዝቡን
ለዚህ ኃላፊነት እንዲበቃ በግንባር ቀደምት
ነት የማስተባበርና የማደራጀት ብቃት ያላ
ቸው መሪዎች አስፈላጊነትም የማይታለፍ
ነባራዊ ግዴታ ነው ። የኒካራጓ ሕዝብ
ባሰለፋቸው መራራ የፀረ—ኢምፔሪያሊ
ስት የትግል ዘመናት በሀቀኝነት ተሰልፈው
መሥዋዕት የሆኑ መሪዎች የነበሩትን ያህል
የሕዝቡን ጥቅምና ፍላጎት ለግላዊ ጥቅም
የሸጡ ከሀዲ መሪዎችም ነበሩት ። የማያ
ልፍ ሥራ ሠርተው ካለፉ የኒካራጓ ጀግኖች
መካከል አንዱ ሳንዲኖ ነው ። ይህ ጀግና
በዩናይትድ እስቴትስ ኢምፔሪያሊዝምና
በሀገሪቱ የገዢ መደቦች ሲጨቆንና ሲመዘ
በር ለኖረው የኒካራጓ ሕዝብ ተቆርቋሪና
የጋለ ፍቅር የነበረው ስመጥር አርበኛ
ነበር። ሳንዲኖ ለቆመለት ሕዝባዊ ዓላማ
ግንባሩን ሳያጥፍ ሕይወቱን ለሀገሩ ሰፊ
ሕዝብ መሥዋዕት አድርጓል ። የሳንዲኖን
ዓላማ ከግቡ ለማድረስ ቆርጠው የተነሡ
የኒካራጓ ታጋዮች ለግማሽ ምዕት ዓመት
ያህል የሳሞዛን አምባገነናዊ መንግሥት
ሲፋለሙ ቆይተው ሥልጣን ለመያዝ በቅተ
ዋል ። በዚህም ትግል ውስጥ 50,000 ያህል
አርበኞች ሕይወታቸውን አጥተዋል።[26]
ከሳሞዛ አምባገነን አገዛዝ ጋር ሲፋለም
ውድ ሕይውቱን መሥዋዕት ያደረገና የሳን
ዲኒስታ ብሔራዊ የአርነት ግንባር ተባባሪ
መሥራች ካርሎስ ፎንሲካ ስለ ሳንዲኖ
ሲጽፍ "ሳንዲኖ የላቲን አሜሪካ ሕዝቦች
ከዩናይትድ እስቴትስ ኢምፔሪያዝም ጋር
ለሚያካሂዱት የረዥም ዘመናት ትግል ዓይ
ነተኛ ዓርማ ሆኗል"[27] ባለው መሠረት
የኒካራጓ ሕዝባዊ ትግልም በሳንዲኖ መሪነ
ትና ትልም ላይ የተመሠረተ በመሆኑ
የ1979 አብዮትም ሳንዲኒስታ ተብሎ ተሰይ
ሟል ። ሳንዳኒስቶችም ሥልጣን እንደያዙ
የሚከተሉት የዕድገት ፈለግ ሶሻሊዝም
መሆኑን ከማስታወቃቸውም በላይ በርካታ
ሥር ነቀል እርምጃዎችን ወስደዋል ።

ከተወሰዱት ዋና ዋና እርምጃዎችም
ጥቂቶቹ ፤

— የሳሞዛን ብሔራዊ ዘብ ማፍረስ ፤
— የሳሞዛን ሕገ—መንግሥት መሻር ፤
— የሳሞዛንና የአፈቀላጤዎቹን ንብረት
የሕዝብ ማድረግ ፤
— በግል ተይዘው የነበሩ ባንኮችንና ሌሎች
ንም የገንዘብ ድርጅቶች መውረስ ፤
— ማይምነትን የማጥፋት ዘመቻ ዕቅድ
ማወጣትና ተግባራዊ እንቅስቃሴ ማካ
ሄድ ፤
— የውጭ ሀገር ተወላጆች ንብረት የሆኑ
ባንኮችን አሠራር በጥብቅ መቆጣጠር ፤
— ሌሎችንም የኢኮኖሚ ዘርፎች መሬ
ትን፤ የውጭ ንግድ ፤ ወዘተ. በመንግ

ሥት ቁጥጥር ሥር ማዋል ናቸው ።[28]

ከላይ የተጠቀሱት ሥር ነቀል ለውጦች
በመወሰዳቸው በኒካራጓ ለዘመናት ተንሰራ
ፍቶ ያለገደብ የሀገሪቱን ሀብትና የሕዝቡን
ጉልበት ሲመዘብሩ የነበሩትን የውስጥና
የውጭ አድኅሮት የሚያስቆጣ በመሆኑ
እነዚሁ አድኅሮት ኃይላት ከፍተኛ መሥዋ
ዕትነት የተከፈለበትን የኒካራጓን አብዮት
ለመቀልበስ የተቀነባበረ ጥቃት አፋፋሙ ።

የሳሞዛ አምባገነናዊ መንግሥት በሕዝ
ባዊ ዐመፅ እንደተወገደ ሕዝቡ የጨለማው
ዘመን አብሮ ያከተመ መሆኑን በማመን
ዲሞክራሲያዊ የሆነ ማኅበራዊና ኢኮኖሚ
ያዊ ሥርዓት ሰላማዊ በሆነ መንገድ ለመገን
ባት የነበረው ጉጉት እጅግ ከፍተኛ ነበር ።
ዳሩ ግን ከሳንዳኒስታ አብዮት ድል ማብሠር
በኋላ የዩናይትድ እስቴትስ መንግሥት የጥ
ቃት ዘመቻውን በማካሄዱ ትግሉ ይበልጥ
ውስብስብና የላቀ መሥዋዕትነትም የሚጠ
ይቅ ሊሆን ችሏል ።

ዩናይትድ እስቴትስ ከውስጥና በአካባ
ቢው ከሚገኙ አድኃርያን ጋር በመመሳጠር
የኒካራጓን አብዮት በለጋው ለመቅጨት
ከፍተኛ ሙከራ ብታደርግም ፤ በካርተር
አስተዳደር ኒካራጓን በተመለከተ ትከተ
ለው የነበረው ፖሊሲ ሙሉ በሙሉ ጣልቃ
በመግባት በወታደራዊ ኃይል ለማንበርከክ
ሙከራ ማድረግ አልነበረም ። ይህም አቋም
የተወሰደው በቬትናም ተሞክሮ ውጤቱ
ሽንፈት በመሆኑ ነበር ። በቀጥታ ጣልቃ
ከመግባት ይልቅ እንደአማራጭ የታየው
በኒካራጓ ላይ ኢኮኖሚያዊ ፤ ፖለቲካዊና
ዲፕሎማሲያዊ ተጽዕኖ በማድረግ በሥል
ጣን ላይ ያለውን ሕዝባዊ መንግሥት
ቀውስ ውስጥ አስገብቶ በመጨረሻም ለማ
ስወገድ ሙከራ ማድረግ ነበር ። ፕሬዚዳ
ንት ሬጋን ሥልጣን ከጨበጡ በኋላ ግን
የዩናይትድ እስቴትስ የውጪ ፖሊሲ ማን
ኛውንም ኃይል በወታደራዊ ኃይል አስገ
ድዶ የተፈለገውን ውጤት ለማቀዳጀት
ይቻላል ከሚል ዕምነት ላይ መሠረቱን
የጣለ ነበር ። እኚሁ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት
በአንድ ወቅት "ነፃነትን" ለማስከበር
ሲባል ዩናይትድ እስቴትስ ቆራጥና አፋ
ጣኝ የሆኑ እርምጃዎችን በአስቸኳይ ካልወ
ሰደች በስተቀር በአሁኑ ወቅት በላቲን
አሜሪካ ውስጥ በተፈጠሩ ግጭቶች ፍርስራ
ሾች ላይ አዳዲስ ኩባዎች ይመሠረታሉ ።"[29]
በማለት የዕብሪት አቋማቸውን በይፋ
ገልጸዋል ። በዚህም መሠረት በመካከለ
ኛው አሜሪካ ውስጥ ሶሻሊስት የዕድገት
ፈለግን በመከተል ላይ የምትገኘውን ኒካራ
ጓን አቅጣጫ ማስቀየር በዩናይትድ እስቴ
ትስ ፖሊሲ ቀማሪዎች ዘንድ ዋንኛ የመነጋ
ገሪያ ርዕስ ሆነ ። የውስጥ ፀረ—አብዮት
ኃይሎችን አደራጅቶ በማስታጠቅ የሳንዲኒ
ስቶችን አብዮት መውጋት የወቅቱ የትግል
ስልት ሆኖ ተመረጠ ። ለዚህ እኩይ ተግባር
በበላይ አስተባባሪነት የተሰመረጠው ሲ.አይ
ኤ. የተባለው የስለላ ድርጅት ነበር ።
ይኸው የስለላ ድርጅት አስፈላጊውን ዕቅድ
አውጥቶ በአስቸኳይ እንዲያቀርብ ከፕሬዚ
ዳንት ሬጋን መመሪያ ተላለፈለት ፤ ይህም
መመሪያ የፕሬዚዳንቱ መመሪያ ቁጥር 17
ተብሎ የሚታወቅ ነው ።[30] የሲ.አይ.ኤ.
ተግባርም የሳንዲንስታን መንግሥት በመ
ፈንቀል የሳሞዛን አገዛዝ በቦታው መተካት
ነው ። ለዚህ ተልዕኮ መሳካት በመሣሪያነት
ያገለግሉ ዘንድ በሕዝባዊ ዐመፅ ተሸናፊ
የሆኑትን የሳሞዛን ብሔራዊ ዘብ አባላት
መልምሎ በማሠልጠንና በማስታጠቅ የኒካ
ራጓ ዲሞክራሲያዊ ኃይል (FDN) በሚል
ስም አደራጀ ።[31]

በብዙ አብዮቶች እንደታየው የቀድሞ
የገዢ መደብ አባላት ከመንግሥታቸው
ሽንፈት በኋላ አገር እየለቀቁ የመደብ አጋሮ

ቻችን ናቸው ወደሚሏቸው መንግሥታት ይኮበልላሉ ወይም እንደየሁኔታው አብዮታዊ ፍርድ ያገኛሉ ። በኒካራጓ ግን በሀገር ውስጥ የነበረው ቡርዧ የሳሞዛን መንግሥት የሚደግፍና የሚፃረር በሚል ከሁለት ተከፍሎ የነበረ በመሆኑ ከሳሞዛ ደጋፊዎች ያፈነገጡ ኃይሎች ሳንዲኒስቶችን የሚደግፉ መስለው ቀርበው ነበር ። ከሳሞዛ ሽንፈት በኋላም በተፈጠረው አመቺ ሁኔታ የብዙኃን የፖለቲካ ድርጅቶች መንቀሳቀስ መቻል ሕጋዊነት ሊኖረው ቻለ ። ይህም በመሆኑ የተወሰኑ የቀድሞ የገገር መደብ አባላት ምንም እርምጃ ሳይወሰድባቸው በኒካራጓ ውስጥ ቆዩ ። ባገኙት አጋጣሚ በመጠቀም ከዩናይትድ እስቴትስ በሚሰጣቸው ሁሉን አቀፍ እገዛ እየተረዱ የኒካራጓ ዲሞክራሲያዊ ኅብረት (ሲ.ዲ.ኤን) የሚባል የውስጥ ፀረ—አብዮት ቡድን መሠረቱ። ይህም ቡድን ከሌሎች ፀረ ሳንዲኒስታ ኃይላት ጋር የትግል አንድነት በመመሥረት የኒካራጓን አብዮት ለመቀልበስ አስፈላጊውን ዝግጅት አከናውኖ ተግባራ ኃይል ሆኖ ወጣ ። ላ ፕሪንሳ የሚባል በየሳምንቱ በመታተም የሚወጣ አድኃሪ ጋዜጣ በማዘጋጀት በኒካራጓ አብዮት ላይ የጎሊና ጦርነቱን ያስተጋባ ጀመር ። የዩናይትድ እስቴትስ መንግሥትም ለግናቸውም ፀረ ሳንዲኒስታ ኃይሎች ዕርዳታ በመስጠት ፈጣን የማጥቃት እርምጃ እንዲወሰድ በማድረግና ለጋ በሆነው የኒካራጓ አብዮት ላይ የማጥቃት ዘመቻውን አካሄደ ። በዚህ ፕሮግራም ውስጥ ተሳታፊ የነበረ አንድ አሜሪካዊ ባለሥልጣን በአንድ ወቅት "በዋሽንግተን በተዘረጋው መርሐ ግብር መሠረት በአሜሪካ ማዕከላዊ የስለላ ድርጅት (ሲ·አይ·ኤ) የሚረዳው የኒካራጓ ሠራዊት በከፍተኛ ደረጃ እየተጠናከረ መጥቶ በ1983 መጨረሻ ላይ ማናጓን በቁጥጥሩ ሥር አድርጎ ሥልጣን እንዲይዝ ለማድረግ ነበር"[32] በማለት ታቅዶ የነበረውን አደገኛ ስልት አጋልጧል ።

በዚህም መሠረት ኮንትራ በመባል የሚታወቁት የኒካራጓ ፀረ አብዮተኞች በ1982 በከፍተኛ ደረጃ ተጠናክረው በሳንዲኒስቶች ላይ ወረራ አካሂደዋል። "የኒካራጓን 'የነፃነት ተዋጊዎች' ኮምኒዝምን መዋጋታቸው ኮንትራ የሚያሰኛቸው ከሆነ እኔም ራሴ ኮንትራ ነኝ"[33] በማለት በይፋ የገለጹት የዩናይትድ እስቴትስ ፕሬዚዳንት ሬጋንም በድብቅም ሆነ በግልፅ ለኮንትራዎች የሚሰጠው ዕርዳታ እንዲጨምር ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል ። በዚህም ኮንትራዎች ኃይላቸውን በማጠናከር በ1983 በሰሜናዊና ደቡባዊ ድንበሮች ፣ በአትላንቲክ ጠረፎች አካባቢና በመካከለኛው የኒካራጓ አምባ ምድር በኩል ሦስት ተከታታይ የማጥቃት ዘመቻዎችን አካሄዱ ።[34]

ዩናይትድ እስቴትስ በኒካራጓ ላይ ያካሄደችው ጥቃት በሦስት ክፍለ ጊዜያት ሊከፈል ይችላል ።

1. ከ1981 ክረምት እስከ 1983 ድረስ ኮንትራ በመባል የሚታወቁት የኒካራጓ ፀረ አብዮተኞች በሆንዱራስና በኮስታሪካ ውስጥ በተዘጋጀላቸው ካምፖች እንዲገለገሉ ከመደረጉም ሌላ የዩናይትድ እስቴትስ የመከላከያ ጉዳይ ሚኒስቴር (ፔንታጎን) በሆንዱራስና በኤልሳልቫዶር ውስጥ ለሎጂስቲክስ የሚያገለግሉ አውታሮችን ዘርግቶላቸዋል ።
2. ከ1983 ክረምት እስከ በልግ ድረስ ደግሞ በሲ.አይ.ኤ. ቁጥጥር ሥር የሆኑት ኮንትራዎች በተደራጁ መልኩ በቡድኖች ተከፋፍለው ወደ ኒካራጓ የግዛት ክልል ሠርገው እንዲገቡ ተደርጓል ። በዚህ ጊዜም የቀድሞው የሲ·አይ·ኤ· ዳይሬክተር ዊልያም ኬይስ 1983 ከመገባደዱ በፊት ኮንትራዎች ድል ይጎናፀፋሉ ሲሉ ተንብየው ነበር ።
3. በ1983 የበልግ ወቅት ደግሞ የቀደሞው የዩናይትድ እስቴትስ ታክቲክ ተቀይሮ ኮንትራዎች በኒካራጓ ላይ የሽብር ድርጊቶችን እንዲፈፅሙ ተደርጎ ነበር ።[35]

የኒካራጓ አብዮተኞች ግን ባደረጉት ቆራጥ ተጋድሎና በከፈሉት መሥዋዕትነት በተለያዩ አቅጣጫዎች የተሰነዘሩባቸውን ጥቃቶች በመከላከል የኒካራጓን አብዮትና ድሎች ለመጠበቅ በቅተዋል ። "ሕዝባዊ ጦርነት" በሚል መፈክር ሥር የተሰባሰበው የኒካራጓ ሰፊ ሕዝብ ባደረገው ንቁ ተሳትፎ በጦር ግንባር በመዋጋትም ሆነ በመሃል ሀገር አብዮቱን በመጠበቅ ከፍተኛ መሥዋዕትነት ከፍሏል ። ሳንዲኒስቶችም በዚህ ወሳኝና አጣዳፊ ወቅት በኒካራጓ ወጣቶች የተገነባ ሕዝባዊ ሠራዊትበመመልመል ፣ በማሠልጠንና በማስታወቅ ለአብዮታዊት እናት ሀገራቸው በቁራጥነት ተሰልፈው መሥዋዕት ለመሆን የተዘጋጁ ዜጎችን በማፍራት ከቋሚ ሠራዊቱ ጐን እሰልፈው የጠላትን ጎራ በማፈራረስ ረገድ የተጫወቱት ሚና ከፍተኛ ነው ። ከዚህ በተጨማሪ ደሀ ገበሬዎችን በማኅበር በማደራጀትና በማስታጠቅ ከፊሉ የግንባታ ተግባራትን እንዲያከናውኑ ከፊሉ ደግሞ አካባቢያቸውን ከፀረ አብዮት ኃይላት እንዲከላከሉ በማድረግ የተወሰደው ርምጃም ቀላል አይደለም ። በማናጓ አካባቢ የሚገኙ የፋብሪካ ሠራተኞችም እንደዚሁ ጠንክረው በምሥራት ትረፍ እየመረቱ የምርት እጥረትን ለማስወገድ ከፍተኛ ጥረት ከማድረጋቸውም በላይ የሀገርን ደህንነት በመጠበቁም ተግባር ሰፊ ተሳትፎ አድርገዋል ።

ይህም በመሆኑ የዩናይትድ እስቴትስ ኢምፔሪያሊዝም ታማኝ አሽንጉሊት የሆነው የኮንትራ ቡድን በማናቸውም ረገድ ያደረጋቸው የማጥቃት ዘመቻዎች ሙሉ በሙሉ ሳይሳኩለት ቀርተዋል ። ከዚህም የተነሣ የቡድኑ እንቅስቃሴ ፣ የኒካራጓን መጠነኛ የግዛት ክልል በመያዝ "የኒካራጓ ጊዜያዊ መንግሥት" በሚል ስያሜ የደፈጣ ውጊያዎችን በማካሄድ ላይ ብቻ ተወስኗ ። በጦር ሜዳ ተደጋጋሚ ሽንፈት የደረሰባቸው የዚሁ ቡድን አባላት በመሃል ሀገር ውስጥ ተሰራጭተው የለየለት የሽብር ፈጠራ ድርጊቶችን ማከናወን ሥራዬ ብለው ተያያዙ ። እነዚህ የሲ.አይ.ኤ. ተልዕኮ ፈጻሚ የሆኑ ሽብር ፈጣሪዎች ፋብሪካዎችን ፣ የኅብረት እርሻዎችን ድልድዮችን በማፍረስ በኒካራጓ ሕዝብና ንብረት ላይ ከፍተኛ ጉዳት አድርሰዋል ። ከመጋቢት ወር 1982 እስከ የካቲት ወር 1984 ድረስ ከ2,500 የሚበልጡ ኒካራጓውያን ለሞቱበት ውጊያ የዩናይትድ እስቴትስ መንግሥት ከ73 ሚሊዮን ዶላር በላይ ወጪ አድርጓል ። በዚሁ ወቅት ጦርነቱ ያስከተለው ቁሳዊ ጉዳት ከ200 ሚሊዮን ዶላር በላይ ይገመታል ።[36] ለዚህ ሁሉ ጥፋት ተጠያቂው የኮንራዎች የበላይ አስተባባሪ የሆነው የዩናይትድ እስቴትስ መንግሥት መሆኑ የሚያጠያይቅ አይደለም ።

የኒካራጓ አብዮት ከተቀጣጠለበት ጊዜ ጀምሮ የዩናይትድ እስቴትስ ኢምፔሪያሊዝም በኒካራጓ ላይ መንግሥታዊ የሽብር ፈጠራ ድርጊቶችን በማካናወን ላይ ይገኛል። ከሆንዱራስና ከኮስታሪካ የገገር መደቦች ጋር በመመሳጠር ሁለቱንም ሀገሮች የሳሞዛ ጀሌዎች ዋንኛ ምሽጎችና የጦር ሠፈሮች አድርጓቸዋል ። "ቢግ ፓይንቲ" እና "ግራናዴር አንድ" ተብለው የሚጠሩና እያሌ የዩናይትድ እስቴትስ የጦር ኃይሎች ተካፋይ የሆኑባቸው የጦር ልምምዶች በሆንዱራስ ውስጥ ተደርገዋል ።[32] ይሁን እንጂ ሳንዲኒስቶች ለሕዝባቸው በሰጡት

በሳልና የሰከነ አመራር የተሰነዘሩት ጥቃቶች በሙሉ ሲከሽፉ ፣ የኮንትራዎች የማሸነፍ ተስፋም ተመናምኗል ።

በ1983 የሲ.አይ.ኤ. ኮማንዶች የኮሮንቶንና ሌሎቹንም የኒካራጓ ወደቦች በፈንጂ በማፈራረስ[38] ያደረሱት ተስፋ የመቁረጥ ጥቃት የሚያመለክተው ኮንትራዎች ሳንዲኒስቶችን በወታደራዊ ኃይል ለማሸነፍ የማይችሉ መሆኑን ነው ። ኮንትራዎች ጠንካራ ኃይል የሌላቸው መሆኑም በተለይ ሲ.አይ.ኤ. ለዩናይትድ እስቴትስ ፕሬዚዳንት በምስጢር ባስተላለፈው ዘገባ “ከእንግዲህ ኮንትራዎች በራሳቸው ሳንዳኒስቶችን በወታደራዊ መስክ ለማሸነፍ አይችሉም”[39] በማለት በገለፀው አቋምና በዩናይትድ እስቴትስ ጋዜጦች በወጣው መረጃ ተገልጿል ። ይሁን እንጂ ፕሬዚዳንት ሬጋን በዚያኑ ወቅት በመማክርት ሸንጎ ስብሰባ ላይ ባሰሙት ንግግር “በማዕከላዊ አሜሪካ የሚገኙ ወዳጆቻችንን በፍጹም የምንክዳቸው አይሆንም ። እነዚህ ወዳጆቻችን ራሳቸውን ከማርክሲስት ሽምቅ ተዋጊዎች መከላከል እንዲችሉ ዋስትና ልንሰጣቸው ይገባል”[40] በማለት አድኃሪ አቋማቸውን አጠናክረው ገልጸዋል ። ስለዚህ በወታደራዊ ኃይል (በተለይ ሕጋዊ መልክ በመስጠት) ውጤቱ ያልሠመረለት የዩናይትድ እስቴትስ መንግሥት የአካባቢውን ሁኔታ እንደገና በመገምገም የተለወጠ ስልት ቀይሶ የኒካራጓን አብዮት በልዩ ልዩ ዘዴ በመፈታተን ላይ ይገኛል ። ይህም ስልት የማዳከም ጦርነት (Low Intensity Warfare) (War of Attrition) በመባል የሚታወቅ ነው ።

የማዳከም ጦርነት — አብዮትን የማኮላሻ ስውር የጦርነት ስልት

ይህ የጦርነት ስልት የዩናይትድ እስቴትስ የጦር ኃይል በኢንዶ ቻይና ከፍተኛ ሽንፈት ከደረሰበት በኋላ በሰሜን አሜሪካ የሚገኙ የፖለቲካ ተንታኞች የሽንፈቱን መንሥኤዎች በመገምገም የመፍትሔ ሐሳብ ከሰጡ በኋላ የተገኘ ነው ። እነዚህ የፖለቲካ ተንታኞችም በላቲን አሜሪካ ውስጥ የተካሄዱ ልዩ ልዩ ጦርነቶችንና ወታደራዊ ስልቶችን አጢነው ከደረሱበት መደምደሚያ ላይ የፕሩሲያው ተወላጅ ካርል ቮን ክሉዝዊትዝ “ጦርነት የፖለቲካ ተቀጥላ ነው”[41] ሲል የሰነዘረው ሐሳብ በአዲሱ እስትራተጂ ውስጥ መታከል እንደአለበት ስምምነት ላይ ደርሰዋል ። ዩናይትድ እስቴትስ እስከ አሁን ባከናወነቻቸው ጦርነቶች ታክቲካዊ ድል የተጎናፀፈች ቢሆንም እስትራቴጅያዊ ሽንፈት የደረሰባት መሆኑን በመግለፅ ወታደራዊ የበላይነት ብቻውን አንድን ኃይል ለማሸነፍ ዋስትና አለመሆኑን አረጋግጠዋል ። “ጉንዳንን በመራጃ ለመግደል መሞከር ዋንኛውን ዓላማ ለማሳካት የሚደረገውን ጥረት ያስተጓጉላል” ሲሉ አስተያየታቸውን ሰንዝረዋል ። እንዲሁም በሦስተኛው ዓለም በሚካሄደው የሕዝቦች እንቅስቃሴ ውስጥ በወታደራዊ ኃይል ጣልቃ መግባት ፣ 1) በሌሎች አካባቢዎች ተዋናይ የመሆን ኃይልን ያዳክማል፣ 2) ዓለም አቀፋዊና ብሔራዊ ፖለቲካዊ ተቃውሞን ከማስከተሉም በላይ በዓለም አቀፍ መድረክም በአጥቂነት ለመሰለፍ የመቻል ኃይልን ከአደጋ ላይ ይጥላል ብለዋል ።[42]

ከዚህም የተነሣ የማዳከም ጦርነት ስልት በኒካራጓ ላይ ለተግባራዊነት የተዘጋጀ ስልት ሆኖ ቀረበ ። የዚህ ጦርነት ዋንኛ ዓላማ የኢኮኖሚ ማዕቀብ በማድረግና በፖለቲካና በዲፕሎማሲ በማግለል በኒካራጓ የሚገኘውን ማኅበረዊ ሁኔታ አናግቶ የሳንዲኒስታ መንግሥት የሕዝቡን መሠረታዊ ጥያቄዎች ለመፍታት እንዳይችል ማድረግና የሳንዲኒስቶችን የመከላከል ኃይል አዳክሞ ለወታደራዊ ጥቃት በቀላሉ እንዲጋለጡ ማመቻቸት ነው ። የማዳከም ጦርነት ይዘት በ1980ዎቹ የዩናይትድ እስቴትስ ፀረ አብዮት እስትራተጂ ረቀቅ ያለ ባሕርይ መላበሱን ያሳያል ።

የማዳከም ጦርነት በተለምዶ በጥቅም ላይ ይውል ከነበረው የጦርነት ዘይቤ እጅግ የተለየ ሲሆን ዓላማውም ፖለቲካዊ ፣ ዲፕሎማሲያዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ ፣ ሥነልቡናዊና ርዕዮተዓለማዊ ወረራዎችን እንደ ቋሚ እስትራተጂ መውሰድ ፣ እንደአስፈላጊነቱም በማፈራረቅ ከወታደራዊ ወረራ ጋር እየአቀናጁ ማካሄድ ነው ። ይህም አቋም ሊወሰድ የቻለው የአብዮታዊ ኃይላት ጥንካሬ የተመሠረተው ከሕዝብ ጋር ካላቸው የቅርብ ቁርኝት በመሆኑ ወታደራዊ ድልን ለመቀዳጀት ከመጣር ይልቅ ፖለቲካዊ ድልን መቀዳጀት የተሻለ ነው ከሚል አቋም የመነጨ ነው ።

የማዳከም ጦርነት ድንገተኛ የሆነ የጦርነት መጋጋም የማይታይበት ሲሆን የሚገኘውም ድል የሚለካው በጦር ሜዳ በወደቁ ሰላባዎች አይደለም ። በዚህ ጦርነት የሚከፈለው መሥዋዕትነትና ዋጋ ዝቅተኛ ሲሆን ግጭቱ ግን የታቀደው ዓላማ ግቡን እስኪመታ ድረስ ሊቀጥል የሚችል ነው ። ይህ ዓይነቱ የማጥቃት ጦርነት ስልት “ጠቅላላ ጦረነት ”በመሆኑ በአብዛኛው ግልፅ ያልሆነ ከመሆኑም ባሻገር ሰላምም ጦርነትም ሙሉ በሙሉ የማይታይበት ሁኔታ ነው ።

በዩናይትድ እስቴትስ አማካኝነት በኒካራጓ ላይ የሚካሄደው የማዳከም ጦርነት የሳንዲኒስታን አመራር ከሕዝቡ በመነጠል ማኅበራዊ መሠረት አሳጥቶ ለማፈን የታለመ ነው ።

ኒካራጓን የማዳከሙ ተግባር በአብዛኛው ያተኮረው የሳንዲኒስታን መንግሥት ተቀናቃኝ የሆኑ ኃይላትን በማደራጀት ፣ በማስታጠቅና በሁሉም መስክ የተቀነባበረ ዕርዳታ በመስጠት ላይ እንደመሆኑ የዩናይትድ እስቴትስ ፕሬዚዳንት ሬጋን የሀገራቸው የመማክርት ሸንጎ ለኮንትራዎች ርዳታ የሚውል በጀት እንዲፈቀድ ባደረጉት ንግግር የኒካራጓ ኮሚኒስቶች ሥልጣን ከያዙ ጀምሮ ጎረቤቶቻቸውን ለማጥቃት ሙከራ በማድረግ ላይ ናቸው ። በማዕከላዊ አሜሪካም ሆነ በሌሎችም የሶቭዬት ኅብረት ወዳጅ የሆኑ ኃይሎች ሥልጣን በያዙባቸው ክልሎች የወረራ ፖሊሲያቸው በኃይል ካልተገታ በስተቀር ሰላም ሊኖር አይችልም ። ይህንን ድርጊት ለሚቃወሙ ኃይሎች ዕርዳታ የምናደርገው እነዚህን ኃይሎች ለመቋቋም ከወታደራዊ ኃይል የተሻለ ሌላ አማራጭ ባለመኖሩ ነው[43] ሲሉ የወራሪነት ፖሊሲአቸውን ይፋ አውጥተዋል ።

እኚሁ “አሜሪካ ለአሜሪካውያን” የሚለውን የሞንሮ ዶክተሪን* አራማጅ የሆኑ ፕሬዚዳንት ኒካራጓ የራሷን ዕድል በራሷ ለመወሰን ያደረገችውን የዕድገት ፈለግ በመቃረን ስለሀገሪቱ ያላቸውን ጥላቻ ሲገ

* የሞንሮ ዶክትሪን 5ኛው የዩናይትድ እስቴትስ ፕሬዚዳንት በነበሩት ጀምስ ሞንሮ ስም የተሰየመ ነው ። ይህም እኚሁ ፕሬዚዳንት በ1823 በዩናይትድ እስቴትስ የመማክርት ሸንጎ ስብሰባ ላይ “ከእንግዲህ የአሜሪካ አህጉሮች የማንም የአውሮፓ ኃይል ቅኝ ግዛት ሊሆኑ አይችሉም ፣ በማንኛውም የአውሮፓ መንግሥት በአሜሪካ አህጉሮች ውስጥ የሚገኙ ሀገሮችን ለመጨቆን ወይም በበላይነት ለመምራት የሚደረግ ሙከራም የሚቆጠረው በዩናይትድ እስቴትስ ላይ እንደተሰነዘረ ጥቃት ነው ።” ሲሉ ከሰነዘሩት ሀሳብ የመነጨ ነው ። ይህ አባባል በወቅቱ የአውሮፓ ኃያላንን መስፋፋት ከአትላንቲክና ከፓስፊክ ውቅያኖሶች እንዳያልፍ ለመገደብ የታለመ ቢመስልም ፣ እየደር ግን እየተጠናከረ ወይም እየተብራራ መጥቶ የዩናይትድ እስቴትስን ተፅዕኖ በአሜሪካ አህጉሮች የበለጠ ለማጠናከር የሚያገለግል ፖሊሲ ሊሆን ችሏል ።

ልጹ ለዩናይትድ እስቴትስ ሕዝብ በቴሌቪዥን ባሰሙት ንግግር “ኒካራጓ በቀላሉ ፈውስ የማይገኝላት የአካባቢውን ሰላም አደፍራሽ የሆነች የካንሰር በሽታ ናት[44] ብለዋል ። በዩናይትድ እስቴትስ የመማክርት ጉባዔ ስብሰባ ላይ ባሰሙት ንግግርም ፣ በአሁኑ ወቅት አጣዳፊ የሆነ እርምጃ ካልወሰድን በስተቀር የኒካራጓ ዛቻ እያደገ መሄዱ ነው ። ከዚህም የተነሣ የመማክርት ሸንጎው ወገናዊነት በተሞላበት መንገድ ሁኔታውን መመልከት ይኖርበታል ። የመማክርት ሸንጎው አማራጮች አሉት ። እነዚህም የነፃነት ተዋጊዎች ከሩሲያ ታንኮችና የጦር መርከቦች ራሳቸውን የሚከላከሉበት ዕርዳታ መስጠት አለበለዚያም የነፃነት ተዋጊዎችን ለኮሚኒስት ጠላቶቻቸው አሳልፎ መስጠት ናቸው ።[45] ሊሉ ኮንትራ የሚባሉትን ወንበዴዎች ዓላማ ያላቸው ለማስመሰል ጥረዋል ። ከዚህም በማያያዝ እጅግ ውሱን የሆነ ቁሳዊና የሰው ኃይል ያላትን ታዳጊ ሀገር በዩናይትድ እስቴትስ የመማክርተ ሸንጎ ስብሰባ ላይ ፣

ኒካራጓ በላቲን አሜሪካ ውስጥ ከሚገኙ ሀገሮች በሙሉ የላቀ ወታደራዊ ኃይል ያላት ሲሆን በሶቭዬት ኅብረትና በኩባ እየታገዘች በአካባቢው የሚገኙ ዲሞክራሲያዊ የሆኑትን አጎራባች መንግሥታት የማስገለበጥ ጥረት በማድረግ ላይ ትገኛለች ። እነዚህ ሁለት ሀገሮችም ኒካራጓን እንደምሽጋቸው በመጠቀም በማዕከላዊ አሜሪካ የማይበገር ኃይል ሆነው ለመውጣት ጥረት እያደረጉ ነው ። ዓላማቸውም ግቡን ከመታ የዩናይትድ እስቴትስ መተላለፊያ የሆነውን በር በመዝጋት በሺህ የሚቆጠሩ ስደተኞች ወደ ሰሜን እንዲሸሹ ያደርጋሉ ። በሺህ የሚቆጠሩ ኩባውያን ፣ ሶቭየቶችና አጠቃላይ ዓለም አቀፍ ሽብርተኞች ከዩናይትድ እስቴትስ ግርጌ በምትገኘው ኒካራጓ ውስጥ መሽገው ለመዋጋት ዝግጁ ሆነዋል[46] በማለት የኒካራጓ ሕጋዊ መንግሥት ህልውናውን ለማስከበርና በሕዝቡ ፈቃድ የዘረጋውን የልማት ትልም ተግባራዊ ለማድረግ ይረዳው ዘንድ ከሶሻሊስት አገሮች የሚያገኘውን ድጋፍ የተዛባ ትርጉም በመስጠት የመማክርት ሸንጎውን ጎትጉተው የ100 ሚሊዮን ዶላር ዕርዳታ ለኮንትራዎች እንዲሰጥ አስወስነዋል ።

በዩናይትድ እስቴትስ የሚገኙ መገናኛ ብዙኃንም ኒካራጓ ፀረ ሰላም አቋም ያላት ሀገር መስላ እንድትታይ ተከታታይ የኀሊና ጦርነት ውርጅብኝ ሲያካሂዱባት ቆይተዋል ። በልዩ ልዩ ታክቲኮች በመጠቀምም የኒካራጓን ሉዓላዊነት ለመድፈር በዩናይትድ እስቴትስ በኩል የተደረገው ሙከራ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ በማናጋትና ዕድገቷንም በመግታት በኩል ያሳደረው ተጽዕኖ በቀላሉ የሚገመት አይደለም ። በተለያዩ የኒካራጓ የግዛት ክልሎች ውስጥ የመሸጉ ፀረ አብዮተኞችም የዩናይትድ እስቴትስ እኩይ ተልዕኮ አስፈጻሚ በመሆን ያደረሱት ጥቃት እጅግ ከፍተኛ ነው ። ይሁን እንጂ የኒካራጓ አብዮት ሕዝባዊ መሠረት ያለው በመሆኑ በቀላሉ አልተበገረም ።

የማዕከላዊ አሜሪካ ሀገሮች የሰላም ጥረትና የዩናይትድ እስቴትስ ተጽዕኖ

የዩናይትድ እስቴትስ መንግሥት ዓለምን በቁጥጥሩ ሥር ለማዋል በሚያደርገው ሙከራ በብዙ የዓለም ክፍሎች ውጥረት እንዳይረግብ ለማድረጉ የኒካራጓ ሁኔታ ብቻ እንኳን ግዙፍ ምሥክር ነው ። በአሁኑ ጊዜ ሉዓላዊነት ባላቸው የማዕከላዊ አሜሪካ ሀገሮች ውስጥ የሚያከናውነው ወታደራዊ ጣልቃ ገብነት ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ጨምሯል ። በአካባቢው የሚገኙ ሀገሮችም እርስ በርስ እንዲተናኰሱና አንዱ በሌላው የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ እንዲገባ ለማድረግ የሚያካሄደው ስውር ደባ የመልካም ጉርብትና አዝማሚያዎች እንዳይኖሩ ደንቃራ ሊሆን ችሏል ። ከዚህም የተነሣ በተለይ ከኮስታሪካ ፣ ከሆንዱራስና ከኤልሳልቫዶር መንግሥታት ጋር በመሆን የኒካራጓ ፀረ አብዮተኞች በግዛታቸው ክልል ውስጥ ተደራጅተው ፣ ሠልጥነውና ታጥቀው የሳንዲኒስታን አብዮት እንዲወጉ በማድረግ ላይ ናቸው ። ይህም ድርጊት በሰላም አብሮ የመኖር መርህን የሚፃረር ከመሆኑም በላይ የአካባቢውን ሰላም በማናጋት በኩል ያሳደረው ሥጋት እጅግ ከፍተኛ ነው ።

የዩናይትድ እስቴትስ መንግሥት በኒካራጓ ላይ ያወጀው ግልፅ ያልሆነ ጦርነትና አካባቢውንም ወደ ጦር ሠፈርነት ለመለወጥ በሚያደርገው ጥረት የተነሣ ከዓለም ሰላም ወዳድ ሕዝቦች ዘንድ ከፍተኛ የሆነ ተቃውሞ አጋጥሞታል ። በተለይ ደግሞ ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከታቸው የማዕከላዊ አሜሪካ ሀገሮች በጥብቅ ኮንነውታል ። እነዚህ ሀገሮች የራሳቸውን ችግሮች ያለ ውጭ ኃይል ተጽዕኖ በራሳቸው ለመፍታት በነጣላም ሆነ በቡድን ጥረት ማድረጋቸው አልቀረም ። ከእነዚህ ሰላም ፈላጊ ኃይሎች ጉልህ ሥፍራ ይዞ የሚገኘው የኮንታዶራ ቡድን በመባል የሚጠራው ነው ።

ኮንታዶራ የሚለው ስያሜ የተሰጠው የቬኔዙዌላ ፣ የኮሎምቢያ ፣ የሜክሲኮና የፓናማ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ከጥር 8-9 1983 ኮንታዶራ ተብላ በምትጠራና ፓናማ ውስጥ በምትገኝ ደሴት ላይ ተሰብስበው በመካከለኛው አሜሪካ ውጥረት እንዲረግብ የጋራ መፍትሔ ለመሻት ውይይት ያደረጉበትን ስብሰባ ምክንያት በማድረግ ነበር ። ስብሰባውም ኢምፔሪያሊስት ኃይሎች በመካከለኛው አሜሪካ የሚያካሂዱት ወታደራዊ ጣልቃ ገብነት እጅግ አስደንጋጭና መገታት ያለበት መሆኑን አንፀባርቋል። የዚህ ቡድን ሐሳብም የኮንታዶራ ቡድን ደጋፊዎች ተብለው በሚታወቁት በአርጀንቲና ፣ በብራዚል ፣ በፔሩና በኡራጓይ ተቀባይነት አግኝቷል ። የኮንታዶራ ቡድን ዓለምአቀፋዊ ይዘት ያለው የትግል አንድነት ያሳየው የአባል ሀገራቱ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ካንኩን (ሜክሲኮ) ውስጥ ስብሰባ ባደረጉበት ወቅት ነበር ። ይህም ስብሰባ ሰላም በመካከለኛው አሜሪካ ሊሰፍን የሚችልበትን መንገድ የሚጠቁም መመሪያ ነድፏል ። በጉባኤው የተነደፈው ረቂቅም የሚከተሉትን ነጥቦች ያካትታል ፣

- በሀገሮች መካከል ጦርነት እንዳይካሄድ መከላከል ፣
- በመካከለኛው አሜሪካ እጅግ በጣም አስፈሪ በሆነ ሁኔታ በመጨመር ላይ የሚገኘውን ወታደራዊ ግንባታ በመቆጣጠር ለመቀነስና ብሎም ለማስወገድ የሚያስችል ስምምነት ላይ መድረስ ፣
- በአካባቢው ሀገሮች መካከል የሚከሰቱ አለመግባባቶችንና ግጭቶችን ሰላማዊ በሆነ መንገድ በመፍታት ጦርነትን አስወግዶ ጤናማ የሆነ ግንኙነትና መተማመን እንዲኖር የሚያደርግ ከሁሉም ሀገሮች የተውጣጣ ኮሚሽን መመሥረት[47] ዋና ዋናዎቹ ናቸው ።

በዚህም መሠረት የኮንታዶራና የቡድኑ ደጋፊ ሀገሮች በላቲን አሜሪካ ውስጥ የተከሰቱ ችግሮች ሰላማዊ በሆነ መንገድ ሊፈቱ

የሚችሉበትን መንገድ ለመቀየስ ተደጋጋሚ ስብሰባዎች በማድረግ ውይይት አካሂደዋል ።

ይህንንም የሰላም ጥሪ የአካባቢው አካል የሆነችው ኒካራጓ በደስታ የምትቀበለው መሆኑን የገለፀች ሲሆን ፣ ቡድኑም ከሳንዳኒስታ መንግሥት ጋር ያለውን የወዳጅነትና የትግል አንድነት ገልጿል ።

የኮንታዶራ ቡድንና ደጋፊዎቹ በአካባቢአቸው ለተከሰቱ ችግሮች ያለምንም የውጭ ኃይል ጣልቃ ገብነት በራሳቸው ፖለቲካዊ መፍትሔ ለመስጠት የሚያደርጉት ጥረት የብዙ ሀገሮችንና ሰላም ወዳድ ሕዝቦችን ትኩረት የሳበ ነው ። ይሁን እንጂ አካባቢውን የራሷ የግዛት ክልል አድርጋ በምትቆጥረው ዩናይትድ እስቴትስ ዘንድ ተቀባይነት አላገኘም ።

በአካባቢው የሳንዳኒስታ አብዮት በአሸናፊነት መውጣትና የሌሎችም ለነፃነታቸው የሚታገሉ ኃይሎች መጠናከር የኢምፔሪያሊስት ኃይላት ሽንፈት የማይቀር መሆኑን ያጋለጠ ጉዳይ ነው ። ይኸው የለውጥ ማዕበል ሥጋት ያሳደረበት የዋሽንግተን አስተዳደር ይህንን ክልል በቁጥጥሩ ሥር ለማዋል እንደ አማራጭ በመውሰድ የተያያዘው በማዕከላዊ አሜሪካ የራሳቸውን የዕድገት ፈለግ በራሳቸው ለመወሰን ቆርጠው በተነሡ ኃይሎች የውስጥ ጉዳይ ቀጥተኛ የሆነ ወታደራዊ ጣልቃ ገብነት መፈጸምን ነው ። ለዚህም የወራሪነት ድርጊት የሚሰጠው ሰበብ "የኮምኒስቶችን ጥቃት" ለመከላከል የሚል ነው ። የኮንታዶራ ቡድን በመካከለኛው አሜሪካ የሚገኘውን ችግር ሰላማዊ በሆነ መንገድ ለመፍታት የሚያደርገው ጥረት በዋሽንግተን ፖሊሲ አራማጆች ዘንድ በበጎ መልኩ አልታየም ። ከዚህም የተነሣ ዩናይትድ እስቴትስ ለቡድኑ አፍአዊ ድጋፍ በመስጠት ውስጥ ውስጡን ግን ያላሰለሰ አፍራሽ ተጽዕኖ በማድረግ ውጤቱ እንዳይሳካ በማድረግ ላይ ነች ። ማናቸውም የኮንታዶራና ደጋፊዎቹ እንቅስቃሴ የዩናይትድ እስቴትስ ተጽዕኖ ሳይደረግበት የቀረ የለም ። ለምሳሌ የቡድኑ መሥራች ስብሰባ በተካሄደበት ወቅት ዩናይትድ እስቴትስ በሆንዱራስ ግዛታዊ ክልል ውስጥ *ቢግ ፓይን* በመባል የሚታወቀውን ወታደራዊ ልምምድ አካሂዳለች ። ጥቂት ቀናት ሰንበት ብላም ከኮስታሪካ ወታደሮች ጋር በመሆን ሌላ ወታደራዊ ልምምድ አካሂዳለች ።[48]

በመካከለኛው አሜሪካ በሚገኙ አድኃሪ መንግሥታት በእጅ አዙር በመጠቀም የአካባቢውን ችግር ለመፍታት በኮንታዶራ ቡድን የተዘጋጀው የካንኩን (ሜክሲኮ) መግለጫ በአባላቱ እንዳይፈረም አደናቅፋለች ። በነሐሴ 1983 በቀድሞው የዩናይትድ እስቴትስ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሄንሪ ኪሲንጀር የሚመራ የኮንታዶራ ቡድን ተፃራሪ ኮሚሽን አቋቁማለች ። ይህም ቡድን በመካከለኛው አሜሪካ የሚገኙ ብሔራዊ የአርነት ኃይሎች እንዳይጠናከሩ በፖለቲካ ፣ በኢኮኖሚና በወታደራዊ መስኮች አስፈላጊውን ሁሉ ጥረት የሚያደርግ ነው[49]

ጥቅምት 5ቀን 1983 ያኮንታዶራ ቡድን አባላትና ሌሎችም በመካከለኛው አሜሪካ የሚገኙ ሀገሮች የአካባቢውን ችግር በሰላም ለመፍታት የሚያስችል የተግባር መመሪያ ፈርመዋል ። ጥቅምት 10 ቀን 1983 ደግሞ ለዚህ ምላሽ የሲ.አይ.ኤ. ቅጥረኞች የሆኑት የኮንትራ ቡድኖች 75% የሚሆነው የኒካራጓ የውጭ ንግድ የሚተላለፍበትን የኮሪንቶን ወደብ በቦምብ ደብድበዋል ።[50]

በ1984 የኮንታዶራ ቡድን በመካከለኛው አሜሪካ የሚገኙ ሀገሮች ሰላምና ትብብር በመካከላቸው ለመፍጠር የሚያስችል የተግባር ዕቅድ በነደፉበት ወቅት እንደዚሁ የዋሽንግተን መስተዳድር በሲ.አይ.ኤ. አማካኝነት ለኮንትራዎች የኒካራጓን ወደቦች እንዲያፈራርሱና ሳንዲኒስቶችንም እንዲገሉ ትዕዛዝና መመሪያ ሰጥቷቸዋል ።[51] ከዚህ በተጨማሪም የኮንታዶራን ቡድን የሰላም ተልዕኮ ለማጨናገፍ ከፍተኛ የጎሊና ጦርነት በመደረግ ላይ ነው ።

የኮሎምቢያው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሲሞን ኮንሶልቪ ይህንኑ አስመልክተው በአንድ ወቅት "አንድ ሚያሚ ከተማ (የዩናይትድ እስቴትስ) ውስጥ የሚገኝ የማስታወቂያ ወኪል የኮንታዶራን ቡድን እንቅስቃሴ ዋጋ አልባ የሚያደርግ የተዛባ ኢንፎርሜሽን (መረጃ) ለማሠራጨት የሚያገለግል 1.8 ሚሊዮን ዶላር የደረሰው መሆኑን አጋልጠዋል ።"[52] ከዚህ በተጨማሪም በቡድኑ ውስጥ የሚገኙ ሀገሮች ርዕዮተዓለማዊ ልዩነትም ለዩናይትድ እስቶትስ ኢምፔሪያሊዝም አፍራሽ ቅስቀሳ አመቺ ሁኔታን ፈጥሯል ። ይሁን እንጂ የሁሉም ሀገሮች የፀረ ቅኝ አገዛዝና የፀረ እጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ አቋም ለአንድነታቸው የፀና መሠረት ሆኖ በመገኘቱ የትግል አንድነታቸው የበለጠ በመጎልበት ላይ ነው ። የኮንታዶራን ቡድን ዕቅድ ትክክለኛነት መላው የዓለም ሰላም ወዳድና የላቲን አሜሪካ ሕዝቦች የሚደግፉት ለመሆኑ በተለያየ መልኩ የትግል አንድነታቸውን ገልጸዋል ። የዩናይትድ እስቴትስ ሕዝብም ሆነ በመማክርት ሸንጎው ውስጥ የሚገኙ አባላት ጭምር የሬጋን መስተዳድር በኒካራጓ የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ መግባትንም ሆነ ባጠቃላይ በማዕከላዊ አሜሪካ ውስጥ የሚያከናውነውን የሽብር ፈጠራ ድርጊት ማውገዝ የሚያመለክተው የኮንታዶራ ቡድን ለአካባቢው ችግር ተግባራዊ ለማድረግ የሚሻው ፖለቲካዊ መፍትሔ ተገቢ መሆኑን ነው ።

የዩናይትድ እስቴትስ መንግሥት በማዕከላዊ አሜሪካ ሀገሮች የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ በመግባት የምታከናውነው የጠብ አጫሪነትና የትንኮሳ ተግባር የኮንታዶራን ቡድንና ደጋፊዎቹንም ሆነ ሌሎችንም በላቲን አሜሪካ የሚገኙ በመብታቸው የመጠቀም ፍላጎት ያላቸው ሀገሮች ከሥጋት ላይ የጣለ ጉዳይ ሆኗል ። ከዚህም የተነሣ ከነሐሴ 7 - 8 ፣ 1987 የኒካራጓ ፣ የጓቲማላ ፣ የሆንዱራስ ፣ የኮስታሪካና የኤልሳልቫዶር ፕሬዚዳንቶች ጓቲማላ ውስጥ ተሰብስበው አካባቢያዊ ሰላምን በማስፈን ረገድ ሰፊ ውይይት አድርገው የሰላም ውል ተፈራርመዋል ። ይህም ውል ከሚያካትታቸው ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ በማዕከላዊ አሜሪካ ውስጥ በሚገኙ መንግሥታትና ተቀናቃኞቻቸው መካከል የተኩስ አቁም ስምምነት እንዲደረግ ፣ አንዱ ሀገር በሌላ ሀገር የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ ከመግባት እንዲቆጠብ ፣ ለፖለቲካ እሥረኞች ምህረት እንዲሰጥ ፣ ብሔራዊ የሰላም ድርድር እንዲደረግና ሌሎችም ዲሞክራሲያዊ እርምጃዎች እንዲወሰዱ የሚሉ ይገኙበታል ።[53]

በጓቲማላ ስምምነት መሠረትም የ13 ሀገሮች የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች በቬንዙዌላ ዋና ከተማ ካራካስ ውስጥ ነሐሴ 23 ቀን 1987 በመገናኘት የጓቲማላ ዕቅድ ተግባራዊ መሆኑን የሚከታተል ኮሚሽን መሥርተዋል ። ኮሚሽኑም የሜክሲኮ ፣ የቬንዙዌላ፣ የኮሎምቢያ ፣ የፓናማ ፣ የአርጀንቲና ፣ የብራዚል ፣ የፔሩና የኡራጓይ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮችንና የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትና የአሜሪካ ሀገሮች ድርጅት (OAS) ዋና ፀሐፊዎችን ወይም እነርሱ የሚወክሏቸውን በአባልነት ያቀፈ ነው ። የማዕከላዊ አሜሪካ ሀገሮችም ሆኑ መላው

የዓለም ሰላም ወዳድ ሕዝቦች የሰላሙ ዕቅድ ተግባራዊነት እንዲፋጠን የበኩላቸውን ጥረት በማድረግ ላይ ቢሆኑም ፡ ዩናይትድ እስቴትስ ዕቅዱ እንዳይሰምር በስውር ከምታደርገው ደባ በተጨማሪ በዚሁ ወቅት ፕሬዚዳንት ሬጋን 270 ሚሊዮን ዶላር ለኮንትራዎች ዕርዳታ እንዲሰጥ የአሜሪካንን የመማክርት ሸንጎ ለማስወሰን በዝግጅት ላይ መሆን መላውን የዓለም ሰላም ወዳድ ሕዝቦች ያስደነቀ ጉዳይ ነበር ።[54] ከዚህም የተነሣ በከንታዶራና ደጋፊዎቹ እንዲሁም በጓቲማላ የሰላም ውል ተፈራራሚዎች የተወጠኑ የሰላም ዕቅዶች ውጤት የተጠበቀውን ያህል ላይ ሆን ቀርቷል ።

ኒካራጓም የሶሻሊስት የዕድገት ፈለግን የምትከተል ሀገር እንደመሆንዋ ተፃራሪ ሥርዓት ከሚከተሉ ሀገሮች ጋር የምታራመደው በሰላም አብሮ በመኖር መርህ ላይ የተመሠረተ ፖሊሲ በዩናይትድ እስቴትስ ጣልቃገብነት የተነሣ ሊሰምር አልቻለም ። በዩናይትድ እስቴትስ መንግሥት የሚደገፉት የኒካራጓ ፀረ አብዮተኞችም (ኮንትራዎች) በኒካራጓ ሰፊ ሕዝብ ላይ የደገኑትን መሣሪያ ፈተው እንደማንኛውም የሀገሪቱ ዜጐች በሀገራቸው ጉዳይ ላይ በሁሉም መስክ ተሳታፊ እንዲሆኑ የተደረገላቸውን የሰላም ጥሪ ባለመቀበላቸው ለችግሩ ፖለቲካዊ መፍትሔ ለመስጠት አልተቻለም ። ሳንዲኒስቶች ግን እያሌ ጥረቶች በማድረግ ላይ ቢሆኑም ፣ የዩናይትድ እስቴትስ የትንኮሳና የማስፈራራት ድርጊት ግን አልተገታም ። በሚያዝያ ወር አጋማሽ 1988 በሆንዱራስ የግዛት ክልልና በኒካራጓ ድንበር አካባቢ 3,200 የዩናይትድ እስቴትስ ወታደሮች ሰፍረው የጦር ልምምድ ማድረግ ይህንኑ የጠብ አጫሪነት ተግባር በውል የሚያረጋግጥ ነው ።[55]

የሳንዲኒስቶች አሸናፊነትና የኮንትራዎች ተስፋ መቁረጥ አዝማሚያ

ዩናይትድ እስቴትስ ለኒካራጓ ፀረ አብዮተኞች (ኮንትራዎች) ከፍተኛ ዕርዳታ ያለማሰለስ በመስጠት ላይ ብትሆንም ኮንትራዎች ከሳንዲኒስቶች ጋር በገጠሙት ጦርነት ሽንፈት እየደረሰባቸው ነው ። የኒውስዊክ መጽሔት ዝግጅት አባል የሆነ አንድ ጋዜጠኛ በሰኔ ፡ 1987 የኮንትራ ሠፈሮችንና መላዋን ኒካራጓ ጎብኝቶ ከተመለሰ በኋላ ሁኔታውን ሲገልፅ "ኮንትራዎች በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነትና ከልብ የመነጨ ድጋፍ የላቸውም ። በዚህ መስክ በሚደረገው ትግል ተበልጠው የሚገኙ በመሆኑ በተለይም ከእነሱ አይሉ ከሚገኝ ብቃት ካለው ሠራዊት ጋር ተዋግተው ድል ይቀዳጃሉ ማለት ዘበት ነው ። የሽምቅ ውጊያ ስልት ከወታደራዊ ፍልሚያ የበለጠ ፖለቲካዊ ነው ። ሳንዲኒስቶች ይህንን ጠንቅቀው ያውቃሉ ። አብዛኞቹ የኮንትራ አባላት ግን ሌሊት እየታፈኑ የተወሰዱና በጠብመንጃ አፈሙዝ ተገደው ወደ ውጊያ እንዲሰማሩ የተደረጉ በመሆኑ የዓላማ ጽናት የላቸውም ። በካምፖቻቸው ውስጥ ተዘዋውሬ በተመለከትኩበት ወቅት ካየኋቸው የኮንትራ አባላት መካከል አንደኛው በዕድሜው ገና ወጣት ሲሆን የመቅበጥበጥና የመበሳጨት ሁኔታ ይታይበት ነበር ። ይህንንም ወጣት አነጋግሬ ለመረዳት የቻልኩት ከተሠማራበት የሥራ መስክ ታፍኖ የተወሰደ መሆኑን ነው"[56] ብሏል ። የዚህን ለጋና ለማያምንበት ዓላማ ተሰልፎ የሞት ዕጭ እንዲቀምስ የተዘጋጀ ወጣት ወላጅ እናት ይኸው ጋዜጠኛ አግኝቶ ባነጋገራቸው ወቅት በልጃቸው ታፍኖ መወሰድ የተሰማቸውን መሪር ሐዘን እንደገለፁለት አስፍሮ

ኮንትራዎችን በተመለከተ ስለአላቸው አስተያየት ጠይቋቸው "እኛንና ሌሎችንም የኒካራጓ ሕዝብ ነፃ ያወጣንን አብዮት ኮንትራዎች ለምን ሊያጠፉት እንደሚፈልጉ እጅግ የሚገርመኝ ጉዳይ ነው"[57] ሲሉ መልሰውልኛል በማለት ጽፏል ። ይኸው የምዕራብ ጋዜጠኛ የኮንትራዎችን ሁኔታ በዐይኑ ተመልክቶ ሲዘግብ ፡ ኮንትራዎች እጅግ የተጎሳቆሉና የተዳከሙ ለመሆኑ ገጽታዎች ራሱ በቂ ማስረጃ ነው ። አብዛኞዎችም ጣዕረሞት የሚተናነቃቸው ሲመስሉ ፣ የራስ ቅላቸው የሚታይና በሸሚዞቻቸው ውስጥ የጎድን አጥንቶቻቸው ሳይቀሩ የሚቆጠሩ ናቸው ። ምግብ ለማግኘት የሚያደርጉት ሽሚያ ለጦርነት ካላቸው ፍላጎት የበለጠ ነው ። የእያንዳንዱ የኒካራጓ ገበሬ ጎጆም የትኩረት ነጥባቸው ነው ። ገበሬውንም በተደጋጋሚ በዝርፊያ ያራቁቱት ስለሆነ አሳሳቢ በሆነ ደረጃ ላይ ነው[58] ብሏል ። ይኸው ጋዜጠኛ የመጨረሻ ዶሮዋ በኮንትራዎች የተወሰደችባት አንዲት የገበሬ ሚስት ከእንግዲህ በአካባቢአችን ዶሮ የሚባል ነገር መጥፋቱ ነው[59] ስትል ምሬቷን የገለጸችለት መሆኑን አስፍሯል ።

በተቃራኒው ደግሞ የሳንዲኒስታ ሠራዊት በአብዮታዊ ሥነ—ሥርዓት የታነፀና የሚዋጋለትን ዓላማ የሚያውቅ ፡ በትግሉም ውስጥ ይበልጥ እየተማረና እየበሰለ በመሄድ ላይ የሚገኝ ስለመሆኑ "የሳንዲኒስታ ወታደሮች የገበሬውን መብት የሚፃረሩ ድርጊቶችን በፍፁም አይፈፅሙም ፤ ውሀ እንኳን ለመጠጣት ቢፈልጉ በመጀመሪያ ከአዛዦቻቸው አስፈቅደውና ገበሬውን በትህትና ጠይቀው ወደ ቤቱ እንኳን ሳይገቡ ከውጭ ቆመው ነው"[60] ሲል ለሕዝቡ ያላቸውን አክብሮትና ፍቅር ጋዜጠኛው ለመግለፅ ተገዷል ። በስኮትላንድ ለኒካራጓ የሕክምና ዕርዳታ ሰጪ ድርጅት ሊቀመንበር የሆኑት ዳስቴርኒ በበኩላቸው ለእንግሊዝ ኮሚኒስት ፓርቲ ሳምንታዊ ጋዜጣ ኒውዎርከር አዘጋጅ በሰጡት ቃለ ምልልስ ስለኮንትራዎች ወታደራዊ ሁኔታ የዐይን ምስክርነት ሲሰጡ ኮንትራዎች በአሁኑ ወቅት የኒካራጓን መንግሥት በወታደራዊ መስክ የሚያሰጉ ኃይሎች አይደሉም ። በ1985 ወደ 12,000 የሚጠጉ ኮንትራዎች በኒካራጓ የነበሩ ሲሆን ፡ በ1986 መጨረሻ ላይ ደግሞ ይህ አኃዝ ከአምስት እስከ ስድስት ሺህ ዝቅ ብሏል ። በኒካራጓ መንግሥት ግምት መሠረትም ከዚህ አኃዝ ወደ አንድ ሺህ አምስት መቶ ያህሉ ኮንትራዎች የተገደሉ ስለሆነ በአሁኑ ወቅት ሳንዲኒስቶችን በመዋጋት ላይ የሚገኘው የኮንትራዎች ሠራዊት ከሦስት ሺህ እስከ አራት ሺህ ቢደርስ ነው ። ይህም ቢሆን በከፍተኛ ደረጃ የተደራጀ ወታደራዊ ሠራዊት ሳይሆን በትናንሽ ቡድኖች የተከፋፈለ ነው ። ከ1984—1985 በነበረው ጊዜም ውስጥ ኮንትራዎች ሰፋት ያለውና የፊት ለፊት ውጊያ ሳንዲኒስቶችን ገጥመዋቸው አያውቁም ። ይህም ሲሆን ዩናይትድ እስቴትስ በሆንዱራስ ድንበር በኩል በአየር ወታደራዊ ዕርዳታ እያደረገችላቸው ነበር ። የሚወስዱአቸው ርምጃዎች በሙሉ ተስፋ የመቁረጥ አዝማሚያን የሚያሳዩ ናቸው[61]

ከላይ ለማሳየት እንደተሞከረው ኮንትራዎች ከእንግዲህ ሳንዲኒስቶችን በወታደራዊ ኃይል ተቋቁመው ለማሸነፍ የማይችሉ ለመሆኑ የምዕራቡ ዓለም ታዛቢዎች ሳይቀሩ ምሥክርነታቸውን ለመስጠት ሁኔታው አስገድዷቸዋል። ሳንዲኒስቶች ግን እስካሁን በወታደራዊ መስክ ባካሄዱት ትግል ከፍተኛ ድል የተቀዳጁ ቢሆንም ከልዩ ልዩ አቅጣጫዎች የተሠነዘረው ጥቃት ያደረሰው የኢኮኖሚ ድቀት በቀላሉ ሊያገግም

የማይችል በመሆኑ በዚህ መስክ ከፊታቸው
የተደቀነው ተግባር እጅግ ውስብስብ ነው።
ከዚህም በላይ ደግሞ መታየት የሚገባው
ሀገሪቱ የምትገኝበት ማኅበራዊና ኢኮኖሚ
ያዊ የዕድገት ደረጃ እጅግ ዝቅተኛ ከሆነ
ዕርከን ላይ መሆኑ ነው ። የሀገሪቱ መሪ ጓድ
ዳንኤል ኦርቴጋ ይህንን አስመልክተው
ሲናገሩ ፤ አብዮታችን የተቀጣጠለው ኋለ
ቀር በሆነና የወዛደሩ መደብ ገና ባላደገበት
ኅብረተሰብ ውስጥ መሆኑ ከግምት ውስጥ
ሊገባ ይገባል ። በመሠረቱ ሀገራችን የገ
በሬ፣ የሠራተኞችና የጥቂት ወዛደሮች ማኅበ
ረሰብ ናት ፤ የሁሉም ማኅበራዊ ፣ ኢኮኖሚ
ያዊና ፖለቲካዊ ኃይሎች ንቁ ተሳታፊነት
ለምናካሂደው የአዲስ ኅብረተሰብ ግንባታ
እጅግ አስፈላጊ ነው [62] እንዳሉት ሁሉ
ከሳንዲኒስታ አብዮት ድል ማብሰር ማግስት
ጀምሮ እያሌ የግንባታ ተግባራት የተከና
ወኑ ከመሆኑም በላይ ሕዝቡን በማንቃትና
በማደራጀት በኩል የተፈፀሙት ክንውኖ
ችም በቀላሉ የሚገመቱ አይደሉም ።

ያለፈውን ሥርዓት ማኅበራዊ ተቋሞች
አፈራርሶ በአዲስና ተራማጅ በሆነ መተ
ካት የማይታለፍ ነባራዊ ግዴታ እንደመ
ሆኑ ሳንዲኒስቶችም ትኩረት የሰጡበት
ጉዳይ ነው ። ሆኖም በልዩ ልዩ ቁልፍ የሆኑ
ቦታዎች የተመደቡ ሁሉም ባለሥልጣናት
ካለፈው ሥርዓት እኩይ ሥነ — ምግባሮች
የፀዱ ባለመሆናቸው ቢሮክራሲያዊ አሠራ
ርን በሕዝባዊ አሠራር ለመተካት የሚደረ
ገው ትግልም እጅግ ውስብስብና አድካሚ
ነው ። እንደ ጉቦ ፣ በሥልጣን መባለግ ፣
ግላዊ ብልፅግናን ብቻ መሻት ወዘተ. የመሳ
ሰሉትን ብልሹ የአሠራር ልምዶች ለማስወ
ገድ እያሌ ርምጃዎች ቢወሰዱም ገና ብዙ
ድካምን የሚጠይቅ ጉዳይ መሆኑ ከብዙ
አብዮቶች ልምድ በተግባር የታየ ነው ።

የሳንዲኒስታ አብዮት ባሳለፋቸው ስም
ንት የትግልና የድል ዓመታት ውስጥ ጠላ
ቶቹ የተረባረቡበት ቢሆንም ብዙ ወዳጆ
ችም አፍርቷል ። የዓለም አብዮታውያን
ኃይላትና የሰላም ወዳድ ሕዝቦች ቁሳዊ ፤
ኅሊናዊና ፤ ዲፕሎማሲያዊ ድጋፍ ከፍተኛ
ግምት የሚሰጠው ነው ። ከእነዚህም መካ
ከል ሶቭየት ኅብረት ፤ ኩባና ሌሎችም
ሶሻሊስት ሀገሮች በወዛደራዊ ዓለም አቀፋ
ዊነት መርህ ላይ በተመረኮዘ መንፈስ ለኒካ
ራጓ በማድረግ ላይ የሚገኙት ዕርዳታ ለሳን
ዲኒስታ አብዮት መጎልበት ያበረከተው
ድርሻ ጉልህ ሥፍራ የሚሰጠው ነው ።
አብዮታዊት ኢትዮጵያም ለፍትህ የሚታገ
ለውን የኒካራጓ ሕዝብና አመራሩን በመደ
ገፍ የበኩሏን አስተዋጽኦ አድርጋለች ።

ዩናይትድ እስቴትስ የኒካራጓን ሉዓላዊ
ነት በመድፈር ፀረ አብዮት ቡድኖችን
በማሠልጠን ፤ በማደራጀትና በማስታጠቅ
የምታደርገው የማንያሀሉኝነት ተግባር
በመላው የዓለም ሕዝብ ፤ በዩናይትድ እስቴ
ትስ ሕዝብና የመማክርት ሸንጎው በርካታ
አባላት ጭምር ከፍተኛ ተቃውሞ ደርሶበ
ታል ። በዚህም መሠረት የሀገሪቱን ሕግ
በመተላለፍ ለኢራን በድብቅ የተሸጠ መሣ
ሪያ ገቢ ለኒካራጓ ወንበዴዎች እንዲተላለፍ
መደረጉ በከፍተኛ ደረጃ በመጣራት ላይ
ሲሆን ፤ የዩናይትድ እስቴትስን ፕሬዚዳ
ንት ቅሌት ውስጥ የከተተ ጉዳይ ሆና
መቆየቱ ይታወቃል ። የካቲት 3 ቀን 1987
የአሜሪካ ምክር ቤት የሕግ መምሪያ ባደረ
ገው ስብሰባ ላይ ፕሬዚዳንት ሬጋን የ36
ሚሊዮን ዶላር ዕርዳታ ለኮንትራዎች ይሰጥ
ሲሉ ያቀረቡት ሐሳብ ተቀባይነት ማጣት
በዩናይትድ እስቴትስ መማክርት ሸንጎም
ውስጥ ቢሆን የሀገሪቱ ቀኝ አክራሪዎች
በኒካራጓ ላይ የሚያራምዱት የወራሪነት
ፖሊሲ ተቀባይነት እያጣ መምጣቱን የሚ
ያመለክት ነው ። በቅርቡ በተገመገመው
የዩናይትድ እስቴትስ ሕዝብ አስተያየትም
መሠረት ለኒካራጓ ፀረ አብዮተኞች ስለሚሰ
ጠው ዕርዳታ ከሀገሪቱ ሕዝብ ከሦስት
ሁለቱ እጅ የተቃወመው መሆኑ ታውቋል።

ባጠቃላይ ዩናይትድ እስቴትስ አሁንም
በኒካራጓ ላይ ጥቃት ከመሰንዘር ያልታቀ
በች ቢሆንም በላቲን አሜሪካ ከኩባ ቀጥሎ
የሳንዲኒስታ አብዮት በአሸናፊነት መው
ጣት በክልሉ ለፀረ — ኢምፔሪያሊስት
ትግል መጠናከር ተጨባጭ አስተዋፅዖ
አድርጓል ። በመላው ዓለም የሚገኙ ምዝብ
ርና ጭቁን ሕዝቦችም የብሔራዊ አርነት
እንቅስቃሴ ትግላቸውን ይበልጥ እንዲያጠ
ናክሩ አበረታች ምሳሌ ሆኗል ።

የግርጌ ማስታወሻ

1. South: The third World magazine No. 70, August 1986, PP.45-46.
2. Review of International Affairs, Volume XXXVII No.875, (September 20, 1986) P.12.
3. Great Soviet Encyclopedia, 3rd edition, Volume 17, P.547. See also Non Aligned countries (London: Harney and Jones Limited, 1982), P.520.
4. Ibid.
5. Ibid.P.521.
6. Op.Cit.
7. Ibid.
8. Great Soviet Encyclopedia, Volume 17, P.548.
9. Ibid.
10. Non-Aligned Countries, P.520.
11. Ibid.
12. ፍራንቺስኮ ማውራ ፤ ኒካራጓ በሳንዲኒስቶች ዓርማ ሥር ፤ ማርክሳዊ ርዕዮት ፤ 6ኛ ዓመት ፤ ቁጥር 2 ፤ 1979 ፤ ገጽ 117 ።
13. Political Affairs: theoretical journal of the Communist Party of USA. Volume LXIV, No. 12. December, 1984, P.23.
14. Ibid, P.24
15. Ibid.
16. Ibid.P.25
17. Ibid.
18. Great Soviet Encyclopedia, Volume 17 P.547.
19. Non Aligned Countries. p.522.
20. Ibid.
21. The dawning of Nicaragua (Instituo-de Information de-Centro America y del Caribe, Managua-Nicaragua April, 1983 p.11. በትግል ለሰላም ፤ ቅጽ 7 ቁጥር 13 ፤ 1979 ፤ ገጽ 48 እንደተጠቀሰው ።
22. William I Rebinson kent Norsworthy, Nicaragua: The strategy of counter Revolution, *Monthly Review*, Volume 37, No.7, (December 1985), p. 11.
23. Political affairs, p.21.
24. ፍራንቺስኮ ማውራ ፤ ገጽ 10 ።
25. ከላይ የተጠቀሰው
26. William I Robinson kent Norsworthy, P.11
27. ፍራንቺስኮ ማውራ ፤ ገጽ 10
28. Non Aligned Countries P.522
29. Granma, March 1, 1982, cited in international Affairs, No.4.1986, p. 193.
30. V.DIMITRIYEV, Supporters and opponents of the Contadora process, International Affairs, No.9 (1985) p. 53.
31. Monthly review, Volume 37, No.7. (December 1985), p.12.
32. Ibid.
33. Facts on File, March 21, 1986, p.179.
34. Monthly Review Volume 37, No.7, December 1985, P.13.
35. Ibid.
36. ፍራንቺስኮ ማውራ ፤ ገጽ 14
37. ከላይ የተጠቀሰው

38. Monthly Review, December 1985 P. 13.
39. Ibid.
40. Facts on File, February 25, 1983, P. 199.
41. Monthly Review, December 1985, P. 14.
42. John. W.Waghelstein, post-Vietnam Counterinsurgency Doctrine, Military Review (May 1985), Cited in Monthly Review. Volume 37, No.7, P.15.
43. Facts on File, March 21, P.199
44. Ibid
45. Ibid.
46. Ibid.
47. Review of International Affairs, Volume XXXVI, No. 848-9, 1986, p. 98.
48. International Affairs, No. 9, 1986, pp.139-140.
49. Ibid.
50. Ibid.
51. Ibid.
52. Vladis liv Chirkov, Nicaragua: The Revlolution needs peace, New Times, No.20 (May 25, 1987) p.4.
53. Review of International Affairs, Volume XXXIII No. 899, September 20, 1987, p.9.
54. Democratic placstine, No.26, September, 1987, p.35.
55. Time, March 28,1988, p.6.
56. News Week, June 1.1987, p.24.
57. Ibid.
58. Ibid.
59. Ibid.
60. Ibid.
61. New Workers, Weekly News paper of the Communist party of Britain, No. 475, 22 may 1987, P.7.
62. Africasia, July 28, 1979. Quoted in International Affairs, No.8, 1984, p. 34.



Proudly Brought to You
By
www.binyamhk.wordpress.Com

ዋጋው ብር 1.25

BSPP